

3.34 የክብር ዘበኛ ጦር፣ 1928

እንዲገቡ መመልመላቸው ነው። ዋናው የክብር ዘበኛ ጦር ሰፈር አዲስ አበባ ሲሆን፣ በዚሁ አምሳል የተደራጁ ክፍሎችም ባንዳንድ ግዛቶች (ለምሳሌ ባሌ፣ ሐረር፣ወለጋ) ይገኙ ነበር። በ1927 ደግሞ በስዊድን ወታደራዊ ኤክስፐርቶች አማካሪነት የመጀመሪያው የጦር ትምህርት ቤት በሆለታ ተከፈተ። ሆኖም ሦስት ዓመት የሚፈጅ የመጀመሪያው የሥልጠና ኮርስ ሳይፈጸም ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወረረች። ዕጩ መኰንኖቹም ወታደራዊ ሕይወታቸውን በመኰንንነት ሳይሆን በአርበኝነት እንዲጀምሩ ተገደዱ።

## ምዕራፍ አራት

# የኢጣልያ ወረራ (1928-1933)

## ጦርነት

ጣልያኖች በ1888 ዐድዋ ላይ ድል ከሆኑ በኋላ ለአጭር ጊዜ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ የሚከተሉትን የመስፋፋት ፖሊሲ እንደመግታት ብለው ነበር። አዲስ የተሾመው ጠቅላይ ሚኒስትር ዲ ሩዲኒም ቀዳሚው ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ያራምድ የነበረውን ፖሊሲ ሽሮታል። ለቅኝ ግዛት ማስፋፊያ የተመደበው በጀት በግማሽ ተቀንሷል። ከዐድዋ በፊት አንገቱን ደፍቶ የነበረው የፀረ ኰሎኒያሊስት ቡድንም አሁን የልብ ልብ አግኝቶ ኢጣልያ እስከናካቴው የአፍሪቃን ምድር ለቃ እንድትወጣ ለመጠየቅ ተዳፈረ። ይህ ሁሉ ግን ለጊዜው ነበር። ኢጣልያ ኢትዮጵያን ትታ አይሆንላትምና እንደገና ጥቅሟን ለማስጠበቅ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቷን ቀጠለች። እንዲያውም የሚገርመው ነገር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አርቀ ሰላም ወርዶ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ለማቋቋም የመጀመሪያዋ አገር ሆነች። ይህም ሊሆን የቻለው በከፊል ፌዴሪኮ ቺኮዲኮላን የመሰለ የበሰለ ዲፕሎማት ወደ ኢትዮጵያ በመላኳ ነው። በሌላ ወገን ስናየው ግን የምኒልክና የኢጣልያ ግንኙነት (ባጠቃላይም የኢትዮጵያውያንና የጣልያኖች ግንኙነት ማለት ይቻላል) ፍቅርና ጠብን አቀላቅሎ የያዘ የመሆኑ ውጤት ነው።

ከእንግሊዝ ቀጥሎ ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም የጋራ ድንበር ያሏቸው ቅኝ ግዛቶች የምታስተዳድረዋ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ችላ ብላ መኖር የምትችልም አልነበረችም። ስለዚህ ቶሎ ብላ እርምጃዎቿን ከሌሎቹ ሁለት አጎራባች ቅኝ ገዥዎች፣ ማለትም ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ፣ ጋር ማቀናጀት ጀመረች። በ1899 ሦስቱ የተፈራረሙት ውልም የዚህ በኢትዮጵያ ላይ የነበረው የተቀናጀ ፖሊሲ የመጀመሪያው ውጤት ነው። የውሉ ዋና ይዘት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላላት ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ ነበር። እንግሊዝና ፈረንሳይ የነበራቸው ቋሚ ጎላማዎች (ማለትም እንግሊዝ በዐባይ ሸለቆ፣ ፈረንሳይ በባቡሩ መሥመር) በግልፅ ሲብራሩ፣ ከኤርትራና ከኢጣልያ ሶማሊላንድ በስተጀርባ ያሉት የኢትዮጵያ ግዛቶች (ማለትም ሰሜንና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ) በጅምላው ለኢጣልያ ተከለሉ። ይህ አልበቃም ብሎ የተናጠሉትን ሁለት ቅኝ ግዛቶቿን የማገናኘት መብቷ ተጠበቀላት። ይህ ሊሳካ የሚችለው ሁለቱን ያለያየው የኢትዮጵያ ምድር ከኢጣልያ ሥር ሲውል እንደሆነ ሲታወቅ ውሉ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር ወይ ግዛቷን ለመቁረስ የሚያደፋፍር ነበር ማለት ይቻላል። ለዚህም ነው አንድ የታሪክ ጸሐፊ ውሉን «ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላት ምኞት ማረጋገጫ ቻርተር» ብሎ የደመደመው። (Baer፣6)

የኢጣልያ ፍላጎት ምን እንደሆነም በአንደኛው ዓለም ጦርነት ወቅት ገሃድ ወጣ። ጦርነቱ በተጀመረ በዓመቱ የቃል ኪዳን መንግሥታቱ (ኢጣልያን ጨምሮ) ከድል በኋላ የጠላቶቻቸውን (ጀርመንና ቱርክ) ግዛቶች እንዴት እንደሚቃረጡ ሲያስሉ የኢጣልያ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በአፍሪቃ ቀንድ ላይ ነበር። የጠየቀችውም በአካባቢው ያለው የግዛትም ሆነ የኢኮኖሚ ጥቅም ድልድል ለሷ በሚያመች መንገድ እንደገና እንዲስተካከል ነው። ዐይን ባወጣ

ድፍረት ማለት ይቻላል በእንግሊዝና በፈረንሳይ ሥር የነበሩት የሶማሌ ግዛቶች ወደሷ እንዲጠቃለሉና በተጨማሪም ሁለቱ ኃያላን በኢትዮጵያ አለን ብለው የሚመኩበት ባንክና የምድር ባቡር በሷ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ ጠየቀች። ይህ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ኢጣልያ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ የባሕር በር ተቆጣጣሪ በሆነች ነበር። ከዚያም አልፎ ባገሪቱ አሉ የሚባሉትን ሁለት የኢኮኖሚ አውታሮች (ባንክና ባቡር) ስትቆጣጠር ኢትዮጵያ ወደ ኢጣልያ ጥገኝነት ተሸጋገረች ማለት ነበር። ነገር ግን ሁለቱ ኃያላን ከአፍሪቃ ቀንድ እንዲህ ውልቃቸውን ለመውጣት ፍላጎት አልነበራቸውም ነበርና የኢጣልያ ጥያቄ መና ቀረ።

በሙሶሊኒ የሚመሩት ፋሽስቶች በ1915 በጣልያን አገር ሥልጣን መያዝ የኢጣልያን ቅኝ ግዛታዊ ምኞት ርእዮተ ዓለማዊ ጥንካሬ ሰጠው። የጥንቱን የሮማን መንግሥት ኃይልና ዝና እንደገና ለማደስ ታጥቆ የተነሣው የፋሽስት ቡድን የመጀመሪያው ዓላማው የዐድዋን ሀፍረት መሻር ነበር። ይሁን እንጂ ሙሶሊኒ ይህን ዓላማውን ከመጀመሪያው ገሃድ አላወጣውም። እንዲያውም የወረራ ዓላማውን ሸፋፍኖ የሚፈልገውን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ለማግኘት ጥረት አደረገ። የኢትዮጵያ ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር መግባት ጥያቄ በተነሣበት ወቅትም አምርራ የተቃወመችው ኢጣልያ ሳትሆን እንግሊዝ ነች። ሙሶሊኒ መጀመሪያ የኢትዮጵያን መግባት የተቃወመ ቢሆንም ኋላ መግባቷ ላይቀር ለምን በጠላትነት እንመዘገባለን ብለው አማካሪዎቹ ስለነገሩት ተቃውሞውን አለዘበ። ራስ ተፈሪ በ1916 አውሮጳን በጐበኙበት ወቅትም በኢጣልያ የተደረገለት አቀባበል ከሌሎቹ ሞቅ ያለ ነበር። ሕዝቡ «ቪቫ ኢትዮጵያ! ቪቫ ተፈሪ!» እያለ ከመቀበሉም በላይ የኢጣልያ መንግሥት አንዳንድ የኢኮኖሚ ጥቅሞቹ ከተከበሩለት የአሰብን ወደብ ለኢትዮጵያ ለመስጠት ዝግጁነቱን አረጋገጠ። ይሁን እንጂ የኢጣልያ ዓላማ ተፈሪን አጅበው የሄዱትን መኳንንት ስላሠጋቸው የውሉ ረቂቅ ሳይጸድቅ ቀረ።

በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው የመቀራረብና የመቻቻል ስሜት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው ሐምሌ 28፣ 1920 የሰላምና የወዳጅነት ውል ሲፈራረሙ ነው። ለነገሩማ ውሉ ለሃያ ዓመታት ጸንቶ የሚቆይ ነው ተብሎ ነበር። ዓለም ሁሉ እንደሚያውቀው ግን ዐሥር ዓመትም አልቆየም። ከውሉ ጋር አብሮ በተደረገ ስምምነትም አሰብና ደሴን የሚያገናኝ የመኪና መንገድ ለማሠራት ተስማምተው ነበር። ይህ ስምምነት ሥራ ላይ ውሎ ቢሆን ኖሮ የኋላ ኋላ ሊሆን እንደቻለው የፈረንሣይ የምድር ባቡር መሥመር ኢትዮጵያን ከውጭ ዓለም በማገናኘቱ ረገድ ወደ ሁለተኛ ደረጃነት ዝቅ ባለ ነበር። ነገር ግን በወቅቱ ኢጣልያም ሆነች ኢትዮጵያ ፕሮጀክቱ ፍጻሜ እንዲያገኝ በሙሉ ልብ አልገፋበትም፤ ኢትዮጵያ ምናልባት በፈረንሳይ ተጽዕኖ ምክንያት፤ ኢጣልያ ዝቅ ብለን እንደምናየው ይህን ዓይነት መቀራረብ በማይሻው ቡድን ግፊት ሊሆን ይችላል።

ይህም ወደ ኢጣልያ ጣምራ ፖሊሲ ያመጣናል። ኢጣልያ ከዲፕሎማሲያዊ መቀራረብ ጐን ለጐን ለወደፊት ወረራ ሁኔታዎችን የሚያመቻች የቡርቦራ ፖሊሲም ታራምድ ነበር። ይህ ጣምራ አስተራረጂ ከዐድዋ ጦርነት በፊት የነበረውን ሁኔታ ያስታውሰናል። ያኔም ጣልያኖች በአንድ በኩል በኤርትራው አገረ ገዥ በአንቶኔሊ ባልዲሴራ አማካይነት «የትግሬ ፖሊሲ» የሚባለውን የምኒልክን ሥልጣን በሰሜን ኢትዮጵያ የሚያዳክም የቡርቦራ ስልት ሲከተሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የውጫሌውን ውል በተፈራረመው ፒዬትሮ አንቶኔሊ አማካይነት «የሸዋ ፖሊሲ» የተባለውን የማግባባት ፖለቲካ



ይከተሉ ነበር። አሁንም እንደዚያን ጊዜ የኤርትራው አገረ ገዥ ኮራዶ ዞሊ በትግሬ፤ በበጌምድር፤ በጎጃምና በወሎ የማዕከላዊውን መንግሥት ሥልጣን ሲሸረሽር፤ አዲስ አበባ የተቀመጠው የሌጋሲዮኑ ኃላፊ ጁሊያና ኮራ ግን ሁለቱን መንግሥታት ለማቀራረብ ይጥር ነበር። ከላይ የጠቀስነው የ1920ው የሰላምና የወዳጅነት ውልም የዚሁ የኮራ ጥረት ውጤት ነው። በተለያየ ወቅት በዐድዋ፤ በጐንደር፤ በደብረ ማርቆስና በደሴ የተከፈቱት የኢጣልያ ቆንስላዎችም በቡርቦራው ተግባር ትልቅ ሚና ከመጫወታቸውም በላይ፤ ጠቃሚ የሆኑ ፖለቲካዊና ወታደራዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ የኢጣልያን ወረራ ለማሳካት ረድተዋል።

የቅድመ ማይጨው ሁኔታ ከቅድመ ዐድዋው የሚመሳሰልበት ሌላም መንገድ አለ። ይኸውም በሁለቱም ወቅት እንግሊዝ ለኢጣልያ የመስፋፋት ዓላማ ቡራኬ መስጠቷ ነው። በ1918 እንግሊዝና ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉት ስምምነት በ1883 እና በ1886 ካደረጓቸው የፕሮቶኮል ስምምነቶች ጋር ይመሳሰላል። አንድ ትልቅ ልዩነት ቢኖር በ19ኛው መቶ ዓመት የተደረጉት ስምምነቶች ግዛት ሲያካልሉ፤ የ1918ቱ ግን የድኅረ ዐድዋ ኢምፔሪያሊስት ስልትን በመከተል በኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው። በዚህም መሠረት እንግሊዝ ምዕራብ ኢትዮጵያን ብቸኛ የኢጣልያ የኢኮኖሚ ተጽዕኖ ክልል ነው ብላ አወቀችላት። በአጸፋው ኢጣልያ እንግሊዝ ጣና ሐይቅ ላይ ግድብ ሠርታ የዐባይን ውሀ ለመቆጣጠር ለነበራት የብዙ ዓመታት ጥረት ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ለመስጠት ቃል ገባች። የሚገርመው ነገር ሁለቱ መንግሥታት ይህን ስምምነት ያደረጉት የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል በሆነች አገር ላይ መሆኑ ነው። በዚህም ድርጊታቸው የማኅበሩ አባላት እኩል መብት አላቸው በሚለው አንቀጽ ላይ አፌዘዋል። በተጨማሪም ድርጊቱ መጪውን አደጋ፤ ማለትም ማኅበሩ የኢጣልያን ወረራ ማቆም እንደማይችል፤ ጠቋሚ ነበር።

ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ለመውረር የወሰነበትን ወቅት ይህ ነው ብሎ በሙሉ ልብ መናገር ቢያዳግትም ከ1924 በኋላ ይመስላል። በተለይም በአውሮጳ መድረክ ይከተል የነበረው የመስፋፋት ፖሊሲ ከከሸፈበት በኋላ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ ማዞር ግድ ሳይሆንበት አልቀረም። በኦስትሪያ ይገባኛል የሚለውን ግዛት እስመልሳለሁ ሲል ከሂትለር ጋር በአልፕስ ተራራ ላይ ከተፋጠጠና ለማፈግፈግም ከተገደደ በኋላ፤ ሐፍረቱን ለመሸፈን በሌላ መድረክ ክብሩን ማደስ ነበረበት። ለዚህም እንደ ኢጣልያ መልክአ ምድራዊ ተቀጽላ ከምትታየው አፍሪቃ አህጉር የተሻለ አማራጭ አልነበረም። ከአፍሪቃም ደግሞ ኢትዮጵያን ለዚሁ ዒላማነት ታሪክ አጭቶ ያቀረባት አገር ነበረች። ፋሺዝም በኢጣልያ ምድር አመጣለሁ ያለው ዘመነ ጥጋብና ፍሥሐም ቀቢጸ ተስፋ ሆኖ ሲቀር የቅኝ ግዛት ድል በማስመዝገብ የሕዝቡን የቆሰለ ሕሊና ማሻር ያስፈልግ ነበር። ጦርነት ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ብቻ ሳይሆን ለእንዲህ ዓይነቱ ስነ ልቡናዊ ስርየት ባለው መሣሪያነትም አስፈላጊ ሆነ። ወረራውን ለመክፈት የሚቀረው አንድ የሆነ ሰበብ ብቻ ነበር። የወልወል ግጭት ይህንኑ ታሪካዊ ሚና ተጫወተ።

በኅዳር 26፣1927 የተከሠተው የወልወል ግጭት ባንድ መልኩ ኢትዮጵያ ካጉራባች ቅኝ ግዛቶች ጋር ያሏት በቅጡ ያልተከለሉ ድንበሮች ውጤት ነው። ምንም እንኳ በ19ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ላይ በተደረገው ስምምነት መሠረት ወልወል በኢትዮጵያ ክልል የሚገኝ ስፍራ ቢሆንም

ከመንግሥቱ አስተዳደራዊ ቁጥጥር ልልነት የተነሣ ሶማሌን የሚያስተዳድሩት ጣልያኖች በዚህ ሁኔታ ተደፋፍረውና የበታውንም የውሀ ሀብት ጠቃሚነት ተረድተው ወደ ግዛታቸው ጠቅልለውት ነበር። በ1920ዎቹ ዓመታት የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ አካባቢ ቁጥጥሩን እያጠናከረ ሲሄድ ግን የቀድሞ መብቱን ለማስመለስ መሞከሩ አልቀረም። ጣልያኖች እናስነካም ብለው ባካባቢው የሰፈሩትን የኢትዮጵያ ወታደሮች መተናኰል ሲጀምሩ ነው በታሪክ የታወቀው ግጭት የተቀሰቀሰው። ምንም እንኳ በግጭቱ ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱት ቁጥር ከጣልያኖች ወገን ሦስት እጅ ቢበልጥም፣ ካሣና ይቅርታ ይገባናል ብለው የማይሆን ጥያቄ ለማቅረብ የተሽቀዳደሙት ጣልያኖች ናቸው። ኢትዮጵያ ጥያቄውን ለመቀበል ፈቃደኛ ካለመሆኗም በላይ ጉዳዩን ለመንግሥታት ማኅበር አቀረበች። እዚያም ጠቡን ለማብረድ ፋይዳ ቢስ ድርድሩ ቀጠለ። በመሀሉ፣ በተለይ በኢጣልያ በኩል፣ ለማይቀረው ጦርነት አስፈላጊው ዝግጅት ይደረግ ነበር። በ1927 አጋማሽ ላይ ለሙሶሊኒ የወረራ ዕቅድ ዲፕሎማሲያዊ መተማመኛ የሰጠ አንድ ሁኔታ ተከሰተ። ይኸውም የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ፒዬር ላቫል አገሩ በኢትዮጵያ ላይ ለረጅም ጊዜ የነበራትን የኢጣልያን ዓላማ የመፃረር ፖሊሲ ሽሮ ሙሶሊኒ የፈለገውን ቢያደርግ እንደማይቃወም ማረጋገጡ ነው። የዘመኑ የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ሁኔታ እያደር ያሳየው እንግሊዝና ፈረንሳይ ሙሶሊኒን ከሂትለር ለማስኮብለል ኢትዮጵያን በመሥዋዕትነት ሊያቀርቡለት እንደተዘጋጁ ነው። እንዲህ ያሉ መተማመኛዎች ይዞ ነው ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ የዘመተው።

በመስከረም 22፣ 1928 የኢጣልያ ጦር ጣጠኛውን የመረብ ወንዝ ተሻግሮ በሦስት መሥመር በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ከፈተ። የጥቃቱ አንዱ ዒላማ ከአርባ ዓመት በፊት የኀፍረት ማቅ የተከናነበባት ዐድዋ ነበረች። ሁለቱ ሌሎች የጥቃት ዒላማዎች እንጢቾና አዲግራት ነበሩ። ወራሪዎቹ በመጀመሪያ ምንም ተቃውሞ አላጋጠማቸውም። የኢትዮጵያ ጦር ጥቃቱን ሳይቋቋም እንዲያፈገፍግ ተደርጎ ነበር። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ነበሩ። አንደኛው በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ የኢጣልያን ወራሪነት በግልጽ ለማሳየት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የኢጣልያን ጦር ወደ መሀል አገር ስቦ በማስገባት በስንቅና ትጥቅ አቅርቦቱ ላይ ችግር ለመፍጠር ነበር። እንደ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ያሉት መሪዎች ግን የኢጣልያን ጦር ላለመቃወም ትእዛዝም አልጠበቁም። አዲግራት በመስከረም 24 በጣልያን ጦር እጅ ስትወድቅ፣ ጓዙን ጠቅልሎና ጠቃሚ መረጃ ይዞ ወደነሱ ካምፕ ገባ። በማግስቱ ጣልያኖች ዐድዋን ከሚያስፈልገው በላይ በቦምብ ደብድበው ያዙ። በጥቅምት 27፣ ዘመቻው በተከፈተ በወር ከአምስት ቀን፣ ከስትራቴጂ አንፃር ቁልፍ የሆነችው መቀሌ ወደቀች። ይሁን እንጂ ክረምት ሳይገባ ዘመቻውን ለማጠናቀቅ ለሚፈልገው ሙሶሊኒ የዘመቻው ፍጥነት የሚያረካ ሆኖ አልተገኘም። ለዚህም ምክንያቱ የጦር አዛዡ የማርሻል ኤሚሊዮ ዴ ቦኖ ዳተኝነት ነው ብሎ ስላመነ እሱን አውርዶ በምትኩ ፒዬትሮ ባዶልዮን ሾመው። ከዚህም በኋላ ነው ጣልያኖች ዓለም ያወገዘውን የመርዝ ጋዝ በጦር መሣሪያነት መጠቀም የጀመሩት።

ጣልያኖች ካሁን አሁን ይገጥመናል እያሉ ሲጠብቁት የነበረው የኢትዮጵያውያን አጸፋ የማጥቃት እርምጃ በጥር 1928 ተጀመረ። የኢትዮጵያ የሰሜን ጦር በሦስት ረድፍ የተሰለፈ ነበር። በስተምዕራብ በራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ የሚመራው የጎጃምና የቤጌምድር ጦር፣ በስተምሥራቅ በጦር ሚኒስትሩ በራስ ሙሉጌታ ይገዙ የሚመራው የንጉሠ ነገሥቱ ጦር፣ በመሀል ደግሞ በራስ




ሥዩም መንገሻና በራስ ካሣ ኃይሉ የሚመራው ጦር ነበር። ራስ ካሣ የሰሜኑ ግንባር ጠቅላይ የጦር አዛዥ ሆኖ መሰየሙ ይህ ሹመት ለኔ ይገባኛል ባዩን የጦር ሚኒስትሩን አስኩርፎ ስለነበር በሁለቱ መካከል የነበረው ቅንብር እምብዛም ነበር። ባጠቃላይ የግንባሩ ድክመት በሦስቱ ረድፎች መካከል አስፈላጊው ቅንጅት ሊኖር አለመቻሉ ነው። በተለይም የራስ እምሩ ጦር የተዋጋው ተጀምሮ እስኪጨረስ ብቻውን ነበር ማለት ይቻላል። መቀሌን በመክበብ ላይ ያተኰረው የኢትዮጵያውያን የአጸፋ ማጥቃት እርምጃ ሊከሽፍ የቻለበት አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ምክንያትም የዚህ የቅንጅት እጦት ነው። ስለዚህም ብዙ ሰው ቢያልቅባቸውም ጣልያኖች የመጀመሪያው የተምቤን ጦርነት የተባለውን (ከጥር 11 እስከ 15) በማሸነፍ የተደላደለ ስፍራቸውን እንደያዙ ለመቆየት ችለዋል።

እንዲያውም ይህን የኢትዮጵያውያን የጥቃት እርምጃ መቋቋማቸው አዲስ የጥቃት እርምጃ ለመውሰድ አደፋፈራቸው። ዒላማቸውም ከመቀሌ በስተደቡብ እምባ አራዶም በተባለው ኮረብታ ላይ መሽጎ የነበረው የራስ ሙሉጌታ ጦር ነበር። እዚህ ላይ ነው የጣልያን አውሮፕላን ሥራውን የሠራው። ስለሆነም እምባ አራዶም የአምባ አላጌ ተቃራኒ ለመሆን በቃ። የዐድዋው አርበኛ ራስ ሙሉጌታ ከአርባ ዓመት በፊት እንደሆነው ሁሉ የማይበገር የሚመስል ምሽግ የያዘው ኃይል ሲሸነፍ ለማየት ዕጣው ሆነ። ልዩነቱ ግን አሁን ሥሉስ ዞሮ ተሸናፊዋ ኢትዮጵያ አሸናፊዋ ኢጣልያ መሆኗ ነው። ጥፋቱም ቀላል አልነበረም። ስድስት ሺ ያህል ኢትዮጵያውያን ሞቱ። ሙሉጌታ ራሱም ከሽንፈቱ በኋላ በነበረው የተደነባበረ ሽሽት ተገደለ። ነገር ሁሉ ካለቀ በኋላ ራስ ካሣ ተጠቂውን ጦር ለመርዳት መጣ።

ካሣና ሥዩም ራሳቸውም ከጣልያኖች ጋር ሁለተኛውን የተምቤን ጦርነት (ከየካቲት 19 እስከ 21) ገጠሙ። እንዲያው ለነገሩ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ጦር እንደሁ ቀሌው ተገፏል። የቴክኒክ የበላይነታቸው አልበቃ ብሎ የጣልያን ጦር በሰው ኃይልም አራት እጅ ይበልጥ ነበር። ከሁሉም እንግዳ የሆነውም ይህ የጣልያኖች የቁጥር ብዛት ነው። ሙሶሊኒ ዐድዋ ላይ የሠሩትን ስሕተት (ማለትም በቁጥር አምስት እጅ መበለጣቸውን) ላለመድገም ቆርጠ የተነሣ ይመስላል። እንዳለውም «ጥቂት ሺ ሰዎች ጨምረን ባለማሰለፋችን ዐድዋ ላይ ተሸነፍን። ያን ዓይነት ስሕተት እንደገና አንሠራም። ቁጥር ከማሳነስ አበዛህ ተብዬ ብወቀስ ይሻለኛል።» (De Bono, 110) ሁለተኛው የተምቤን ጦርነት በሰሜን ግንባር የተሰለፈውን የኢትዮጵያን ጦር ዋናና መካከለኛ ረድፍ በታተነው። መሪዎቹ ካሣና ሥዩምም የጣልያኖችን ከበባ ለጥቂት አምልጠውና የተረፈ ሠራዊታቸውን ይዘው ኮረም ላይ ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር ተቀላቀሉ።

የኢትዮጵያ ጦር ትንሽ የተሻለ ውጤት ያሳየው በራስ እምሩ በሚመራው በሽሬ ግንባር ነበር። በተለይም በታኅሣሥ 15 ደምበግዊና በተባለ ሥፍራ በሜጀር ሉዊጂ ክሪኒቲ በሚመራው የአስካሪዎች (የቅኝ ግዛት ወታደሮች) ጦር ላይ ከፍተኛ ድል ተቀዳጁ። በዚያም ሳቢያ የእምሩ ስም በጣልያኖች ዘንድ የተፈራም የተጠላም ሆነ። ይሁን እንጂ በዚህም በኩል ችግር አልነበረም ማለት



4.1 በራስ ሙሉጌታ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ከባድ ሽንፈት ያየበት የአምባ አራዶም ከረብታ

አይደለም። በተለይም የጎጃም አለቃዎችና የስሜኑ መሪ ደጃች አያሌው ብሩ ለጦርነቱ ያላቸው የቀዘቀዘ ስሜት የጦሩን የመዋጋት ችሎታ አዳክሞታል። ያም ሆኖ በጦሩ ላይ የደረሰው ኪሳራ ከመካከለኛውና ከምሥራቁ ግንባር ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑ የእምሩን የተሻለ የጦር አመራር የሚያስመሰክር ነው። በሁለቱ በተጠቀሱት ግንባሮች የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር ሲበታተን፣ ዐሥር ሺ የሚያህለው በሽሬ ግንባር የተሰለፈው ጦር ግን በሥርዓት አፈግፍጎ ተከዜን ለመሻገር በቅቷል። ጣልያኖች አዲስ አበባ ከገቡ በኋላም እምሩ ችግር ሊፈጥርባቸው የቻለበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው።


የ1928ቱ ጦርነት በተለምዶ አነጋገር የማይጨው ጦርነት ይባላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ማይጨው በሰሜኑ ግንባር ከተደረጉት ውጊያዎች አንዱና የመጨረሻው ሲሆን፣ ከዚያ በፊት ነገር ዓለሙ ያለቀ በመሆኑም ከማሳረጊያነት የተሻለ ሚና አልነበረውም። የእምሩ ጦር ከቶም አልተሳተፈበትም። የሙሉጌታ ጦር እንደሁ ቀደም ብሎ አምባ አራዶም ላይ ተጠናቋል። ከካሣና ሥዩም ጦር የተረፉትም ቀደም ባሉት ውጊያዎች ባካልም በሞራልም ደቀው ማይጨው ላይ ብዙ ትርጉም ያለው ሥራ ሊሠሩ አይችሉም ነበር። ማይጨው ላይ የታየው አዲስ ጉልበት የዘመናዊው የክብር ዘበኛ ጦር ብቻ ነው። እዚያ ሠራዊት ውስጥ ለተመለመሉት ወጣት ኢትዮጵያውያንም ሆነ ለዘመናይቱ ኢትዮጵያ ማይጨው የመፈተኛቸው አውድማ ሆነች። ውጊያው ሳይጀምር ያለቀለት መሆኑ ቢታወቅም፣ የሠራዊቱ ሪከርድ የሚያሳፍር አልሆነም።





4.2 የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታ ይገዙ

ጣልያኖች በማይበገር ምሽግ ውስጥ ተቀምጠው፣ ለማዩን ያላንዳች ተቀናቃኝ ኃይል ተቆጣጥረው፣ ይሸነፋሉ ብሎ መገመት ዘበት ነበር። ይህ አልበቃ ብሎ በኢትዮጵያ አመራር በኩል የታየው ዳተኝነት ችግሩን አባባሰው። የኢትዮጵያ ጦር ለማሸነፍ ጠባብ ዕድል እንኳ የሚኖረው ቶሎ ቢያጠቃ ነበር። ነገር ግን ንጉሡ ነገሥቱ የማጥቂያውን ጊዜ ካንዴም ሁለቴ ሲያስተላልፍ ይህም ዕድል እስከናካቴው ጨለመ። በመጨረሻ ውጊያው መጋቢት 22 ተካሄደ። አሥራ ሦስት ሰዓት በፈጀው ውጊያ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ጦር ቢያጠቃም የማታ ማታ ድሉ የጣልያኖች ሆነ። የኢትዮጵያ ጦር ተበተነ። በጦር ሜዳ ካለቀው ሠራዊት የበለጠ ሰውም በተዝረከረከው ሽሽት አለቀ። ከጥቂት ዓመታት በፊት በተደረገበት ዘመቻ ቂም ቋጥሮ የነበረው የራያና አዘቦ ሕዝብ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ የሚሸሸውን ሠራዊት በመዝረፍና በመስለብ የበቀል እርምጃ ወሰደ። ሠራዊቱን በዚህም በቃ ቢለው አንድ ነበር። የመጨረሻው አሳዛኝ ድራማ በአሸንጌ ሐይቅ ዳርቻ ላይ ታየ። መግቢያ ያጣው ሠራዊት የጣልያን የጦር አውሮፕላኖች መለማመጃ ዒላማ ሆነ። በምብና የመርዝ ጋዝ እየዘነበበት ከፊሉ በየሜዳው ወደቀ። ከፊሉ ሲብሰበት የሚያበርድለት እየመሰለው ሐይቁ ውስጥ ገብቶ አለቀ። ከዚህ በኋላ የደሴ መንገድ ለጣልያኖች ክፍት ሆነ። ሠራዊታቸውም ሰተት ብሎ በመጋቢት 27 ደሴ፣ ከዚያም በወሩ በሚያዝያ 27 አዲስ አበባ ገባ።



4.1 በራስ ሙሉጌታ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ከባድ ሽንፈት ያየበት የአምባ አራዶም ኮረብታ

አይደለም። በተለይም የጎጃም አለቃዎችና የሰሜኑ መሪ ደጃች አያሌው ብሩ ለጦርነቱ ያላቸው የቀዘቀዘ ስሜት የጦሩን የመዋጋት ችሎታ አዳክሞታል። ያም ሆኖ በጦሩ ላይ የደረሰው ኪሳራ ከመካከለኛውና ከምሥራቁ ግንባር ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑ የእምሩን የተሻለ የጦር አመራር የሚያስመሰክር ነው። በሁለቱ በተጠቀሱት ግንባሮች የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር ሲበታተን፣ ዐሥር ሺ የሚያህለው በሽሬ ግንባር የተሰለፈው ጦር ግን በሥርዓት አፈግፍጎ ተከዜን ለመሻገር በቅቷል። ጣልያኖች አዲስ አበባ ከገቡ በኋላም እምሩ ችግር ሊፈጥርባቸው የቻለበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው።

የ1928ቱ ጦርነት በተለምዶ አነጋገር የማይጨው ጦርነት ይባላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ማይጨው በሰሜኑ ግንባር ከተደረጉት ውጊያዎች አንዱና የመጨረሻው ሲሆን፣ ከዚያ በፊት ነገር ዓለሙ ያለቀ በመሆኑም ከማሳረጊያነት የተሻለ ሚና አልነበረውም። የእምሩ ጦር ከቶም አልተሳተፈበትም። የሙሉጌታ ጦር እንደሁ ቀደም ብሎ አምባ አራዶም ላይ ተጠናቋል። ከካሣና ሥዩም ጦር የተረፉትም ቀደም ባሉት ውጊያዎች ባካልም በሞራልም ደቀው ማይጨው ላይ ብዙ ትርጉም ያለው ሥራ ሊሠሩ አይችሉም ነበር። ማይጨው ላይ የታየው አዲስ ጉልበት የዘመናዊው የክብር ዘበኛ ጦር ብቻ ነው። እዚያ ሠራዊት ውስጥ ለተመለመሉት ወጣት ኢትዮጵያውያንም ሆነ ለዘመናይቱ ኢትዮጵያ ማይጨው የመፈተኛቸው አውድማ ሆነች። ውጊያው ሳይጀምር ያለቀለት መሆኑ ቢታወቅም፣ የሠራዊቱ ሪኮርድ የሚያሳፍር አልሆነም።





4.2 የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታ ይገዙ

ጣልያኖች በማይበገር ምሽግ ውስጥ ተቀምጠው፣ ሰማዩን ያሳንዳች ተቀናቃኝ ኃይል ተቆጣጥረው፣ ይሸነፋሉ ብሎ መገመት ዘበት ነበር። ይህ አልበቃ ብሎ በኢትዮጵያ አመራር በኩል የታየው ዳተኝነት ችግሩን አባባሰው። የኢትዮጵያ ጦር ለማሸነፍ ጠባብ ዕድል እንኳ የሚኖረው ቶሎ ቢያጠቃ ነበር። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ የማጥቂያውን ጊዜ ካንዴም ሁለቴ ሲያስተላልፍ ይህም ዕድል እስከናካቴው ጨለመ። በመጨረሻ ውጊያው መጋቢት 22 ተካሄደ። አሥራ ሦስት ሰዓት በፈጀው ውጊያ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ጦር ቢያጠቃም የማታ ማታ ድሉ የጣልያኖች ሆነ። የኢትዮጵያ ጦር ተበተነ። በጦር ሜዳ ካለቀው ሠራዊት የበለጠ ሰውም በተዝረከረከው ሽሽት አለቀ። ከጥቂት ዓመታት በፊት በተደረገበት ዘመቻ ቂም ቋጥሮ የነበረው የራያና አዘቦ ሕዝብ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ የሚሸሸውን ሠራዊት በመዝረፍና በመስለብ የበቀል እርምጃ ወሰደ። ሠራዊቱን በዚህም በቃ ቢለው አንድ ነበር። የመጨረሻው አሳዛኝ ድራማ በአሸንጌ ሐይቅ ዳርቻ ላይ ታየ። መግቢያ ያጣው ሠራዊት የጣልያን የጦር አውሮፕላኖች መለማመጃ ዒላማ ሆነ። በምብና የመርዝ ጋዝ እየዘነበበት ከፊሉ በየሜዳው ወደቀ። ከፊሉ ሲብሰበት የሚያበርድለት እየመሰለው ሐይቁ ውስጥ ገብቶ አለቀ። ከዚህ በኋላ የደሴ መንገድ ለጣልያኖች ክፍት ሆነ። ሠራዊታቸውም ስተት ብሎ በመጋቢት 27 ደሴ፣ ከዚያም በወሩ በሚያዝያ 27 አዲስ አበባ ገባ።



4.3 ወደ አጋዬን ግንባር የሚዘምት ወታደር ዘመዶቹን ሲሰናበት

የሰሜኑ ግንባር ወሳኙ ይሁን እንጂ ጦርነቱ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅም ነበር። በዚህኛው ግንባር የኢጣልያን ጦር የሚመራው ስመ የፋሺስት አገዛዝ ዕልመታዊ ምስል የሆነው ማርሻል ሮዶልፍ ግራዚያኒ ነበር። እሱም ለጌታው ለሙሶሊኒ «ኢትዮጵያን ሲሆን ከኢትዮጵያውያን ጋር አለዚያም ያለነሱ እስረክብሃለሁ» ብሎ መዛቱ ይነገርለት ነበር (Del Boca, 113)። መጀመሪያ የተሰጠው ተልእኮ ሊያጋጥም የሚችል የኢትዮጵያን የአጸፋ ጥቃት መከላከል ቢሆንም፣ ለድል ዘንባባ የተቅበጠበጠው ግራዚያኒ የመከላከል ተግባሩን ወደ ማጥቃት ዘመቻ ለወጠው። የኢትዮጵያ ጦር የሚመራው በደቡብ በሲዳሞው ገዥ በራስ ደስታ ዳምጠው፣ በደቡብ ምሥራቅ ደግሞ በደጃች ነሲቡ ዛማኑኤል፣ የሐረር ገዥ፣ ነበር። ከሰሜኑ ግንባር ጋር ሲነፃፀር የደቡቡ በመሣሪያ አቅርቦትም ሆነ በአመራሩ የውጊያ ስሜት የተሻለ ነበር ማለት ይቻላል።

በኦጋዴን ግንባር ለተደረገው ጦርነት ቁልፉ ቆራሄ ነበር። ይህን እስትራቴጂካዊ ስፍራ ላለማስወሰድ ሲከላከል የሞተው ስመጥር አርበኛ ግራዝማች (ከሞተ በኋላ ደጃዝማች) አፈወርቅ እንዳለው «ጣልያኖች ቆራሄን ከያዙ መላ ኦጋዴንን እንደያዙ ይቆጠራል።» (Graziani, 185) ሆኖም የአፈወርቅና የሠራዊቱ ቆራጥ መከላከል ቆራሄን በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ በጣልያኖች እጅ ከመውደቅ አላዳነም። ቆራሄን ከያዙም በኋላ የኢትዮጵያን ጦር



ለማሸበር ጂጂጋና ሐረር ድረስ ርቀው ሄደው በቦምብ እየደበደቡ ኦጋዴንን በሦስት አቅጣጫ ወረሩት። ነገር ግን ምንም እንኳ የጣልያን ጦር በቴክኒክም በሰው ብዛትም ብልጫ ቢኖረው ጉዞው ቀላል አልሆነለትም። በተለይም በደጃች መኩንን እንዳልካቸው ከሚመራው የኢሉባቦር ጦር ብርቱ ተቃውሞ ገጠመው። በዚህም ምክንያት ጣልያኖች በሰሜን ከደረሰባቸው የበለጠ ጉዳት በዚህኛው ግንባር ደርሶባቸዋል። ግራዚያኒም በፈለገው ፍጥነት ወደፊት መገስገስ ባለመቻሉ አንጀቱ እያረረ ባዶልዮ አዲስ አበባ ሲገባ እሱ ገና የሐረርን በር ማንኳኳት ነበረበት።

በደቡብ ግንባር ራስ ደስታ በጣልያኖች ላይ ድፍረት የተሞላበት ጥቃት ሰንዝሮ ነበር። ቆራሄ ላይ ለጥቂት ጊዜ ደርሶባቸው የነበረውን መዋከብ በመጠቀም ሠራዊቱን ድንበር ላይ በምትገኘው በዶሎ አዘመተ። ነገር ግን የጉዞው ረጅምነትና አድካሚነት፣ የስንቅ እጥረትና የበሽታ መዛመት ተዳምረው ሠራዊቱን የጣልያኖች ጭዳ አደረገው። ገናሌ ዶርያ ላይ ከጥር 3 እስከ 5 የተደረገው ውጊያ ጦርነት ሳይሆን ለኢትዮጵያውያን እልቂት ሆነ። የግራዚያኒን የድል ፈንጠዝያ ያደፈረሰው ነገር ቢኖር ዘጠኝ መቶ የሚደርሱ ኤርትራውያን አስካሪዎች የኢጣልያን ጦር ከድተው ወደ ራስ ደስታ ጦር መግባታቸው ነው። ይህ የኤርትራውያን ጣልያንን እየከዱ መሄድ በሌላ ጊዜና በሌሎችም የጦር ግንባሮች የታየ ክስተት ነው። የነሱ በራስ ደስታ ጦር ውስጥ መገኘትም ነው ጦሩን ከእንደዚያ ያለ ሽንፈት በኋላ አገግሞ መሪያቸው በየካቲት 1929 ተይዞ እስከተገደለ ድረስ ለጣልያኖች የእግር እሳት ለመሆን ያበቃው። ኤርትራውያኑ መማረክ ወይም እጅ መስጠት ማለት ሞት መሆኑን ስላወቁ ጣልያኖቹን የሚወጉት በታላቅ ቆራጥነት ነበር።

በ1928ቱ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ላይ የዐድዋ ትዝታ ያንዣብብ ነበር ማለት ይቻላል። ጣልያኖች የጉደፈ ስማቸውን ለማደስ፣ ኢትዮጵያውያን ያባቶቻቸውን ገድል ለመድገም ነበር የሚዋጉት። ይሁን እንጂ በዚህም ሆነ በዚያ ዐድዋ ሊደገም አልቻለም። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከሁሉም ግልጽ ሆኖ የሚታየው ጣልያኖች የነበራቸው ግዙፍ የሆነ የጦር መሣሪያ የበላይነት ነው። ዐድዋ ላይ በሁለቱ ተፋላሚዎች በኩል የነበረው የጦር መሣሪያ ልዩነት በዓይነትም ሆነ በብዛት ይህን ያህል የጎላ አልነበረም። ከአርባ ዓመት በኋላ ሲመጡ ግን ጣልያኖች ዘመናዊ ሚሊታሪ ቴክኖሎጂ ያፈራውን በሙሉ አስከፍጢማቸው ታጥቀው ነው። ባንፃሩ ኢትዮጵያ ለብዙ ዓመታት በተጣለባት የጦር መሣሪያ ማዕቀብ የተነሣ ባላጋራዋን ልትተካከል ቀርቶ ጫፏም አትደርስ ነበር። በጠቅላላው በኢትዮጵያውያን ዘንድ የነበረው የጠመንጃ ብዛት (እሱም አሮጌ ጠመንጃ ነው) ከጎምሣና ስድሳ ሺ አይበልጥም ነበር። የኢትዮጵያ ትልቁ ጉዳት ግን በጠመንጃው ሳይሆን በጥይቱ ነበር። እንደሚባለው በኢትዮጵያውያን ዘንድ የነበረው ጠቅላላ የጥይቱ ብዛት ጣልያኖች በሁለት ውጊያ የሚጨርሱትን ያህል ብቻ ነበር። በመትረየስና በመድፍ አቅም ያለውም ልዩነት ከዚህ ቢጎላ እንጂ አያንስም። ከሁሉም ለኢትዮጵያ መቅሠፍት የሆነው ግን የኢጣልያ አየር ኃይል ነው። ጣልያኖች በሰሜን ሦስት መቶ፣ በደቡብ አንድ መቶ የጦር አወሮፕላን አሰልፈው መላ ሰማዩን ሲቆጣጠሩ ኢትዮጵያ ማሰለፍ የቻለችው ስምንት አውሮፕላኖች ብቻ ነበር። እነዚህም አብዛኛዎቹ ለጭነት እንጂ ለውጊያ የሚያገለግሉ አልነበሩም። በዚህ ላይ የጣልያኖች የመርዝ ጋዝ ሲጨመርበት ኢትዮጵያውያን መሸነፋቸው ሳይሆን ያን ያህል መዋጋታቸው ነው የሚገርመው።



4.3 ወደ ኦጋዴን ግንባር የሚዘምት ወታደር ዘመዶቹን ሲሰናበት

የሰሜኑ ግንባር ወሳኝ ይሁን እንጂ ጦርነቱ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅም ነበር። በዚህኛው ግንባር የኢጣልያን ጦር የሚመራው ስሙ የፋሺስት አገዛዝ ዕልመታዊ ምስል የሆነው ማርሻል ሮዶልፎ ግራዚያኒ ነበር። እሱም ለጌታው ለሙሶሊኒ «ኢትዮጵያን ሲሆን ከኢትዮጵያውያን ጋር አለዚያም ያለነሱ አስረክብሃለሁ» ብሎ መዛቱ ይነገርለት ነበር (Del Boca, 113)። መጀመሪያ የተሰጠው ተልእኮ ሊያጋጥም የሚችል የኢትዮጵያን የአጸፋ ጥቃት መከላከል ቢሆንም፣ ለድል ዘንባባ የተቅበጠበጠው ግራዚያኒ የመከላከል ተግባሩን ወደ ማጥቃት ዘመቻ ለወጠው። የኢትዮጵያ ጦር የሚመራው በደቡብ በሲዳሞው ገዥ በራስ ደስታ ዳምጠው፣ በደቡብ ምሥራቅ ደግሞ በደጃች ነሲቡ ዛማኑኤል፣ የሐረር ገዥ፣ ነበር። ከሰሜኑ ግንባር ጋር ሲነፃፀር የደቡቡ በመሣሪያ አቅርቦትም ሆነ በአመራሩ የውጊያ ስሜት የተሻለ ነበር ማለት ይቻላል።

በኦጋዴን ግንባር ለተደረገው ጦርነት ቁልፉ ቆራሄ ነበር። ይህን እስትራቴጂካዊ ስፍራ ላለማስወሰድ ሲከላከል የሞተው ስመጥር አርበኛ ግራዝማች (ከሞተ በኋላ ደጃዝማች) አፈወርቅ እንዳለው «ጣልያኖች ቆራሄን ከያዙ መላ ኦጋዴንን እንደያዙ ይቆጠራል።» (Graziani, 185) ሆኖም የአፈወርቅና የሠራዊቱ ቆራጥ መከላከል ቆራሄን በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ በጣልያኖች እጅ ከመውደቅ አላዳነም። ቆራሄን ከያዙም በኋላ የኢትዮጵያን ጦር



ለማሸበር ጂጂጋና ሐረር ድረስ ርቀው ሄደው በቦምብ እየደበደቡ ኦጋዴንን በሦስት አቅጣጫ ወረሩት። ነገር ግን ምንም እንኳ የጣልያን ጦር በቴክኒክም በሰው ብዛትም ብልጫ ቢኖረው ጉዞው ቀላል አልሆነለትም። በተለይም በደጃች መኩንን እንዳልካቸው ከሚመራው የኢሉባቦር ጦር ብርቱ ተቃውሞ ገጠመው። በዚህም ምክንያት ጣልያኖች በሰሜን ከደረሰባቸው የበለጠ ጉዳት በዚህኛው ግንባር ደርሶባቸዋል። ግራዚያኒም በፈለገው ፍጥነት ወደፊት መገስገስ ባለመቻሉ አንጀቱ እያረረ ባዶልዮ አዲስ አበባ ሲገባ እሱ ገና የሐረርን በር ማንኳኳት ነበረበት።

በደቡብ ግንባር ራስ ደስታ በጣልያኖች ላይ ድፍረት የተሞላበት ጥቃት ለንዝሮ ነበር። ቆራሄ ላይ ለጥቂት ጊዜ ደርሶባቸው የነበረውን መዋከብ በመጠቀም ሠራዊቱን ድንበር ላይ በምትገኘው በዶሎ አዘመተ። ነገር ግን የጉዞው ረጅምነትና አድካሚነት፣ የስንቅ እጥረትና የበሽታ መዛመት ተዳምረው ሠራዊቱን የጣልያኖች ጭዳ አደረገው። ገናሌ ዶርያ ላይ ከጥር 3 እስከ 5 የተደረገው ውጊያ ጦርነት ሳይሆን ለኢትዮጵያውያን እልቂት ሆነ። የግራዚያኒን የድል ፈንጠዝያ ያደፈረሰው ነገር ቢኖር ዘጠኝ መቶ የሚደርሱ ኤርትራውያን አስካሪዎች የኢጣልያን ጦር ከድተው ወደ ራስ ደስታ ጦር መግባታቸው ነው። ይህ የኤርትራውያን ጣልያንን እየከዱ መሄድ በሌላ ጊዜና በሌሎችም የጦር ግንባሮች የታየ ክስተት ነው። የነሱ በራስ ደስታ ጦር ውስጥ መገኘትም ነው ጦሩን ከእንደዚያ ያለ ሽንፈት በኋላ አገግሞ መረያቸው በየካቲት 1929 ተይዞ እስከተገደለ ድረስ ለጣልያኖች የእግር እሳት ለመሆን ያበቃው። ኤርትራውያኑ መማረክ ወይም እጅ መስጠት ማለት ሞት መሆኑን ስላወቁ ጣልያኖቹን የሚወጉት በታላቅ ቆራጥነት ነበር።

በ1928ቱ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ላይ የዐድዋ ትዝታ ያንዣብብ ነበር ማለት ይቻላል። ጣልያኖች የጉደፈ ስማቸውን ለማደስ፣ ኢትዮጵያውያን ያባቶቻቸውን ገድል ለመድገም ነበር የሚዋጉት። ይሁን እንጂ በዚህም ሆነ በዚያ ዐድዋ ሊደገም አልቻለም። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከሁሉም ግልጽ ሆኖ የሚታየው ጣልያኖች የነበራቸው ግዙፍ የሆነ የጦር መሣሪያ የበላይነት ነው። ዐድዋ ላይ በሁለቱ ተፋላሚዎች በኩል የነበረው የጦር መሣሪያ ልዩነት በዓይነትም ሆነ በብዛት ይህን ያህል የጎላ አልነበረም። ከአርባ ዓመት በኋላ ሲመጡ ግን ጣልያኖች ዘመናዊ ሚሊታሪ ቴክኖሎጂ ያፈራውን በሙሉ አስካፍጢማቸው ታጥቀው ነው። ባንፃሩ ኢትዮጵያ ለብዙ ዓመታት በተጣለባት የጦር መሣሪያ ማዕቀብ የተነሣ ባላጋራዋን ልትተካከል ቀርቶ ጫፏም አትደርስ ነበር። በጠቅላላው በኢትዮጵያውያን ዘንድ የነበረው የጠመንጃ ብዛት (እሱም አሮጌ ጠመንጃ ነው) ከኀምሣና ስድሳ ሺ አይበልጥም ነበር። የኢትዮጵያ ትልቁ ጉዳት ግን በጠመንጃው ሳይሆን በጥይቱ ነበር። እንደሚባለው በኢትዮጵያውያን ዘንድ የነበረው ጠቅላላ የጥይቱ ብዛት ጣልያኖች በሁለት ውጊያ የሚጨርሱትን ያህል ብቻ ነበር። በመትረየስና በመድፍ አቅም ያለውም ልዩነት ከዚህ ቢጎላ እንጂ አያንስም። ከሁሉም ለኢትዮጵያ መቅሠፍት የሆነው ግን የኢጣልያ አየር ኀይል ነው። ጣልያኖች በሰሜን ሦስት መቶ፣ በደቡብ አንድ መቶ የጦር አወሮፕላን አሰልፈው መላ ሰማዩን ሲቆጣጠሩ ኢትዮጵያ ማሰለፍ የቻለችው ስምንት አውሮፕላኖች ብቻ ነበር። እነዚህም አብዛኞዎቹ ለጭነት እንጂ ለውጊያ የሚያገለግሉ አልነበሩም። በዚህ ላይ የጣልያኖች የመርዝ ጋዝ ሲጨመርበት ኢትዮጵያውያን መሸነፋቸው ሳይሆን ያን ያህል መዋጋታቸው ነው የሚገርመው።

በስንቅና ትጥቅም ረገድ ልዩነቱ እጅግ የሰፋ ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት ዘመናዊ የስንቅና ትጥቅ ድርጅት ያለው አልነበረም። ቁስለኞች ሕክምና ማግኘት የሚችሉትም ጦሩን ለመርዳት ብለው በፈቃዳቸው ከውጭ አገር በመጡ የሕክምና ሰዎች አማካይነት እንጂ የተደራጀ የሕክምና ክፍል አልነበረም። የሬዲዮ ግንኙነት ባለመኖሩ ወይም በቅጡ ባለመሥራቱ ወታደራዊ እርምጃን ማቀናጀት አስቸጋሪ ነበር። ይህ በተለይ በሰሜኑ ግንባር ጎልቶ የወጣ ችግር ነው። ከሁሉም እንግዳ የሆነው ግን የሰው ኃይል ሚዛንም ቢሆን ወደ ጣልያኖች ማጋደሉ ነው። ቀደም ብለን እንዳየነው በተለይ በኦጋዴን ግንባር፣ ጣልያኖች ብዙውን ጊዜ የቁጥር የበላይነት ነበራቸው። ይህም የሆነው ከቅኝ ግዛቶቻቸው፣ ከሊቢያ፣ ከኤርትራና ከጣልያን ሶማሊላንድ «አስካሪዎች» መልምለው በማሰለፋቸው ነው። ይህን የጣልያኖችን የቴክኒክና የቁጥር የበላይነት ኢጣልያዊው ታሪክ ጸሐፊ አንጄሎ ዴል ቦካ እንዲህ ሲል ይተርከዋል፤ «[ኢትዮጵያውያን] ከጣልያኖች ጋር ፊት ለፊት ከመጋጠማቸው በፊት አምስት ገሀነመ እሳት ማለፍ ይኖርባቸዋል። ከሰማይ የሚዘንበው ቦምብ፣ ተምዘግዝጎ የሚመጣው የመድፍ ጥይት፣ የመትረየሱ እሩምታ፣ ታንኮች፣ አስካሪዎች።» በዚህ የኃይል ሚዛን የኢትዮጵያውያን ዕድል በእጅጉ የጨለመ ነበር። የኢጣልያኖች የመርዝ ጋዝ ደግሞ ጨለማውን ፍፁም አደረገው።

ዞሮ ዞሮ ግን የኢትዮጵያ ሽንፈት መሠረቱ ራሱ ያገሪቱ ኅብረተሰብ ሁኔታ ነበር። አንዳንድ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያ የተሸነፈችው ፊውዳል በመሆኗ ነው ይላሉ። ይህ ግን የሚታመን አይደለም። ኢትዮጵያ ከ1928 ይልቅ በ1888 የበለጠ ፊውዳል ነበረች። ግን ያኔ ዐድዋን የመሰለ አንጸባራቂ ድል ተጎናጸፈች። ነገሩ እንቆቅልሽ ቢመስልም ኢትዮጵያስ የተሸነፈችው ፊውዳል ስለሆነች ሳይሆን ፊውዳልነቷ እየቀነሰ በመምጣቱ ነው። እንግሊዛዊቷ ጸሐፊ ማርጀሪ ፐርሃም ይህን ተንተርሳ ነው በጦርነቱ ዋዜማ የነበረውን ያገሪቱን የጦር ሠራዊት "ከመካከለኛው ዘመን (ሚዲዬቫል) ወደ ዘመናዊ ስልት በሚወስደው አደገኛ የሽግግር ወቅት ውስጥ የሚገኝ" ብላ የገለጸችው (Perham, 167)። በፖለቲካ መልኩም ቢሆን የምኒልክ ኢትዮጵያ ፊውዳላዊ እርቀ ሰላም የሰፈነባት ነበረች። የኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያ ግን ፍጹማዊ አገዛዝን ለመውለድ በምጥ ላይ ነበረች። ስለሆነም ከኃይለ ሥላሴ ይልቅ ምኒልክ የተባበረች ኢትዮጵያን ይዞ መዝመት ችሏል። በኃይለ ሥላሴ ዘመን የማዕከላዊው መንግሥት መጠናከር ግዛታዊ ሥልጣናቸውን የሸረሸረባቸው ወይም እስከናካቴው የነጠቃቸው አያሌ አኩራፊ መሳፍንት ነበሩ። ከዚያም በላይ አርባ ዓመት ያህል በቅኝ ግዛቶች ታጥሮ መኖሩ የዳር አገሩን ሕዝብ ልብ አሸፍቷል።

በተጨማሪም ከዐድዋ እስከ ማይጨው የተደረጉት ዐበይት ጦርነቶች ሁለት ብቻ ናቸው፤ ሰገሌ (1909) እና አንችም (1922)። ይህ አንፃራዊ ሰላም የሕዝቡን፣ በተለይም የመሪዎቹን፣ የጦረኝነት ስሜት አዳክሞታል። የዐድዋ አዝማቾች በጦርነት ተወልደው፣ በጦርነት ያደጉ፣ በጦርነትም የሚሞቱ ነበሩ። ከአርባ ዓመት በኋላ የተነሡት አዝማቾች ግን ሕይወታቸውን ከጦር ሜዳ ይልቅ በቢሮ ያሳለፉ ናቸው። አንዳንዶቹም እንዳየነው በንግድ ዓለም መሰማራት ጀምረዋል። ኃይለ ሥላሴ ራሱ የዚህ አዲስ አዝማሚያ ምሳሌ ነው። ትከሻው ጦርነትን ለመሸከም አልተፈጠረም። ስለሆነም ለኔም ላገሬም መድኅኑ የዓለም መንግሥታት ሰላምና ጸጥታን ለማስከበር የሚያደርጉት ጥረት (ኮሌክቲቭ ሴኩሪቲ) ነው የሚል የተሳሳተ እምነት ነበረው። ይህ የተሳሳተ እምነት እና




የሰው ልጅ ዓይነተኛ ባሕርይ የሆነው «ራስክን አድን» የሚለው መርህም ነው በጦር ሜዳ ሲሸነፍ ወደ አውሮጳ እንዲሄድ የገፋፋው። አገሪቷ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ከዓለም ኅብረተሰብ ጋር በመቀላቀሏ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የስደት ምርጫ ያጋጠመው ንጉሠ ነገሥት እሱ ነበር። ያን ምርጫ ለመውሰድም አላመነታም።

## የኢጣልያ አገዛዝ

ሚያዝያ 24 ቀን ንጉሠ ነገሥቱ አገር ጥሎ ሲሰደድ ጣልያኖች ወዲያው አዲስ አበባ አልገቡም። በመሀል ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ከተማይቱ መዓት ወረደባት። ሕግና ሥርዓት ፈርሶ ዝርፊያ፣ ዒላማ የሌለው ተኩስና ቃጠሎ ነገሠ። ሁከቱ በተለይ ያናወጠው አራዳ እየተባለ የሚታወቀውን መሀል ከተማ ነበር። ጅምላ እብደትንና እንጭጭ የመደብ ጦርነትን ያዋሐደ፣ ተስፋ መቁረጥና እምቢተኝነት የተቀላቀለበት እንቆቅልሽ ክሥተት ነበር። ተኩሱም ሆነ ዝርፊያው ዒላማ አለው ከተባለ፣ ዒላማዎቹ ሀብታሞችና የውጭ አገር ነዋሪዎች ነበሩ። ቤተ መንግሥቱም ቢሆን በውስጡ ያለው መሣሪያ ተፈላጊ ስለነበረ ከዝርፊያው አልዳነም። ብዙ የውጭ አገር ዜጎች እንዲህ ያለ ነገር መምጣቱ አይቀርም ብለው ለረጅም ጊዜ እራሳቸውን ሲያዘጋጁ በቆዩት ሌጋሲዮኖች ተጠልለው መዓቱን አሳለፉ። ዞሮ ዞሮ ግን ሁከቱ እንደማናቸውም ተመሳሳይ ሁከቶች ሁሉ ዕውር ነበር ማለት ይቻላል። ጠላትና ወዳጅ የሚለይ አልነበረም። ብዙ የተጎዱትም በአብዛኛው የተነጣጠረባቸው ፈረንጆች ሳይሆኑ ኢትዮጵያውያን ነበሩ።

በእንዲህ ያለ የትርምስ ሁኔታ አዲስ አበባ የገባው የኢጣልያ ሠራዊት የሰላምና መረጋጋት መልአክ ሆኖ ቢታይ አያስደንቅም። እንዲያውም ጣልያኖች ከተማው ሳይገቡ ሦስት ቀን ያደፈጡት ሰው በዚህ ዐይነ እንዲመለከታቸው አስበው ነው የሚል አስተያየትም አለ። ያም ሆነ ይህ ማርሻል ባዶልዮ ሠራዊቱን እየመራ አዲስ አበባ ሚያዝያ 27 ሲገባ በተለይ የውጭ አገር ዜጎች ትልቅ እፎይታ ነው የተሰማቸው። ባዶልዮ መጀመሪያ ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ ለሙሶሊኒ የድሉን የምሥራች ማብሠር ነበር። ሙሶሊኒም ወትሮውን ከሚደነፋበት ከቬኔትሲያ አደባባይ ሰገነቱ ይህንኑ ዜና ለጣልያን ሕዝብ ዐወጀ። በንግግሩ መጨረሻም «ኢትዮጵያ የኢጣልያ ሆናለች» በማለት ተከታታይ የኢጣልያ ትውልዶች ያለሙትን ሕልም እውን መሆን አረጋገጠ። ይህ ማረጋገጫ ምን ያህል ባዶ ቀፎ እንደሆነ በጥቂት ወራት ውስጥ ሊታይ ነው።

ጣልያኖች እንዲህ አርገው በአፍሪቃ ቀንድ የገነቡትን ግዛት የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪቃ፣ በጣልያንኛ «አፍሪካ ኦሪየንታሌ ኢታልያና»፣ ብለው ሰየሙት። ይህን አንድ ወጥ ግዛት ሊፈጥሩ የቻሉትም ቀድሞ የነበሯቸውን ቅኝ ግዛቶች (ኤርትራና የኢጣልያ ሶማሊላንድ) ከኢትዮጵያ ጋር በማዋሐድ ነው። በዚህም በ1899ኙ የሦስቱ ኃያላን ስምምነት የተተለመው ኤርትራንና የኢጣልያ ሶማሊላንድን የማገናኘቱ ዓላማ ተግባራዊ ሆነ። አዲሱ የኢጣልያ ግዛት የቀድሞ ዓለም አቀፍ ድንበሮችን በመሻር በስድስት ክልሎች ተከፍሎ ነበር። እነሱም ኤርትራ (ትግራይን ጨምሮ)፣ አማራ (በጌምድር፣ ወሎ፣ ጎጃምና ሰሜን ሸዋን




5. «የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪቃ» 1928-1933



አካትቶ)፣ ጋላና ሲዳማ (ለኦሮሞና ለደቡብ ሕዝብ የተሰጠ የጥቅል ስም)፣ አዲስ አበባ (ኋላ ወደ ሸዋ የተለወጠ)፣ ሐረር እና ሶማሊያ (ኦጋዴንን ጨምሮ) ነበሩ:: ዋና ከተሞቹም፣ በተከታታይ አሥመራ፣ ጐንደር፣ ጅማ፣ አዲስ አበባ፣ ሐረርና ሞቃዲሾ ነበሩ:: ለእያንዳንዱ ክልል አገረ ገዥ ሲሰየም፣ ከዚያ በታች ደግሞ በተዋረድ የአውራጃ ኮሚሽነሮች፣ ሬዚዴንሲያዎችና ምክትል ሬዚዴንሲያዎች ነበሩ:: ከነዚህ አስተዳደር እርከኖች ሁሉ ምናልባት ቁልፍ ቦታ ነበረው የሚባለው ሕዝቡን በቀጥታ የሚቆጣጠረውና በክልሉም ፍጹማዊ ሥልጣን የነበረው ሬዚዴንሲያው ነው::

የፋሽስቱ አገዛዝ ቁንጮ አዲስ አበባ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት የሚቀመጠው የኢጣልያው ንጉሥ እንደራሴ ነው:: ይህን ሥልጣን በግንቦት 1928 ወደ ኢጣልያ እስከተመለሰ ድረስ በመጀመሪያ የያዘው (ማለትም ከሁለት ወር ላነሰ ጊዜ) የጦር አዝማቹ ማርሻል ባዶሊዮ ነው:: እሱን የተካው ግራዚያኒም የካቲት 12፣ 1929 አርበኞች በጣሉበት ቦምብ እስከቆሰለ ድረስ ቀጠለ:: የግራዚያኒ ተከታይና የመጨረሻው እንደራሴ ከግራዚያኒ ጋር ሲነፃፀር ሰላማዊ ሊባል የሚችል አስተዳደር የመሠረተው የአኦስታው መስፍን (ዱክ ኦፍ አኦስታ) ነው:: እሱም ሰፋ ያለ ጥናት ያደረገበትንና የሚያደንቀውን የእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ለመከተል ፍላጎት እንደነበረውም ይነገርለት ነበር:: የዱክ ኦፍ አኦስታ ምክትል የታወቀው የኢትዮጵያ ጥናት ሊቅ ኤንሪኮ ቼሩሊ ሲሆን፣ የሱም ለዚህ ማዕረግ መብቃት በምርምርና በቅኝ ግዛታዊ አስተዳደር መካከል ለነበረው ቅንጅት ጥሩ ማስረጃ ነው:: ይሁንና እንደራሴውና ምክትሉ ሳይጣጣሙ ስለቀሩ፣ ቼሩሊ ወደ ሐረር ተዛውሮ በቀድሞው የሐረር ገዥ ጁሊዩልሞ ናዚ ተተክቷል:: ወረድ ብለን እንደምናየው፣ ባይሳካለትም ናዚ ስመጥሩውን አርበኛ ራስ አበበ አረጋይን አግባብቶ እጁን እንዲሰጥ ለማድረግ ብዙ ጥሯል::

የኢጣልያ አስተዳደር ዓይነተኛ ባሕርይ የተንዛዛ ቢሮክራሲና በሥልጣን መባለግ ነበር:: አንድ ጸሐፊ እንዳለው «በኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪቃ ውስጥ ከቢሮክራሲያዊ መዋቅሩ ውስጥ ስድሳ በመቶ የሚሆነው ራሱን ለማስተዳደር የሚዳክር ነበር» (Sbacchi, 80):: በተለይም ራስን ከተጠያቂነት ለማዳን ይመስላል ለሆነ ላልሆነው ኮሚቴዎችና ኮሚሲዮኖች የማቋቋም ልክፍት ነበር:: አያሌ የሆኑ የአስተዳደር ሹሞች በችሎታ ቢስነታቸው፣ በጠባብ አስተያየታቸውና በዋልጌነታቸው የታወቁ ነበሩ:: ዱክ ኦፍ አኦስታ ራሱ ከሹማምንቱ ውስጥ ኅምሳ በመቶው ችሎታ የሌላቸው፣ ሃያ አምስት በመቶው ደግሞ ሌቦች ናቸው ብሎ ተናግሮ ነበር:: የሁሉም ጥረት ቶሎ ለመክበር ነበር:: ባዶሊዮ ራሱ በወረራው ማግስት ከኢትዮጵያ ባንክ ከተወረሰው ገንዘብ ውስጥ 1700000 ማርትሬዛ ብር ኪሱ አስገብቶ ነበር ይባላል::

ወረድ ብለን በሰፊው በምናትተው የአርበኞች ትግል ምክንያት፣ የኢጣልያ አገዛዝ ባብዛኛው በከተማዎች የተወሰነ ነበር:: ስለሆነም አገዛዙ አሻራውን ትቶ የሄደውም በነዚህ ከተሞች ነው:: በተለይም ለኢጣልያ ዘመን ቋሚ ሐውልት ሆነው የቆዩላቸው እስካሁንም በጐንደር፣ ጅማ፣ ሐረርና አዲስ አበባ የሚታዩት በዚያን ጊዜ የታነጹት ሕንጻዎች ናቸው:: ለረጅም ዘመን በኢጣልያ ሥር የነበሩት አሥመራና ሞቃዲሾማ በጠቅላላው የኢጣልያ ፍጡሮች ነበሩ ማለት ይቻላል:: የግዛታቸው ዋና መዲናና የእንደራሴው መቀመጫ ለሆነችው ለአዲስ አበባ ጣልያኖች ሰፊ ንድፍ (ማስተር ፕላን) አዘጋጅተውም ነበር:: ግን እድሜያቸው አጠረና ዕቅዱም ከንድፍ ደረጃ ሳያልፍ ቀረ:: ይሁን

እንጂ የንድፉ አንዳንድ ገጽታዎች በተግባር ተተርጉመው የከተማይቱን መልክ በመጠኑም ቢሆን ቀይረውታል:: ለምሳሌም ለአገሬው ሕዝብ መገበያያ ተብሎ የተሠራው የመርካቶን መፈጠር፣ ከወረራውም በፊት ጀምሮ የነበረው የከተማይቱ ወደ ደቡብ የመስፋፋት ሂደት መፋጠን፣ እንደ ካዛንቼስ (በጣልያንኛ "ካዜ ኢንቼስ" ፤ ወይም የመንግሥት ሹማምንት መኖሪያ) እና ካዛፖፖላሬ (በጣልያንኛ «ካዜ ፖፖላሬ»፣ ወይም የሠራተኛው መደብ መኖሪያ) የመሳሰሉት ሰፈሮችን መፈጠር መጥቀስ ይቻላል:: መዲናይቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የኤሌክትሪክ መብራትና የተጣራ ውሀ ማግኘት የጀመረችውም በዚሁ በጣልያን ጊዜ ነው፤ ውሀው ከገፈርሳ፣ መብራቱ ደግሞ የኢትዮጵያ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ወላጅ ከሆነው ከኮኔል («ኮምፓኚያ ናትሲዮናሌ ኢምፕሬዜ ኤሌትሪኪ»):: እያሌ ፋብሪካዎችም ተቋቁመዋል፤ ድሬዳዋ የሚገኙት የጥጥና የሲሚንቶ ፋብሪካና ባገሪቱ ተናኝተው የሚገኙት የዘይት መጭመቂያዎች፣ የእህል ወፍጮዎችና የእንጨት መሰንጠቂያዎች::

በማኅበራዊ ኑሮ ረገድ፣ ምንም እንኳ የፋሽስቱ ሥርዓት በዘር ለመከፋፈል ቢሞክርም፣ በጣልያኖችና በኢትዮጵያውያን መካከል ያለውን ግንኙነት ሊቆርጥ አልቻለም:: የአበሻ ሴት ማግባት (በጣልያንኛ አጠራሩ ማዳሚዝሞ) ለጣልያኖች በሕግ የተከለከለ ነበር:: ይሁን እንጂ ባንድ በኩል የጣልያን ወንዶች ቁጥር ከሴቶቹ እጅግ የላቀ በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ድሮውንም ቢሆን ላቲኖች ለዘረኝነት ፍልስፍና አመቺ ባለመሆናቸው ሕጉን ማስከበር ቀላል አልነበረም:: ለዚህም ነው የጣልያን ዘመን የተወው አንዱ ቅርስ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ክልሶች የሆነው:: ከጋብቻ ውጭም መጀመሪያ መንግሥት ራሱ ካውሮጳ በማስመጣት፣ ኋላ ደግሞ ሁኔታው ራሱ በፈጠረው ግፊት ባገር እየተስፋፋ የሴትኛ አዳሪነት ሙያ ሥር ሊሰድ ቻለ:: ብዙውን ጊዜ የጣልያን አገዛዝ ሲወሳ እንደ አንድ ጉልህ ቅርስ የሚጠቀሰውም ይኸው ሴትኛ አዳሪነት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ከወረራው በፊትም በተለይ በከተማው ሕዝብ ዘንድ የጀመረው የአውሮጳን የአኗኗር ስልትና ዘይቤ መቅሰም በሰፋት ቀጥሏል:: እንደዚሁም ማቆጥቆጥ የጀመረው የገንዘብ ኤኮኖሚ ይበልጥ ሥር ሰደደ::

ከሁሉም በላይ የኢጣልያ አገዛዝ ትቶ ያለፈው መዘክር የመንገድ ሥራ ነው:: ሆኖም ይህም ቢሆን ያለቅጥ ተጋኖ ሲወሳ ቆይቷል:: መጀመሪያ ነገር ጣልያኖች ለመንገድ ሥራ የተጉት በሰሜኑ ክፍል ነው እንጂ በደቡብ ይህን ያህል አልነበረም:: ይህም ያለ ምክንያት አይደለም:: መንገዶች የተቀየሱት ለወረራው ካላቸው አመችነት አንፃር እንጂ ላገር ልማት ተብሎ አልነበረም:: በተጨማሪም የተሠሩት መንገዶችም ቢሆን ለነፃነት በተደረገው ተጋድሎ ወድመው ከነፃነት በኋላ እንደገና መሠራት ነበረባቸው:: ይህም ሆኖ ግን በርግጥም ጣልያኖች ወደፊት ሊስፋፋና ሊሻሻል የሚችል የአውራ ጐዳና መሠረት ጥለው አልፈዋል:: ከዚሁም ጐን ለጐን የሞተር ትራንስፖርት አገልግሎትም አንድ እመርታ ሊያሳይ ችሏል:: ጣልያኖች ሲሸነፉ ጥለዋቸው የሄዱት አውቶሞቢሎች፣ የጭነት መኪናዎችና የጋራዥ ባለሙያዎች ከነፃነት በኋላ ለተቋቋሙት እንደነ የሕዝብ ትራንስፖርት መሥሪያ ቤት (በኋላ የአንበሳ አውቶቡስ ኩባንያ ለሆነው) መቋቋሚያ በመሆን አገልግለዋል:: ከጣልያን ጊዜ በኋላ የኖረው ትውልድ እንደሚያስታውሰው እንደ «ትሬንታ ኳትሮ» (በጣልያንኛ 34፤ ያንድ መኪና ሞዴል ቁጥር) እና «አውታንቲ» (የሾፌር ረዳት) የመሳሰሉ ቃላት ከጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት ጋር በጥብቅ የተያያዙ ሆነው ቆይተዋል:: እስካሁንም ድረስ የሜካኒኮች ቋንቋ ከአማርኛም ሆነ ከእንግሊዝኛ



ይልቅ ጣልያንኛ ነው:: ለምሳሌ ፍሪሲዮን፣ ሬጅስትሮ፣ ላቫጆ፣ ፈረፋንጎ፣ ዲናሞ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል::

በኤኮኖሚው መስክ የኢጣልያ አገዛዝ የፋሽስት ፍልስፍናን በመከተል ለመንግሥት ጎላ ያለ ድርሻ ይሰጥ ነበር:: ለዚህ እንዲያመችም መጀመሪያ ኢጣሊያዊ ያልሆኑ የውጭ አገር ኩባንያዎችን ማዳከምና ጭራሹኑ ማጥፋት አስፈላጊ ነበር:: የዚህ ፖሊሲ ሰለባ ከሆኑት መካከል ጎላ ብለው የሚታዩት ከወረራው በፊት በውጭ ንግዱ ላይ ነግሠው የነበሩት የሕንዱ ነጋዴ ሙሐመድ ዓሊና ፈረንሳዊው ኩባንያ ኢቤስ ናቸው:: (ይሁንና ቤስ ከነፃነት በኋላ ተመልሶ ከአብዮት በኋላ ተወርሶ በመንግሥት ኮርፖሬሽን (ኢ.ዲ.ዲ.ሲ) እስከተተካ ድረስ እንደገና የውጭ ንግዱን ባንደኛ ደረጃ ሊቆጣጠር በቅቷል::) በነሱ ቦታ የኢንዱስትሪ፣ የንግድና የእርሻውን ዘርፍ የሚያንቀሳቅሱ መንግሥታዊ ድርጅቶች ተቋቋሙ:: በተለይም ጣልያኖች ልዩ ትኩረት የሰጡትን የጣልያን ገበሬዎችን በኢትዮጵያ የማስፈር ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ሦስት ድርጅቶች ተቋቁመው ነበር:: ይህ የማስፈር ፖሊሲ ከፍተኛ ዋጋ የተሰጠው እንደኛ በጣልያን አገር (በተለይም በደቡብ ክፍል) ይታይ የነበረውን የሕዝብ መጨናነቅ ለማስተንፈስ፣ ሁለተኛ በፋሺስት የኤኮኖሚ ፍልስፍና መሠረት አንድ ቅኝ ግዛት ራሱን መመገብ መቻል አለበት የሚል አስተሳሰብ ስለነበረ ነው:: እንዲያውም ከዚያም አልፎ አቅኚውን አገር (ኢጣልያን) ለመመገብም ይበቃል የሚልም ተስፋ ነበር:: ለእንዲህ ዓይነቱ የሰፈራ ፕሮግራም የተመረጡት ሦስት ቦታዎች ወገራ (ስሜን)፣ ጨርጨርና ጅማ ነበሩ::

ነገር ግን ፕሮግራሙ የተጠበቀውን ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም:: ኢጣልያን መመገቡ ቀርቶ ቅኝ ግዛቱ እንኳ ራሱን ለመቻል አልበቃም:: እንዲያውም ወትሮ ያልተለመደውን ያህል እህል በገፍ ከውጭ ማስገባት አስፈላጊ ሆነ:: በተለይም ፓስታ ለመሥራት አስፈላጊ የሆነው ስንዴ በብዛት ከውጭ መገዛት ነበረበት:: ይህ ሰፊ የእርሻ ዕቅድ እንደዚህ ሊከሽፍ የቻለበት ዋናው ምክንያት ጣልያኖች ገጠሩን ለመቆጣጠር ያላቸው አቅም ደካማ በመሆኑ ነው:: ሰፋሪዎቹ የነፃነት ታጋይ አርበኞች ምን ጊዜም አደጋ ሊጥሉባቸው እንደሚችሉ እስካወቁ ድረስ ተረጋግተውና ተዝናንተው ሊያርሱ አልቻሉም:: ስለዚህም ባጭር ጊዜ ከድኅነት ቀንበር ተላቀን እንበለፅጋለን እያሉ ሕልማቸውን በሰፊው አድርተው የመጡት ሰፋሪዎች የነሱን ፈለግ ተከትለው ለመምጣት ላሰቡ ዘመዶቻቸው አርፈው እዚያው እሉበት እንዲቀመጡ ለመጻፍ ተገደዱ:: መጀመሪያ በፍጥነት እያደገ የነበረው የሰፋሪዎች ቁጥርም ማሽቆልቆል ጀመረ:: ጣልያኖች ተሸንፈው ከኢትዮጵያ ሲወጡ ከሰፈራው ዕቅዳቸው መፈጸም የቻሉት ከመቶ ዐሥሩን ያህል ብቻ ነው:: የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የቻሉት በንግድና በኢንዱስትሪ መስክ ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት በነዚህ መስክ ያሉት እንቅስቃሴዎች በከተማዎች ክልል ስለሆኑና ከተማዎቹንም ለመቆጣጠር ጣልያኖች የተሻለ ዐቅም ስለነበራቸው ነበር::



4.4 ስመ ጥሩው አርበኛ ራስ አበበ አረጋይ

## የአርበኞች ትግል

የኢጣልያ አገዛዝ ምንም እንኳ ከላይ የጠቀስናቸውን አንዳንድ አሻራዎች ትቶ ቢያልፍም በሌሎች የአፍሪቃ አገሮች የነበረው መደበኛ የቅኝ አገዛዝ ባሕርይ አልነበረውም። ባንድ በኩል የዘመኑ አጭርነት፣ በሌላ በኩል የተደላደለና የተረጋጋ መልክ ለመያዝ አለመቻሉ ሲጤን ረጅሙን የኢትዮጵያ ታሪክ ሂደት ለጊዜው አቋረጠው እንጂ ወሳኝ በሆነ መልኩ አለወጠውም። እንደዚህ ዘላቂነት ከነሱት ድርጊቶች ዋነኛው በመላ አገሪቱ የተቀጣጠለው የአርነት ተጋድሎ ነው። በመጨረሻም ዕለተ ሞቱን ያቀረበው ሙሶሊኒ ሂትለርን ደግፎ ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ውስጥ በመግባቱ የተጫወተው የፖለቲካ ቁማር ነው።

ሙሶሊኒ ወረራውን እያካሄደ እያለም ሆነ ወረራው ከተሳካለት በኋላ ያተኮረበት አንድ ነጥብ ለወታደራዊ እርምጃው ሕጋዊ ዕውቅና ማስገኘት ነበር። የዓለም መንግሥታት ማኅበር ሲያስፈራራው የነበረውን የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ እንዳይጥልበትም የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት የተቻላቸውን ያህል



ደክመውለታል። ጦርነቱ በተጀመረ በሁለት ወሩ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰር ሳሙኤል ሆርና የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፒዬር ላቫል በስማቸው የሚጠራውን የሆር ላቫል የሰላም ዕቅድ አወጡ። ይህ ዕቅድ ኢጣልያ በጦር ሜዳ ያገኘችውን ድል በማጽደቅ አጋዴንን፣ በከፊል፣ የትግራይን ግዛት (ከአክሱም በስተቀር) በአብዛኛው የኢጣልያ የኢኮኖሚ ጥገኛ የሚያደርግ ነበር። በዐጸፋው ለኢትዮጵያ የታሰበላት በአሰብ በኩል ነፃ የባሕር ግንኙነት ለማግኘት መቻል ብቻ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ግን ይህን ዕቅድ አልተቀበለውም። ዕቅዱ በአውሮፓ ይፋ ሲወጣም ብዙ ተቃውሞ ከማስነሣቱ የተነሣ ሁለቱ ሚኒስትሮች ከሥራቸው ለመሰናበት ተገደዋል።

ጦርነቱ እየገፋ ሲሄድ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል አንዳንድ የምስጢር ግንኙነቶች ተደርገዋል። በዚህም ረገድ አገናኝ ሆነው የሚያገለግሉት ኢትዮጵያውያንም የውጭ አገር ሰዎችም ነበሩ። ኢትዮጵያውያኑ ጦርነቱ ሲጀምር በሮማ የኢትዮጵያ መንግሥት ሚኒስትር የነበረው አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሲሆኑ፣ የውጭ አገር ዜጎቹ ደግሞ ጃሲር ቤይ የሚባል ፍልስጤማዊ፣ ኢጣልያዊው ምሁርና ኋላ ምክትል እንደራሴ የሆነው ኤንሪኮ ቼሩሊ እና የኃይለ ሥላሴ የግል ሐኪም የነበረው ግሪኩ አድርያን ዜርቮስ ነበሩ። በጣልያኖች በኩል፣ የጦር ሜዳው ፍልሚያ እየሠመረላቸው ስለሄደ ይመስላል፣ በሆር ላቫል ዕቅድ ከተተለመላቸው የበለጠ እንጂ ያነሰ ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም። በአዲሱ የእርቅ ሐሳብ የኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ከሸዋ እንዳያልፍ ተከልሎ ነበር። ከጭንቀት ይመስላል የኢጣልያን አገዛዝ ለማምለጥ ኃይለ ሥላሴ የእንግሊዝን ምግዚትነት እስከመጠየቅም ደርሶ ነበር ይባላል። በተመሳሳይ መንገድ 1928 ማለቂያ ላይ የወለጋ ባላባቶች «የምዕራብ ጋላ ኮንፌዴሬሽን» የሚባል ኅብረት በመፍጠር የእንግሊዝን ሞግዚታዊ አስተዳደር ጠይቀው ነበር።

ጣልያኖች የመጨረሻውን ድል አግኝተው ንጉሠ ነገሥቱም ከተሰደደ በኋላ እነዚህ የምስጢር ግንኙነቶች ቀጥለው ነበር። በዚህን ወቅት አገናኝ ሆኖ የሚያገለግለው ግብፃዊው ልዑል መሐመድ ኢክነም ሪዛ ነበር። ጣልያኖች ያቀረቡት አንዱ ሐሳብ የገንዘብ ካሣ ተደርጎለት ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣኑን በይፋ እንዲለቅ ነው። የገንዘብ አቅሙ ከጊዜ ወደጊዜ እየደቀቀ ለመጣው ንጉሠ ነገሥት ይህ እጅግ የሚፈታተን ሐሳብ ነበር። ሆኖም ሐሳቡን ለመቀበል ስለተቸገረ ድርድሩ ፍሬ አላገኘም። ንጉሠ ነገሥቱም ከገንዘብ ክብርን መርጦ የኢጣልያ ወደ ሁለተኛው ዓለም ጦርነት መግባት እንደገና ወደ ማዕከላዊው መድረክ እስካወጣው ድረስ ባዝ በምትባለው በምዕራብ እንግሊዝ በምትገኝ አነስተኛ ከተማ በስደት ኖረ። ጣልያኖች በተመሳሳይ መንገድ ከአልጋ ወራሹ ከአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ጋር ያደረጉት ድርድርም ፍሬ አልባ ነበር።

ኢትዮጵያ ውስጥም ጣልያኖች በመጀመሪያ በገበሩላቸው መሳፍንት አማካይነት አገሪቱን ለመግዛት አስበው ነበር። ኋላ ግን ባንድ በኩል ጥቁር ለመገዛት እንጂ ለመግዛት ብቁ አይደለም ከሚል እስተሳሰብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አሠራሩ ፍጹማዊ የፋሽስት አገዛዝን የሚፃረር በመሆኑ ይህን ፖሊሲ ወደ ጎን ተዉት። መሳፍንቱም ማዕረጋቸውንና ወርሃዊ አበላቸውን ይዘው እንዲቀመጡ ተደረገ። በዚህም መሠረት ለምሳሌ ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት 40000 ሊሬ፣ ለራስ አባተ ቧያለው ልጅና በተከታታይ ሚኒስትር፣ አምባሳደርና አገረ ገዥ ለነበረው ራስ ጌታቸው አባተ 7000 ሊሬ ሲቆረጥላቸው፣ ሌሎች መሳፍንት



4.4 ስመ ጥሩው አርበኛ ራስ አበበ አረጋይ

## የአርበኞች ትግል

የኢጣልያ አገዛዝ ምንም እንኳ ከላይ የጠቀስናቸውን አንዳንድ አሻራዎች ትቶ ቢያልፍም በሌሎች የአፍሪቃ አገሮች የነበረው መደበኛ የቅኝ አገዛዝ ባሕርይ አልነበረውም። ባንድ በኩል የዘመኑ አጭርነት፣ በሌላ በኩል የተደላደለና የተረጋጋ መልክ ለመያዝ አለመቻሉ ሲጤን ረጅሙን የኢትዮጵያ ታሪክ ሂደት ለጊዜው አቋረጠው እንጂ ወሳኝ በሆነ መልኩ አለወጠውም። እንደዚሁ ዘላቂነት ከነሱት ድርጊቶች ዋነኛው በመላ አገሪቱ የተቀጣጠለው የአርነት ተጋድሎ ነው። በመጨረሻም ዕለተ ሞቱን ያቀረበው ሙሶሊኒ ሂትለርን ደግፎ ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ውስጥ በመግባቱ የተጫወተው የፖለቲካ ቁማር ነው።

ሙሶሊኒ ወረራውን እያካሄደ እያለም ሆነ ወረራው ከተሳካለት በኋላ ያተኮረበት አንድ ነጥብ ለወታደራዊ እርምጃው ሕጋዊ ዕውቅና ማስገኘት ነበር። የዓለም መንግሥታት ማኅበር ሲያስፈራራው የነበረውን የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ እንዳይጥልበትም የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት የተቻላቸውን ያህል ደከመውለታል። ጦርነቱ በተጀመረ በሁለት ወሩ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰር ሳሙኤል ሆርና የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፒዬር ላቫል በስማቸው የሚጠራውን የሆር ላቫል የሰላም ዕቅድ አወጡ። ይህ ዕቅድ ኢጣልያ በጦር ሜዳ ያገኘችውን ድል በማጽደቅ ኦጋዴንን፣ በከፊል፣ የትግራይን ግዛት (ከአክሱም በስተቀር) በአብዛኛው የኢጣልያ የኢኮኖሚ ጥገኛ የሚያደርግ ነበር። በዐጸፋው ለኢትዮጵያ የታሰበላት በአሰብ በኩል ነፃ የባሕር ግንኙነት ለማግኘት መቻል ብቻ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ግን ይህን ዕቅድ አልተቀበለውም። ዕቅዱ በአውሮፓ ይፋ ሲወጣም ብዙ ተቃውሞ ከማስነሣቱ የተነሣ ሁለቱ ሚኒስትሮች ከሥራቸው ለመሰናበት ተገደዋል።



ጦርነቱ እየገፋ ሲሄድ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል አንዳንድ የምስጢር ግንኙነቶች ተደርገዋል። በዚህም ረገድ አገናኝ ሆነው የሚያገለግሉት ኢትዮጵያውያንም የውጭ አገር ሰዎችም ነበሩ። ኢትዮጵያውያኑ ጦርነቱ ሲጀምር በሮማ የኢትዮጵያ መንግሥት ሚኒስትር የነበረው አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሲሆኑ፣ የውጭ አገር ዜጎቹ ደግሞ ጃሲር ቤይ የሚባል ፍልስጤማዊ፣ ኢጣልያዊው ምሁርና ኋላ ምክትል እንደራሴ የሆነው ኤንሪኮ ቼሩሊ እና የኃይለ ሥላሴ የግል ሐኪም የነበረው ግሪኩ አድርያን ዜርቮስ ነበሩ። በጣልያኖች በኩል፣ የጦር ሜዳው ፍልሚያ እየሠመረላቸው ስለሄደ ይመስላል፣ በሆር ላቫል ዕቅድ ከተተለመላቸው የበለጠ እንጂ ያነሰ ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም። በአዲሱ የእርቅ ሐሳብ የኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ከሸዋ እንዳያልፍ ተከልሎ ነበር። ከጭንቀት ይመስላል የኢጣልያን አገዛዝ ለማምለጥ ኃይለ ሥላሴ የእንግሊዝን ሞግዚትነት እስከመጠየቅም ደርሶ ነበር ይባላል። በተመሳሳይ መንገድ 1928 ማለቂያ ላይ የወለጋ ባላባቶች «የምዕራብ ጋላ ኮንፌዴሬሽን» የሚባል ኅብረት በመፍጠር የእንግሊዝን ሞግዚታዊ አስተዳደር ጠይቀው ነበር።

ጣልያኖች የመጨረሻውን ድል አግኝተው ንጉሠ ነገሥቱም ከተሰደደ በኋላ እነዚህ የምስጢር ግንኙነቶች ቀጥለው ነበር። በዚህን ወቅት አገናኝ ሆኖ የሚያገለግለው ግብፃዊው ልዑል መሐመድ ኢክነም ሪዛ ነበር። ጣልያኖች ያቀረቡት አንዱ ሐሳብ የገንዘብ ካሣ ተደርጎለት ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣኑን በይፋ እንዲለቅ ነው። የገንዘብ አቅሙ ከጊዜ ወደጊዜ እየደቀቀ ለመጣው ንጉሠ ነገሥት ይህ እጅግ የሚፈታተን ሐሳብ ነበር። ሆኖም ሐሳቡን ለመቀበል ስለተቸገረ ድርድሩ ፍሬ አላገኘም። ንጉሠ ነገሥቱም ከገንዘብ ክብርን መርጦ የኢጣልያ ወደ ሁለተኛው ዓለም ጦርነት መግባት እንደገና ወደ ማዕከላዊው መድረክ እስካወጣው ድረስ ባዝ በምትባለው በምዕራብ እንግሊዝ በምትገኝ አነስተኛ ከተማ በስደት ኖረ። ጣልያኖች በተመሳሳይ መንገድ ከአልጋ ወራሹ ከአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ጋር ያደረጉት ድርድርም ፍሬ አልባ ነበር።

ኢትዮጵያ ውስጥም ጣልያኖች በመጀመሪያ በገበሩላቸው መሳፍንት አማካይነት አገሪቱን ለማግዛት አስበው ነበር። ኋላ ግን ባንድ በኩል ጥቁር ለመገዛት እንጂ ለመግዛት ብቁ አይደለም ከሚል አስተሳሰብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አሠራሩ ፍጹማዊ የፋሽስት አገዛዝን የሚፃረር በመሆኑ ይህን ፖሊሲ ወደ ጎን ተዉት። መሳፍንቱም ማዕረጋቸውንና ወርሃዊ አበላቸውን ይዘው እንዲቀመጡ ተደረጉ። በዚህም መሠረት ለምሳሌ ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት 40000 ሊሬ፣ ለራስ አባተ ቧያለው ልጅና በተከታታይ ሚኒስትር፣ አምባሳደርና አገረ ገዥ ለነበረው ራስ ጌታቸው አባተ 7000 ሊሬ ሲቆረጥላቸው፣ ሌሎች መሳፍንት

ደግሞ እንደየማዕረጋቸውና ተፈላጊነታቸው በሁለቱ አጋዞች መሀል የሚገኝ አበል ተመድቦላቸው ነበር። ነገር ግን ይህም አልዘለቀላቸውም። የካቲት 12፣ 1929 በግራዚያኒ ላይ ቦምብ በመጣሉ ምክንያት ፋሽስቶች እንዳበደ ውሻ ሁሉንም ሲለክፉ እነዚህ አሜን ብለው የገቡላቸውን መሳፍንትም አልማሩም ነበር። ብዙዎቹ ወደ ኢጣልያ ተጋዙ። እንደገና የፋሽስቱን መንግሥት ሞገስ ያገኙት በዱክ ኦፍ አኦስታ ለዘብተኛ አስተዳደር ዘመን ነው። በ1931 እንደገና ወዳገራቸው እንዲመለሱ ተደርጎ አንዳንዶቹ በአማካሪነትና በዳኝነት ሥራ ሲመደቡ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ የማዕረግ እድገት አግኝተው በቀድሞ ግዛታቸው ላይ ተሾሙ። በዚህም መሠረት ራስ ኃይሉ ወደ ጎጃም፣ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ወደ ትግራይ ሲመለሱ፣ ደጃች አያሌው ብሩም ራስ ተብሎ የአማራ ግዛት ጠቅላይ እንደራሴ ሆኖ ተሾመ። ይሁን እንጂ ጣልያኖች ሕዝቡን ለመያዝ የወሰዱት እንዲህ ያለ እርምጃ ዘግይቶ የመጣ በመሆኑ ከመጭው ጥፋት አላዳናቸውም።

የጣልያን አገዛዝ ከተመሠረተ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ አገር አቀፍ የሆነ ተቃውሞ ነው ያጋጠመው። ምንም እንኳ ጣልያኖች በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ተቃውሞውን ለማዳከም ቢሞክሩም፣ ሰጥ ለጥ ብሎ የተገዛላቸው አንድም ክልል ወይም ብሔረሰብ አልነበረም። ፀረ ጣልያን ተቃውሞውን በሁለት ዐቢይ ምዕራፎች ከፍሎ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ምዕራፍ ከግራዚያኒ እልቂት በፊት የነበረው ሲሆን እሱም በመሠረቱ የጦርነቱ ተከታይ የሆነ፣ ከመደበኛ ጦርነት እምብዛም ያልተለየና ባብዛኛውም በመሳፍንቱ የሚመራ የነበረ ነው። ከዓይነተኛ ባሕርዮቹ አንዱም ማወላወልና ለመደራደርም ዝግጁነት ማሳየት ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ ከግራዚያኒ እልቂት በኋላ የነበረው ሲሆን መልኩም ባብዛኛው በዝቅተኛ መኳንንት የሚመራ የደፈጣ ውጊያ ነው። ዝቅ ብለን እንደምናየው አንዳንድ መሠረታዊ ድክመቶች ቢኖሩትም ይህ ምዕራፍ የኢጣልያን አገዛዝ እምርሮና ያለማመንታት የሚቃወም ነበር።

በመጀመሪያው ምዕራፍ ተቃውሞ የመሪነቱን ሥፍራ በመያዝ ጎላ ብለው የሚታዩት ራስ እምሩ፣ ራስ ደስታና ወንድማማቾቹ አበራና አስፋወሰን ካሣ (የራስ ካሣ ልጆች) ናቸው። ቀደም ብለን እንዳየነው በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ራስ እምሩ በሽሬ ግንባር ያሳየው የአመራር ችሎታ የሚደነቅ ነበር። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ጦር ከተፈታና በተለይም የጣልያኖችን የማይበገር የመሣሪያ ኃይል በቅርብ ከተመለከተ በኋላ ውጊያውን የመቀጠል ሐሞቱ ፈሰሰ። ንጉሠ ነገሥቱ ሲሰደድ እምሩን እንደራሴ አድርጎ ቢሰይመውም የፀረ ጣልያን ተቃውሞ አስተባባሪነትን ተግባር ለመሸከም ዝግጁ አልነበረም። እንዲያውም ተስፋ በመቁረጥ እሱም በበኩሉ ወደ ሱዳን ወይ ወደ ኬንያ ለመሰደድ ሐሳብ ነበረው። ነገር ግን እያፈገፈገ ጎሬ ሲደርስ፣ ባሳለበው መንገድ ራሱን ተበታትኖ የነበረው የኢትዮጵያ ኃይል ሁሉ አሰባሳቢና አለኝታ ሆኖ አገኘው። በዚያን ጊዜ ጎሬ ንጉሠ ነገሥቱ ከተሰደደ በኋላ እሱን ወክሉ የሚሠራ መንግሥት የተቋቋመበት መዲና ነበረች። ይህ «የጎሬ መንግሥት» በእርግጥ ሙሉ በሙሉ የመንግሥትነት ባሕርይ ነበረው ለማለት ቢያዳግትም፣ የኢጣልያን አገዛዝ ሕጋዊ ዕውቅና ለመንሣት ለሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ትግል መጠነኛ ጠቃሜታ ነበረው። የራስ እምሩን ወደ ጎሬ መምጣት በታላቅ ደስታ ከተመለከቱት ቡድኖች ዋነኛው ጥቁር አንበሳ በሚል ስም የሚታወቀው ምሁራንና የሆለታ ወጣት መኮንኖች ያቋቋሙት ድርጅት ነው።





4.5 ከፊት ለፊት በስተቀኝ ያለው፣ የሽሬ ጦር ግንባር አዛዥና የጥቁር አንበሳ ጦር መሪ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ

በተለይም ትግሉ ይቀጥል የሚል መልእክት በስደት ላይ ከሚገኘው ንጉሠ ነገሥት ይዤ መጥቻለሁ የሚለው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ልጅ ፊቃደ ሥላሴ ኅሩይ ራስ እምሩን ሳይወድ ገፋፍቶ የአርበኞች መሪ እንዲሆን በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ ይነገርለታል። እምሩ ከሰሜን ይዞ የመጣውን ጦር፣ የጥቁር አንበሳን ወጣት አርበኞችና በወለጋና ኢሉባቦር ሰፍረው የነበሩትን ነፍጠኞች አስተባብሮ በድፍረት ዘመቻውን ወደ አዲስ አበባ አቀና። ግን አዲስ አበባ እንዲህ ቅርብ አልነበረችም። ቀደም ብለው በነበረው አገዛዝ ያኮረፉት የኦሮሞ ነዋሪዎችም ጦሩ አገራቸውን አቋርጦ እንዲያልፍ ፈቃደኛ አልነበሩም። በተስፋና በቅልጥፍና የተነሣው የእምሩ ጦርም ያገሬው ሰው ያበረራቸው መጤዎች እየተጠጉት ጓዝ ብዙ ሆኖ እንዲሁ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሲንከራተት ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ጐጀብ ወንዝ አጠገብ ለጣላት እጁን ለመስጠት ተገደደ።

በደቡብ ኢትዮጵያ የራስ ደስታ ጦር በዶሎ ላይ የሰነዘረው ደፋር የማጥቃት እርምጃ ከሽፎበት ተሸማቆ ከተመለሰ በኋላ ጣልያኖችን ዕረፍት መንሣቱን አላቋረጠም። በዚህም፣ በተለይ መጀመሪያው ላይ በደጃች በየነ መርዕድ ጦርና

ደግሞ እንደየማዕረጋቸውና ተፈላጊነታቸው በሁለቱ አጋዞች መሀል የሚገኝ አበል ተመድቦላቸው ነበር:: ነገር ግን ይህም አልዘለቀላቸውም:: የካቲት 12፣ 1929 በግራዚያኒ ላይ ቦምብ በመጣሉ ምክንያት ፋሽስቶች እንዳበደ ውሻ ሁሉንም ሲለክፉ እነዚህ አሜን ብለው የገቡላቸውን መሳፍንትም አልማሩም ነበር:: ብዙዎቹ ወደ ኢጣልያ ተጋዙ:: እንደገና የፋሽስቱን መንግሥት ሞገስ ያገኙት በዱክ ኦፍ አኦስታ ለዘብተኛ አስተዳደር ዘመን ነው:: በ1931 እንደገና ወዳገራቸው እንዲመለሱ ተደርጎ አንዳንዶቹ በአማካሪነትና በዳኝነት ሥራ ሲመደቡ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ የማዕረግ እድገት አግኝተው በቀድሞ ግዛታቸው ላይ ተሾሙ:: በዚህም መሠረት ራስ ኃይሉ ወደ ጎጃም፣ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ወደ ትግራይ ሲመለሱ፣ ደጃች አያሌው ብሩም ራስ ተብሎ የአማራ ግዛት ጠቅላይ እንደራሴ ሆኖ ተሾመ:: ይሁን እንጂ ጣልያኖች ሕዝቡን ለመያዝ የወሰዱት እንዲህ ያለ እርምጃ ዘግይቶ የመጣ በመሆኑ ከመጭው ጥፋት አላዳናቸውም::

የጣልያን አገዛዝ ከተመሠረተ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ አገር አቀፍ የሆነ ተቃውሞ ነው ያጋጠመው:: ምንም እንኳ ጣልያኖች በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ተቃውሞውን ለማዳከም ቢሞክሩም፣ ሰጥ ለጥ ብሎ የተገዛላቸው አንድም ክልል ወይም ብሔረሰብ አልነበረም:: ፀረ ጣልያን ተቃውሞውን በሁለት ዐቢይ ምዕራፎች ከፍሎ ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው ምዕራፍ ከግራዚያኒ እልቂት በፊት የነበረው ሲሆን እሱም በመሠረቱ የጦርነቱ ተከታይ የሆነ፣ ከመደበኛ ጦርነት እምብዛም ያልተለየና ባብዛኛውም በመሳፍንቱ የሚመራ የነበረ ነው:: ከዓይነተኛ ባሕርዮቹ አንዱም ማወላወልና ለመደራደርም ዝግጁነት ማሳየት ነው:: ሁለተኛው ምዕራፍ ከግራዚያኒ እልቂት በኋላ የነበረው ሲሆን መልኩም ባብዛኛው በዝቅተኛ መኳንንት የሚመራ የደፈጣ ውጊያ ነው:: ዝቅ ብለን እንደምናየው አንዳንድ መሠረታዊ ድክመቶች ቢኖሩትም ይህ ምዕራፍ የኢጣልያን አገዛዝ አምርሮና ያለማመንታት የሚቃወም ነበር::

በመጀመሪያው ምዕራፍ ተቃውሞ የመሪነቱን ሥፍራ በመያዝ ጎላ ብለው የሚታዩት ራስ እምሩ፣ ራስ ደስታና ወንድማማቾቹ አበራና አስፋወሰን ካሣ (የራስ ካሣ ልጆች) ናቸው:: ቀደም ብለን እንዳየነው በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ራስ እምሩ በሽሬ ግንባር ያሳየው የአመራር ችሎታ የሚደነቅ ነበር:: ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ጦር ከተፈታና በተለይም የጣልያኖችን የማይበገር የመሣሪያ ኃይል በቅርብ ከተመለከተ በኋላ ውጊያውን የመቀጠል ሐሞቱ ፈሰሰ:: ንጉሠ ነገሥቱ ሲሰደድ እምሩን እንደራሴ አድርጎ ቢሰይመውም የፀረ ጣልያን ተቃውሞ አስተባባሪነትን ተግባር ለመሸከም ዝግጁ አልነበረም:: እንዲያውም ተስፋ በመቁረጥ እሱም በበኩሉ ወደ ሱዳን ወይ ወደ ኬንያ ለመሰደድ ሐሳብ ነበረው:: ነገር ግን እያፈገፈገ ጐሬ ሲደርስ፣ ባላሰበው መንገድ ራሱን ተበታትኖ የነበረው የኢትዮጵያ ኃይል ሁሉ አሰባሳቢና አለኝታ ሆኖ አገኘው:: በዚያን ጊዜ ጐሬ ንጉሠ ነገሥቱ ከተሰደደ በኋላ እሱን ወክሎ የሚሠራ መንግሥት የተቋቋመባት መዲና ነበረች:: ይህ «የጐሬ መንግሥት» በእርግጥ ሙሉ በሙሉ የመንግሥትነት ባሕርይ ነበረው ለማለት ቢያዳግትም፣ የኢጣልያን አገዛዝ ሕጋዊ ዕውቅና ለመንሣት ለሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ትግል መጠነኛ ጠቃሚታ ነበረው:: የራስ እምሩን ወደ ጐሬ መምጣት በታላቅ ደስታ ከተመለከቱት ቡድኖች ዋነኛው ጥቁር አንበሳ በሚል ስም የሚታወቀው ምሁራንና የሆለታ ወጣት መኰንኖች ያቋቋሙት ድርጅት ነው::





4.5 ከፊት ለፊት በስተቀኝ ያለው፣ የሽሬ ጦር ግንባር አዛዥና የጥቁር አንበሳ ጦር መሪ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ

በተለይም ትግሉ ይቀጥል የሚል መልእክት በስደት ላይ ከሚገኘው ንጉሠ ነገሥት ይዤ መጥቻለሁ የሚለው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ልጅ ፈቃደ ሥላሴ ኅሩይ ራስ እምሩን ሳይወድ ገፋፍቶ የአርበኞች መሪ እንዲሆን በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ ይነገርለታል:: እምሩ ከሰሜን ይዞ የመጣውን ጦር፣ የጥቁር አንበሳን ወጣት አርበኞችና በወለጋና ኢሉባቦር ሰፍረው የነበሩትን ነፍጠኞች አስተባብሮ በድፍረት ዘመቻውን ወደ አዲስ አበባ አቀና:: ግን አዲስ አበባ እንዲህ ቅርብ አልነበረችም:: ቀደም ብለው በነበረው አገዛዝ ያኰረፉት የኦሮሞ ነዋሪዎችም ጦሩ አገራቸውን አቋርጦ እንዲያልፍ ፈቃደኛ አልነበሩም:: በተስፋና በቅልጥፍና የተነሣው የእምሩ ጦርም ያገሬው ሰው ያባረራቸው መጤዎች እየተጠጉት ጓዘ ብዙ ሆኖ እንዲሁ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሲንከራተት ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ጐጀብ ወንዝ አጠገብ ለጠላት እጁን ለመስጠት ተገደደ::

በደቡብ ኢትዮጵያ የራስ ደስታ ጦር በዶሎ ላይ የሰነዘረው ደፋር የማጥቃት እርምጃ ከሸፎበት ተሸማቆ ከተመለሰ በኋላ ጣልያኖችን ዕረፍት መንሣቱን አላቋረጠም:: በዚህም፣ በተለይ መጀመሪያው ላይ በደጃች በየነ መርዕድ ጦርና



4.6 የደቡብ ጦር ግንባር አዛዥ ራስ ደስታ ዳምጠው በጣሊያኖች እጅ ከወደቀ በኋላ

በደጃች ገብረ ማርያም ጋሪ ጦር ይታገዝ ነበር። ጣልያኖች ባደረጉት ራስ ደስታን የማደን ዘመቻዎች ግራዚያኒ ራሱም ተሳትፎ ነበር። በራስ ደስታ በኩል የታየው አንድ ድክመት ተቃውሞውን በመቀጠልና እጅ በመስጠት መካከል ማወላወሉ ነው። እንደሚባለውም በትግሉ እንዲገፋበት ያስገደደው ወደሱ ጦር የገቡት ኤርትራውያን አስካሪዎች የነበራቸው የማያወላውል አቋም ነው። በነሱ ግምት እጅ መስጠት ማለት እርግጠኛ ሞት ስለነበር ጦርነቱን ከመቀጠል ሌላ አማራጭ አይታያቸውም ነበር። ይሁን እንጂ የደስታ ማወላወል ዞሮ ዞሮ የሌሎች ተከታዮቹን ሞራል ማዳከሙ አልቀረም። ስለዚህም መጀመሪያ የነበረው የሰው ኃይል እየመነመነ ሄዶ እሱም ከቦታ ቦታ ሲባረር በመጨረሻ በየካቲት 1929 በጉራጌ አገር ጎጌቲ በተባለ ስፍራ ተሸንፎ ተያዘ። ጣልያኖችም እንደ አደገኛ ጠላት የሚያዩትን ምርኮኛቸውን ሳይውል ሳያድር ረሸኑት። እንዳጋጣሚ ይህ ሁሉ የሆነው አዲስ አበባ የግራዚያኒ እልቂት በሚካሄድበት ወቅት ነው።

የመጀመሪያውን ምዕራፍ ተቃውሞ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው በ1928 ማለቂያ ላይ የተደረገው በቅጡም ያልተቀናጀው አዲስ አበባን የማጥቃት እርምጃ ነው። በእቅዱ መሠረት ከገጠር የአርበኞቹ ኃይል በተለያየ አቅጣጫ ሲያጠቃ፣ ከተማው ውስጥ ደግሞ ሕዝባዊ አመፅ ተቀስቅሶ የኢጣልያን አገዛዝ ባጭሩ



ለመቅጨት ነበር። ከገጠር የሚያጠቁት በሰሜን በኩል አበራና አስፋወሰን ካሣ፣ በደቡብ ደጃች ባልቻ ሳፎ፣ በሰሜን ምዕራብ ባላምባራስ (ኋላ ራስ) አበበ አረጋይ፣ በምሥራቅ ደግሞ ደጃች ፍቅረ ማርያም ይናዱ ነበሩ። የአርበኞቹን መንፈስ በማነቃቃት ከፍተኛ ሚና የተጫወተው የኢጣልያን አገዛዝ በጽኑ የሚቃወመው የወሎው ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ነበር። የሆነ ሆኖ ይህ ብዙ ኃይሎችን ያቀፈ እቅድ በኅብረት የጣልያንን ጦር ማጥቃቱ ቀርቶ የተበታተኑ ጀብዱዎች የታዩበት ሆነና ተሰናከሉ ቀረ። አቡነ ጴጥሮስ ተይዞ ሥቃይ ከበዛበት ምርመራ በኋላ በአደባባይ ተረሸኑ። አበራና አስፋወሰን እስከ መሀል ከተማ ድረስ ካጠቁ በኋላ ወደ ሰላሌ እንዲያፈገፍጉ ተገደዱ። ከዚያ በኋላ ራስ ኃይሉ ምንም አይደርስባችሁም ብሎ አግባብቷቸው እጃቸውን ከሰጡ በኋላ ጣልያኖች ያለምሕረት ረሸኗቸው። ደጃች ባልቻም ከጠላት ጦር ጋር ተናንቆ ሞተ።

የኢጣልያ ፋሺዝም ፅልመታዊ ገጽታ ቁልጭ ብሎ የወጣው በየካቲት 12፣ 1929 ነው። አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የተባሉ ሁለት ወጣቶች በግራዚያኒ ላይ ቦምብ ጥለው ካቆሰሉት በኋላ አዲስ አበባ ላይ መዓት ወረደባት። «ጥቁር ሸሚዝ» እየተባሉ የሚታወቁት የፋሽስት ደቀ መዛሙርት በፋሽስቱ አገዛዝ አይዞህ ባይነት አዲስ አበባን ቄራ አደረጓት። የሰው ልጅ ጭንቅላት እንደ ዶሮ እየተቀነጠሰ ወደቀ። ቤቶች ከነነዋሪዎቻቸው ጋዩ። እርጉዝ ሴቶች በሳንጃ ተወጉ። የጭፍጨፋው ተቀዳሚ ዒላማ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በተለይም የጥቁር አንበሳ አባላት ከራስ እምሩ ጋር እጃቸውን ከሰጡ በኋላ በከተማይቱ ይገኙ ስለነበር በወረንጦ እየተለቀሙ ተረሸኑ። ይህ የምሁራን ጭፍጨፋ አንድ ትውልድ እንዳለ ያጠፋ በመሆኑም ባገሪቱ የፖለቲካና ምሁራዊ ታሪክ ላይ የማይሽር ቁስል ጥሎ አለፈ። ይህ የፋሽስት ጭፍጨፋ በሌላ መልኩ በወራሪና ተወራሪ መካከል ያለውን ቅራኔ መካረር በማመልከት የፀረ ኢጣልያ ተቃውሞውም ከመጀመሪያው ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ፣ ከመደበኛ ወይም ከፊል መደበኛ ጦርነት ወደ ሽምቅ ውጊያ መሸጋገሩን አረጋገጠ።

ይህን ሁለተኛ የተቃውሞ ምዕራፍ በተመለከተ ማለት የሚቻለው አንድ ዐቢይ ነገር ሀገር አቀፍ መሆኑ ነው። ምንም እንኳ የአርበኞቹ እንቅስቃሴ ጎላ ብሎ የሚታየው በሸዋ፣ በጎጃምና በበጌምድር ቢሆንም ጣልያኖች ያለተቃውሞ የገዙት ክፍለ ሀገር አልነበረም። ሀገሪቱ በታደለችው የተፈጥሮ ምሽጎች እየተጠቀሙ ደፈጣ ተዋጊዎቹ ጣልያኖችን ጤናና ፋታ ነሷቸው። እንደሁኔታው አመችነት ስልታቸውን ከማጥቃት ወደ መከላከል፣ ከመከላከል ወደ ማጥቃት እየለወጡ የመገናኛ መሥመሮችን ይቆርጡ፣ በተነጣጠለ የጠላት ጦር ላይ አድፍጠው አደጋ ይጥሉ፣ ወይም ደግሞ ፊት ለፊት ጦርነት ይገጥሙ ነበር። እንደ ማንኛቸውም የደፈጣ ተዋጊዎች ሁሉ ትልቁ የትግል መሣሪያቸው በፍጥነት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀሳቸውና እንደ አስፈላጊነቱ ለመበታተንና ለመሰባሰብ መቻላቸው ነበር። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ የአየር መቃወሚያ መሣሪያ ባይኖራቸውም በዚህ የትግል ስልታቸው አማካይነት ጣልያኖችን መጀመሪያ በሁሉም ጦር ግንባር የነበራቸውን የአየር ላይ የበላይነት ነሷቸው።

የአርበኞቹ ዐቢይ ችግር የስንቅ እጥረት ነበር። ብዙውን ጊዜ ቀለባቸውን ማግኘት የሚችሉት መከረኛውን ባላገር በማስጨነቅ ሆነ። በዚህም ረገድ በየገበሬው ቤት ፋኖ እስከ መምራት ተደርሶ ነበር። ይሁን እንጂ ከዚህ ሻል ያለ ሠራዊቱን የመቀለብ ዘዴ መሞከሩ አልቀረም። በንዳንድ ቦታዎች ሠራዊቱ



4.6 የደቡብ ጦር ግንባር አዛዥ ራስ ደስታ ዳምጠው በጣሊያኖች እጅ ከወደቀ በኋላ

በደጃች ገብረ ማርያም ጋሪ ጦር ይታገዝ ነበር። ጣልያኖች ባደረጉት ራስ ደስታን የማደን ዘመቻዎች ግራዚያኒ ራሱም ተሳትፎ ነበር። በራስ ደስታ በኩል የታየው አንድ ድክመት ተቃውሞውን በመቀጠልና እጅ በመስጠት መካከል ማወላወሉ ነው። እንደሚባለውም በትግሉ እንዲገፋበት ያስገደደው ወደሱ ጦር የገቡት ኤርትራውያን አስካሪዎች የነበራቸው የማያወላውል አቋም ነው። በነሱ ግምት እጅ መስጠት ማለት እርግጠኛ ሞት ስለነበር ጦርነቱን ከመቀጠል ሌላ አማራጭ አይታያቸውም ነበር። ይሁን እንጂ የደስታ ማወላወል ዞሮ ዞሮ የሌሎች ተከታዮቹን ሞራል ማዳከሙ አልቀረም። ስለዚህም መጀመሪያ የነበረው የሰው ኃይል እየመነመነ ሄዶ እሱም ከቦታ ቦታ ሲባረር በመጨረሻ በየካቲት 1929 በጉራጌ አገር ጎጌቲ በተባለ ስፍራ ተሸንፎ ተያዘ። ጣልያኖችም እንደ አደገኛ ጠላት የሚያዩትን ምርኮኛቸውን ሳይውል ሳያድር ረሸኑት። እንዳጋጣሚ ይህ ሁሉ የሆነው አዲስ አበባ የግራዚያኒ እልቂት በሚካሄድበት ወቅት ነው።

የመጀመሪያውን ምዕራፍ ተቃውሞ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው በ1928 ማለቂያ ላይ የተደረገው በቅጡም ያልተቀናጀው አዲስ አበባን የማጥቃት እርምጃ ነው። በእቅዱ መሠረት ከገጠር የአርበኞቹ ኃይል በተለያየ አቅጣጫ ሲያጠቃ፣ ከተማው ውስጥ ደግሞ ሕዝባዊ አመፅ ተቀስቅሶ የኢጣልያን አገዛዝ ባጭሩ



ለመቅጨት ነበር። ከገጠር የሚያጠቁት በሰሜን በኩል አበራና አስፋወሰን ካሣ፣ በደቡብ ደጃች ባልቻ ሳፎ፣ በሰሜን ምዕራብ ባላምባራስ (ኋላ ራስ) አበበ አረጋይ፣ በምሥራቅ ደግሞ ደጃች ፍቅረ ማርያም ይናዱ ነበሩ። የአርበኞቹን መንፈስ በማነቃቃት ከፍተኛ ሚና የተጫወተው የኢጣልያን አገዛዝ በጽኑ የሚቃወመው የወሎው ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ነበር። የሆነ ሆኖ ይህ ብዙ ኃይሎችን ያቀፈ እቅድ በንብረት የጣልያንን ጦር ማጥቃቱ ቀርቶ የተበታተኑ ጀብዱዎች የታዩበት ሆነና ተሰናክሎ ቀረ። አቡነ ጴጥሮስ ተይዞ ሥቃይ ከበዛበት ምርመራ በኋላ በአደባባይ ተረሸነ። አበራና አስፋወሰን እስከ መሀል ከተማ ድረስ ካጠቁ በኋላ ወደ ሰላሌ እንዲያፈገፍጉ ተገደዱ። ከዚያ በኋላ ራስ ኃይሉ ምንም አይደርስባችሁም ብሎ አግባብቷቸው እጃቸውን ከሰጡ በኋላ ጣልያኖች ያለምሕረት ረሸኗቸው። ደጃች ባልቻም ከጠላት ጦር ጋር ተናንቆ ሞተ።

የኢጣልያ ፋሺዝም ፅልመታዊ ገጽታ ቁልጭ ብሎ የወጣው በየካቲት 12፣ 1929 ነው። አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የተባሉ ሁለት ወጣቶች በግራዚያኒ ላይ ቦምብ ጥለው ካቆሰሉት በኋላ አዲስ አበባ ላይ መዓት ወረደባት። «ጥቁር ሸሚዝ» እየተባሉ የሚታወቁት የፋሽስት ደቀ መዛሙርት በፋሽስቱ አገዛዝ አይዞህ ባይነት አዲስ አበባን ቄራ አደረጓት። የሰው ልጅ ጭንቅላት እንደ ዶሮ እየተቀነጠሰ ወደቀ። ቤቶች ከነነዋሪዎቻቸው ጋዩ። እርጉዝ ሴቶች በሳንጃ ተወጉ። የጭፍጨፋው ተቀዳሚ ዒላማ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በተለይም የጥቁር አንበሳ አባላት ከራስ እምሩ ጋር እጃቸውን ከሰጡ በኋላ በከተማይቱ ይገኙ ስለነበር በወረንጦ እየተለቀሙ ተረሸኑ። ይህ የምሁራን ጭፍጨፋ አንድ ትውልድ እንዳለ ያጠፋ በመሆኑም ባገሪቱ የፖለቲካና ምሁራዊ ታሪክ ላይ የማይሽር ቁስል ጥሎ አለፈ። ይህ የፋሽስት ጭፍጨፋ በሌላ መልኩ በወራሪና ተወራሪ መካከል ያለውን ቅራኔ መካረር በማመልከት የፀረ ኢጣልያ ተቃውሞውም ከመጀመሪያው ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ፣ ከመደበኛ ወይም ከፊል መደበኛ ጦርነት ወደ ሽምቅ ውጊያ መሸጋገሩን አረጋገጠ።

ይህን ሁለተኛ የተቃውሞ ምዕራፍ በተመለከተ ማለት የሚቻለው አንድ ዐቢይ ነገር ሀገር አቀፍ መሆኑ ነው። ምንም እንኳ የአርበኞቹ እንቅስቃሴ ጎላ ብሎ የሚታየው በሸዋ፣ በጎጃምና በበጌምድር ቢሆንም ጣልያኖች ያለተቃውሞ የገዙት ክፍለ ሀገር አልነበረም። ሀገሪቱ በታደለችው የተፈጥሮ ምሽጎች እየተጠቀሙ ደፈጣ ተዋጊዎቹ ጣልያኖችን ጤናና ፋታ ነሷቸው። እንደሁኔታው አመችነት ስልታቸውን ከማጥቃት ወደ መከላከል፣ ከመከላከል ወደ ማጥቃት እየለወጡ የመገናኛ መሥመሮችን ይቆርጡ፣ በተነቃናቂ የጠላት ጦር ላይ አድፍጠው አደጋ ይጥሉ፣ ወይም ደግሞ ፊት ለፊት ጦርነት ይገጥሙ ነበር። እንደ ማንኛቸውም የደፈጣ ተዋጊዎች ሁሉ ትልቁ የትግል መሣሪያቸው በፍጥነት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀሳቸውና እንደ አስፈላጊነቱ ለመበታተንና ለመሰባሰብ መቻላቸው ነበር። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ የአየር መቃወሚያ መሣሪያ ባይኖራቸውም በዚህ የትግል ስልታቸው አማካይነት ጣልያኖችን መጀመሪያ በሁሉም ጦር ግንባር የነበራቸውን የአየር ላይ የበላይነት ነሷቸው።

የአርበኞቹ ዐቢይ ችግር የስንቅ እጥረት ነበር። ብዙውን ጊዜ ቀለባቸውን ማግኘት የሚችሉት መከረኛውን ባላገር በማስጨነቅ ሆነ። በዚህም ሬገድ በየገበሬው ቤት ፋኖ እስከ መምራት ተደርሶ ነበር። ይሁን እንጂ ከዚህ ሻል ያለ ሠራዊቱን የመቀለብ ዘዴ መሞከሩ አልቀረም። ባንዳንድ ቦታዎች ሠራዊቱ



4.7 በማርሻል ግራዚያኒ ላይ ቦምብ ከመጣሉ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት

በሁለት ተከፍሎ «ደረቅ ጦር» የተባለው ሙሉ በሙሉ በውጊያው ላይ ሲያተኩር «መደዴ ጦር» የተባለው ግን ውጊያው ተግ ሲል በእርሻ ተግባር እንዲሠማራ ተደርጓል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ከጠላት ጋር ያበሩ ሰዎችን እህል በመዝረፍ ሕሊናን ብዙ በማያውክ መንገድ የሠራዊቱን ቀለብ ማበራከት ተችሏል። ሲከፋ ሲከፋ ደግሞ የዱር አራዊት ማደንና ፍራፍሬ እየለቀሙ መብላትም የተለመደ ነበር። ሌላው የአርበኞቹ ችግር መድኃኒት ነበር። ጠላት መሀል ሆነው ከሚቦረቡሩት የውስጥ አርበኞች ጋር ግንኙነት ኖሯቸው መድኃኒት ካላገኙ በቀር፣ ያላቸው ምርጫ በባሕላዊ ወጌሻዎችና መድኃኒት የተወሰነ ነበር። የጦር መሣሪያን በተመለከተ ደግሞ አርበኞቹ ትጥቃቸውን የማያደረጁባቸው ሁለት ዋና መንገዶች በምርኮና ጠላትን ከድተው በሚቀላቀሏቸው ተዋጊዎች አማካይነት ነው። በሌላ ጊዜ ደግሞ የጠላትን አውሮፕላን አቅጣጫ በማሳት ስንቅና ትጥቅ አርበኞች በመሸጉበት አካባቢ እንዲጥል ያስደርጉ ነበር።

ፋኖዎቹ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴም ነበራቸው። ወደ ጠላት ጦር ጠጋ ብለው የሚያደፍጡ ቃፊሮች የጠላትን ጦር እንቅስቃሴ ይዘግቡላቸው ነበር። ከሁሉም በላይ መረጃ በመሰብሰብ በኩል ቁልፍ ሚና የተጫወቱት ግን የውስጥ አርበኞች ነበሩ። ከጠላት ጋር አብረው እየዋሉ እያደሩ፣ የጠላትን ጦር ጥንካሬ፣ የታለሙ ዘመቻዎችንም ሆነ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ አርበኞቹን አስቀድመው በማስጠንቀቅ የጠላትን ዕቅዶች ያጨናግፉ ነበር። ከዚያም አልፈው በአስተዳደሩ ውስጥ ባላቸው ኃላፊነት በመጠቀም ለአርበኞቹ የሐሰት የይለፍ





4.8 በማርሻል ግራዚያኒ ላይ ቦምብ ከመጣሉ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ

ፈቃድና መታወቂያ ወረቀት ያወጡ፣ ጠላት ለሚያሳድዳቸውም መሸሸጊያ ይሰጡ ነበር። ምግብ፣ ልብስና መድኃኒትም ያቀርቡላቸው ነበር። አንዳንዶቹም የሚያውቋቸውን የኢጣልያን ባለሥልጣኖች በመማጠን በተያዙ አርበኞች ላይ የሚተላለፈውን ፍርድ ያለዝቡ ነበር። ይህ ሕጋዊ ሽፋናቸውን እንደጠበቁ የሚያደርጉት ሲሆን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ማንነታቸውን በመሸሸግ ተቋማትን በማፍረስና በሽብር ፈጠራ ተግባርም ይሠማሩ ነበር።

ለዚህም ሁሉ ሥራ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ስለማይጠረጠሩ በተለይ ያመቹ ነበሩ። ከሴቶች የውስጥ አርበኞችም ከፍተኛ ዝና ያገኙችው አርበኞች አዲስ ዓለም የመሸገውን የጠላት ጦር እንዲደመስሱ ሁኔታዎችን ያመቻቸችላቸው ሸዋረገድ ገድሌ ናት። የውስጥ አርበኞች ድርጅት ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ የቻለው በሁለቱ ከተሞች፣ በአዲስ አበባና በጐንደር፣ ነው። በተለይም በዋና ከተማው የምድር ባቡር ሠራተኞች በመዋቅሩ የተጫወቱት ቁልፍ ሚና እንቅስቃሴውን ላብ አደራዊ ባሕርይ ሰጥቶት ነበር። ባጠቃላይ ጣልያኖች ናላቸው የዞረው አርበኞቹ ከሚያደርሱባቸው ጥቃት ይልቅ የውስጥ አርበኞቹ በሚያደርጉባቸው ግዝገዛ ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም አርበኞቹ በርቀት የሚወጓቸው ሲሆኑ፣ የውስጥ አርበኞቹ ግን እነሱኑ መስለው፣ አንዳንዴም ቢጠራጠሩ እንኳ እንዳይያዙ የሽፋን ስም እየተጠቀሙ በመሆኑ ነው።



4.7 በማርሻል ግራዚያኒ ላይ ቦምብ ከመጣሉ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት

በሁለት ተከፍሎ «ደረቅ ጦር» የተባለው ሙሉ በሙሉ በውጊያው ላይ ሲያተኩር «መደዴ ጦር» የተባለው ግን ውጊያው ተግ ሲል በእርሻ ተግባር እንዲሠማራ ተደርጓል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከጠላት ጋር ያበሩ ሰዎችን እህል በመዝረፍ ሕሊናን ብዙ በማያውክ መንገድ የሠራዊቱን ቀለብ ማበራከት ተችሏል፡፡ ሲከፋ ሲከፋ ደግሞ የዱር አራዊት ማደንና ፍራፍሬ እየለቀሙ መብላትም የተለመደ ነበር፡፡ ሌላው የአርበኞቹ ችግር መድኃኒት ነበር፡፡ ጠላት መሀል ሆነው ከሚቦረቡሩት የውስጥ አርበኞች ጋር ግንኙነት ኖሯቸው መድኃኒት ካላገኙ በቀር፣ ያላቸው ምርጫ በባሕላዊ ወጌሻዎችና መድኃኒት የተወሰነ ነበር፡፡ የጦር መሣሪያን በተመለከተ ደግሞ አርበኞቹ ትጥቃቸውን የማያደረጁባቸው ሁለት ዋና መንገዶች በምርኮና ጠላትን ከድተው በሚቀላቀሏቸው ተዋጊዎች አማካይነት ነው፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ የጠላትን አውሮፕላን አቅጣጫ በማሳት ስንቅና ትጥቅ አርበኞች በመሸጉበት አካባቢ እንዲጥል ያስደርጉ ነበር፡፡

ፋኖዎቹ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴም ነበራቸው፡፡ ወደ ጠላት ጦር ጠጋ ብለው የሚያደፍጡ ቃፊሮች የጠላትን ጦር እንቅስቃሴ ይዘግቡላቸው ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ መረጃ በመሰብሰብ በኩል ቁልፍ ሚና የተጫወቱት ግን የውስጥ አርበኞች ነበሩ፡፡ ከጠላት ጋር አብረው እየዋሉ እያደሩ፣ የጠላትን ጦር ጥንካሬ፣ የታለሙ ዘመቻዎችንም ሆነ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ አርበኞቹን አስቀድመው በማስጠንቀቅ የጠላትን ዕቅዶች ያጨናግፉ ነበር፡፡ ከዚያም አልፈው በአስተዳደሩ ውስጥ ባላቸው ኃላፊነት በመጠቀም ለአርበኞቹ የሐሰት የይለፍ





4.8 በማርሻል ግራዚያኒ ላይ ቦምብ ከመጣሉ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ

ፈቃድና መታወቂያ ወረቀት ያወጡ፣ ጠላት ለሚያሳድዳቸውም መሸሸጊያ ይሰጡ ነበር፡፡ ምግብ፣ ልብስና መድኃኒትም ያቀርቡላቸው ነበር፡፡ አንዳንዶም የሚያውቋቸውን የኢጣልያን ባለሥልጣኖች በመማጠን በተያዙ አርበኞች ላይ የሚተላለፈውን ፍርድ ያለዝቡ ነበር፡፡ ይህ ሕጋዊ ሽፋናቸውን እንደጠበቁ የሚያደርጉት ሲሆን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ማንነታቸውን በመሸሸግ ተቋማትን በማፍረስና በሽብር ፈጠራ ተግባርም ይሠማሩ ነበር፡፡

ለዚህም ሁሉ ሥራ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ስለማይጠረጠሩ በተለይ ያመቹ ነበሩ፡፡ ከሴቶች የውስጥ አርበኞችም ከፍተኛ ዝና ያገኘችው አርበኞች አዲስ ዓለም የመሸገውን የጠላት ጦር እንዲደመስሱ ሁኔታዎችን ያመቻቸችላቸው ሸዋረገድ ገድሌ ናት፡፡ የውስጥ አርበኞች ድርጅት ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ የቻለው በሁለቱ ከተሞች፣ በአዲስ አበባና በጐንደር፣ ነው፡፡ በተለይም በዋና ከተማው የምድር ባቡር ሠራተኞች በመዋቅሩ የተጫወቱት ቁልፍ ሚና እንቅስቃሴውን ላብ አደራዊ ባሕርይ ሰጥቶት ነበር፡፡ ባጠቃላይ ጣልያኖች ናላቸው የዞረው አርበኞቹ ከሚያደርሱባቸው ጥቃት ይልቅ የውስጥ አርበኞቹ በሚያደርጉባቸው ግዝገዛ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አርበኞቹ በርቀት የሚወጓቸው ሲሆኑ፣ የውስጥ አርበኞቹ ግን እነሱኑ መስለው፣ አንዳንዶም ቢጠራጠሩ እንኳ እንዳይያዙ የሽፋን ስም እየተጠቀሙ በመሆኑ ነው፡፡



4.9 ስመ ጥሩዋ የውስጥ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ

እዚህ ላይ የአርበኞቹን የትግል ስልት በተመለከተ ሊጠቀስ የሚገባው አንድ ሌላ ነገር አንዳንዴ የሚጠቀሙበት የማዘናጋት ታክቲክ ነው። በተለይም በ1932 ራስ አበበ አረጋይ የኢጣልያን ሹማምንት እጁን ለመስጠት ዝግጁ ነኝ ብሎ ማቂሉ ለዚህ አንድ ጥሩ ማስረጃ ነው። እንዲህ ያለ የመታለል ፅዋ የደረሰበትም ምክትል እንደራሴና የሸዋ ገዥ የነበረው ጄኔራል ናዚ ነው። አበበ ለናዚ እጅ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ይግለጽ እንጂ በጎን ለሌሎች የአርበኞች መሪዎች ይህ ሁሉ ፋታ ለማግኘት እንጂ ከምር እንዳልሆነ በስውር ልኮባቸው ነበር። የሆነ ሆኖ እውነቱን ሊጠረጥር ያልቻለው ናዚ በነገሩ ተታሎ የሰላም ድርድሩን ከልቡ ተያይዞት ነበር። በመጨረሻ ራስ አበበ ጠሩ ቀደም ብሎ ከደረሰበት ጥቃት ማገገሙን በቅጡ ካረጋገጠ በኋላ፣ ጣልያኖች በሌሎች አርበኞች ላይ ያደረሱትን አንድ ዕልቂት ሰበብ በማድረግ ድርድሩን አፍርሶ ትግሉን ቀጥሏል።

በአጠቃላይ መልኩ ስናየው የአርበኞች የነፃነት ትግል በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ አኩሪ ምዕራፍ ነው። ኢትዮጵያውያን ለአርነትና ለነፃነት ሲሉ ለመሞት ዝግጁ ለመሆናቸው አንድ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ትግሉን የበለጠ ግምት የሚያሰጠው የወራሪውን ኃይልና ጭካኔ በመገንዘብ አመቺ የሆኑ




አዲስ ስልቶች ለመቀየስ መቻሉ ነው። አርበኞች በጠላት ላይ ያገኗቸው ድሎች የወሳኝነት ባሕርይ ባይኖራቸውም የኢጣልያ ሠራዊት በአርበኞች ጥቃት ተደናብሮና ተንሳቅሎ በመጨረሻ እንግሊዞች አገሪቱን ነፃ ለማውጣት ለከፈቱት ዘመቻ ክፉኛ ተጋለጠ።

ይህን ካልን በኋላ ግን የአርበኞቹ ተጋድሎ ያሳያቸውን አንዳንድ ድክመቶች ሳንጠቁም ብናልፍ ከነፃነት በኋላ ባገሪቱ የሰፈነውን ሥርዓት በቅጡ ለመረዳት ያዳግተናል። መጀመሪያ ነገር የነፃነት ትግሉ በሰፊት አገር አቀፍ ቢሆንም ቅሉ በጥልቀት ሁሉን አቀፍ አልነበረም። በታሪክ ተደጋግሞ እንደሚታየው ለአርነት ተጋድሎ ባለበት ሥፍራ ሁሉ፣ ከጨቋኝ ጋር አብሮ መሥራትም (ባንዳነትም) አለ። በዚህ መሠረትም አያሌ ኢትዮጵያውያን በግል ጥቅም ተታለው ወይም «ራስክን አድን» በሚለው መርህ የኢጣልያን ባንዳ ሆነዋል። ውስጠ ዐዋቂ በመሆናቸውም እነዚህ ባንዳዎች በአርነት ትግሉ ላይ የኢጣልያ ሠራዊት ካደረሰው የበለጠ ጉዳት አድርሰዋል። ይህም ሆኖ ግን ነፃነት ከተመለሰ ወዲህ በስደተኞችና በባንዳዎች መካከል የተፈጠረው ግንባር ተጠቃሚ በመሆን ከቅጣትና ውርደት ይልቅ የጠበቃቸው ሹመትና ሽልማት ነበር።

ለነፃነት ለመታገል በቆረጡት መሀልም ቢሆን ብዙውን ጊዜ ከኅብረት ይልቅ ልዩነት ነበር የሚታየው። በአያሌ የሽምቅ ተዋጊ ቡድኖች መካከል የሰፈነው ስሜት የጎጠኝነትና የእርስ በርስ መፎካከር ነበር። የአንድ ጓድ አባላት አፈንግጠው ከሌላው መቀላቀል፣ ይህም የሚያስከትለው የአንዱ ማበጥና የሌላው መኰስመን ግንኙነቶችን ለማቃቃር ረድቶ ነበር። ስለሆነም አርበኞቹ ብዙ ጊዜ ጠላትን አብረው ከመውጋት ይልቅ እርስ በርስ መፋጀቱን ነበር የተያያዙት። ለዚህም ሁኔታ በምሳሌነት መጥቀስ የሚቻለው በጎጃም በደጃች መንገሻ ጀምበሬና በደጃች ነጋሽ በዛብህ መካከል፣ እንዲሁም በልጅ ኃይሉ በለውና በልጅ በላይ ዘለቀ መካከል የነበረውን ችግር ነው። በአርበኞቹ መካከል ኅብረት ለመፍጠር ያዳገተው የሚጋሩት ርእዮትና የፖለቲካ ድርጅት ቀርቶ ሁሉም መሪያችን ብሎ የሚመለከተው አንድ ሰው ባለመኖሩ ነው።

አርበኛው ያውራ ያለህ በማለቱ ይመስላል አሁንም ስሙ ያልሞተው የኢያሱ ልጆች ፊት መኖራቸው እንኳ ያልታወቀውን ያህል በችግሩ ጊዜ የአርበኞች መሰባሰቢያ አድባር ለመሆን የበቁት። በዚህም መሠረት ዮሐንስ ኢያሱ የጉንደርን አርበኞች ሲያስተባብር፣ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ደግሞ የሸዋ አርበኞች አውራ ሆኖ ማዕረግና ሹመት ሊሰጥ ችሏል (ለምሳሌ አበበ አረጋይን ራስ ማለትን)። ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ደግሞ ሪፑብሊካዊ ዝንባሌ የነበረው ታከለ ወልደ ሐዋርያት ከክፍለ ሀገር ክፍለ ሀገር እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሱዳን፣ ከሱዳን ኢትዮጵያ በመመላለስ አርበኞቹን በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጥላ ሥር ለማሰባሰብ ያልተሳካ ሙከራ አድርጓል። የአርበኞቹ ትግል የጉጠኝነት ባሕርዩን እንደያዘ በመዝለቁም ግልጽ የሆነ የፖለቲካ አቅጣጫ ማግኘት ተስኖታል። ፖለቲካዊው በወታደራዊ፣ እስትራቴጂው በታክቲክ ተውጦ ቀርቷል።

ይህን ድክመት በመጠኑ ሊያካክሱ የቻሉ ሁለት ክስተቶች ነበሩ። እነዚህም የጥቁር አንበሳ ድርጅትና በሱዳን በነበሩ ስደተኞች ዘንድ የተጀመረው ሪፑብሊካዊ ንቅናቄ ናቸው። እርግጥ ሁለቱም በነፃነት ትግሉ ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ ውሱን ነበር። የመጀመሪያው ጣልያኖች በገቡ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ባጭሩ ሲቀጭ፣ ሁለተኛው ደግሞ ካገሪቷ ክልል ውጭ የሚካሄድ



4.9 ስመ ጥሩዋ የውስጥ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ

እዚህ ላይ የአርበኞቹን የትግል ስልት በተመለከተ ሊጠቀስ የሚገባው አንድ ሌላ ነገር አንዳንዴ የሚጠቀሙበት የማዘናጋት ታክቲክ ነው። በተለይም በ1932 ራስ አበበ አረጋይ የኢጣልያን ሹማምንት እጁን ለመስጠት ዝግጁ ነኝ ብሎ ማቄሉ ለዚህ አንድ ጥሩ ማስረጃ ነው። እንዲህ ያለ የመታለል ፅዋ የደረሰበትም ምክትል እንደራሴና የሸዋ ገዥ የነበረው ጄኔራል ናዚ ነው። አበበ ለናዚ እጅ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ይግለጽ እንጂ በጎን ለሌሎች የአርበኞች መሪዎች ይህ ሁሉ ፋታ ለማግኘት እንጂ ከምር እንዳልሆነ በስውር ልኮባቸው ነበር። የሆነ ሆኖ እውነቱን ሊጠረጥር ያልቻለው ናዚ በነገሩ ተታሎ የሰላም ድርድሩን ከልቡ ተያይዞት ነበር። በመጨረሻ ራስ አበበ ጦሩ ቀደም ብሎ ከደረሰበት ጥቃት ማገገሙን በቅጡ ካረጋገጠ በኋላ፣ ጣልያኖች በሌሎች አርበኞች ላይ ያደረሱትን አንድ ዕልቂት ሰበብ በማድረግ ድርድሩን አፍርሶ ትግሉን ቀጥሏል።

በአጠቃላይ መልኩ ስናየው የአርበኞች የነፃነት ትግል በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ አኩሪ ምዕራፍ ነው። ኢትዮጵያውያን ለአርነትና ለነፃነት ሲሉ ለመሞት ዝግጁ ለመሆናቸው አንድ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ትግሉን የበለጠ ግምት የሚያሰጠው የወራሪውን ኃይልና ጭካኔ በመገንዘብ አመቺ የሆኑ አዲስ ስልቶች ለመቀየስ መቻሉ ነው። አርበኞች በጠላት ላይ ያገኟቸው ድሎች የወሳኝነት ባሕርይ ባይኖራቸውም የኢጣልያ ሠራዊት በአርበኞች ጥቃት ተደናብሮና ተንሳቁሎ በመጨረሻ እንግሊዞች አገሪቱን ነፃ ለማውጣት ለከፈቱት ዘመቻ ክፉኛ ተጋለጠ።

ይህን ካልን በኋላ ግን የአርበኞቹ ተጋድሎ ያሳያቸውን አንዳንድ ድክመቶች ሳንጠቁም ብናልፍ ከነፃነት በኋላ ባገሪቱ የሰፈነውን ሥርዓት በቅጡ ለመረዳት ያዳግተናል። መጀመሪያ ነገር የነፃነት ትግሉ በስፋት አገር አቀፍ ቢሆንም ቅሉ በጥልቀት ሁሉን አቀፍ አልነበረም። በታሪክ ተደጋግሞ እንደሚታየው ለአርነት ተጋድሎ ባለበት ሥፍራ ሁሉ፣ ከጨቋኝ ጋር አብሮ መሥራትም (ባንዳነትም) አለ። በዚህ መሠረትም አያሌ ኢትዮጵያውያን በግል ጥቅም ተታለው ወይም «ራስክን አድን» በሚለው መርህ የኢጣልያን ባንዳ ሆነዋል። ውስጠ ዐዋቂ በመሆናቸውም እነዚህ ባንዳዎች በአርነት ትግሉ ላይ የኢጣልያ ሠራዊት ካደረሰው የበለጠ ጉዳት አድርሰዋል። ይህም ሆኖ ግን ነፃነት ከተመለሰ ወዲህ በስደተኞችና በባንዳዎች መካከል የተፈጠረው ግንባር ተጠቃሚ በመሆን ከቅጣትና ውርደት ይልቅ የጠበቃቸው ሹመትና ሽልማት ነበር።

ለነፃነት ለመታገል በቆረጡት መሀልም ቢሆን ብዙውን ጊዜ ከኅብረት ይልቅ ልዩነት ነበር የሚታየው። በአያሌ የሽምቅ ተዋጊ ቡድኖች መካከል የሰፈነው ስሜት የጎጠኝነትና የእርስ በርስ መፎካከር ነበር። የአንድ ጎድ አባላት አፈንግጠው ከሌላው መቀላቀል፣ ይህም የሚያስከትለው የአንዱ ማበጥና የሌላው መኰስመን ግንኙነቶችን ለማቃቃር ረድቶ ነበር። ስለሆነም አርበኞቹ ብዙ ጊዜ ጠላትን አብረው ከመውጋት ይልቅ እርስ በርስ መፋጀቱን ነበር የተያያዙት። ለዚህም ሁኔታ በምሳሌነት መጥቀስ የሚቻለው በጎጃም በደጃች መንገሻ ጀምበሬና በደጃች ነጋሽ በዛብህ መካከል፣ እንዲሁም በልጅ ኃይሉ በለውና በልጅ በላይ ዘለቀ መካከል የነበረውን ችግር ነው። በአርበኞቹ መካከል ኅብረት ለመፍጠር ያዳገተው የሚጋሩት ርእዮትና የፖለቲካ ድርጅት ቀርቶ ሁሉም መሪያችን ብሎ የሚመለከተው አንድ ሰው ባለመኖሩ ነው።

አርበኛው ያውራ ያለህ በማለቱ ይመስላል አሁንም ስሙ ያልሞተው የኢያሱ ልጆች ፊት መኖራቸው እንኳ ያልታወቀውን ያህል በችግሩ ጊዜ የአርበኞች መሰባሰቢያ አድባር ለመሆን የበቁት። በዚህም መሠረት ዮሐንስ ኢያሱ የጉንደርን አርበኞች ሲያስተባብር፣ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ደግሞ የሸዋ አርበኞች አውራ ሆኖ ማዕረግና ሹመት ሊሰጥ ችሏል (ለምሳሌ አበበ አረጋይን ራስ ማሰኘት)። ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ደግሞ ሪፐብሊካዊ ዝንባሌ የነበረው ታከለ ወልደ ሐዋርያት ከክፍለ ሀገር ክፍለ ሀገር እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሱዳን፣ ከሱዳን ኢትዮጵያ በመመላለስ አርበኞቹን በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጥላ ሥር ለማሰባሰብ ያልተሳካ ሙከራ አድርጓል። የአርበኞቹ ትግል የጉጠኝነት ባሕርዩን እንደያዘ በመዝለቁም ግልጽ የሆነ የፖለቲካ አቅጣጫ ማግኘት ተስኖታል። ፖለቲካዊው በወታደራዊ፣ እስትራቴጂው በታክቲክ ተውጦ ቀርቷል።

ይህን ድክመት በመጠኑ ሊያካክሱ የቻሉ ሁለት ክስተቶች ነበሩ። እነዚህም የጥቁር አንበሳ ድርጅትና በሱዳን በነበሩ ስደተኞች ዘንድ የተጀመረው ሪፐብሊካዊ ንቅናቄ ናቸው። እርግጥ ሁለቱም በነፃነት ትግሉ ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ ውሱን ነበር። የመጀመሪያው ጣልያኖች በገቡ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ባጭሩ ሲቀጭ፣ ሁለተኛው ደግሞ ካገሪቷ ክልል ውጭ የሚካሄድ



4.10 የጥቁር አንበሣ ድርጅት ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዓለመ ወርቅ በየነ

በመሆኑ የነበረው ጠቀሜታ ከፖለቲካዊ ይልቅ አካዳሚያዊ ነበር ማለት ይቻላል:: ይሁን እንጂ ሁለቱም የነፃነት ትግሉን ፖለቲካዊና ርእዮታዊ ፈር ለማስያዝ የተደረጉ የሚደነቁ ጥረቶች ነበሩ::

የጥቁር አንበሳ ድርጅት ከሆለታ ወጣት መኰንኖችና ከውጭ አገር ተምረው ከተመለሱ ምሁራን የተውጣጣ ሲሆን፣ ፕሬዚዳንቱ በእንግሊዝ አገር የከብት ሕክምና ያጠናው ዶ/ር አለመወርቅ በየነ ነበር:: የድርጅቱን የፖለቲካ አመራር የሚሠጠው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲሆን በተጨማሪም በኤርትራዊው መኰንን በሌ/ኰሎኔል በላይ ኃይለ አብ የሚመራ የሥልጠና ካውንስል ነበረው:: ድርጅቱ የሚተዳደረው በባለ ዐሥር አንቀጽ የመተዳደሪያደንብ ሲሆን፣ ከነዚህም በከፍተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው የፖለቲካው አመራር በወታደራዊ አመራሩ ላይ ያለውን የበላይነት የሚያረጋግጠው አንቀጽ ነው:: አሁን እንደሚታወቀው ይህ የሽምቅ ውጊያ አደረጃጀት መሠረታዊ ሕግ ሆኗል:: ከዚህ በተጨማሪ መተዳደሪያ ደንቡ አባላቱ ገበሬውን እንዳያንገላቱ አጥብቆ ከመከልከሉም በላይ ለጦር ምርኮኞች ሰብአዊ ርኅራኄ እንዲያሳዩ፣ ስደትን እንዳይሹና በጠላት እጅ ከመውደቅ ይልቅ ሕይወታቸውን እንዲያጠፉ ይደነግግ ነበር:: የመጨረሻውን የፖለቲካ ሥልጣን



በተመለከተ ግን ድርጅቱ ለአፄ ኃይለ ሥላሴና ለንጉሣዊው ቤተሰብ ያለውን ታማኝነት አረጋግጦ ነበር::

በዚህ በኋላኛው ረገድ ሬፐብሊካዊው እንቅስቃሴ ንጉሣዊ አገዛዝን በሬፐብሊክ ለመተካት በማለሙ አንድ እርምጃ ወደፊት የሄደ ነበር:: ንቅናቄው ማቆጥቆጥ የጀመረው ከኢጣልያ ወረራ በፊት ድሬዳዋ በነበሩ የፈረንሳይ ትምህርትና ባህል በቀመሱ ምሁራን አካባቢ ነው:: በስደት ላይ የነዚህን ፈለግ የተከተሉት ሬፐብሊካውያን ከሁሉም በላይ የአርበኞችን ኅብረት አበክረው ጠየቁ:: ኋላ እንግሊዞች በኢትዮጵያ ላይ የሜነትን ጥገኝነት አስቀድመው በመተንበይ ይመስላል የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን በራሱ ነፃ ማውጣት እንዳለበት እንጂ በውጭ እርዳታ መተማመን እንደሌለበትም በጥብቅ አስገነዘቡ:: ከነፃነት በኋላም ፍላጎታቸው ሕዝብ የመረጠው መንግሥት እንዲቋቋም እንጂ ዘውዳዊ አገዛዝ እንደገና ተመልሶ እንዲቋቋም አልነበረም:: አሁን ካለንበት የታሪክ ወቅት አንፃር ይህ ንቅናቄ የበለጠ ጠቀሜታ የሚኖረው የኢትዮጵያን የተለያዩ ግዛቶች ባሕርያት ለማቻቻል እንዲያመች የፌዴራላዊ ቅርጸ መንግሥት ሐሳብ ማቅረቡ ነው:: ይህን ተንተርሰም ነው «የሸዋ አበባ ያብባል ገና» የሚለውን የአጆብ ዘፈን «አዲስ አበባ ያብባል ገና» በሚል የተካው:: የንቅናቄው አባላት አስተሳሰብ የመጀመሪያው አንድ ግዛት የሚያሞካሽ በመሆኑ የዚያው ግዛት ተወላጅ ባልሆኑት ላይ ቅሬታ ሲፈጥር፣ ሁለተኛው ግን የጋራ የሆነችውን ዋና ከተማ በማወደሱ ሁሉን ለማሰባሰብ ይችላል የሚል ነው:: ከነፃነት በኋላ ግን ሁኔታው ለንቅናቄው አመቺ አልነበረም:: አባላቱ በንጉሡ ነገሥቱም ሆነ ሞግዚቱ በነበሩት እንግሊዞች ዘንድ በበጎ ዐይን አልታዩም:: ንጉሠ ነገሥቱ በሬፐብሊካዊነታቸው፣ እንግሊዞች ደግሞ በአፍቃሬ ፈረንሳይነታቸው ጠምደዋቸው ደብዛቸው ሊጠፋ በቃ::

የአርነት ትግሉ የመጨረሻውንና ወሳኙን ምዕራፍ የያዘው አርበኞቹ በጉጉት ይጠብቁ እንደነበሩት ጦርነቱ ዓለም አቀፋዊ ስፋት ሲያገኝ ነው:: በሰኔ 1932 ሙሶሊኒ ምናልባትም በሕይወቱ ዐቢይ ሊባል የሚችለውን ስሕተት ፈጸመ:: ይኸውም የሂትለር አጋር በመሆን ሁለተኛ ዓለም ጦርነት ውስጥ መግባቱ ነው:: በዚህ እርምጃም የኢትዮጵያ ወረራውን ያሳካለትን የእንግሊዝና የፈረንሳይን አይዞህ ባይነት ከመቅጽበት አጣ:: በተለይም እንግሊዞች በፊት እንደዋዛ ያልተመለከቱትን ያህል አሁን በምሥራቅ አፍሪቃ ቅኝ ግዛቶቻቸው ላይ እንደሚያንዣብብ አደገኛ መቅሠፍት አዩት:: በዚህም አኳኋን ከ19ኛው መቶ ዓመት መገባደጃ ጀምሮ የኢጣልያ ጽኑ ወዳጅ የነበረችው እንግሊዝ ወደ ቀንደኛ ጠላትነት ተለወጠች:: ባንፃሩም የኃይለ ሥላሴ የፖለቲካ ጠቀሜታ ገዝፎ መታየት ጀመረ:: ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ሊያስተባብርላቸው የሚችል ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ስላገኙት እንግሊዞች በስደት ከነበረበት የገጠር ከተማ አውጥተው ወደ ጦር ግንባሩ አሸጋገሩት::

እንግሊዞች በኢጣልያ ላይ ጦር የከፈቱት ከሱዳንና ከኬንያ ነበር:: በሜጀር ጀኔራል ሰር ዊልያም ፕላት የሚመራ ጦር በኤርትራ የሚገኘውን የኢጣልያ ጦር ሲያጠቃ፣ በኮሎኔል ዳንኤል ሳንፎርድና በሻለቃ አርድ ቻርልስ ዊንጌት የሚመራው «የጌዴዎን ጦር» የተባለው ንጉሡን እጅቦ ወደ ጎጃም አመራ:: በደቡብ በኩል ደግሞ በሌተናል ጀኔራል ሰር አላን ከኒንግሃም የሚመራው ጦር ወደ ኢጣልያ ሶማሊላንድ፣ ብሎም ወደ ሐረር አቀና:: ሆኖም የኢጣልያ ጦር በቀላሉ የሚበገር አልሆነም:: በተለይ እንግሊዞች ከረንን መያዝ



4.10 የጥቁር አንበሣ ድርጅት ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዓለመ ወርቅ በየነ

በመሆኑ የነበረው ጠቀሜታ ከፖለቲካዊ ይልቅ አካዳሚያዊ ነበር ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ ሁለቱም የነፃነት ትግሉን ፖለቲካዊና ርእዮታዊ ፈር ለማስያዝ የተደረጉ የሚደነቁ ጥረቶች ነበሩ።

የጥቁር አንበሳ ድርጅት ከሆለታ ወጣት መኰንኖችና ከውጭ አገር ተምረው ከተመለሱ ምሁራን የተውጣጣ ሲሆን፣ ፕሬዚዳንቱ በእንግሊዝ አገር የከብት ሕክምና ያጠናው ዶ/ር አለመወርቅ በየነ ነበር። የድርጅቱን የፖለቲካ አመራር የሚሠጠው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲሆን በተጨማሪም በኤርትራዊው መኰንን በሌ/ኰሎኔል በላይ ኃይለ አብ የሚመራ የሥልጠና ካውንስል ነበረው። ድርጅቱ የሚተዳደረው በባለ ዐሥር አንቀጽ የመተዳደሪያደንብ ሲሆን፤ ከነዚህም በከፍተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው የፖለቲካው አመራር በወታደራዊ አመራሩ ላይ ያለውን የበላይነት የሚያረጋግጠው አንቀጽ ነው። አሁን እንደሚታወቀው ይህ የሽምቅ ውጊያ አደረጃጀት መሠረታዊ ሕግ ሆኗል። ከዚህ በተጨማሪ መተዳደሪያ ደንቡ አባላቱ ገበሬውን እንዳያንገላቱ አጥብቆ ከመከልከሉም በላይ ለጦር ምርኮኞች ሰብአዊ ርኅራኄ እንዲያሳዩ፣ ሰደትን እንዳይሹና በጠላት እጅ ከመውደቅ ይልቅ ሕይወታቸውን እንዲያጠፉ ይደነግግ ነበር። የመጨረሻውን የፖለቲካ ሥልጣን



በተመለከተ ግን ድርጅቱ ለአፄ ኃይለ ሥላሴና ለንጉሣዊው ቤተሰብ ያለውን ታማኝነት አረጋግጦ ነበር።

በዚህ በኋላኛው ረገድ ሬፐብሊካዊው እንቅስቃሴ ንጉሣዊ አገዛዝን በሬፐብሊክ ለመተካት በማለሙ አንድ እርምጃ ወደፊት የሄደ ነበር። ንቅናቄው ማቆጥቆጥ የጀመረው ከኢጣልያ ወረራ በፊት ድሬዳዋ በነበሩ የፈረንሳይ ትምህርትና ባህል በቀመሱ ምሁራን አካባቢ ነው። በስደት ላይ የነዚህን ፈለግ የተከተሉት ሬፐብሊካውያን ከሁሉም በላይ የአርበኞችን ኅብረት አበክረው ጠየቁ። ኋላ እንግሊዞች በኢትዮጵያ ላይ የሚኑትን ጥገኝነት አስቀድመው በመተንበይ ይመስላል የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን በራሱ ነፃ ማውጣት እንዳለበት እንጂ በውጭ እርዳታ መተማመን እንደሌለበትም በጥብቅ አስገነዘቡ። ከነፃነት በኋላም ፍላጎታቸው ሕዝብ የመረጠው መንግሥት እንዲቋቋም እንጂ ዘውዳዊ አገዛዝ እንደገና ተመልሶ እንዲቋቋም አልነበረም። አሁን ካለንበት የታሪክ ወቅት አንፃር ይህ ንቅናቄ የበለጠ ጠቀሜታ የሚኖረው የኢትዮጵያን የተለያዩ ግዛቶች ባሕርያት ለማቻቻል እንዲያመች የፌዴራላዊ ቅርጸ መንግሥት ሐሳብ ማቅረቡ ነው። ይህን ተንተርሶም ነው «የሸዋ አበባ ያብባል ገና» የሚለውን የአጀብ ዘፈን «አዲስ አበባ ያብባል ገና» በሚል የተካው። የንቅናቄው አባላት አስተሳሰብ የመጀመሪያው አንድ ግዛት የሚያሞካሽ በመሆኑ የዚያው ግዛት ተወላጅ ባልሆኑት ላይ ቅሬታ ሲፈጥር፤ ሁለተኛው ግን የጋራ የሆነችውን ዋና ከተማ በማወደሱ ሁሉን ለማሰባሰብ ይችላል የሚል ነው። ከነፃነት በኋላ ግን ሁኔታው ለንቅናቄው አመቺ አልነበረም። አባላቱ በንጉሠ ነገሥቱም ሆነ ሞግዚቱ በነበሩት እንግሊዞች ዘንድ በበጎ ዐይን አልታዩም። ንጉሠ ነገሥቱ በሬፐብሊካዊነታቸው፣ እንግሊዞች ደግሞ በአፍቃሪ ፈረንሳይነታቸው ጠምደዋቸው ደብዛቸው ሊጠፋ በቃ።

የአርነት ትግሉ የመጨረሻውንና ወሳኙን ምዕራፍ የያዘው አርበኞቹ በጉጉት ይጠብቁ እንደነበሩት ጦርነቱ ዓለም አቀፋዊ ስፋት ሲያገኝ ነው። በሰኔ 1932 ሙሶሊኒ ምናልባትም በሕይወቱ ዐቢይ ሊባል የሚችለውን ስሕተት ፈጸመ። ይኸውም የሂትለር አጋር በመሆን ሁለተኛ ዓለም ጦርነት ውስጥ መግባቱ ነው። በዚህ እርምጃም የኢትዮጵያ ወረራውን ያሳካለትን የእንግሊዝና የፈረንሳይን አይዞህ ባይነት ከመቅጽበት አጣ። በተለይም እንግሊዞች በፊት እንደዋዛ ያልተመለከቱትን ያህል አሁን በምሥራቅ አፍሪቃ ቅኝ ግዛቶቻቸው ላይ እንደሚያንዣብብ አደገኛ መቅሠፍት አዩት። በዚህም አኳኋን ከ19ኛው መቶ ዓመት መገባደጃ ጀምሮ የኢጣልያ ጽኑ ወዳጅ የነበረችው እንግሊዝ ወደ ቀንደኛ ጠላትነት ተለወጠች። ባንፃሩም የኃይለ ሥላሴ የፖለቲካ ጠቀሜታ ገዝፎ መታየት ጀመረ። ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ሊያስተባብርላቸው የሚችል ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ስላገኙት እንግሊዞች በስደት ከነበረበት የገጠር ከተማ አውጥተው ወደ ጦር ግንባሩ አሸጋገሩት።

እንግሊዞች በኢጣልያ ላይ ጦር የከፈቱት ከሱዳንና ከኬንያ ነበር። በሜጀር ጄኔራል ሰር ዊልያም ፕላት የሚመራ ጦር በኤርትራ የሚገኘውን የኢጣልያ ጦር ሲያጠቃ፣ በኰሎኔል ዳንኤል ሳንፎርድና በሻለቃ ኦርድ ቻርልስ ዊንጌት የሚመራው «የጌዴዎን ጦር» የተባለው ንጉሡን አጅቦ ወደ ጎጃም አመራ። በደቡብ በኩል ደግሞ በሌተናል ጄኔራል ሰር አላን ከኒንግሃም የሚመራው ጦር ወደ ኢጣልያ ሶማሊላንድ፣ ብሎም ወደ ሐረር አቀና። ሆኖም የኢጣልያ ጦር በቀላሉ የሚበገር አልሆነም። በተለይ እንግሊዞች ከረንን መያዝ

የቻሉት በሁለቱም ወገን ብዙ መሥዋእትነት ከተከፈለ በኋላ ነው። ከከተማይቱ ወጣ ብሎ የሚታየው የአያሌ እንግሊዞች መቃብር ለፍልሚያው መራራነት ቋሚ ማስረጃ ነው። ጣልያኖች በተጨማሪም ለአጭር ጊዜ የእንግሊዝ ሶማሌላንድን ለመያዝና በመተማ በኩል የተሰነዘረውንም ጥቃት ለመመከት ችለው ነበር። ይሁን እንጂ አምስቱ ዓመት የአርበኞች ትግል ያመነመነው ጦር በመጨረሻ የሽንፈት ጽዋ ከመቅመስ ሊድን አልቻለም። የእንግሊዝና የአርበኞች ጦር ማጥቃቱን ቀጥሎ፣ አዲስ አበባ በመጋቢት 28፣ 1933 ከጠላት ነፃ ለመሆን ቻለች። ከዚያም በሚያዝያ 27 ጣልያኖች በገቡበት ልክ በአምስት ዓመቱ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደ መናገሻ ከተማው በመግባት ለሠላሳ ሦስት ዓመት የሚቆየውን ሥልጣኑን እንደገና መሠረተ።

## ምዕራፍ አምስት

# ከነፃነት እስከ አብዮት 1933-1966

ከ1933 እስከ 1966 ያለው ዘመን በዚህ መጽሐፍ እስካሁን የተዘረዘረው ታሪክ ማሳረጊያ ነበር ማለት ይቻላል። በ19ኛው መቶ ዓመት ቴዎድሮስ ያደረገው ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የማቋቋም ሙከራ በኃይለ ሥላሴ ፍጹማዊ አገዛዝ ተቋጨ። የባሕር በር ለማግኘት የተደረገው የረጅም ዘመን ጥረት ኤርትራ መጀመሪያ በፌዴሬሽን ኋላም በውሕደት ስትቀላቀል ለጊዜውም ቢሆን ተሳካ። ቀላድ ሲጣል የተጀመረው የግል የመሬት ባለቤትነት ሥርዓት እየተጠናከረ መጣ። መንግሥት ለሹማምንቱና ለደጋፊዎቹ መሬት በስፋት ሲቸር በተለይ በደቡቡ ክፍል ወደ ጭሰኝነት የሚያሽቆለቁለው የገበሬ ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ ጨመረ። ከጣልያን ወረራ በፊት ብርቅ የነበሩት የገበሬው አመፆች ከነፃነት ወዲህ በስፋት ይከሠቱ ጀመር። በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ወደ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሠርጎ ለመግባት ደጅ ሲጠና የቆየው የውጪ ካፒታል አሁን የተሻለ ዕድል አጋጠመው። ቀድሞ በኃያላን መንግሥታት ፉክክር በመጠቀም አንፃራዊ ነፃነቱን ጠብቆ የቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት አሁን እያደር ከአሜሪካ ጋር እየተቆራኘ መጣ። ይህ አዲስ ወዳጅነትም ነው ለፍጹማዊ አገዛዝ መጠናከር መሠረታዊ ድጋፍ የሰጠው።

ይሁን እንጂ ነገሩ እንቆቅልሽ ቢመስልም ይኸው ዘመን የኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ እየተዳከመ መጥቶ በመጨረሻም የወደቀበት ወቅት ነበር። ሥርዓቱ የወለደውና በሴራ የጀመረው ተቃውሞ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አማካይነት የከረረ መልክ ያዘ። ለዘብ ባለ ድምፅ ለውጥ ይጠይቁ የነበሩት የቅድመ 1928 ምሁራን በከፍተኛ ድምፅ ለኅብረተ ሰብ ሹም ሽር በሚጮሁት ተማሪዎች ተተኩ። ይህ ነበር የአብዮቱ መቅድም።

## ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ

### የእንግሊዝ የበላይነት ዘመን

ከነፃነት በኋላ ባሉት የመጀመሪያ ዐሥር ዓመታት ውስጥ አገሪቱ የነበራትን የውጭ ግንኙነት ባሕርይ የወሰነው የአርነት ዘመቻው ሂደት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ከራሳቸው ዓለም አቀፍ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ በመነሣት እንግሊዞች የተጫወቱት ግንባር ቀደም ሚና ከነፃነት በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የበላይነት ስፍራ አቀዳጃቸው። ከ1928 በፊት በእንግሊዝ፣ በኢጣልያና በፈረንሳይ መካከል ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር የነበረው የሦስት ማዕዘን ፉክክር በእንግሊዝ ብቸኛ የበላይ ተቆጣጣሪነት ተተካ። ይህም ሁኔታ ሕጋዊ መሠረት ማግኘት የቻለው በ1934 እና በ1937 ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ጋር እንድትፈራረም በተደረጉት ሁለት ስምምነቶች አማካይነት ነው። በነዚህ ስምምነቶች አማካይነትና ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ገና ያልተገባደደ በመሆኑ፣ ለቃል ኪዳን

አገሮች ደኅንነት አስፈላጊዎቹን ሁኔታዎች ማመቻቸት ያስፈልጋል በሚል ሰበብ እንግሊዞች በኢትዮጵያ ውስጥ ገንዘብን በሚመለከቱ ጉዳዮች፣ በአስተዳደርና በግዛታዊ አንድነት ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ለማድረግ በቁ።

በመጀመሪያው (ማለትም በ1934ቱ) ስምምነት፣ ምንም እንኳ እንግሊዞች ለይስሙላ የኢትዮጵያን ነፃ ህልውና ቢያውቁም፣ እያንዳንዱ አንቀጽ ማለት ይቻላል፣ የኢትዮጵያን ጥገኝነትና የእንግሊዝን የበላይነት የሚያረጋግጥ ነበር። በኢትዮጵያ ያለው የእንግሊዝ አምባሳደር ከሌሎች አምባሳደሮች ሁሉ የላቀ ልዩ ስፍራ ተሰጠው። የእንግሊዝ ዜጎች በአስተዳደር ውስጥ በአማካሪነትም ሆነ በዳኝነት ቁልፍ ቦታ ያዙ። ያገሪቱ የፖሊስ ሠራዊት ሙሉ በሙሉ በእንግሊዝ ቁጥጥር ስር ዋለ። የኢትዮጵያ መንግሥት ሌሎች የውጭ አገር ዜጎችን መቅጠር የሚችለው የእንግሊዞችን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ብቻ እንዲሆን ተደረገ።

የእንግሊዝ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት መጠነኛ የገንዘብ ድጎማ ቢያደርግም፣ ይህ ድጎማ በየዓመቱ እየቀነሰ የሚሄድ ከመሆኑም በላይ በዚህ ሳቢያ እንግሊዞችን ያገሪቱን የገንዘብ ፖሊሲ ለመቆጣጠር አስቻላቸው። በተጨማሪም የኢጣልያ የጦር ምርኮኞችንና ሲቪል ኢጣልያውያንን በተመለከተ የመጨረሻውን ውሳኔ የማሳለፉን ሥልጣን እንግሊዞች ወሰዱ። የኢትዮጵያ አየር ክልል ለእንግሊዝ አወሮፕላኖች እንጂ ለሌሎች የተከለከለ ነበር። ምናልባት የኢትዮጵያ ነፃነት የቁን ያህል ሰንካላ እንደነበር ጉልህ ማስረጃው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የአንድ ነፃ መንግሥት ዓይነተኛ ሥልጣን የሆነውን ጦርነትን ማወጅ የሚችለው በምሥራቅ አፍሪቃ የእንግሊዝ የጦር ኃይል አዛዥ የነበረውን ካስፈቀደ በኋላ መሆኑ ነው። ባንፃሩም ይኸው የእንግሊዝ የጦር መኰንን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ልዩ ሥልጣን የሚሰጠውን ያስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ እንዲያውጅ ንጉሠ ነገሥቱ ግዴታ ነበረበት።

ስምምነቶቹ የሰጣቸውን ሕጋዊ ሥልጣን ተገን በማድረግም ባገሪቱ ያሉት የእንግሊዝ ባለሥልጣኖችና የጦር መኰንኖች ከፍተኛ የትምክሕተኝነት ስሜት ያሳዩ ነበር። እንግዳ በሆነ አጠራር «የኢትዮጵያ ሠራዊት» በመባል የታወቀው የእንግሊዝ ጦር ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትም ሆነ የነፃነት ስሜት ከበሬታ አልነበረውም። ያለ ንጉሠ ነገሥቱ ዕውቀትና ፈቃድ ንብረት ይወርስና ሌላም ተመሳሳይ ከባድ እርምጃዎች ይወስድ ነበር። ባጭሩ ሠራዊቱ ባገሪቱ ያለው አመለካከት «በቁጥጥር ሥር የዋለ የጠላት አገር አስተዳደር» ብለው እንግሊዞች በሰጡት ኦፊሲዬላዊ ስያሜ ተጠቃሎ ነበር ማለት ይቻላል።

ይህ ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱን ማስቀየሙ አልቀረም። ዙፋኑን እንደገና እንዲይዝ ሳደረጉለት እርዳታ ባለውለታ ቢሆንም ሥልጣኑ እንዲህ ሲሰናከል ዝም ብሎ ለማየት ፈቃደኛ አልነበረም። ፍጹማዊ ሥልጣኑን በጠንካራ መሠረት ለማደስ የእንግሊዞችን አጋርነት እንጂ አለቅነታቸውን አልፈለገም። የእንግሊዞች ፍላጎት ግን አገሪቱ በጠላት ጊዜ ያገኘቻቸውን አንዳንድ ጠቀሜታዎች እንኳ በመንፈግ ወደ ቅድመ 1928 ሁኔታዋ ለመመለስ የነበረ ይመስላል።

በ1937 በሁለቱ መንግሥታት መካከል የተደረገው ሁለተኛው ስምምነት በመጠኑም ቢሆን የኢትዮጵያን ሉዓላዊ መብቶች እንደገና ሊያስመልስ ችሏል። የእንግሊዝ አምባሳደር በሌሎች እቻዎቹ ላይ የነበረው የበላይነት ቀረ። የኢትዮጵያ መንግሥት ማናቸውንም የውጭ ዜጎች በአማካሪነትም ሆነ በሹምነት



ለመቅጠር ያለው ነፃነት ተረጋገጠ። በተጨማሪም እንግሊዞች የጅቡቲ አዲስ አበባን የባቡር መሥመር ለኢትዮጵያ ለመመለስ መስማማታቸው ሳገሪቱ ኢኮኖሚያዊም ወታደራዊም ጠቀሜታ ነበረው። ባንድ በኩል አገሪቱ እንደገና ነፃ የውጭ ንግድ መሥመር ስታገኝ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ለመጠባበቂያ የሚሆናት የጦር መሣሪያ የምታስገባበት በር ተከፈተላት። እንዲሁም እንግሊዞች «በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ወታደራዊ ተልእኮ» የሚባል ቡድን በማቋቋም ያገሪቱን የመከላከያ አቋም በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት ተስማሙ። ተጠሪነቱ ሳገሪቱ የጦር ሚኒስቴር የሆነው ይህ ተልእኮ በስምምነቱ የተሰጠው ተግባር «የኢትዮጵያን የጦር ሠራዊት በማደራጀት፣ በማሠልጠንና በማስተዳደር» የኢትዮጵያን መንግሥት ለማገዝ ነበር።

ምንም እንኳ የ1937ቱ ስምምነት ለኢትዮጵያ መንግሥት ከበፊቱ ሰፋ ያለ ነፃነት ቢሰጠውም፣ እንግሊዞች ባገሪቱ ሕይወት ላይ ለመዳኘት ያላቸው ኃይል እምብዛም አልሟሸሸም። በተለይም ኢትዮጵያ በነበራት የግዛት ጥያቄ ላይ ፈላጭ ቆራጮቹ እነሱው ነበሩ። በዚህም ረገድ በአካባቢው ባላቸው ወታደራዊ የበላይነት ተጠቅመው ኤርትራንና ኦጋዴንን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ነበር። ከዚያም አልፈው የነዚህን ግዛቶች የወደፊት ዕድል በተመለከተ ዕቅድ ማውጣት ያዙ። የዕቅዱ መሠረታዊ ዓላማም ሁለቱንም ግዛቶች ከኢትዮጵያ ነጥሎ ለማስቀረት ነበር። ኦጋዴንን በተመለከተ የእንግሊዞች ሐሳብ ከእንግሊዝና ከኢጣልያ ሶማሊላንድ ጋር በመደመር «ታላቂቱ ሶማሊያ» የሚል ስያሜ የተሰጠው ግዛት ለመመሥረት ነበር።

ከነፃነት በኋላ የሶማሌ መንግሥት ለረጅም ጊዜ በኦጋዴን ላይ ያነሣው የይገባኛል ጥያቄ ዘር የተዘራውም በዚህን ወቅት ነው ማለት ይቻላል። እንግሊዞች ለኤርትራ የደገሱላት ከኦጋዴን ለየት ያለ ነበር። የኤርትራ ቆላማው ክፍል በጂምግራፊ፣ በዘርና በሃይማኖት ከሚቀራረበው ከሱዳን ጋር ሲደመር፣ ባብዛኛው ክርስቲያን የሆነውን ደጋማውን ክፍል ደግሞ ከትግራይ ወገኑ ጋር በማዋሐድ ከኢትዮጵያ የተለየ አንድ ግዛት እንዲሆን ነበር። በዚህም ዕቅድ መሠረት ኤርትራን ለማስመለስ የምትጥረው ኢትዮጵያ ጭራሽ ትግራይንም ልታጣ የምትችልበት ሁኔታ ተፈጠረ። ሌላው ሊስተዋል የሚገባው ነገር ለኤርትራ ቆላማው ክፍል የወጠኑለትን ወደጕን ከተውን፣ የእንግሊዞች ዕቅድ ጣልያኖች በአምስቱ ዓመት ይዞታቸው የደነገጉትን አስተዳደራዊ ክልል የሚያጸድቅ መሆኑ ነው።

ከኢጣልያ አገዛዝ ነፃ ከወጣች ጀምሮ ኢትዮጵያ በኦጋዴንና በኤርትራ ላይ ያላትን የይገባኛል ጥያቄ ከማንሣት አልተቆጠበችም። የኦጋዴን ግዛት እስከ 1928 ድረስ ዓለም አቀፋዊ እውቅና ያገኘ የኢትዮጵያ አካል የነበረ ነው። ስለሆነም እንግሊዞች ይህን ግዛት ከቀረው የኢትዮጵያ ምድር ነጥለው በቁጥጥራቸው ሥር ማድረጋቸው ሕጋዊነት ያለው እርምጃ አልነበረም። ኤርትራም ብትሆን ምንም እንኳ ከ1882 ጀምሮ በኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ሥር ብትቆይም፣ ከቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር በታሪክ ከመተሳሰሯም በላይ ባንድ ወገን የጠላትን ዳግመኛ ወረራ ለመከላከል፣ በሌላ ወገን ደግሞ ነፃ የባሕር ወደብ ለማግኘት ታስፈልገኛለች ስትል ኢትዮጵያ ጠንካራ ጥያቄ አቀረበች። ኤርትራ እስከ 1882 መረብ ምላሽ በሚል መጠሪያ የምትታወቅ የኢትዮጵያ አካል ነበረች። ጣልያኖች ሁለት ጊዜ (በ1888 እና በ1928) ኢትዮጵያን የወረሩት ይህንኑ

ግዛት መቆናጠጫ አድርገው ነው። ከዚያም በላይ የኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ቋሚ ጥረት የመጨረሻውን መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው ኤርትራ እንደገና የኢትዮጵያ አካል ስትሆን ብቻ ነው የሚል ጠንካራ ስሜት ነበር። በዚህ ሁሉ ምክንያት ኢትዮጵያ ለኤርትራ ጥያቄ ትክክለኛው መልስ ወደ እናት አገሯ እንድትመለስ ማድረግ ነው በማለት ተከራከረች።

ይሁን እንጂ የኦጋዴንና የኤርትራ ጥያቄ መልስ ሊያገኝ የቻለው ዐሥር ዓመት ያህል ከተጓተተ በኋላ ነው። የኦጋዴን ጥያቄ በሁለቱ መንግሥታት፣ ማለትም በኢትዮጵያና በእንግሊዝ፣ ድርድር ሲያልቅ፣ የኤርትራው ግን ዓለም አቀፍ ትኩረትን ለመሳብ በቃ። እንግሊዞች ከኦጋዴን ይልቅ በኤርትራ ጥያቄ ላይ የኢትዮጵያን መንግሥት አቋም ለማስተናገድ የተዘጋጁ ይመስሉ ነበር። እንዲያውም ባንድ ወቅት ኢትዮጵያ በኦጋዴን ላይ ያላትን የይገባኛል ጥያቄ ካነሣች ኤርትራን ሊተዉላት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው ነበር። የ1937ቱን ስምምነት ለመፈራረም በሚደራደሩበት ወቅት ይኸው የኦጋዴን ነገር ተነሥቶ እንግሊዞች ሞቼ እገኛለሁ በማለት ይዞታቸውን ለማጽደቅ በቁ። ስለዚህም ይህ ስምምነት ምንም እንኳ ከሁለት ዓመት በፊት ከተደረገው ስምምነት ጋር ሲነፃፀር ለኢትዮጵያ ሰፋ ያለ ነፃነት ቢሰጥም፣ ኦጋዴንን ለማስመለስ ባለመቻሉ ውጤቱ አመርቂ አልነበረም። በዓመቱ ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት በድል አድራጊነት የተወጡት ኃያላን መንግሥታት ለንደን ላይ ያደረጉት ጉባዔ ኢትዮጵያ በኦጋዴንና በኤርትራ ላይ ያቀረበችውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉም፣ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የነበራትን ተስፋ የሚያዳፍን ይመስል ነበር። ሆኖም ሁኔታዎች ተለዋውጠው በ1940 እንግሊዝ «ሃውድ» ተብሎ የሚታወቀውን የሰሜን ምሥራቅ ክፍልና ከዚያ እስከ ጅቡቲ ያለውን የምድር ወሽመጥ «የተከለለ አካባቢ» የሚል ስያሜ ሰጥታ በማስቀረት የተቀረውን የኦጋዴን ክልል ለኢትዮጵያ መለሰች። ከዚያም በ1947 ጠቅላላውን የኦጋዴን ምድር ለቃ ወጣች።

የኦጋዴን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ግን አንድ ችግር ሲፈታ ሌላ ችግርን ወለደ። የሶማሌ ብሔርተኛ ፓርቲ የሆነው የሶማሌ ወጣቶች ሊግ («ሶማሊ ዩዝ ሊግ») የኦጋዴንን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ በመቃወም የአካባቢውን ሕዝብ ማነሣሣት ጀመረ። ሶማሌዎችን በሙሉ አንድ ለማድረግ የጀመረው ቅስቀሳ ከእንግሊዝና ከኢጣልያ ቅኝ ግዛቶች ጀምሮ ወደ ኦጋዴንም ተዛመተ። ከዚያም በ1952 ሁለቱ ቅኝ ግዛቶች ነፃ በወጡ ማግሥት ተዋሕደው «የሶማሌ ሪፐብሊክ» የተባለውን ሲመሠርቱ ነገሩ ያንድ የፖለቲካ ቡድን ቅስቀሳ ከመሆን አልፎ ሁለት መንግሥታትን የሚያፋጥጥ ሆነ። አዲሲቱ የሶማሊያ ሪፐብሊክ በአምስት ግዛቶች (የእንግሊዝ ሶማሊላንድ፣ የኢጣልያ ሶማሊላንድ፣ የፈረንሳይ ሶማሊላንድ ወይም ጅቡቲ፣ ኦጋዴን፣ እና የሰሜን ጠረፍ ግዛት ተብሎ የሚታወቀው የኬንያ ክልል) ተበታትነው የቆዩትን ሶማሌዎች ባንድ ባንዲራ ሥር ማሰባሰቡን ዋና ዓላማዋ አድርጋ ተያያዘችው። ከሁሉም ያዲሱን የሶማሌን መንግሥት ትኩረት የሳበው ግን ኦጋዴን ነበር። ይህም ሁኔታ ነው በ1956 ሁለቱን አገሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ጦር ያማዘዘው። ይሁን እንጂ የሶማሊያ ጥያቄ በተለይም በአፍሪቃ ውስጥ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ሊያገኝ አልቻለም። በ1955 የተቋቋመው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ነግ በኔ በሚል የአባላቱ ሥጋት ይመስላል የዓለም አቀፍ ድንበሮች፣ በምንም ሆነ በምን ሁኔታ ይከለሉ፣ የተከበሩ ሆነው መቆየት እንዳለባቸው አረጋገጠ።



የኤርትራ ጥያቄ ከኦጋዴኑ ይበልጥ የተወሳሰበ ቢሆንም፣ አንድ ዓይነት መፍትሔ ሊያገኝ የቻለው የኦጋዴን ግዛት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ከመወሰኑ አንድ አራት ዓመት ቀደም ብሎ ነው። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማሳረጊያ የሆነው የፓሪስ ጉባዔ ኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶቿን ለቃ እንድትወጣ ቢያስገድድም የእነዚህ የወደፊት ዕጣቸው ምን እንደሚሆን አልወሰነም ነበር። ስለሆነም የኤርትራን ዕድል በተመለከተ የተለያዩ ወገኖች የተለያየ የመፍትሔ ሐሳብ ማቅረብ ጀመሩ። ሐሳቦቹ ሲጠቃለሉ በነፃነት ወይም በአንድነት ዙሪያ የሚሽከረከሩ ነበሩ። በወቅቱ ከተቋቋሙት የፖለቲካ ቡድኖች በኤርትራ ሕዝብ ዘንድ ሰፊ መሠረትና ጥንካሬ ሊያገኝ የቻለው ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሐድ የሚታገለው የአንድነት ቡድን ነበር። የዚህ ቡድን ተፃራሪ ሆኖ የወጣው የነፃነት ወገን ለአንድነት ያላቸው ተቃውሞ ብቻ ያስተሳሰራቸው የተለያዩ ቡድኖች ጥምር ነበር። የዚህ ወገን አባላት ቡድኖች መሠረቱን በቆላማው የኤርትራ ክፍል ያደረገው የሙስሊም ሊግ (ወይም በዐረብኛ አጠራሩ ራቢጣ አልኢስላሚያ)፣ ኤርትራን ከትግራይ ጋር አጣምሮ ነፃ አገር ለመመሥረት የሚታገለው ደገኛው የሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ እና በነፃነት ሽፋን የኢጣልያ ተጽዕኖ እንዲቀጥል የሚሹት የኢጣልያውያን ነዋሪዎች፣ የክልሶችና የቀድሞ የኢጣልያ ወታደሮች ነበሩ።

ብዙውን ጊዜ የኤርትራ ክርስቲያኑ ክፍል ለአንድነት፣ ሙስሊሙ ደግሞ ለነፃነት እንደታገሉ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ትርጓሜ ግን ሙሉ በሙሉ እውነተኛ አይደለም። ለአንድነት የታገሉ ሙስሊሞች እንደነበሩ ሁሉ ለነፃነት የታገሉ ክርስቲያኖችም ነበሩ። ለምሳሌ ከሙስሊም ሊግ ተገንጥሎ የተቋቋመው «ነፃ የምፅዋ ሙስሊም ሊግ» የተባለው ቡድን የኤርትራውያን ሙስሊሞች መብት እስከተከበረ ድረስ አንድነትን ለመቀበል ዝግጁነቱን አስታውቋል። ባንፃሩ ደግሞ ለነፃነት ይታገሉ የነበሩት የ«ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ» አባላት ባብዛኛው ክርስቲያኖች ነበሩ። ሌላው እውነታ ደግሞ ሁለቱም ወገኖች ማለትም የነፃነትም ሆነ ያንድነት፣ የውጭ ደጋፊ ኃይሎች ነበሯቸው። በዚህም ረገድ የአንድነት ኃይሎች የኢትዮጵያን መንግሥት ድጋፍ ሲያገኙ፣ «ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ» ደግሞ ከሞላ ጎደል የእንግሊዞች ፍጡር ነው ማለት ይቻላል። እንደሚታወሰው እንግሊዞች ኤርትራን ለመከፋፈል ባወጡት ዕቅድ ቆላማውን ክፍል ወደ ሱዳን ደርበው ትግርኛ ተናጋሪውን ክፍል ከመረብ ማዶ ከሚገኘው ወገኑ ጋር አዋሕዶ ነፃ መንግሥት ለማቋቋም ነበር። ይህንኑ ዕቅድ ነው የ«ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ» በተግባር ለመተርጐም የሞከረው። እንደዚሁም «የአፍቃሬ ኢጣልያ ፓርቲ» ከኢጣልያ መንግሥት ጠቀም ያለ የገንዘብ እርዳታ ያገኝ ነበር። ኢጣልያ በጦርነት ያጣችውን ኤርትራ በሞግዚትነት ለማስተዳደር ያደረገችው ሙከራ ከከሸፈባት በኋላ ስልቷን በመቀየር፣ የማታ ማታ በእጅ አዙር መቆጣጠሬ አይቀርም በማለት ይመስላል፣ ለኤርትራ ነፃነት ተሟጋች ሆነች። ስለሆነም በስሟ የሚንቀሳቀሰው ወገን ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው የነፃነት ወገን ዋና ደጋፊ ነበረች።

አራቱ ኃያላን መንግሥታት (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ሶቪየት ኅብረትና አሜሪካ) የኤርትራን ጉዳይ ካነሳበጡት በኋላ አንዳች ስምምነት ላይ ሳይደርሱ በ1941 ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አስተላለፉት። ድርጅቱም ከበርማ፣ ጓቴማላ፣ ኖርዌይ፣ ፓኪስታንና ደቡብ አፍሪቃ የተውጣጣ ኮሚሽን በማቋቋም የኤርትራውያንን ፍላጎት እንዲገመግም ወደዚያው ላከ። ከኖርዌይ በስተቀር

የኮሚሽኑ አባል አገራት ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ አለኝ የምትለውን የይገባኛል ጥያቄ የሚቃወሙ ነበሩ:: ሆኖም በኤርትራ ጉብኝታቸው ወቅት ያጋጠማቸው ጠንካራ ያንድነት ስሜት ካራቱ ሁለቱን (ማለትም በርማና ደቡብ አፍሪቃን) አቋማቸውን እንዲቀይሩ አደረጋቸው:: የኢጣልያ ደጋፊ የሆኑትን የላቲን አሜሪካ አገሮች የወከለችው ጓቴማላና ራሷን የኤርትራ ሙስሊሞች ጠበቃ ያደረገችው ፓኪስታን ኤርትራ ነፃ አገር እንድትሆን ሐሳብ ሲያቀርቡ፣ ደቡብ አፍሪቃና በርማ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትተሳሰር፣ ኖርዌይ ደግሞ ጭራሹኑ እንድትዋሐድ መረጡ:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በህዳር 23፣ 1943 በቁጥር 390 ውሳኔው ፌዴሬሽኑን እንደ አስታራቂ ሐሳብ አድርጎ ተቀበለው:: ነገር ግን ሁለቱንም ተፃራሪ ወገኖች ያረካል ተብሎ የጸደቀው ሐሳብ በሁለቱም የተጠላ ሆነ:: የነፃነትም ሆነ የአንድነት ወገኖች በየፊናቸው ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ሥራዬ ብለው ተያያዙት::

ለፌዴሬሽኑ ፎርሙላ መጽደቅ የሁለቱ ኃያላን መንግሥታታ፣ ማለትም የእንግሊዝና የአሜሪካ ድጋፍ፣ የራሱን አስተዋፅኦ ጎድርጓል:: እንግሊዝ በምትኩ አጋዴንን ለመጠቅለል በመሻት ይመስላል ቀደም ሲል በኤርትራ ላይ የነበራትን አክራሪ አቋም በማለዘብ ቢያንስ ደጋው የኤርትራ ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሐድ መደገፍ ጀመረች:: በዚህም መሠረት ቀደም ብላ ስታራምድ የነበረውን ኤርትራን የመከፋፈል መፍትሔ በማሻሻል፣ ቆላው ራሷ ከምትገዛው ከሱዳን ጋር እንዲቀላቀል መጠየቋን ስትቀጥል፣ ደጋው ክፍል ግን በፊት እንዳቀደችው ከትግራይ ጋር ተደምሮ ነፃ መንግሥት መሆኑ ቀርቶ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ደገፈች:: ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መንግሥት የኦጋዴንን ግዛት ሊለቀላት ከቶም ፈቃደኛ እንዳልሆነ ስትገነዘብ እንግሊዝ አቋሟን እንደገና ለመለወጥ ፈልጋ ነበር:: ነገር ግን የፌዴሬሽኑ ፎርሙላ ብዙ ተቀባይነት እያገኘ መጥቶ ስለነበር የትም ለመድረስ አልቻለችም::

የአሜሪካ መንግሥት የፌዴሬሽኑን ሐሳብ በበጎ ዐይን መመልከቱም ለውሳኔው መጽደቅ አጋዥነት ነበረው:: የአሜሪካ መንግሥት ዋና ትኩረት ከጣልያኖች የወረሰችውና በአሥመራ የሚገኘው «ሬዲዮ ማሪና» የተሰኘው የመገናኛ ጣቢያ ደህንነት ነበር:: ለዚህም ምንነቷ ካልታወቀ ነፃ ኤርትራ ይልቅ ኢትዮጵያ ትሻለኛለች በሚል ስሌት የፌዴሬሽኑን ፎርሙላ ደገፈች:: ስለዚህም ፌዴሬሽኑ በኢትዮጵያ የውስጥ የፖለቲካ ዕድገት ላይ ካለው ተጽዕኖ ባሻገር፣ በውጭ ግንኙነቷም ላይ ዐቢይ ለውጥ አስከትሏል ማለት ይቻላል:: ዐሥር ዓመት ኢትዮጵያን በበላይነት ስትቆጣጠር የቆየችው እንግሊዝ ገሸሽ ተደርጋ አሜሪካ ወደ መድረክ ብቅ በማለት እስከ 1966 አብዮት ዋዜማ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና አጋር ሆነች::

## ኢትዮጵያና አሜሪካ

የሁለቱ አገሮች የኦፊሲዬል ግንኙነት የጀመረው በ1896 በሮበርት ፒ እስኪነር የሚመራ የልዑካን ቡድን ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ከአፄ ምኒልክ ጋር በተፈራረመው የወዳጅነትና የንግድ ውል አማካይነት ነው:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳ የአሜሪካ ሸቀጦች፣ በተለይም አቡጀዲ፣ በኢትዮጵያ ገበያ ተወዳጅነት እያገኙ ቢመጡም፣ እስከ 1928 ያገሪቱን የውጭ ግንኙነት ይቆጣጠሩ የነበሩት ሦስቱ አጎራባች ቅኝ ገዥዎች እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣልያ ነበሩ:: የአሜሪካ ሚና እየጎላ የመጣው




ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ነው:: ይህም ባጠቃላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአሜሪካ ፖለቲካዊ ኀያልነት ነጸብራቅ ነው:: በሌሎች የዓለም ክፍሎች እንደተከሰተው ሁሉ፣ በኢትዮጵያም የረጅም ዘመን ቅኝ ገዥነቱ ያደከማቸው እንግሊዞች እያቅማሙም ቢሆን ስፍራውን በትኩስ ኃይል ለሚንቀሳቀሰው አጋራቸው ተዉ::

ይሁንና በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ለመመሥረት መጀመሪያ የተጉት ካሜሪካኖች ይልቅ ኢትዮጵያውያን ናቸው:: የእንግሊዞች ጥብቅ ቁጥጥር አላላውስ እያለው የተቸገረው ንጉሠ ነገሥት ይህንን ለመቋቋም ይረዳው ዘንድ የአሜሪካኖችን ድጋፍ መፈለግ ጀመረ:: ከላይ እንደተገለጸው ያን ያህልም በማያመረቃ ወታደራዊና የገንዘብ እርዳታ አሳበው እንግሊዞች ባገሪቱ አስተዳደርና የገንዘብ ሀብት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ጀምረዋል:: ንጉሠ ነገሥቱ በክፉ ቀን ጥገኝነት ስለሰጡትና ኋላም ወደ ዙፋኑ ስለመለሱት ባለውለታቸው ቢሆንም፣ ሥልጣኑን ሲሸሙት ዝም ብሎ ለማየት ፈቃደኛ አልነበረም:: ስለዚህም ፍጹማዊ ሥልጣንን እንደገና ለማደስ የምችለው እድሌንና ያገሬን ዕድል ለጋስነቷ ከሚወራላት ከአሜሪካ ጋር ባቆራኝ ነው ብሎ አሰበ::

ሁለቱ አገሮች ግንኙነታቸውን ባዲስ ምዕራፍ መጻፍ የጀመሩት በ1935 በጊዜው የገንዘብ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር የነበረው ይልማ ዴሬሳ አሜሪካን በጐበኘበት ወቅት ነው:: በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ በኩል የቀረበው ጥያቄ ወታደራዊ እርዳታ እንዲሰጣት፣ የገንዘብና የሕግ አማካሪዎች እንዲመደብላት ነበር:: አሜሪካም በዚያን ጊዜ ለዓለም በመቸር የነበረችውን የ«ሌንድ ሊዝ» ስምምነት ከኢትዮጵያም ጋር በመፈራረምና በ1936 ሁኔታዎችን የሚያጠና አንድ የቴክኒክ ቡድን በመላክ አዎንታዊ መልስ ሰጠች:: የቡድኑ መሪ በሆነው በፔሪ ፊሎውስ ስም የተጠራው ይህ ቡድን ነው ለብዙ ዓመታት የቆየውን የአሜሪካና የኢትዮጵያ ተራድኦ መሠረት የጣለው:: ቡድኑ ጥናቱን አገባዶ ያቀረባቸው ሐሳቦች ያተኮሩት መሠረታዊ የእድገት አውታሮችን (ኢንፍራስትራክቸር) በመዘርጋቱ ላይ ነበር:: የጥናቱና የጥረቱ ማሳረጊያም በግንቦት 7፣ 1944 በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈረመው የ«ፖይንት ፎር» ስምምነት ሆነ:: በሚቀጥሉት ሃያ ዓመታት የአሜሪካና ኢትዮጵያ ተራድኦ ዋና መለዮ የሆነው «ፖይንት ፎር» ካከናወናቸው ተግባራት ውስጥ የእርሻና የጤና ጥበቃ ትምህርት ማስፋፋት፣ እንበጣ መከላከል፣ የሕዝብ አስተዳደር (ፐብሊክ አድሚንስትሬሽን) ሥልጠናና እያሌ ኢትዮጵያውያንን ለትምህርት ወደ ውጭ አገር መላክ ይገኙበታል::

እነዚህ የእድገት እንቅስቃሴዎች ላገሪቱ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ቢኖራቸውም የመንግሥት ዋና ትኩረት በወታደራዊ እርዳታና የእንግሊዝን አምባገነንነት ለመቋቋም የአሜሪካን ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ከማግኘቱ ላይ ነበር:: በ1937 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጋር በምድረ ግብፅ ተገናኝቶ ለኢትዮጵያ ዋና በሆኑ ጉዳዮች (ኤርትራ፣ኦጋዴንና የአዲስ አበባ ጅቡቲ የምድር ባቡር) ላይ ለመነጋገር ቻለ:: ለአሜሪካዊው የፔትሮሊየም ኩባንያ ለሲንክሌር ሊዊስ በኦጋዴን የፍለጋ ጥናት እንዲያካሄድ ኢትዮጵያ ፈቃድ የሰጠችውም ከኢኮኖሚያዊ ይልቅ በፖለቲካዊ ስሌት ተገፋፍታ ነው:: በዚህ ፈቃድ አማካይነት ባንድ ወገን በግዛቱ



5.1 የአሜሪካ የጦር ሰፈር በቃኘው /አሥመራ/

ላይ ያላትን የይገባኛል ጥያቄ እንደገና ስታጠናክር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአሜሪካን እጅ በማስገባት አጋዴንን የሙጥኝ ብለው በያዙት እንግሊዞች ላይ የአሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲያርፍ ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ላይ አሜሪካኖች የኢትዮጵያን የግዛት ጥያቄ ለመደገፍም ሆነ ወታደራዊ እርዳታ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም።

ነገሩ መለወጥ የጀመረው ከ1943 በኋላ ነው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንደተሳሰረች፣ አሜሪካም አሥመራ ባላት የመገናኛ ጣቢያ ምክንያት የመካከለኛ ምሥራቅ እስትራቴጂካዊ ጥቅሟ ከኢትዮጵያ ጋር ተያያዘ። በዚሁ ዓመት የእንግሊዝ ወታደራዊ ተራድኦ ቡድን ከኢትዮጵያ ነቅሎ ሲወጣ፣ ኢትዮጵያ የአሜሪካን ወታደራዊ እርዳታ ለማግኘት ስታደርግ የቆየችው ውትወታም ተደማጭነት አገኘ። በ1944 በግብፅ የተካሄደው አብዮትም አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅና በቀይ ባሕር ዳርቻ ያላትን የወዳጅና ጠላት አሰላለፍ እንደገና እንድታጤን አስገደዳት። እነዚህ ሁኔታዎች ናቸው በ1945 በኢትዮጵያና አሜሪካ መካከል ለተደረገውና ለሚቀጥለት 20 ዓመታት ያህል የግንኙነታቸው መሠረት ለሆነው ስምምነት መነሾ የሆኑት። በስምምነቱም መሠረት አሜሪካ ባዲስ ስያሜው «ቃኘው» በተባለው የአሥመራ የመገናኛ ጣቢያ ላይ የነበራትን ይዞታ ስታረጋግጥ፣ በአጸፋውም ሰፊ የወታደራዊ እርዳታ ፕሮግራም ለመጀመር ተስማማች። «ማግ» በተባለው የወታደራዊ እርዳታ አማካሪ ቡድን አማካይነት



አምስት ሚሊዮን ዶላር ወጪ አድርጋ 60000 ሰው ያለው ባለሦስት ክፍለ ጦር ሠራዊት አቋቋመች። ይህ ዓይነት እርዳት በተከታዮቹ ዓመታት እየቀጠለ ሄዶ በአብዮቱ ዋዜማ አሜሪካ ለአፍሪቃ ከምትሰጠው ወታደራዊ እርዳታ ውስጥ 60 በመቶው የሚውለው ኢትዮጵያ ላይ ሊሆን ቻለ።

ስለዚህም ከ1945 በኋላ ያሉት ዓመታት አሜሪካ በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት መድረክ ላይ መሪ ተዋናይ የሆነችበትና ወሳኝ ሚና የተጫወተችበት ወቅት ነበር ማለት ይቻላል። የአሜሪካ ተጽዕኖ ባገሪቱ ሕይወት የተለያዩ ገጽታዎች የተንጸባረቀ ቢሆንም በተለይ ጎልቶ የታየው በወታደራዊ ድርጅት፣ በመገናኛና በትምህርት ዘርፍ ነው። በወታደራዊው መስክ ይህ ተጽዕኖ ጎልቶ የታየው በጦር ሠራዊት ውስጥ ሲሆን፣ እያደር ግን በሌሎች ቀድሞ አሜሪካውያን ባልሆኑ የውጭ አማካሪዎች ይመሩ ወደነበሩት የጦር ኃይሉ ክፍሎችም ተዛመተ። በዚህ ዓይነት መጀመሪያ በስዊድኖች ቁጥጥር ሥር የነበረው የአየር ኃይልና በኖርዌጆያኖች ይተዳደር የነበረው የባሕር ኃይል ወደ አሜሪካኖች ዞረ። በእንግሊዙ የሳንድኸርስት የጦር አካዳሚ አምሳያ የተፈጠረውና የእንግሊዛውያን ግርፍ በሆኑት ሕንዶች የሚተዳደረው የሐረር የጦር አካዳሚ እንኳ የአሜሪካ የሰውና የማቴሪያል እርዳታ አልተለየውም ነበር። ምናልባት የአሜሪካ ዱካ ያልደረሰባቸው ሁለት የጦር ክፍሎች ቢኖሩ የፖሊስ ሠራዊትና የክብር ዘበኛ ናቸው። ፖሊስ በጀርመንና በእስራኤል፣ ክብር ዘበኛ ደግሞ በስዊድን የሰለጠኑ ነበሩ። ያም ሆኖ ግን ከአሜሪካ አቻዎቻቸው ጋር ትከሻ ለትከሻ ሆነው ኮርያ የተዋጉት «የቃኘው» ሠራዊት አባላት አብዛኛዎቹ የተመለመሉት ከክብር ዘበኛ ነበር።

የአሜሪካ ተጽዕኖ ከሁሉም ጎልቶ የታየው በሥልጠናና በትጥቅ መስክ ነበር። ከ1938 እስከ 1964 ድረስ አሜሪካ ያደረገችው ወታደራዊ እርዳታ በ180 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚገመት ነበር። ከ1945 እስከ 1960 ባለው ጊዜ ከ2500 በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካን አገር የተለያየ ወታደራዊ ሥልጠና አግኝተዋል። ከዚህ በተረፈ ጂቱ፣ ጸረ አውሮፕላን መቃወሚያው፣ የባሕር ኃይል መርከቡና ጀልባው፣ የእግረኛው መሣሪያና አንዳንዴ ዩኒፎርሙም ሳይቀር የሚመጣው ከአሜሪካ ነበር። በትጥቅም ሆነ በሥልጠና የአሜሪካ ወታደራዊ እርዳታ ቁንጮ ውጤት ተብሎ የሚገመተውና በዘመናዊነቱና በቅልጥፍናውም ዝናን ያተረፈው የአየር ኃይሉ ነበር።

የአሜሪካን አሻራ በአየር ኃይሉ ብቻ ሳይሆን በአየር መገናኛም ጉልህ ነበር። በ1938 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ለማቋቋም በተጠራው ጉባኤ ለመሳተፍ አሜሪካ ሄዶ የነበረው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ባገሪቱ የአየር መንገድ ለማቋቋም የአሜሪካን እርዳታ ጠየቀ። በሚቀጥለው ዓመትም በኢትዮጵያ መንግሥትና «ትራንስኮንቲኔንታል ኤንድ ዌስተርን ኤይርላይን» (በእንግሊዝኛ ምሕጻረ ቃሉ ቲ ደብልዩ ኤ) በተባለው የአሜሪካ የአየር መንገድ ኩባንያ መካከል በተደረገው ስምምነት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተቋቋመ። ሠላሳ ዓመታት ያህል በቆየው በዚህ ስምምነት መሠረትም አሜሪካኖች ለአየር መንገድ ሥራ አስኪያጆችና የቴክኒክ ተቆጣጣሪዎች ሲመድቡ ቆዩ። የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ቅርስ በሆነ አምስት ሲ 47 የተባሉ አውሮኘላኖች ሥራውን የጀመረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ሦስቱን ለመንገደኛ እንዲያመች አሻሽሎ



5.1 የአሜሪካ የጦር ሰፈር በቃኘው /አሥመራ/

ላይ ያላትን የይገባኛል ጥያቄ እንደገና ስታጠናክር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአሜሪካን እጅ በማስገባት አጋዴንን የሙጥኝ ብለው በያዙት እንግሊዞች ላይ የአሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲያርፍ ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ላይ አሜሪካኖች የኢትዮጵያን የግዛት ጥያቄ ለመደገፍም ሆነ ወታደራዊ እርዳታ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም።

ነገሩ መለወጥ የጀመረው ከ1943 በኋላ ነው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንደተሳሰረች፣ አሜሪካም አሥመራ ባላት የመገናኛ ጣቢያ ምክንያት የመካከለኛ ምሥራቅ እስትራቴጂካዊ ጥቅሟ ከኢትዮጵያ ጋር ተያያዘ። በዚሁ ዓመት የእንግሊዝ ወታደራዊ ተራድኦ ቡድን ከኢትዮጵያ ነቅሎ ሲወጣ፣ ኢትዮጵያ የአሜሪካን ወታደራዊ እርዳታ ለማግኘት ስታደርግ የቆየችው ውትወታም ተደማጭነት አገኘ። በ1944 በግብፅ የተካሄደው አብዮትም አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅና በቀይ ባሕር ዳርቻ ያላትን የወዳጅና ጠላት አሰላለፍ እንደገና እንድታጤን አስገደዳት። እነዚህ ሁኔታዎች ናቸው በ1945 በኢትዮጵያና አሜሪካ መካከል ለተደረገውና ለሚቀጥለት 20 ዓመታት ያህል የግንኙነታቸው መሠረት ለሆነው ስምምነት መነሾ የሆኑት። በስምምነቱም መሠረት አሜሪካ ባዲስ ስያሜው «ቃኘው» በተባለው የአሥመራ የመገናኛ ጣቢያ ላይ የነበራትን ይዞታ ስታረጋግጥ፣ በአጸፋውም ሰፊ የወታደራዊ እርዳታ ፕሮግራም ለመጀመር ተስማማች። «ማግ» በተባለው የወታደራዊ እርዳታ አማካሪ ቡድን አማካይነት




እምስት ሚሊዮን ዶላር ወጪ አድርጋ 60000 ሰው ያለው ባለሦስት ክፍለ ጦር ሠራዊት አቋቋመች። ይህ ዓይነት እርዳታ በተከታዮቹ ዓመታት እየቀጠለ ሄዶ በአብዮቱ ዋዜማ አሜሪካ ለአፍሪቃ ከምትሰጠው ወታደራዊ እርዳታ ውስጥ 60 በመቶው የሚውለው ኢትዮጵያ ላይ ሊሆን ቻለ።

ስለዚህም ከ1945 በኋላ ያሉት ዓመታት አሜሪካ በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት መድረክ ላይ መሪ ተዋናይ የሆነችበትና ወሳኝ ሚና የተጫወተችበት ወቅት ነበር ማለት ይቻላል። የአሜሪካ ተጽዕኖ ባገሪቱ ሕይወት የተለያዩ ገጽታዎች የተንጸባረቀ ቢሆንም በተለይ ጎልቶ የታየው በወታደራዊ ድርጅት፣ በመገናኛና በትምህርት ዘርፍ ነው። በወታደራዊው መስክ ይህ ተጽዕኖ ጎልቶ የታየው በጦር ሠራዊት ውስጥ ሲሆን፣ እያደር ግን በሌሎች ቀድሞ አሜሪካውያን ባልሆኑ የውጭ አማካሪዎች ይመሩ ወደነበሩት የጦር ኃይሉ ክፍሎችም ተዛመተ። በዚህ ዓይነት መጀመሪያ በስዊድኖች ቁጥጥር ሥር የነበረው የአየር ኃይልና በኖርዌጆያኖች ይተዳደር የነበረው የባሕር ኃይል ወደ አሜሪካኖች ዞረ። በእንግሊዙ የሳንድኸርስት የጦር አካዳሚ አምሳያ የተፈጠረውና የእንግሊዛውያን ግርፍ በሆኑት ሕንዶች የሚተዳደረው የሐረር የጦር አካዳሚ እንኳ የአሜሪካ የሰውና የማቴሪያል እርዳታ አልተለየውም ነበር። ምናልባት የአሜሪካ ዱካ ያልደረሰባቸው ሁለት የጦር ክፍሎች ቢኖሩ የፖሊስ ሠራዊትና የክብር ዘበኛ ናቸው። ፖሊስ በጀርመንና በእስራኤል፣ ክብር ዘበኛ ደግሞ በስዊድን የሰለጠኑ ነበሩ። ያም ሆኖ ግን ከአሜሪካ አቻዎቻቸው ጋር ትከሻ ለትከሻ ሆነው ኮርያ የተዋጉት «የቃኘው» ሠራዊት አባላት አብዛኛዎቹ የተመለመሉት ከክብር ዘበኛ ነበር።

የአሜሪካ ተጽዕኖ ከሁሉም ጎልቶ የታየው በሥልጠናና በትጥቅ መስክ ነበር። ከ1938 እስከ 1964 ድረስ አሜሪካ ያደረገችው ወታደራዊ እርዳታ በ180 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚገመት ነበር። ከ1945 እስከ 1960 ባለው ጊዜ ከ2500 በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካን አገር የተለያየ ወታደራዊ ሥልጠና አግኝተዋል። ከዚህ በተረፈ ጀቱ፣ ጸረ አውሮፕላን መቃወሚያው፣ የባሕር ኃይል መርከቡና ጀልባው፣ የእግረኛው መሣሪያና አንዳንዴ ዩኒፎርሙም ሳይቀር የሚመጣው ከአሜሪካ ነበር። በትጥቅም ሆነ በሥልጠና የአሜሪካ ወታደራዊ እርዳታ ቁንጮ ውጤት ተብሎ የሚገመተውና በዘመናዊነቱና በቅልጥፍናውም ዝናን ያተረፈው የአየር ኃይሉ ነበር።

የአሜሪካን አሻራ በአየር ኃይሉ ብቻ ሳይሆን በአየር መገናኛም ጉልህ ነበር። በ1938 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ለማቋቋም በተጠራው ጉባኤ ለመሳተፍ አሜሪካ ሄዶ የነበረው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ባገሪቱ የአየር መንገድ ለማቋቋም የአሜሪካን እርዳታ ጠየቀ። በሚቀጥለው ዓመትም በኢትዮጵያ መንግሥትና «ትራንስኮንቲኔንታል ኤንድ ዌስተርን ኤይርላይን» (በእንግሊዝኛ ምሕጻረ ቃሉ ቲ ደብልዩ ኤ) በተባለው የአሜሪካ የአየር መንገድ ኩባንያ መካከል በተደረገው ስምምነት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተቋቋመ። ሠላሳ ዓመታት ያህል በቆየው በዚህ ስምምነት መሠረትም አሜሪካኖች ለአየር መንገድ ሥራ አስኪያጅችና የቴክኒክ ተቆጣጣሪዎች ሲመድቡ ቆዩ። የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ቅርስ በሆነ አምስት ሲ 47 የተባሉ አውሮፕላኖች ሥራውን የጀመረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ሦስቱን ለመንገደኛ እንዲያመች አሻሽሎ



5.2 የጭነት ከብቶችና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዲ.ሲ. 3 አውሮፕላን ሜዳውን ሲሸሙ

ዲ. ሲ. 3 የሚል ስያሜ በመስጠት፣ ከዚያ ዲ. ሲ. 6 የተባሉ ባለ አራት ሞተር አውሮፕላኖች በማስመጣት አገልግሎቱን ካሰፋ በኋላ፣ በመጨረሻ በ1955 ወደ ጄት ዓለም ተሸጋገረ::

በአየር መንገድ ታሪክ ውስጥ ጎላ ያለ ሥፍራ የያዘው አስተዳደሩን ከአሜሪካውያን ወደ ኢትዮጵያውያን የማሸጋገሩ ሂደት ነው:: ይህ በ1966ቱ አብዮት ዋዜማ በሁሉም መስክ (በረራ፣ የቴክኒክ አገልግሎትና አስተዳደር) የተሳካ ቢሆንም እዚያ ለመድረስ ብዙ ትግል ጠይቋል:: አሜሪካኖቹ በአየር መንገዱ ላይ የነበራቸውን ቁጥጥር ለማስረከብ እምብዛም ፈቃደኛ አልነበሩም:: ሆኖም በ1964 የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሲሾም የአየር መንገዱ ፍጹም ኢትዮጵያዊነት በውል ተረጋገጠ:: አየር መንገዱ በየብስ መገናኛ ለማገናኘት አዳጋች ሆነው የቆዩትን ያገሪቱን ክፍሎች በማቀራረብና በማስተሳሰር፣ እንደ ቡና ያሉትን ሸቀጦች ከደቡብ ምዕራብ ዳርቻዎች በፍጥነትና በብዛት በማጓጓዝ፣ ባገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውቷል:: በዓለም አቀፍ በረራ አገልግሎቱም አዳዲስ ምዕራፎች ከፍቷል:: በዚህም ረገድ በተለይ ሊጠቀስ የሚገባው የአፍሪቃን አገሮች ከቅኝ ገዥዎቻቸው ጋር ያቆራኘውን እትብት የቆረጠውና እንዲጋጣሚ በአፍሪቃ የነፃነት ዓመት እ.ኤ.አ 1960 የተመረቀው ምሥራቅ አፍሪቃን ከምዕራብ አፍሪቃ ያገናኘው




መሥመር ነው:: እንደዚሁም በ1965 ዓለም አቀፍ ግርዶሽን ጥሶ ወደ ቤይጂንግ በሙብረር የመጀመሪያው አፍሪቃዊ አየር መንገድ ሆኗል::

የኢትዮጵያና አሜሪካ ግንኙነት ጠቃሚ ወጤቶችን ያስመዘገበው በአየር መገናኛ ብቻ ሳይሆን በየብስም ጭምር ነው:: በ1933 ጣልያኖች ከኢትዮጵያ ሲወጡ ዝናን ያተረፉላቸው አውራ ጐዳናዎች በጦርነቱ ምክንያት ፈራርሰው ይገኙ ነበር:: ስለዚህም እነዚህን መንገዶች መጠገኑ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከተደቀኑበት አስቸኳይ ተግባራት አንዱ ነበር:: በሌላው መስክ እንደታየው ሁሉ በዚህም እንግሊዞች እርዳታ ለመስጠዝር ፈቃደኛ አልነበሩም:: ስለሆነም ኢትዮጵያ በግድ ፊቷን ወደ አሜሪካ ማዞር ነበረባት:: በአሜሪካ አጋዥነትም በ1943 የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን ተቋቋሞ ያገሪቱን መንገዶች የመጠገኑንና አዳዲስ መንገዶችንም የመሥራቱን ኃላፊነት ተረከበ:: የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በአሜሪካው የሕዝብ መንገዶች (ኦፊስ ኦፍ ፐብሊክ ሮድስ) አምሳያ ከመቀረፁም በላይ ኢትዮጵያውያን እ.ኤ.አ. በ1962 የሥራ አስኪያጅነቱን ሥልጣን እስከሚረከቡም ድረስ የሚካሄደው በአሜሪካውያን ነበር:: የባለሥልጣኑ የመንገድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ሊከናወኑ የቻሉትም በአሜሪካን ጥላ ሥር ከሚገኘው ከዓለም አቀፍ የመልሶ መገንባትና ልማት ባንክ (ኢንተርናሽናል ባንክ ኦፍ ሪኮንስትራክሽን ኤንድ ዴቨሎፕመንት) በተገኘ ብድር ሲሆን በዚህም አማካይነት ባንኩ በባለሥልጣኑ ተግባራት ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር ኃይል ነበረው ማለት ይቻላል::

የኋላ ኋላ ቴሌኮምዩኒኬሽን የስዊድኖች ቤት ቢሆንም በቦርድ የሚተዳደር የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት የማቋቋም ሐሳብ መጀመሪያ የመነጨው ከሜሪካኖች ነው:: የቴሌ አገልግሎት በኢትዮጵያ ረዘም ያለ ታሪክ አለው:: ባኤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የማዕከላዊውን መንግሥት ቁጥጥር ለማጠናከር ያገዘ ያገር ውስጥ የቴሌፎን መሥመር ከመዘርጋቱም በላይ አገሪቱ በምዕዋና በጅቡቲ በኩል ዓለም አቀፍ የቴሌፎን ግንኙነት ነበራት:: በኢጣልያ ወረራ ዋዜማ የሬዲዮ ግንኙነት መጀመሩም አገሪቱን በጎረቤት ቅኝ ግዛት አገሮች ላይ ከነበራት ጥገኝነት በመጠኑ ነፃ ሊያደርጋት ቻለ:: ነፃነት ከተመለሰ ወዲህ በየብስ መገናኛ እንደታየው በቴሌ አገልግሎትም እንደገና ለመደራጀት የሚጠብቀው ሥራ ከባድ ነበር:: እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ከአሜሪካ በርዳታ በተገኙ ትራንስሚተሮች አማካይነት ዋና ዋና ከተሞችን በሬዲዮ ለማገናኘት ተችሎ ነበር:: በተጨማሪም ከአሜሪካዊው ድንበር ዘለል ኩባንያ «ኢንተርናሽናል ቴሌፎን ኤንድ ቴሌግራፍ» (በእንግሊዝኛ ምሕጻረ ቃሉ አይ ቲ ቲ) ጋር በመዋዋል የተበላሹ የቴሌፎን መሥመሮችን ለመጠገን ሙከራ ተደርጓል:: በመጨረሻም በዚሁ ኩባንያ በተደረገ ጥናት መሠረት ነው የንጉሠ ነገሥቱ የቴሌኮምዩኒኬሽን ቦርድ በ1945 የተመሠረተው:: ለስሙ የአክሲዮን ኩባንያ ይባል እንጂ አክሲዮኖቹ በሙሉ በመንግሥት የተገዙ በመሆናቸው የመንግሥት ድርጅት ነበር:: በ1958 ኢትዮጵያዊ ሥራ አስኪያጅ እስከሚሾም ድረስ ቦርዱ የሚተዳደረው በስዊድናውያን ነበር::

ምናልባት የአሜሪካኖች ተጽዕኖ ጎልቶ የማይታይበት ዘመናዊ መስክ ቢኖር የባንክ አገልግሎት ነው:: ከነፃነት ወዲህ የነበረው የባንክ አገልግሎት የትውልድ ሐረግ ከጣልያን በፊት ከነበሩት በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ከነበረው የአበሻ ባንክና ኋላ መንግሥት ከወረሰው የኢትዮጵያ ባንክ ጋር የተያያዘ ነው::



5.2 የጭነት ከብቶችና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዲ.ሲ 3 አውሮፕላን ሜዳውን ሲሻሙ

ዲ. ሲ 3 የሚል ስያሜ በመስጠት፣ ከዚያ ዲ ሲ 6 የተባሉ ባለ አራት ሞተር አውሮፕላኖች በማስመጣት አገልግሎቱን ካሰፋ በኋላ፣ በመጨረሻ በ1955 ወደ ጀት ዓለም ተሸጋገረ።

በአየር መንገድ ታሪክ ውስጥ ጎላ ያለ ሥፍራ የያዘው አስተዳደሩን ከአሜሪካውያን ወደ ኢትዮጵያውያን የማሸጋገሩ ሂደት ነው። ይህ በ1966ቱ አብዮት ዋዜማ በሁሉም መስክ (በረራ፣ የቴክኒክ አገልግሎትና አስተዳደር) የተሳካ ቢሆንም እዚያ ለመድረስ ብዙ ትግል ጠይቋል። አሜሪካኖቹ በአየር መንገዱ ላይ የነበራቸውን ቁጥጥር ለማስረከብ እምብዛም ፈቃደኛ አልነበሩም። ሆኖም በ1964 የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሲሾም የአየር መንገዱ ፍጹም ኢትዮጵያዊነት በውል ተረጋገጠ። አየር መንገዱ በየብስ መገናኛ ለማገናኘት አዳጋች ሆነው የቆዩትን ያገሪቱን ክፍሎች በማቀራረብና በማስተሳሰር፣ እንደ ቡና ያሉትን ሸቀጦች ከደቡብ ምዕራብ ዳርቻዎች በፍጥነትና በብዛት በማጓጓዝ፣ ባገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውቷል። በዓለም አቀፍ በረራ አገልግሎቱም አዳዲስ ምዕራፎች ከፍቷል። በዚህም ረገድ በተለይ ሊጠቀስ የሚገባው የአፍሪቃን አገሮች ከቅኝ ገዥዎቻቸው ጋር ያቆራኘውን እትብት የቆረጠውና እንዳጋጣሚ በአፍሪቃ የነፃነት ዓመት እ.ኤ.አ 1960 የተመረቀው ምሥራቅ አፍሪቃን ከምዕራብ አፍሪቃ ያገናኘው



መሥመር ነው። እንደዚሁም በ1965 ዓለም አቀፍ ግርዶሽን ጥሶ ወደ ቤይጂንግ በመብረር የመጀመሪያው አፍሪቃዊ አየር መንገድ ሆኗል።

የኢትዮጵያና አሜሪካ ግንኙነት ጠቃሚ ወጤቶችን ያስመዘገበው በአየር መገናኛ ብቻ ሳይሆን በየብስም ጭምር ነው። በ1933 ጣልያኖች ከኢትዮጵያ ሲወጡ ዝናን ያተረፉላቸው አውራ ጉዳናዎች በጦርነቱ ምክንያት ፈራርሰው ይገኙ ነበር። ስለዚህም እነዚህን መንገዶች መጠገኑ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከተደቀኑበት አስቸኳይ ተግባራት አንዱ ነበር። በሌላው መስክ እንደታየው ሁሉ በዚህም እንግሊዞች እርዳታ ለመስጠዝር ፈቃደኛ አልነበሩም። ስለሆነም ኢትዮጵያ በግድ ፊቷን ወደ አሜሪካ ማዞር ነበረባት። በአሜሪካ አጋዥነትም በ1943 የአውራ ጉዳና ባለሥልጣን ተቋቋቁሞ ያገሪቱን መንገዶች የመጠገኑንና አዳዲስ መንገዶችንም የመሥራቱን ኃላፊነት ተረከበ። የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በአሜሪካው የሕዝብ መንገዶች (ኦፊስ ኦፍ ፐብሊክ ሮድስ) አምሳያ ከመቀረፁም በላይ ኢትዮጵያውያን እ.ኤ.አ. በ1962 የሥራ አስኪያጅነቱን ሥልጣን እስከሚረከቡም ድረስ የሚካሄደው በአሜሪካውያን ነበር። የባለሥልጣኑ የመንገድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ሊከናወኑ የቻሉትም በአሜሪካን ጥላ ሥር ከሚገኘው ከዓለም አቀፍ የመልሶ መገንባትና ልማት ባንክ (ኢንተርናሽናል ባንክ ኦፍ ሪኮንስትራክሽን ኤንድ ዴቬሎፕመንት) በተገኘ ብድር ሲሆን በዚህም አማካይነት ባንኩ በባለሥልጣኑ ተግባራት ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር ኃይል ነበረው ማለት ይቻላል።

የኋላ ኋላ ቴሌኮምዩኒኬሽን የስዊድኖች ቤት ቢሆንም በቦርድ የሚተዳደር የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት የማቋቋም ሐሳብ መጀመሪያ የመነጨው ካሜሪካኖች ነው። የቴሌ አገልግሎት በኢትዮጵያ ረዘም ያለ ታሪክ አለው። ባዳ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የማዕከላዊውን መንግሥት ቁጥጥር ለማጠናከር ያገዘ ያገር ውስጥ የቴሌፎን መሥመር ከመዘርጋቱም በላይ አገሪቱ በምፅዋና በጅቡቲ በኩል ዓለም አቀፍ የቴሌፎን ግንኙነት ነበራት። በኢጣልያ ወረራ ዋዜማ የሬዲዮ ግንኙነት መጀመሩም አገሪቱን በጎረቤት ቅኝ ግዛት አገሮች ላይ ከነበራት ጥገኝነት በመጠኑ ነፃ ሊያደርጋት ቻለ። ነፃነት ከተመለሰ ወዲህ በየብስ መገናኛ እንደታየው በቴሌ አገልግሎትም እንደገና ለመደራጀት የሚጠብቀው ሥራ ከባድ ነበር። እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ከአሜሪካ በርዳታ በተገኙ ትራንስሚተሮች አማካይነት ዋና ዋና ከተሞችን በሬዲዮ ለማገናኘት ተችሎ ነበር። በተጨማሪም ከአሜሪካዊው ድንበር ዘለል ኩባንያ «ኢንተርናሽናል ቴሌፎን ኤንድ ቴሌግራፍ» (በእንግሊዝኛ ምሕጻረ ቃሉ አይ ቲ ቲ) ጋር በመዋዋል የተበላሹ የቴሌፎን መሥመሮችን ለመጠገን ሙከራ ተደርጓል። በመጨረሻም በዚሁ ኩባንያ በተደረገ ጥናት መሠረት ነው የንጉሠ ነገሥቱ የቴሌኮምዩኒኬሽን ቦርድ በ1945 የተመሠረተው። ለስሙ የአክሲዮን ኩባንያ ይባል እንጂ አክሲዮኖቹ በሙሉ በመንግሥት የተገዙ በመሆናቸው የመንግሥት ድርጅት ነበር። በ1958 ኢትዮጵያዊ ሥራ አስኪያጅ እስከሚሾም ድረስ ቦርዱ የሚተዳደረው በስዊድናውያን ነበር።

ምናልባት የአሜሪካኖች ተጽዕኖ ጎልቶ የማይታይበት ዘመናዊ መስክ ቢኖር የባንክ አገልግሎት ነው። ከነፃነት ወዲህ የነበረው የባንክ አገልግሎት የትውልድ ሐረግ ከጣልያን በፊት ከነበሩት በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ከነበረው የአበሻ ባንክና ኋላ መንግሥት ከወረሰው የኢትዮጵያ ባንክ ጋር የተያያዘ ነው።

በአምስቱ ዓመት የጣልያን አገዛዝ አያሌ የኢጣልያ ባንኮች (ለምሳሌ ባንኮ ዲ ሮማ፣ ባንኮ ዲ ናፖሊ) ቅርንጫፎቻቸውን በኢትዮጵያ ከፍተው ነበር:: ጣልያኖች ከወጡ በኋላ በ1934 የቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እንደ ንግድ ባንክም እንደ ብሔራዊ ባንክም ሲያገለግል ከቆየ በኋላ፣ በ1955 በወጣው ዐዋጅ መሠረት ሁለቱን ተግባራት ለይተው የሚያከናውኑ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ብሔራዊ ባንክ ተቋቋሙ:: በዚያው ዓመት አዲስ አበባ ባንክ የተባለ የግል ባንክ ተመሥርቶ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የመንግሥት ባንኩ ተፎካካሪ ለመሆን በቃ:: የቅድመ አብዮት የባንክ አገልግሎት ሌሎች ሁለት ዘርፎች ነበሩት:: እነሱም በ1962 አንጋፋውን የልማት ባንክንና የኢንቨስትሜንት ኮርፖሬሽንን በማዋሐድ የተደራጀው የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክና በ1958 የተመሠረተው የቁጠባና ሞርጌጅ ባንክ ናቸው::

አሜሪካኖች በትምህርት መስክ የነበራቸው ተጽዕኖ ደግሞ ፈጽሞ የሚያጠያይቅ አልነበረም:: ከአንድ ሁለት የእንግሊዝና የፈረንሳይን ሥርዓት ከሚያንጸባርቁ ምርጥ ትምህርት ቤቶች በስተቀር፣ ያገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ባብዛኛው በአሜሪካው አምሳያ የተፈጠረ ነበር ማለት ይቻላል:: ወጣት ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ትምህርት ለመገብየት የሚሄዱትም ባብዛኛው ወደ አሜሪካ ሆነ:: እንደ ፖይንት ፎር፣ ዩ.ኤስ.ኤይድ፣ አፍግራድና አፍሪካን አሜሪካን ኢንስቲትዩት የመሳሰሉት ድርጅቶች ነበሩ ለነዚህ ወጣቶች ዋና የነፃ ትምህርት ዕድል ከፋቾች:: ባገሪቱ ውስጥ የተቋቋመው ዩኒቨርሲቲም በምዝገባም ሆነ በትምህርት ውጤት መመዘኛ ሥርዓቱ ከመደበኛ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ አሠራር የተለየ አልነበረም:: ከዚያም አልፎ የዩኒቨርሲቲ የአስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንትነት ስፍራ ለረጅም ጊዜ ለአሜሪካ ዜጎች የተመደበ ነበር:: በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም፣ በተለይ በ1950ዎቹ የመጡት የአሜሪካ የሰላም ጓድ ልዑካን እስከዚያን ጊዜ ድረስ ገኖ የነበረውን የሕንድ መምህራን የበላይነት በብርቱ አዳከሙት::

ይህን ያህል የአሜሪካ ተጽዕኖ ባገሪቱ ሕይወት ጎልቶ መታየቱ ቅሬታንና ጥላቻን መፍጠሩ አልቀረም:: በተለይም ተማሪዎች ይህን ሁኔታ እንደ አሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ነጸብራቅ ነበር የሚያዩት:: ስለዚህም በ1960ዎቹ ዓመታት ፀረ አሜሪካዊነት የተማሪው የፖለቲካ ባሕል አንድ አይነተኛ መለዮ ሆኖ ነበር:: እንዲጋጣሚ ሆኖ ግን የአሜሪካ ጥላቻ እየከረረ በመጣበት ወቅት አሜሪካም እራሷ ከኢትዮጵያ ገሸሽ ለማለት የፈለገችበት ወቅት ነበር:: በሳተላይት መረጃን የመሰብሰብ ጥበብ እያደገ ሲሄድ የኢትዮጵያና አሜሪካ ወዳጅነት መሠረት የነበረው የቃኘው ጣቢያም ጠቃሚነቱ እየቀነሰ መጣ:: በተጨማሪም በእንዋር ሳዳት አመራር ግብፅ የቀድሞ የውጭ ፖሊሲዋን ከልሳ አፍቃሬ ምዕራብ እየሆነች ስትሄድ፣ በአሜሪካ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ ወስጥ ኢትዮጵያ ያላት እርባናም እንደበፊቱ መሆኑ ቀረ:: ስለዚህም እንዲጋጣሚ ሆኖ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ፍጻሜው ሲቃረብ ሁነኛ ወዳጁን ማጣት ጀመረ::

## ማኅበራዊና ኢኮኖማያዊ ኑሮ

ከ1933 በኋላ አያሌ ከተሞች ቢቆረቆሩና አንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ቢቋቋሙም ቅሉ፣ ያገሪቱ አጠቃላይ ሕይወት የገጠሬነት ባሕርይ አለቀቀውም ነበር:: ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ የሚተዳደረው በእርሻ ሲሆን ካገሪቱ ጠቅላላ




ሀብት 60 በመቶው የሚገኘውም ከዚሁ ከእርሻ ነበር:: እንደዚሁም ወደ ውጭ ከሚላኩት ሸቀጦች 90 በመቶ የእርሻ ውጤቶች ሲሆኑ፣ ከነዚህም 60 በመቶው ቡና ነበር:: ባገር ወስጥ ንግድ ደግሞ የመሪነትን ስፍራ የያዘው የእህል ዘር ሲሆን ከዚያም ቀጥሎ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ነበሩ:: ያገሪቱ የቀንድ ከብት ሀብትም ሆነ ሕዝቡ በነፍስ ወከፍ የነበረው የሥጋ ፍጆታም በአፍሪቃ አህጉር ውስጥ አቻ የሌለው ነበር:: እርሻ በብሔራዊ ኢኮኖሚው ውስጥ ጉልህ ስፍራ በመያዙ ምክንያት መሬትና ይዞታውም ቁልፍ ቦታ እንዲኖረው አደረገ::

## እርሻና የመሬት ይዞታ

በድኅረ ነፃነት ዘመን በመሬት ይዞታ ረገድ የታየው ዐቢይ ቁም ነገር ከ1928 በፊት የጀመረው መሬት ግላዊ ሀብት እየሆነ የመምጣቱ ሂደት መፋጠን ነው:: ይህ ሂደት በተለይ በስፋት የታየው በደቡቡ ያገሪቱ ክፍል ነበር:: ሂደቱ ሦስት ገጽታዎች ነበሩት፤ ባንድ መልኩ ቀደም ሲል የደቡቡ ገበሬ በገባርነት ያገለግላቸው የነበሩት ከሰሜን የመጡ ሰፋሪዎች ቀስ በቀስ ከግብሩና ካገልግሎቱ አልፈው መሬቱን በግዥም ሆነ በንጥቂያ የራሳቸው ማድረግ ጀመሩ:: ሁለተኛ ለመንግሥት ባለሚሎች በደሞዝ ፈንታ በማደሪያነት የተሰጠው መሬት ከጊዜ በኋላ ወደ ርስትነት ተለወጠ:: የግል ይዞታ የተስፋፋበት ሦስተኛውና ምናልባትም ዋነኛው መንገድ መንግሥት በስፋት ከያዘውና የመንግሥት መሬት ከተባለው እየቆረሰ ለአገልጋዮቹ መስጠቱ ነው::

መንግሥት መሬት እንደዚህ መቸር የፈለገበት ዋና ምክንያት የድጋፍ መሠረቱን ለማስፋት አቅዶ ይመስላል:: ይህ ፖሊሲ በሥራ ላይ መዋል የጀመረው ነፃነት እንደተመለሰ ነው:: ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው ግን የኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ማክተሚያ ላይ ባንድ በኩል ሕዝባዊ ተቃውሞ እያደገበት ሲሄድ በሌላ በኩል ደግሞ ደጋፊዎቹን ለማብራከት በሚጥርበት ወቅት ነው:: የዚህ የመንግሥት የመሬት ችሮታ ዋና ተጠቃሚዎች አርበኞች፣ ስደተኞች፣ ወታደሮችና የሲቪል ሠራተኞች ነበሩ:: ወደ ኋላ ፖሊሲውን የፍትሕና የልማት ሽፋን ለመስጠት ታስቦ መሬት የሌላቸውና ሥራ አጥ የሆኑ ኢትዮጵያውያንም ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተገልጾ ነበር:: ይሁን እንጂ አጠቃላይ የመሬት ስርጭቱ ሲታይ ዋና ተጠቃሚዎቹ እነማን እንደነበሩ ግልጽ ነው:: መንግሥት ቅድሚያ የሚሰጠው በጦርነትም ሆነ በሰላም በታማኝነት ለሚያገለግሉት ሆነ:: ይህንንም በአኀዝ ለማስረዳት ከ1933 በኋላ ከታደለው 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ መሬት አልባ ወይም ሥራ አጥ የሆኑት ሊያገኙ የቻሉት ጥቂት ሺዎቹን ብቻ ነበር::

የግል መሬት ይዞታ መስፋፋት አያሌ ውጤቶች ነበሩት:: መጀመሪያ በቃላት ትርጓሜ ደረጃ አንዳንድ ለውጦች መታየት ጀመሩ:: ለምሳሌ ርስት የሚለው ቃል ቀደም ሲል በዘር ሐረግ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን መሬት የመጠቀም መብት ሲያመለክት፤ አሁን ግን ፍጹማዊ የሆነ የግል ሀብትን የሚጠቁም ሆነ:: እንደዚሁም ገባር ቀድሞ መበዝበዝን፣ መረገጥን፣ የሚያመለክት ሲሆን አሁን ግን የግብር ከፋይ ዜጋነትን ትርጉም ያዘለ ሆነ::




6. ኢትዮጵያ በ1966

የፍጹማዊ ግላዊ ሀብት (absolute private property) ዓይነተኛ ባሕርይ በሽያጭም ሆነ በሌላ መንገድ ለሌላ የማስተላለፍን ያልተገደበ መብት ማመልከቱ ነው:: በኋላ፣ በተለይም በአብዮቱ መዳረሻ ላይ፣ የመሬት ሽያጭ እየተስፋፋ መጣ:: ባንፃሩም የመሬት ዋጋ ከፍ አለ:: ለምሳሌ በ1940ዎቹና በ1950ዎቹ መካከል ብቻ በምሥራቅ ሸዋ የመሬት ዋጋ ሦስት እጅ አደገ:: የዚህ የመሬት ሽያጭ አንዱ ውጤትም መሬት በጥቂት ሰዎች እጅ እየተጠራቀመ መምጣቱ ነው:: በተለይም ግላዊ የመሬት ይዞታ ይበልጥ በተስፋፋበት በደቡብ ኢትዮጵያ ትላልቅ የመሬት



ይዞታዎች የተለመዱ ሆኑ:: አንዳንድ ባለፀጎች እስከ ሁለት መቶ ሺህ ሄክታር የሚደርሱ ይዞታዎች ነበሯቸው:: በተቃራኒው በሰሜን ኢትዮጵያ የውርስ የመሬት ይዞታ ሥር ሰዶ በመቆየቱ ዋናው ችግር ከፍተኛ የመሬት መሸንሸንና በይገባኛል የሚነሡ የመሬት ሙግቶች ሆኑ::

የግል ይዞታ መጠናከር አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ውጤት የጭሰኝነት መስፋፋት ነው:: ባገሪቱ ካሉት ከ50 እስከ 60 በመቶ የሚሆኑ ይዞታዎች በዚህ ዘርፍ የሚመደቡ ነበሩ:: ጭሰኝነት ይበልጥ የተስፋፋው ከሰሜኑ ይልቅ በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል ነበር:: ለምሳሌ የጭሰኝነት ስርጭት በሐረርጌ 75 ከመቶ፣ በሸዋ 68 ከመቶ፣ በከፋ ደግሞ 62 ከመቶ ነበር:: ባንፃሩ በሰሜኑ ክፍል፣ በበጌምድር 15 ከመቶ፣ በጎጃም 20 ከመቶ፣ በትግሬ ደግሞ 25 ከመቶ ነበር:: የጭሰኝነት ሌላ ገጽታው ደግሞ የአርሻ ባለመሬቶች ከገጠር ይልቅ በከተማ መከማቸታቸው ነው:: በ1950ዎቹ ዓመታት ከጠቅላላው ባለመሬቶች ውስጥ 25 ከመቶው እያሳረሱ እነሱ በከተማ የሚኖሩ ነበሩ:: አብዛኛው የጭሰኝነት ውሉች በጽሑፍ ሳይሆን በቃል የሚደረጉ ሲሆን፣ በውሉም መሠረት እንደየሁኔታው ጭሰኛው ካፈራው ሰብል ለባለመሬቱ ሩቡን፣ ሲሶውን ወይም እኩሌታውን ይከፍላል:: ጭሰኛው ለባለመሬቱ ከሚከፍለው ከዚህ ድርሻ በተጨማሪ የዐሥራትና አንዳንዴ ከዚያም አልፎ የመሬት ግብር ዕዳ ተሸካሚ ነበር:: የመሬት ዋጋ እየጨመረ ሲሄድም ባለመሬቱ በጭሰኛው ላይ የሚያደርገው ጫናም እያደገ መጣ:: በተለይ ባንዳንድ ደቡብ ግዛቶች ጭሰኛውን እስከናካቴው አባሮ በትራክተር ማረስም ተስፋፋ::

ከዚህ የግል ይዞታ መስፋፋት ጎን ለጎን ማዕከላዊው መንግሥት ከመሬት የሚያገኘውን ገቢ ለማሳደግ የሚያደርገው ጥረት ባጠቃላይ መልኩ ሲታይ በመንግሥትና በገበሬው መካከል ሆነው ገቢውን የሚቀራመቱትን አካሎች በማስወገድ መንግሥት ራሱ የተረፈ ምርት ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረግ ገጽታ ነበረው:: በሌላ መልኩም ቀድሞ በዓይነትና በጉልበት ይከፈል የነበረውን ግብር በገንዘብ እንዲሆን የማድረግ አዝማሚያ ነበረው:: ከጣልያን ወረራ በፊት የጀመረው ይህ ሂደት ከነፃነት መመለስ በኋላ እየተፋጠነ ሄደ:: ይሁን እንጂ ከ1933 በኋላ ባሉት የመጀመሪያ ዓመታት መንግሥት በጠቅላይ ግዛቶች ላይ የነበረው ቁጥጥር የላላ በመሆኑ በጥንቃቄ መራመድ ነበረበት:: ለምሳሌ በ1934 በወጣው የመሬት ግብር ዐዋጅ ላይ እንደተገለጸው፣ በአምስቱ ዓመታት የጠላት ወረራ ወቀት በሕዝብና በአገር ላይ የደረሰውን ጉዳት በማመዛዘን የመሬት ግብር ከ1928 በፊት የነበረው ተመን እኩሌታ እንዲሆን ተደንግጎ ነበር:: በዚህም መሠረት በአንድ ጋሻ የተለካ መሬት የሚከፈለው በለም 15 ብር፣ በለም ጠፍ 10፣ በጠፍ 5 እንዲሆን ተወሰነ::

ይሁን እንጂ ለግብር ከፋዩ ሕዝብ የተደረገለት ሐዘኔታ ሊቀጥል የሚችል አልነበረም:: ስለሆነም በ1937 የወጣው አዲስ ዐዋጅ በተለካ መሬት የሚሰበሰበውን ግብር በጋሻ ወደ 50 ብር (ለለም)፣ 40 (ለለም ጠፍ) እና 15 (ለጠፍ) ከፍ አደረገው:: ተመኑን ከፍ ያደረገውም በዓይነት ይከፈል የነበረውን የዐሥራት ግብር የተካው በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለው ግብር ነው:: ይህ አዲስ ተመን በሥራ ላይ የዋለው በሸዋ፣ በሐረር፣ በወሎ፣ በወለጋ፣ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በኢሉባቦር፣ በገሙ ጎፋና በከፋ በሚገኙ የተለኩ መሬቶች ላይ ነበር:: በሸዋ የርስት መሬት ላይ ከዚህ ተመን ዝቅ ያለ ግብር ሲጣልበት፣ የጎጃም፣

የትግሬና የበጌምድር መሬት ግን ግብሩ በ1928 ተመን ሆኖለት ዐሥራት በተገመተ እንዲከፍል ተደረገ።

ለነገሩ ይህ የ1937 ዐዋጅ የመሬትን ግብር አሰባሰብ ሥርዓት ለማስያዝ የተወሰደ አንድ ትልቅ እርምጃ ነው ማለት ይቻላል። በተለይም ለዚህ አባባል ማስረጃ የሚሆነው ቀደም ሲል በገበሬው ላይ ተጭነው የነበሩት ልዩ ልዩ ክፍያዎችና የጉልበት ሥራዎች መሻራቸው ነው። ይሁን እንጂ ዐዋጁ ሙሉ በሙሉ በተግባር ሊተረጎም አልቻለም። የተጠቀሱት የጉልበት ሥራዎች በዐዋጅ ይሻሩ እንጂ በገቢር እንደቀጠሉ ቆዩ። እንዲያውም በ1940 የወጣ ዐዋጅ እስከናካቴው ይህ ዐዋጅ ቤተ ክህነትን እንደማይመለከት ደነገገ። የመሬትን ግብር በተመለከተም ለመንግሥት መግባት የሚገባው በርከት ያለ ገቢ የሚሄደው ወደ ርስተ ጉልተኞች፣ ሚሶ ጉልት ወደያዙ ባላባቶችና የሰሞን መሬት ተጠቃሚ ወደ ሆነችው ወደ ቤተ ክህነት ነበር። እንደዚሁም መሬታቸውን ወደርስትነት ለውጠው መደበኛ ገባር ካልሆኑ በስተቀር ከባለማደርያ መሬቶችም ግብር አይሰበሰብም ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ በ1940 እና በ1951 መንግሥት የደነገጋቸው የትምህርትና የጤና ታክሶች የመንግሥትን የገቢ መሠረት ለማስፋት የተደረጉ ነበሩ ብሎ መገመት ይቻላል።

በ1958 የታወጀው ሦስተኛው የመሬት ግብር ዐዋጅ በመንግሥትና በገበሬ መካከል ለዘመናት ሰፍሮ የቆየውን ጉልተኛ ለማስወገድ የታቀደ እርምጃ ነው። በዚህ ዐዋጅ መሰረት በርስተ ጉልትና በሚሶ ጉልት ውስጥ የሚገኙ ባለመሬቶች ግብሩን እንደደቀድሞው ለጉልተኛው ሳይሆን በቀጥታ ለመንግሥት እንዲያገቡ ተደነገገ። ይህ እርምጃ ተፈጻሚነት ቢያገኝ ኖሮ፣ ርስተ ጉልትንና ሚሶ ጉልትን የመሻር ያህል ነበር። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቶቹ ባለመብቶች፣ በተለይም ርስተ ጉልተኞች፣ ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር ባላቸው የተሳሰረ ግንኙነት ተጠቅመው የዐዋጁን ተግባራዊነት ለማሰናከል ችለዋል። የቤተ ክህነትን የጉልት መብት የመንካቱ ጉዳይ እንደሆን ከቶም አልታሰበም።

ከዚህ በላይ እንደታየው፣ ከመሬት የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ አያሌ ጥረቶች ቢደረጉም መንግሥት ሊያገኝ የሚችለውን ወይም የሚገባውን ለማግኘት አልቻለም። በ1950ዎቹ መጨረሻ ላይ ያገሪቱ ኤኮኖሚ መሠረት ከሆነው ከግብርና የሚገኘው ገቢ ከጠቅላላው 7 በመቶ ያህል ብቻ ነበር። በዚህ ሁኔታ ተገፋፍቶ ነው መንግሥት የእርሻ ገቢን ለማሳደግ የመጨረሻው እርምጃ የሆነውን የእርሻ ገቢ ታክስ በ1960 ያወጀው። ላይ ላዩን ሲታይ አዲሱ የታክስ ታሪፍ የእርሻ ግብርን ለመሰብሰብ የተሻለ መሠረት የሚጥል ይመስል ነበር። እስከዚያን ጊዜ ድረስ በተለካና ባልተለካ መሬት መካከል ይደረግ የነበረው ልዩነት ቀርቶ፣ ግብር የመሬቱን ዓይነትና ደረጃ ሳይመለከት በእርሻ ምርቱ መጠን ብቻ እንዲተመን ተደረገ። በተጨማሪም የግብር አዳ በርከት ያለ ገቢ ባላቸው ላይ እንዲያመዝን በመደረጉ፣ ይበልጥ ፍትሓዊ ከመሆኑም በላይ የመንግሥትን ገቢም የሚያጎለብት ነበር። ይሁን እንጂ ዐዋጁን በተግባር የሚፈጽሙት ገማች ኮሚቴዎች ለተለያዩ ተጽዕኖ የተጋለጡ በመሆናቸው፣ ገቢን በመተመኑ ላይ አድልዎ የሌለበት ሥራ የሚሠሩ ሆነው አልተገኙም። በተጨማሪም አዲሱ ታክስ የርስት መሬት ባለባቸው የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው። ይህም የሆነበት ምክንያት አዲሱ ታክስ በስውር ቀላድ ለመጣል የተወጠነ ዘዴ ነው ብለው ስላመኑ ነበር። ለምሳሌ በ1960 በጎጃም



የተነሣውን የገበሬዎች አመፅ የለኮሰው መንግሥት አዲሱን ታክስ በተግባር ለማዋል ያደረገው ጥረት ነው።

መንግሥት ለእርሻ ልማት የቀየሰውን እስትራቴጂ ስንመለከትም ውጤቱን አመርቂ ሆኖ አናገኘውም። በ1959 የበጀት ዓመት ውስጥ መንግሥት ለእርሻ የመደበው ወጪ 2 በመቶ ብቻ ነው። ስለሆነም በእርሻ መስክ የተመዘገበው የዕድገት መጠን እጅግ አነስተኛ ሆነ። በመጨረሻ በሦስተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ (1961–1973) መንግሥት ትኩረቱን ወደ እርሻ ሲያዞርም፣ ቅድሚያ የተሰጠው አብዛኛው ሕዝብ ለሚተዳደርበት ለግብርና መስክ ሳይሆን በውጭ ንግድ ላይ ሳተኮረው የንግድ እርሻ ነበር። ይህም ባንድ በኩል መንግሥት የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ያለውን ጉጉት ሲያመለክት፣ በሌላ በኩል መደበዊ ጥቅሙን ለማስከበር የተወሰደ እርምጃ ነበር ለማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም በንግድ እርሻ መስፋፋት የመጀመሪያዎቹ ተጠቃሚዎች ባለትልቅ መሬቶች በመሆናቸው ነው። ስለዚህም የመንግሥቱ የመጨረሻ ዐሥር ዓመታት በውጭ ንግድ ላይ ያተኮረ ከፍተኛ የትራክተር እርሻ የታየበት ወቅት ነው። የእርሻ ከበርቴ መደብም አቆጠቆጠ ተብሎ የተነገረበት ጊዜ ነው።

በዚህ አዲስ የእርሻ እንቅስቃሴ በመሪነት የሚሳተፉት ሦስት ወገኖች ነበሩ፤ ኢትዮጵያውያን ባለግል ሀብቶች፣ በኮንሴሲዮን መሬት ያገኙ የውጭ አገር ኩባንያዎችና መንግሥት። የመጀመሪያዎቹ ቀድሞ ከሩቁ ተረፈ ምርቱን በመሰብሰብ ብቻ ይረኩ የነበሩ አሁን ግን ባጭር ታጥቀው በትራክተር ማረሱን የተያያዙት ባለመሬቶች ባንድ ወገን ሲሆኑ፤ በሌላ ወገን ደግሞ መሬት ተከራይተው የሚያርሱ የእርሻ ባለሙያዎች ናቸው። እነዚህ የግል አራሾች በብዛት የተሰማሩትም በደቡብ ሸዋና በስቲት ሁመራ ነበር። በውጭ አገር ካፒታለስቶች ከተደራጁት ሰፋፊ እርሻዎች መካከል በተለይ ሊጠቀሱ የሚገባቸው በኤርትራ የጣልያን ከበርቴዎች ያቋቋሙት የኤላበረድ እርሻና በአዋሽ ሸለቆ ደግሞ በእንግሊዛዊው ሚቸል ኮትስ ኩባንያ የተቋቋመው የተንዳሆ የጥጥ እርሻ ልማት ናቸው። እንደዚሁም በመንግሥት በኩል ደግሞ በ1954 በተቋቋመው በአዋሽ ሸለቆ ባለሥልጣን አማካይነት ሰፋ ያለ የእርሻ፣ የአግሮ ኢንዱስትሪና የሀይድሮ ኤሌክትሪክ እንቅስቃሴ ይካሄድ ነበር።

መንግሥት ትኩረቱን ወደ ተራው ገበሬ ያዞረው እጅግ ዘግይቶ ሲሆን፣ ውጤቱም እምብዛም የሚያረካ አልነበረም። በመሀል አገር ሁለ ገብ የእርሻ ልማት በተሰኘ ፕሮግራም አማካይነት ለድሀ ገበሬዎች ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ በማደል ግብርናን ለማሳደግ ተሞከረ። ይህንንም ተግባር ለማስተባበር ኃላፊነቱ የተሰጠው የእርሻ ዘዴና ጥቅም ማስፋፊያ ተብሎ ለሚታወቀው የመንግሥት አካል ነበር። በተመሳሳይ መንገድ የስዊድን ዓለም አቀፍ ልማት ድርጅትም (ሲዳ) የገበሬውን የልማት እንቅስቃሴ የሚያግዙ ፕሮግራሞች ቀይሶ ነበር። ከነዚህም ከፍተኛ ዝናን ያገኘው የጭላሎ እርሻ ልማት ድርጅት «ካዱ» ነው። «ካዱ» ሲቋቋም ዓይነተኛ ዓላማው ደሀውን ገበሬ ለመጥቀም ታስቦ ቢሆንም፣ ይበልጥ ተጠቃሚ የሆኑት ሀብታም ባለመሬቶች ናቸው። ምንም እንኳን የድርጅቱ የእርዳታ ደንብ እነሱን የሚያግድ ቢሆንም፤ እገዳውን ጥሰው ዋነኛ ተጠቃሚ ለመሆን ተዘዋዋሪ ዘዴ አላጡም። በተጨማሪም ፕሮግራሙ የትራክተር እርሻ በማበረታታቱ ለአያሌ ጭሰኞች መፈናቀል ምክንያት ሆነ። ምክንያቱም

ባለመሬቶች በጭሰኛ ከማሳረስ ይልቅ መሬታቸውን በንግድ እርሻ ለተሰማሩት ባለሙያዎች ማከራየቱን የበለጠ አትራፊ ሆኖ ስላገኙት ነው:: በዓለም ባንክ እርዳታ የተቋቋመው የወላይታ እርሻ ድርጅት «ዋዱ» በሰፈራ ኘሮግራሙ አማካይነት የመሬት መጣበብን ለማቃለል በመቻሉ ደሀውን ገበሬ በማገዝ ረገድ የተሻለ ወጤት ሊያሳይ በቅቶ ነበር ማለት ይቻላል::

ከዚህ በላይ በዝርዝር ያየነው ሂደትና ፖሊሲ ድምር ውጤት የገጠሩን ማኅበረሰብ፣ በተለይም የደቡቡን ክፍል፣ በሁለት ተፃራሪ ጎራ፣ ማለትም በባለመሬትና በጭሰኛ መከፋፈል ነው:: የጭሰኛውም ችግር እያፈጠጠ ከመምጣቱ የተነሣ መንግሥት መፍትሔ ለመሻት ተገደደ:: አብዛኛውን በውጭ እርዳታ ሰጭዎች ግፊት የመሬት ይዞታን ለማሻሻል ማሰላሰል ጀመረ:: በዚህ ሁኔታ በ1954 የተቋቋመው ይህንኑ የሚመለከት ኮሚቴ በ1957 ወደ የመሬት ይዞታ መሻሻልና ልማት ባለሥልጣን አድጎ፣ ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር ለመሆን በቃ:: ይሁን እንጂ የጭሰኛውን ሁኔታ ለማሻሻል የሚወሰዱ እርምጃዎች ሁሉ የመንግሥቱን አውታር የሚቆጣጠረውን የባለመሬቱን መደብ ጥቅም የሚፃረሩ ሆነው በመገኘታቸው ሊገፉባቸው አልተቻለም:: በተለይም በዚህ ረገድ የሚቀርቡ የለውጥ ሐሳቦች ላይ ውሀ በመቸለስ ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወተው የሕዝብን ጥቅም ያስጠብቃል ተብሎ የተቋቋመው ፓርላማ ራሱ ነበር:: በፓርላማው ውስጥ ከፍተኛውን ውክልና ያገኙት ባለመሬቶች መሆናቸው ሲታወቅ የምክር ቤቱ አቋም እምብዛም የሚያስገርም አይደለም:: የጭሰኛውን ሁኔታ ለማሻሻል የሕግ ረቂቅ ለምክር ቤቱ መጀመሪያ የቀረበው እ.ኤ.አ. በ1964 ሲሆን፣ የረቂቁ መጨናገፍም ነው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች «መሬት ላራሹ» ብለው ሰልፍ እንዲወጡ የገፋፋቸው:: ይህ ሰልፍና መፈክርም በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ከፈተ::

ሌላውና ሰፋ ያለ ይዘት ያለው የጭሰኛ ሕግ ለምክር ቤቱ የቀረበው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ዕድሜ ማክተሚያ ላይ ነው:: ረቂቁ ይህን ያህል ሥር ነቀል የሚባል አልነበረም:: ለምሳሌ በጭሰኛና በባለመሬት መካከል የሚደረገው ውል በጽሑፍ መስፈር አለበት ብሎ እንኳ አልደነገገም:: ጭሰኛው የሚከፍለውን ኪራይ በተመለከተም ከምርቱ እስከ ኀምሣ በመቶ ሊደርስ እንደሚችልም ይጠቁም ነበር:: ለጭሰኛውም ምንም ዓይነት ዋስትና አያረጋግጥለትም ነበር:: ባለመሬቱ በፈለገው ጊዜ ውሉን ለማፍረስ ከመቻሉም በላይ፣ መሬቱን በትራክተር ማረስ ወይ ማሳረስ ቢፈልግ ጭሰኛውን ማባረር እንደሚችል ይደነግግለት ነበር:: ምናልባት የረቂቁ አንድ ተራማጅ ገጽታ ቢኖር ጥቅም ላይ ያልዋለ መሬት ከግብር ነፃ እንደማይሆን መወሰኑ ይሆን ይሆናል:: ያም ሆነ ይህ ረቂቁ ብዙ ደጋፊዎች አልነበሩትም:: ጥቂቶቹ ለጭሰኛው ምንም እርባና አያመጣም ብለው ሲቃወሙት፣ አብዛኞቹ ያን ያህልም በመሄዱ ነቀፉት:: ለመከረኛው ጭሰኛ ከዚህ ሁሉ ግርግር የተረፈው ሳንቀደም እንቅደም ብለው በተነሡ ባለመሬቶች በገፍ መባረር ነው::

እንግዲህ የገበሬውን ሁኔታ ስናጠቃልል የነበረው ሥዕል ባንድ ወገን በመንግሥትና በወኪሎቹ ሲገፋ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ድርቅና የአንበጣ መንጋ ለመሳሰሉ የተፈጥሮ መቅሠፍቶች ተጋልጠ በቀላሉ ለረሀብ የተዳረገ ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህንንም በተለይ በሰሜኑ ክፍል በተደጋጋሚ በተከሠቱት ረኀቦች ማጤን እንችላለን:: ለምሳሌ በ1950 በትግሬ የደረሰው ረኀብ ለመቶ ሺ ያህል



ገበሬዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሲሆን፤ በ1958 ደግሞ ተራው የወሎ ነበር:: በመንግሥት በኩል ለነዚህ ሁኔታዎች የሚሰጠው መልስ ከፍ ሲል ቸልተኝነት፣ ዝቅ ሲል ደግሞ አገር አማን ነው ለማሰኘት መሸፋፈን ነበር:: ይህ በተለይም ገሃድ የወጣው በወቅቱ ከፍተኛ እልቂት ባስከተለው በ1965ቱ የወሎ ረሃብ ወቅት ነበር:: መንግሥት ሸፋፍኖት የቆየው ረሃብ በዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎች እና በውጭ አገር ጋዜጠኞች አማካይነት ሲጋለጥ፣ የመንግሥት ክስረትና ግዴለሽነት ቁልጭ ብሎ በመውጣቱ ለውድቀቱ አንድ ምክንያት ሲሆን በቃ::

## ንግድና ኢንዱስትሪ

በብሔራዊ ኤኮኖሚ ውስጥ ንግድና ኢንዱስትሪ የነበራቸው ድርሻ እጅግ አነስተኛ ነበር:: በ1950ዎቹ ዓመታት ንግድ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ውጤት ውስጥ 7 ከመቶውን የያዘ ሲሆን፣ የኢንዱስትሪ ድርሻ ደግሞ ከዚያም ያነስ ነበር:: ይህም የሚያሳየው የዕቃዎች ልውውጥ ምን ያህል በዝቅተኛ ደረጃ ይገኝ እንደነበረና ያገሪቱ የኢንዱስትሪ ደረጃም በእንጭጩ መሆኑን ነው:: የንግዱም ዓይነት ያገሪቱን በእርሻ ላይ የተመሠረተ ህልውና የሚያንጸባርቅ ነበር:: አብዛኛዎቹ ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦች የእርሻ ውጤቶች ነበሩ:: ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ከጠቅላላው የውጭ ንግድ ከ50 እስከ 60 በመቶ የሚሆነውን የሚይዘው ቡና ሲሆን ከዚያ ቀጥሎ ቆዳና ሌጦ፣ ከዚያ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ነበሩ::

ቡና በውጭ ንግድ ንጉሥነቱ ያለተቀናቃኝ ሲቀጥል የገቢ ንግድን በተመለከተ ግን ጉልህ የሆነ ለውጥ መካሄድ ጀመረ:: ቀድሞ በዚህ ንግድ የመሪነት ሥፍራ የያዙት ጨርቃ ጨርቆች በማምረቻ መሣሪያዎችና ኬሚካሎች ተተኩ:: ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት የመንግሥትን የኢንዱስትሪ ፖሊሲ መሠረት በማድረግ እያሌ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ በመቋቋማቸው ነው:: የንግድ ግንኙነቱም ያገሪቱን የዓለም አቀፍ ግንኙነት አቅጣጫ የተከተለ በመሆኑ 40 በመቶው ከአሜሪካ ጋር ሲሆን፣ በተለይ የቡናን ንግድ በተመለከተ 70 በመቶው በአሜሪካ ገበያ የሚጣራ ነበር:: በገቢ ንግድ ረገድ ግን አንደኛነትን ደረጃ የያዘችው ኢጣልያ ስትሆን ሁለተኛ ጃፓን፣ ሦስተኛ ደግሞ አሜሪካ ነበረች:: የንግድ ሚዛኑ ባብዛኛው በኢትዮጵያ ኪሳራ ነበር:: ይህንንም ሁኔታ ካባባሱት ምክንያቶች አንዱ የወጪ ሸቀጦች ዋጋ እያቆለቆለ የገቢ ሸቀጦች ዋጋ ደግሞ እየናረ መምጣቱ ነው::

የአገር ውስጥ ንግድን በተመለከተ በ19ኛው መቶ ዓመት የጀመረው የአዲስ አበባ ማዕከላዊነት ይበልጡኑ እየተጠናከረ መጣ:: ሸቀጥ ሲሻሟት የነበሩት የጠረፍ መናኸሪያዎች እየቀዘቀዙ መጥተው የቅኝ አገዛዝ ፍጻሜውን ሲያገኝ ደግሞ ከዚያው ጋር አብረው ከሰሙ:: የከተማይቱን የንግድ አሰፋፈር ስንመለከትም ጣልያኖች አንድ ቋሚ ቅርስ ትተው አልፈዋል:: ከጣልያን በፊት መናኸርያ የነበረው አራዳ በጣልያኖች ፒያሳ ተብሎ ክርስትና ሲነሣ የንግዱ ዐውድማ አዲስ ወደ ቆረቆሩት መርካቶ ዞረ:: ከዚሁ ተያይዞም በተለይ በችርቻሮ ንግድ የውጭ ዜጎች የነበራቸው የበላይነት እየተሸረሸረ መጥቶ በኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ይተኩ ጀመር:: በዚህ ረገድ የብሔራዊ ታታሪነት አርአያ ሆኖ

ሊነገርለት የሚችለው በተለይ በመርካቶ ጉራጌዎች በየመን ዐረቦች ቁጥጥር ሥር የነበረውን የችርቻሮ ንግድ ለመቆጣጠር መብቃታቸው ነው።

ይህ ማለት ግን ብሔራዊ የንግድ ከበርቴ ህልውና አግኝቶ ነበር ማለት አይደለም። በተለይ በአስመጪና ላኪ ንግድ የኢትዮጵያውያን ሚና አሁንም ዝቅተኛ ነበር። መጀመሪያ ላይ ከጣልያኖች ተምረው ይመስላል የኢትዮጵያ ገዢ መደብ አባላት መንግሥትን ተገን ያደረጉ ድርጅቶች በማቋቋም የውጭውን ንግድ በቁጥጥራቸው ሥር አዋሉት። የዚህንም ፈር የቀደደው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ኮርፖሬሽን ተብሎ የታወቀው ድርጅት ነው። ይህ ነፃነት እንደተመለሰ በንግድና እርሻ ሚኒስትሩ በአቶ መኰንን ሀብተወልድ የተቋቋመው ድርጅት በተለይ በጦርነት ኢኮኖሚዋ ለደቀቀው አውሮጳ እህል በማቅረብ ብዙ ትርፍ ለማግኘት ችሏል። ለዚህም አመቺ ሁኔታ የፈጠረው ኢትዮጵያ ነፃ ከወጣች በኋላ አውሮጳ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ለአራት ዓመታት ያህል ስትታመስ መቆየቷ ነው። እ.ኤ.አ. በ1944 የኮርፖሬሽኑ ትርፍ £1200000 ይደርሳል ተብሎ ይገመት ነበር። ባንፃሩም የንግድና ትራንስፖርት ማኅበር ተብሎ የተሰየመው ድርጅት (በተለምዶ አጠራር «ማኅበር ቤት» ተብሎ የሚታወቀው) ጨርቃ ጨርቅ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ሞኖፖል ነበረው። እንግዲህ ይህንኑ ፈለግ ተከትለው ይመስላል ወደ ኋላም አሉ የሚባሉትን የውጪ ንግድ ሸቀጦች የሚቆጣጠሩት የቡና ቦርድ፣ የሥጋ ቦርድና የእህል ኮርፖሬሽን የተቋቋሙት።

ንግድ ለመንግሥት ያለው ዋና ጠቀሜታ ከጉምሩክ ገቢው ላይ ነው። የገቢ ምንጩን ለማስፋት የሚፈልግ መንግሥትም ለጉምሩክ ልዩ ትኩረት መስጠቱ የማይቀር ነው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መንግሥት ከጠላት በፊት የአክሳይዝ ቀረጥ ዐዋጅ ሲያወጣ እንዳስመሰከረው ሁሉ፣ ያዋጣኛል ያለውን የወጪና የገቢ ንግድ ቀረጥ መደንገጉን ቀጠለ። እንዲያውም በዳበሳ የተጀመረው የጉምሩክ ሥርዓት በስፋትና በጥልቀት የተያዘው ከነፃነት በኋላ ነው ማለት ይቻላል። በዚህ ረገድ መሠረቱ የተጣለው በ1935 በወጣው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦችን ሁሉ ታሪፍ በደነገገው ዐዋጅ ነው። ዐዋጁ ያተኮረው በሚወጡ ሳይሆን በሚገቡ ሸቀጦች ነበር። በወጪ ንግድ በኩል ታሪፋቸው የተደነገገው አራት ሸቀጦች ብቻ ነበሩ፤ ቆዳና ሌጦ፣ ዝባድ፣ ሰምና ቡና። ስለሆነም በጉልህ እንደታየው ከገቢ ንግድ የሚገኘው ቀረጥ ከጠቅላላ የመንግሥት ገቢ ሩቡን ሲሸፍን ከወጪ ንግድ የሚገኘው ግን ከዚህ በጣም ያነሰ ነበር። የጉምሩክ ገቢ ለመንግሥት ካዝና የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ለመገንዘብ የሚከተሉትን አኀዞች መጥቀሱ ይበቃል። እ.ኤ.አ. በ194 ጠቅላላ የመንግሥት ገቢ ከሆነው £2843600 ውስጥ £650000 ከጉምሩክ የተገኘ ሲሆን £590000 ደግሞ ከመሬት ግብር የተገኘ ነበር።

የኢንዱስትሪው መስክ በደፈናው ሲታይ አመርቂ ባይመስልም፣ ከ1928 በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ጉልህ የሆነ እድገት ይታይበት ነበር። ይህም ባንድ በኩል ጣልያኖች ትተው በሄዱት መሠረት ላይ የተገነባ ሲሆን፣ በሌላ ወገን ደግሞ ከነፃነት በኋላ የተደረጉ ጥረቶች ውጤት ነበር። ቀደም ብለን እንዳየነው፣ ጣልያኖች የጨርቃ ጨርቅና የሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣ የዘይት መጭመቂያዎች፣ የእንጨት መሰንጠቂያዎችና የእህል ወፍጮዎች አቋቁመው ነበር። ከዚህም በላይ በዋና መዲናይቱ በአዲስ አበባ የቃጫ ፋብሪካና ከከተማይቱ በስተደቡብ አባ ሳሙኤል ተብሎ ከሚታወቀው ግድብ የተጠለፈ የመብራት ኃይልም ነበር። (በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚችል አንድ ነገር ኋላ ለረጅም ጊዜ



የአገሪቱ የመብራት ኃይል ምንጭ የሆነው የቆቃ ግድብም በጣልያን የጦር ካሣ ገንዘብ የተሠራ መሆኑ ነው።)

የመንግሥት የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ያተኮረው ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን አገር ውስጥ በማምረት ለመተካት ነበር። በዚህም ረገድ በተለይ ከፍተኛ ትኩረት የተደረገበት ዋናው የገቢ ንግድ ሸቀጥ በነበረው በጨርቃ ጨርቅ ላይ ነው። ይህንኑ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ከተቋቋሙት የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች መካከል ጎላ ብለው የሚታዩት አቃቂ የሚገኘው የኢንዶ ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካና የባሕር ዳሩ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ናቸው። ሌላው ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን ለመተካት የታሰበበት መስክ ደግሞ መጠጥ ነበር። ከጣልያን ወረራ በፊት የተመሠረተውና ለንጉሡ ነገሥቱም አንድ የገቢ ምንጭ የነበረው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ የረጅም ዘመን ሞኖፖሉን ከሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካ ጋር መጋራት ጀመረ። እንደዚሁም ዓለም አቀፍ ዝናን ያተረፉት ኮካ ኮላና ፔፕሲ ኮላ በምድረ ኢትዮጵያ ብቅ ማለት ጀመሩ።

ይሁን እንጂ በድኅረ 1933 የኢንዱስትሪ መስፋፋት ታሪክ ውስጥ ቁንጮውን ሥፍራ የያዘው በሆላንዱ ኩባንያ በኤች.ቪ.ኤ. ይካሄድ የነበረው የስኳር ኢንዱስትሪ ነው። ቀድሞ ከተንሰራፋበት ከኢንዶኔዥያ አገሪቱ ነፃነቷን ስትቀዳጅ የተባረረው ኤች.ቪ.ኤ. በኢትዮጵያ መሬት አመቺ የኢንቬስትመንት መስክ አገኘ። በ1946 ሁለት የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎች በአዋሽ ሸለቆ አቋቋመ፤ አንደኛው በወንጂ፣ ሁለተኛው በመተሀራ። እንደ ሌሎች አያሌ የድኅረ ነፃነት የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የወንጂ ስኳር ፋብሪካም ኢጣሊያዊ መሠረት ነበረው። ፋብሪካው የተቋቋመው በጣልያን ጊዜ የሸንኮራ አገዳ ተክል ማሳ በነበረበት ስፍራ ነው። በ1953 የሆላንዱ ኩባንያ የኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ እንዲያጎለብት ተብሎ እንደገና ሲዋቀር ስሙም ወደ ኤች.ቪ.ኤ. ኢትዮጵያ ተለወጠ። ይሁንና በኢትዮጵያውያን እጅ የነበረው የአክሲዮን መጠን ከቶም ከ20 በመቶ በልጦ አያውቅም ነበር። ኩባንያው ባንድ ወገን የመንግሥት ኢንቬስትመንት ፖሊሲ ብዙም የሚጋፋው ባለመሆኑ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ለረጅም ጊዜ ሠራተኛውንም ረግጦ ለመያዝ በመቻሉ ደለብ ያለ ትርፍ ለማግኘት ችሎ ነበር። ለምሳሌ የ1959 ትርፉ ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ነበር። ባንፃሩ ደግሞ የስኳር ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ መንግሥት ከውጭ ከማስገባት ይልቅ ባገር ውስጥ ማምረትን የማበረታታቱ ፖሊሲ ምን ያህል ለሸማቹ እርባና እንዳለው አጠያያቂ ሆነ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ለኤች.ቪ.ኤ አመርቂ ውጤት ትልቅ አስተዋፅኦ ካደረጉት ነገሮች አንዱ መንግሥት ይከተለው የነበረው ኢንቬስትመንትን የሚያበረታታ ፖሊሲ ነው። በ1941 የተደነገገው የገቢ ቀረጥ ዐዋጅ ከ200 ሺ በላይ ካፒታል ያለውና በማዕድን፣ በኢንዱስትሪና በትራንስፖርት መስክ የተሰማራ ማንኛውም ኢንቬስተር ለመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት የሚያገኘው ትርፍ ከቀረጥ ነፃ ነበር። በንግድ ኩባንያዎች የተጣራ ትርፍ ላይ የሚሰበሰበው ቀረጥም ከ15 በመቶ እንዳይበልጥ ተደንግጎ ነበር። በሦስተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ መሠረትም ትራክተሮችና ኬሚካሎች ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ተችሏል። ሌሎች የውጭ ካፒታል የሚጋብዙ ሁኔታዎች ደግሞ የሰፋ የሐዋላ ዕድል መስጠት፣ ከውጭ በሚገቡ ተፎካካሪ ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ

መጫንና (በስኳር ኢንዱስትሪው እንዳየነው) አገር ውስጥ የሚመረቱ ሸቀጦች በከፍተኛ ዋጋ እንዲሸጡ መተባበር ነበሩ።

ከ1928 በፊት ብዙ የውጭ ካፒታሊስቶችን በጉጉት የሳበው የማዕድን ኢንዱስትሪ ፍሬያማ ውጤት ማሳየት የጀመረው ከነፃነት በኋላ ነው። በምእተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በኢትዮጵያ ምድር ወርቅ አፍሳለሁ ብሎ ያልዳከረ ፈረንጅ አልነበረም። እያሌ የሞኖፖል ውሎች (ኮንሴሲዮኖች) ተፈርመውም ነበር። በአውሮጳ መዲናዎችም እያሌ የአክሲዮን ኩባንያዎች ተቋቁመው ፣ የአፍሪቃን ወርቅ የሚታፈስበት ምድር (ኤልዶራዶ) ለመቀራመት አስልተው ነበር። ይሁንና በወለጋ በዩብዶ ኢጣልያዊው አልቤርቶ ኘራሶ ካቋቋመው የኘላቲንየም ፋብሪካ በስተቀር፣ ያ ሁሉ ልፋትና ጥረት ፍሬ አልባ ሆኖ ነው የቀረው። ከ1933 በኋላ ግን በወለጋ ሳይሆን በሲዳሞ በአዶላ የተጀመረው የወርቅ ማዕድን የመንግሥትን ካዝና ለመሙላት በቃ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ1944 ከመንግሥት ገቢ ውስጥ አንድ አምስተኛው የተገኘው ከዚሁ ከአዶላ ወርቅ ነው። ስለዚህም ይመስላል የአዶላም ስም ወደ ክብረ መንግሥት የተቀየረው። በሕዝቡ ሕሊና ግን አዶላ የሰቆቃ ምሳሌ ሆኖ ቀረ፤ አንድም ከየከተማው እየታፈሱ በግድ በማዕድኑ እንዲሠሩ በሚደረጉት ቦዘኔዎች ምክንያት፣ አንድም በማዕድኑ በሠፈነው የግዞት ካምፕ ባሕርይ።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ባብዛኛው የተማከለው በሦስት ከተሞች ነበር፤ አዲስ አበባ፣ አሥመራና ድሬዳዋ። ባገሪቱ ካሉት ፋብሪካዎች ውስጥ ግማሹ የሚገኙት በአዲስ አበባ ነበር። ይህም ያገሪቱ ያልተመጣጠነ እድገት ነጸብራቅ ነበር። የኢንዱስትሪው በጥቂት ቦታዎች መከማቸት የሠራተኛውንም መሰባሰብ አስከተለ። ይህም በኢንዱስትሪም ሆነ በፖለቲካው መስክ በሚደረገው ትግል ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ነበረው። በአብዮቱ መዳረሻ ላይ የሠራተኛው ቁጥር በ50000 የሚገመት ቢሆንም፣ ይህ ከላይ የተጠቀሰው በጥቂት ስፍራዎች መሰባሰብ ለሠራተኛው መደብ ከቁጥሩ የላቀ ኃይል ሰጥቶት ነበር። ስለሆነም ሠራተኛው ሳይውል ሳያድር ለተሻለ ክፍያና የሥራ ሁኔታ መታገሉን ጀመረ። ለምሳሌ የወንጂ ሠራተኞች የመጀመሪያውን የሥራ ማቆም አድማ ያደረጉት ፋብሪካው በተቋቋመበት ዓመት ነው። የሠራተኛ ማኅበራትም የእድርና የዕቁብ መልክ ይዘው ማቆጥቆጥ ጀመሩ። ግፊታቸው እየየለ በመሄዱም መንግሥት በ1954 የመጀመሪያውን የሠራተኛ ማኅበር ዐዋጅ ለመደንገግ ተገደደ። በዓመቱም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ተቋቋመ። እንዲህ እያለም ለረጅም ጊዜ በመጀመሪያዎቹ ላብ አደሮች በሆኑት በምድር ባቡር ሠራተኞች ትከሻ ላይ ብቻ ወድቆ የነበረው የሠራተኛው ትግል ወደ ቃጫ ፋብሪካ፣ ኢንዶ ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ፣ ወንጂ ስኳር፣ አየር መንገድ፣ አንበሳ አውቶቡስና ሌሎች ድርጅቶች ተዛመተ።

የድኅረ 1933 ኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ሁኔታ ስናጠቃልል የምንደርስበት መደምደሚያ ኤኮኖሚው ባለበት ቆሟል ባንልም ፈጣን እድገት አሳይቷል ለማለት አንደፍርም። በተለይም ከቀረው ዓለም ጋር ሲነፃፀር ኋላ ቀርነት ያገሪቱ ዓይነተኛ ባሕርይ ነበር ማለት እንችላለን። የሕዝቡ የአማካይ የዓመት ገቢ 150 ብር (72 ዶላር ከአምሳ ሳንቲም) ሲሆን ይህም በዓለም እጅግ ዝቅተኛ ከሚባሉት ነው። ከሕዝቡ ከ90 በመቶ በላይ ማይም ነበር። በሕክምናም ረገድ ሐኪሞች ከማነሳቸው የተነሣ ባማካይ አንድ ሐኪም 70 ሺህ ያህል ሕሙማን ማስተናገድ ነበረበት። አንዳንድ የኢንዱስትሪ ተቋሞች ብቅ ብቅ ማለት ቢጀምሩም



ኤኮኖሚው በመሠረቱ እርሻ ነክና ገጠሬ ነበር። ይህም ሆኖ በእርሻ ከሚተዳደረው ሕዝብ 90 በመቶው ሸቀጥ አምራች ሳይሆን ከእጅ ወደ አፍ የሚኖር ነበር። እናሳ የሆነው የኢንዱስትሪውም መስክ ባብዛኛው በውጭ አገር ካፒታሊስቶች እጅ ነበር። ይህን ጥገኝነት ያባባሰው መንግሥት ወጪውን ለመሸፈን ሲል ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ ያለ የውጭ ብድር እንዲሻ መገደዱ ነው። ይህም የውጭ እዳ እ.ኤ.አ. በ1966 30,310,000 ብር ሲሆን ከሦስት ዓመት በኋላ በ1969 ደግሞ ወደ 445189000 ብር ከፍ ሲል በቅቷል፡ ከዚህም ዕዳ ውስጥ 75 በመቶው ከአሜሪካ መሆኑ ኢትዮጵያ በአሜሪካ ላይ ያላት ጥገኝነት ሁለንተናዊ ባሕርይ እየያዘ መምጣቱን ይጠቁማል።


## የፍጹማዊ አገዛዝ መጠናከር

ከ1933 በኋላ ያሉት ዓመታት በኢትዮጵያ ፍጹማዊ አገዛዝ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ወቅት ነው። ከ1928 በፊት ዳር ዳር ማለት የጀመረው የፍጹም አጼያዊ አገዛዝ አሁን ሥር እየሰደደ መጣ። መንግሥት ዜጎቹን ለመቆጣጠር የነበረው ችሎታ ከዚያ በፊት ባገሪቱ ታውቆ በማያውቅ ደረጃ አደገ። ይህ ሁኔታ በክፍለ ሀገር አስተዳደር፣ በወታደራዊ አወቃቀርና በማዕከላዊ የገንዘብ ቁጥጥር ይንጸባረቅ ነበር። የዚህ ሥልጣን ተጠቃሚ የሆነው የገዢ መደብ የሀብቱ መሠረት መሬት ቢሆንም ዐይኑን ወደ ንግድና ኢንዱስትሪም ማማተር ጀምሯል። የዚህ የገዢ መደብ ቁንጮና የፍጹማዊው ሥርዓት መሀንዲስ አፄ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ።

### ንጉሠ ነገሥቱ

ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ የኢትዮጵያ ሕይወት የተሽከረከረው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ነው። ኃይለ ሥላሴ የመንግሥቱ ብቻ ሳይሆን ያገሪቱም አምሳያ ለመሆን በቃ። ስለሆነም በአዳም ልጆች መለኪያ የማይለካ መለኮታዊ ባሕርይ ያለው ሆኖ ታየ። እንደ አገሪቱ ተራሮችና ጅረቶች ሁሉ ዘለዓለማዊና ጊዜ የማይሽረው መሰለ። በዚህ ሁኔታ ንጉሠ ነገሥቱ እኔ ከሄድኩ በኋላ የሥልጣን ሽግግሩን የሠመረ ላድርግ ብሎ እምብዛም አልተጨነቀም። በንጉሠ ነገሥቱ ግርማና ሞገስ የፈዘዙት ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ የውጭ አገር ዜጎችም ጭምር ነበሩ። እንዲያውም በነሱ ይብስ ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የአገዛዙ ክፉ ጎን ሳያገኛቸው እነሱ ከብዙ ምእተ ዓመት በፊት ያሳለፉትን የፖለቲካ ሥርዓት እንደ ኤግዚቢሺን ለማየት በመታደላቸው ነው።

አፄ ኃይለ ሥላሴ የተወደሰውን ያህል ብዙ ኩነናም ደርሶበታል። በተለይ በዘመነ መንግሥቱ መጨረሻ ዓመታት ላይ ወጣቱ ትውልድ ባገሪቱ ታሪክ ውስጥ ዜጋ ለንጉሡ ምንጊዜም አሳይቶ የማያውቀውን ንቀት አሳይቶታል፤ ውግዘትም አውርዶበታል። ደርግም ይህን ጥላቻ ወርሶ ከግማሽ ምእት ዓመት በላይ ኢትዮጵያን የገዛና ከማናቸውም መሪ ይልቅ የዘመናዊቱ ኢትዮጵያ ፈጣሪ



5.3 ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ


የሆነውን ኃይለ ሥላሴን ከታሪክ ገጽ ለመፋቅ ሞክሯል:: አሁን ደግሞ እንደ ሰዓት ፔንዱለም የሰው አስተያየት ወደሌላው ጫፍ ሄዶ የቀድሞውን ንጉሠ ነገሥት ለብዕና የማጨት አዝማሚያ ይታያል::



ሐቁ ግን፣ እንደ ብዙ የሕይወት አጋጣሚዎች፣ መሀል ቤት ነው:: ማለትም ኃይለ ሥላሴ ጋኔንም ቅዱስም አይደለም:: በተወሰነ የታሪክ ወቅት ትክክል ነው ብሎ ባመነበት አቅጣጫ አገሩን ለመምራት የሞከረ ሰው ነው:: እስከተወሰነ ደረጃ ድረስም ዘመነ መንግሥቱ ተራማጅ ባሕሪያት እንደነበሩት የታሪክ ምርምሮች ያረጋገጡት ነገር ነው:: በተለይም በአልጋ ወራሽነቱ ዘመን (1909-1923)፣ ከጣልያን ወረራ በፊት በነበረው አጭር የንግሥ ዘመኑና (1923-1928) ከነፃነት በኋላም በመጀመሪያዎቹ ዐሥርና ዐሥራ አምስት ዓመታት ዘመነ መንግሥቱ በጎ አዝማሚያና ማኅበረሰባዊ እርባና ነበረው:: ማዕከላዊ አስተዳደር የተመሠረተው፣ የትምህርት እድል የተከፈተው፣ የመገናኛ አውታሮች የተዘረጉት በነዚሁ ዓመታት ነው:: ለዚህም ነው ከዘር ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ የፖለቲካ ሥልጣን አገሪቱን ከፋፍለው ሲገዙ የነበሩትን መሳፍንት ለማንበርከክ ያደረገውን ትግል እንደ ፀረ ፊውዳል ትግል አድርጎ የቆጠረው:: የፊውዳል ሥርዓት ቁንጮ ተብሎ እንዳልተወገዘ ሁሉ እሱ ራሱን ፀረ ፊውዳል አድርጎ ማየቱ ፊውዳሊዝምን በኢኮኖሚ ሳይሆን በፖለቲካ ይዘቱ ብቻ ስለተመለከተው ነው:: ይህን መሳፍንቱን የማንበርከኩንና ማዕከላዊ መንግሥቱን የማጠናከሩን ተልእኮ ከፈጸመ በኋላ ግን የኃይለ ሥላሴ እርባና ያከተመ ይመስላል:: ከዚያ በኋላ ሥልጣን የእድገት መሣሪያ መሆኑ ይቀርና የሕይወት መነሻም መድረሻም (አልፋና ኦሜጋ) ሆነ::

በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው እንዲህ ዓይነት አዝማሚያ ደግሞ ፍጻሜው ራስን መውደድንና ከኔ በላይ ለአሳር የሚለውን አመለካከት መውለድ ነው:: አላፊ ነኝ ብሎ ማሰብ ይቀርና ራስን ከማታልፈው አገር ጋር አቆራኝቶ ማየት ይመጣል:: የአፄ ኃይለ ሥላሴም አመለካከት እኔ ኢትዮጵያ ነኝ፣ ኢትዮጵያም እኔ ነች ወደሚለው አቅጣጫ አዘነበለ:: ረጅም ዘመን በንጉሠ ነገሥትነት በመግዛቱ ዘላቂ ሕያውነትን የተጐናፀፈ መስሎ ታየው:: ስለሆነም ከኔ በኋላ አገሪቱ በቀና መንገድ እንድትሄድ ሥልጣን የሚሸጋገርበትን መንገድ ላስናዳ ብሎ ለማሰብ አልቃጣውም:: ይህም ምናልባት ከሁሉም በላይ ኃይለ ሥላሴ በታሪክ የሚጠየቅበት ግድፈት ነው ማለት ይቻላል:: ከ1953 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላም ሆነ የስንበት በዓል ይመስል ከነበረው ከ80ኛው ልደት በዓሉ በኋላም ሥልጣኑን የመልቀቅ ቀርቶ በወጉ የማጋራት ዝንባሌም አላሳየ:: የንጉሠ ነገሥቱ መላ ጥረትና ጉልበት ያረፈው ሥልጣኑን ሳይቸረቸሩና ሳይበረዝ ማቆየትና ይህን ተቀናቃኝ የሆነውን ማናቸውንም ኃይል ማጥፋቱ ላይ ነው:: ስለዚህም ነው ደኅንነት (ፀጥታ) በሥልጣን እወቃቀሩ ቅድሚያ የተሰጠው:: ባገሪቱ ላይ የስለላ መረብ ዘርግቶ ዜጎቹን ከመቼውም ይበልጥ ለመቆጣጠር በቃ:: የዚህ የስለላ መዋቅር ቁንጮ በ1952 የተቋቋመው «ልዩ ካቢኔ» የተባለው ድርጅት ነው:: ይህ ተቋም የተመሠረተው እንደ ንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ የአማካሪ ቡድን ሲሆን፣ ዋና ሥራው ሰላዮቹን እንኳ ሳይቀር በመሰለል ለንጉሠ ነገሥቱ የነጠረ መረጃ ማቅረብ ነበር::

ሌላው የአፄ ኃይለ ሥላሴ ፍጹማዊ ሥልጣን ነፀብራቅ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱን ከሰብአዊው ዓለም አውጥቶ መለኮታዊ ባሕርይ የሰጠው የውዳሴ ባህል ነው:: ይህ ባህል ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ከወረደ በኋላም ኢትዮጵያን እንደተጠናወተ ቀርቷል፣ እንዲያውም ባንዳንድ መልኩ ብሷል ማለት ይቻላል:: መንግሥቱ ኃይለማርያም ቆራጡ አብዮታዊው ከመባሉም በላይ የኢኮኖሚክስም፣ የታሪክም ምሁር ለመሆን ይቃጣው ነበር:: በዘመናዊት ኢትዮጵያ የዚህን ዓይነት



5.3 ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

የሆነውን ኃይለ ሥላሴን ከታሪክ ገጽ ለመፋቅ ሞክሯል። አሁን ደግሞ እንደ ሰዓት ፔንዱለም የሰው አስተያየት ወደሌላው ጫፍ ሄዶ የቀድሞውን ንጉሠ ነገሥት ለብፅዕና የማጨት አዝማሚያ ይታያል።



ሐቁ ግን፣ እንደ ብዙ የሕይወት አጋጣሚዎች፣ መሀል ቤት ነው። ማለትም ኃይለ ሥላሴ ጋኔንም ቅዱስም አይደለም። በተወሰነ የታሪክ ወቅት ትክክል ነው ብሎ ባመነበት አቅጣጫ አገሩን ለመምራት የሞከረ ሰው ነው። እስከተወሰነ ደረጃ ድረስም ዘመነ መንግሥቱ ተራማጅ ባሕሪያት እንደነበሩት የታሪክ ምርምሮች ያረጋገጡት ነገር ነው። በተለይም በአልጋ ወራሽነቱ ዘመን (1909-1923)፣ ከጣልያን ወረራ በፊት በነበረው አጭር የንግሥ ዘመኑና (1923-1928) ከነፃነት በኋላም በመጀመሪያዎቹ ዐሥርና ዐሥራ አምስት ዓመታት ዘመነ መንግሥቱ በጎ አዝማሚያና ማኅበረሰባዊ እርባና ነበረው። ማዕከላዊ አስተዳደር የተመሠረተው፣ የትምህርት እድል የተከፈተው፣ የመገናኛ አውታሮች የተዘረጉት በነዚህ ዓመታት ነው። ለዚህም ነው ከዘር ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ የፖለቲካ ሥልጣን አገሪቱን ከፋፍለው ሲገዙ የነበሩትን መሳፍንት ለማንበርከክ ያደረገውን ትግል እንደ ፀረ ፊውዳል ትግል አድርጎ የቆጠረው። የፊውዳል ሥርዓት ቁንጮ ተብሎ እንዳልተወገዘ ሁሉ እሱ ራሱን ፀረ ፊውዳል አድርጎ ማየቱ ፊውዳሊዝምን በኢኮኖሚ ሳይሆን በፖለቲካ ይዘቱ ብቻ ስለተመለከተው ነው። ይህን መሳፍንቱን የማንበርከኩንና ማዕከላዊ መንግሥቱን የማጠናከሩን ተልእኮ ከፈጸመ በኋላ ግን የኃይለ ሥላሴ እርባና ያከተመ ይመስላል። ከዚያ በኋላ ሥልጣን የእድገት መሣሪያ መሆኑ ይቀርና የሕይወት መነሻም መድረሻም (አልፋና ኦሜጋ) ሆነ።

በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው እንዲህ ዓይነት አዝማሚያ ደግሞ ፍጻሜው ራስን መውደድንና ከኔ በላይ ለአሳር የሚለውን አመለካከት መውለድ ነው። አላፊ ነኝ ብሎ ማሰብ ይቀርና ራስን ከማታልፈው አገር ጋር አቀራኝቶ ማየት ይመጣል። የአፄ ኃይለ ሥላሴም አመለካከት እኔ ኢትዮጵያ ነኝ፣ ኢትዮጵያም እኔ ነች ወደሚለው አቅጣጫ አዘነበለ። ረጅም ዘመን በንጉሠ ነገሥትነት በመግዛቱ ዘላቂ ሕያውነትን የተጐናፀፈ መስሎ ታየው። ስለሆነም ከኔ በኋላ አገሪቱ በቀና መንገድ እንድትሄድ ሥልጣን የሚሸጋገርበትን መንገድ ላሰናዳ ብሎ ለማሰብ አልቃጣውም። ይህም ምናልባት ከሁሉም በላይ ኃይለ ሥላሴ በታሪክ የሚጠየቅበት ግድፈት ነው ማለት ይቻላል። ከ1953 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላም ሆነ የስንብት በዓል ይመስል ከነበረው ከ80ኛው ልደት በዓሉ በኋላም ሥልጣኑን የመልቀቅ ቀርቶ በወጉ የማጋራት ዝንባሌም አላሳየ። የንጉሠ ነገሥቱ መላ ጥረትና ጉልበት ያረፈው ሥልጣንን ሳይቸረቸሩና ሳይበረዝ ማቆየትና ይህን ተቀናቃኝ የሆነውን ማናቸውንም ኃይል ማጥፋቱ ላይ ነው። ስለዚህም ነው ደኅንነት (ፀጥታ) በሥልጣን አወቃቀሩ ቅድሚያ የተሰጠው። ባገሪቱ ላይ የስለላ መረብ ዘርግቶ ዜጎቹን ከመቼውም ይበልጥ ለመቆጣጠር በቃ። የዚህ የስለላ መዋቅር ቁንጮ በ1952 የተቋቋመው «ልዩ ካቢኔ» የተባለው ድርጅት ነው። ይህ ተቋም የተመሠረተው እንደ ንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ የአማካሪ ቡድን ሲሆን፣ ዋና ሥራው ሰላዮቹን እንኳ ሳይቀር በመሰለል ለንጉሠ ነገሥቱ የነጠረ መረጃ ማቅረብ ነበር።

ሌላው የአፄ ኃይለ ሥላሴ ፍጹማዊ ሥልጣን ነፀብራቅ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱን ከሰብአዊው ዓለም አውጥቶ መለኮታዊ ባሕርይ የሰጠው የውዳሴ ባህል ነው። ይህ ባህል ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ከወረደ በኋላም ኢትዮጵያን እንደተጠናወተ ቀርቷል፣ እንዲያውም ባንዳንድ መልኩ ብሷል ማለት ይቻላል። መንግሥቱ ኃይለማርያም ቀራጡ አብዮታዊው ከመባሉም በላይ የኢኮኖሚክስም፣ የታሪክም ምሁር ለመሆን ይቃጣው ነበር። በዘመናዊት ኢትዮጵያ የዚህን ዓይነት

መሪን የማወደስ ባህል መስፋፋት የጀመረው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ነው። በዚሁ ዘመን የመገናኛ ዘዴዎች (ራዲዮ፣ ጋዜጣ ወዘተ) መስፋፋት ለዚህ ሁኔታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። የትምህርትም ሥርዓት ቢሆን የኃይለ ሥላሴን ገናናነት በሚያንፀባርቅ መልኩ የታነፀ ነበር። ተማሪዎች ንጉሠ ነገሥቱን የሚያወድሱና ለሱም የማቱሳላን እድሜ የሚመኙ ግጥሞች እያነበነቡ ነበር የሚያድጉት። ንጉሠ ነገሥቱም ለተማሪዎቹ እንደ ሁለተኛ አባት በመሆን በተለይ በገና ዕለት የብስኩት፣ የብርቱካንና የሹራብ ስጦታ ያበረክትላቸው ነበር። እንደ ተፈሪ መኰንን፣ እንደ ኮተቤና እንደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ያሉ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርት ሥፍራዎችም በየሳምንቱ በንጉሠ ነገሥቱ ይጎበኙ ነበር። በዋና ከተማው ውስጥ በሱ ስም ያልተሰየመ የሕዝብ መገልገያ ለማግኘት ያዳግት ነበር። ሁለት ትምህርት ቤቶች፣ አንድ ሆስፒታል፣ አንድ የቴያትር አዳራሽ እና የከተማው ስታዲዮም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ስም የያዙ ነበሩ። በአያሌ የክፍለ ሀገር ከተሞችም እንዲሁ። የልደት ቀኑና ዕለተ ንግሡም በዓሎች እንዲሆኑ ተደንግገው ነበር። የዘውድ በዓሉ የብር ብሔራዊ ዓመት በዓሎች እንዲሆኑ ... ኢዮቤልዩ (1948) ከዚያ በፊት ታይቶ ለማይታወቅ ፈንጠዝያ ምክንያት ሆነ። 80ኛ ዓመት የልደት በዓሉም (1964) አጀብና ሽብርቅ የበዛበት ዘመነ መንግሥት ማሳረጊያ ነበር ማለት ይቻላል።

የዚህ ሁሉ ሽርጉድ ድምር ውጤት ንጉሠ ነገሥቱን ከተራው ዓለም አምጥቆ የተለየ ክቡር ስፍራ ማሰጠት ሆነ። የጉልተኛው መደብ ዋና አፈ ቀላጤ እንዳልሆነ ሁሉ መደብ አልባ፣ ዓይነተኛው የፖለቲካ ከያኒ ከፖለቲካ በላይ ሆኖ ተገኘ። በሠናይ ተግባራት እሱ ሲመሰገን፣ መጥፎ መጥፎው በበታች ሹማምንት ተላከከ። አነስተኛው ዜጋ ከፍተኛውን በሱ ፊት ሊከስ እንዲችል በማድረግ የገለልተኛ ዳኝነትን ካባ ለበሰ። የሥርዓቱ አድራጊ ፈጣሪ እሱ ቢሆንም በዳይና ተበዳይን የሚዳኝ ሆኖ ቀረበ።

ዘመነ መንግሥቱ እየገፋ ሲሄድ ንጉሠ ነገሥቱ ከአገር ውስጥ ጉዳዮች ገለል እያለ የውጭ ግንኙነት ላይ ማተኮር ያዘ። ይህም የሆነበት አንዱ ምክንያት የውስጥ ጉዳዮቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰቡና ችግር እየወለዱ በመምጣታቸው ነው። ሌላው ደግሞ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ሐቅን ከመንገር ይልቅ ሸንገላን ስለሚወድ ልዩ መስሕብነት ስላለው ነው። በእርግጥም በመላ ዘመነ መንግሥቱ እሱን ማቆላመጥ ይወዱ የነበሩት ካገሩ ዜጎች ይልቅ የውጭ አገር ሰዎች ነበሩ። እሱም ዐጸፋውን በመመለስ ላይ አልቦዘነም። ውጭ አገሮችን በመጎብኘት አፄ ኃይለ ሥላሴን የሚወዳደር የአገር መሪ ማግኘቱ ያዳግታል። እነዚህ የማያቋርጡ ጉብኝቶች የርእዮተ ዓለምም ሆነ የጂዎግራፊ ግርዶሽን አያውቁም ነበር። የዚህ ሁሉ ጥረት ውጤትም ንጉሠ ነገሥቱን በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ መድረክ ልዩ የክብር ስፍራ ማሰጠት ሆነ። በተለይም ከምዕራቡም ሆነ ከምሥራቁም ዓለም ነፃ ነኝ ይል በነበረው የገለልተኛ መንግሥታት ንቅናቄ ዓቢይ ስፍራ ይዘው ከነበሩት መሪዎች አንዱ ኃይለ ሥላሴ ነበር። በራሱ ሊቀመንበርነት በ1955 የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም ደግሞ ከዚያም የተሻለ መድረክ ተገኘ።

ችግሩ ግን ንጉሠ ነገሥቱ ዓለም አቀፍ ዝናና ክብርን ሲያሳድድ እየተብላላ የመጣውን የውስጥ ችግር ማየት ተሳነው። ብልጭ ድርግም የሚለው የተቃውሞ ረመጥ የቋያ እሳት ሆኖ አንድ ቀን ሊያጠፋው እንደሚችል ከቶ ውልም ያለበት አይመስልም። ስለዚህም የ1966 አብዮት የመጣበት እንደ ፈረሰኛ ጎርፍ ነበር ማለት ይቻላል። አብዮቱ በፈነዳበት በመጀመሪያዎቹ ወራት ይህንን



ማዕበል ተቆጣጥሮ በፈለገው መንገድ ለመምራት መከጀሉ የእርጅና አንዱ ምልክት ነው። አንዳንድ የንጉሠ ነገሥቱ ድርጊቶች እንደሚጠቁሙት በመጨረሻ በመስከረም 2፣ 1967 ከዙፋን እስከሚያወርዱት ድረስ የደርግን አባላት ያያቸው የነበረው በምእት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለሥልጣን መወጣጫ ከተጠቀመባቸው የመሀል ሰፋሪ ሠራዊት ባልተለየ ሁኔታ ነበር ማለት ይቻላል።

መኳንንቱ

ንጉሠ ነገሥቱ አብዛኛውን ጊዜውንና ትኩረቱን በውጭ ጉዳዮች ላይ እያዋለ ሲመጣ፣ የዕለተ ተዕለት አስተዳደር ጉዳይ የሚኒስትሮቹ ኃላፊነት ሆነ። በዘመነ መንግሥቱ መጀመሪያ ዓመታት የነበረው ጉዳዮችን በዝርዝር የመከታተሉ ባሕርይ ጊዜ እየገፋ ሲሄድ ገሸሽ አለ። ይህ ማለት ግን ሚኒስትሮቹ ሙሉ ሥልጣን ተጎናፅፈው ነበር ማለት አይደለም። ንጉሠ ነገሥቱ ሳያውቃቸውና ሳያጸድቃቸው የሚያልፉ ዐበይት የፖሊሲ ውሳኔዎች አልነበሩም። የአብዛኛዎቹ ሚኒስትሮች የመደብ ጀርባም በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ነፃ አቋም ለመውሰድ የሚያደፋፍር አልነበረም። ብዙዎቹ የመሳፍንት ወገን ባለመሆናቸውና ሹመትና ክብሩንም በቀጥታ ከንጉሠ ነገሥቱ ያገኙ በመሆናቸው ታማኝነታቸው የተረጋገጠ ነበር። በዚህም አኳኋን ንጉሠ ነገሥቱ ሚኒስትሮቹን የመሳፍንቱን ኃይል ለመቋቋም ዓይነተኛ መሣሪያው አድርጓቸው ነበር። የድኅረ 1933 የኢትዮጵያ ፖለቲካ አንዱ ገጽታ ይህ በመኳንንቱና በመሳፍንቱ መካከል ይካሄድ የነበረው ስውር ትግል ነበር ማለት ይቻላል።

ከነፃነት በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ካተኮረባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን እንደገና ማቋቋም ነው። በዚህም ረገድ በ1935 እና በ1936 የወጡ ሁለት ትእዛዞች ዐሥራ አንድ ሚኒስቴሮችንና የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጽሕፈት ቤት አቋቋሙ። ምንም እንኳ ሚኒስቴሮቹ የውስጥ ደንባቸውን ለማውጣትና የበታች ሹማምንትን ለመሰየም ሥልጣን ቢኖራቸውም፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸው ተገዥነት በማያወላዳ ቋንቋ የተገለጸ ነበር። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተብሎ የተቋቋመውም እንዲያው ለወጉ እንጂ በሌሎች አገሮች እንደተለመደው ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል አልነበረም። በ1958 የጠቅላይ ሚኒስትሩን ኃላፊነትና ሥልጣን ለመደንገግ የወጣው ትእዛዝም ቢሆን በዚህ የሥልጣን አወቃቀር ላይ መሠረታዊ ለውጥ አላመጣም። እርግጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብረውት የሚሠሩትን ሚኒስትሮች ለመምረጥ ሥልጣን ተሰጠው፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤትም የካቢኔ ባሕርይን ወደመያዙ ተቃረበ።

ይሁን እንጂ የፖሊሲ ውሳኔዎችን መውሰዱም ሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩንም ጨምሮ ሚኒስትሮችን፣ ምክትል ሚኒስትሮችንና ረዳት ሚኒስትሮቹን የመሾሙ ሥልጣን አሁንም የንጉሠ ነገሥቱ ነበር። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተግባር ሹመቶችንና ውሳኔዎችን ከማስተናገድ እምብዛም የላቀ አልነበረም ማለት ይቻላል። እስከ 1950 ድረስ ይህን የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የያዘው ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ነበር። ቁመናው ግርማ ሞገስን የተላበሰውን ያህል የፖለቲካ ሥልጣኑ ግን የኮሰሰው መኰንን ቀደም



5.4 ከ1933 እስከ 1948 ባለው ጊዜ ሥልጣኑ ገኖ የነበረው ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ

ሲል በ1928 ጦርነት በአጋዴን ግንባር ስመ ጥር የጦር መሪ የነበረ ሲሆን፣ የፋሽስት ጦር ድል ከተቀዳጀ በኋላም አምስቱን ዓመት በስደት አሳልፎ ነበር።

ዝንባሌው ከፖለቲካ ይልቅ ወደ ሥነ ጽሑፍ በመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ እንዲያው ለይስሙላ ነበር ማለት ይቻላል። እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ከፍተኛ ሥልጣን የጨበጠው ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ነበር። ወልደ ጊዮርጊስ እንድም ከዝቅተኛ ቤተሰብ በመምጣቱ፣ አንድም ደግሞ በስደት ዘመን የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ጸሐፊ በመሆኑ ከፍተኛ ሥልጣን ተቀዳጅቶ ነበር። ለቤተ መንግሥቱ የቀረበውን የጽሕፈት ሚኒስቴር ለረጅም ጊዜ በመያዙና በፖለቲካ ሽኩቻም የተካነ በመሆኑ ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ እጅግ የተፈራና የተከበረ ሰው ነበር። በዚሁ ዘመኑ ጸሐፊ ትእዛዝ ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ጊዜያት የአገር አገዛዝንና የፍርድ ሚኒስትርነትንም ይዞ ነበር።

በመጨረሻ የወልደ ጊዮርጊስን ውድቀት ለማምጣት ተግተው ከሠሩት መካከል ከሱ ቀጥሎ በድኅረ 1933 የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፍተኛ ሚና





5.5 ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው፣ ደራሲና ጠቅላይ ሚኒስትር



5.6 ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር

የተጫወተው መኰንን ሀብተ ወልድ ይገኝበታል። የቄስ ልጅ የነበረው መኰንን የፖለቲካ ሕይወቱ የጀመረው እንደ ወልደ ጊዮርጊስ ከ1928 በፊት ሲሆን፣ በአምስቱ ዓመት የፋሽስት ኢጣልያ አገዛዝ ወቅትም ፈረንሳይ አገር በስደት ቆየ። ነፃነት ከተመለሰ በኋላ የንግድና ቀጥሎም የእርሻ ሚኒስትር ሆኖ ካገለገለ በኋላ፣ ለረጅም ጊዜ ከስሙ ጋር የተቆራኘውንና ከፍተኛ አስተዋፅኦም ያደረገበትን የገንዘብ ሚኒስትርነት ያዘ። ሰዎችን በማቅረብና በመርዳት ብዙ ተከታዮች ከማፍራቱም በላይ የግሉ የሆነ የስለላ መረብ በመዘርጋት በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድም ቅርበት ለማግኘትና ብሎም ወልደ ጊዮርጊስን ለመፈንገል ቻለ። በመጨረሻ በ1953 በነመንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት ከሌሎች መሳፍንትና መኳንንት ጋር ከታገተ በኋላ ተረሸነ።

ታናሽ ወንድሙ አክሊሉ ሀብተወልድ ወደ ፖለቲካ መድረክ ሊወጣ የቻለው በመኰንን ጥላ ሥር ነው። የኋላ ኋላ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ረጅም ዘመን ሊያገለግል የበቃው አክሊሉ የፖለቲካ ሕይወቱን የጀመረው በውጭ ጉዳይ መስክ ነው። በተለይም የኤርትራ ጥያቄ ለተባበሩት መንግሥታት ቀርቦ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያን የይገባኛል ክርክር በመምራት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በ1950 በራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው እግር ተተክቶ እስከ 1953 በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ ከዚያም እስከ አብዮቱ በጠቅላይ



5.4 ከ1933 እስከ 1948 ባለው ጊዜ ሥልጣኑ ገኖ የነበረው ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ

ሲል በ1928 ጦርነት በአጋዴን ግንባር ስመ ጥር የጦር መሪ የነበረ ሲሆን፣ የፋሽስት ጦር ድል ከተቀዳጀ በኋላም አምስቱን ዓመት በስደት አሳልፎ ነበር::

ዝንባሌው ከፖለቲካ ይልቅ ወደ ሥነ ጽሑፍ በመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ እንዲያው ለይስሙላ ነበር ማለት ይቻላል:: እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ከፍተኛ ሥልጣን የጨበጠው ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ነበር:: ወልደ ጊዮርጊስ አንድም ከዝቅተኛ ቤተሰብ በመምጣቱ፣ አንድም ደግሞ በስደት ዘመን የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ጸሐፊ በመሆኑ ከፍተኛ ሥልጣን ተቀዳጅቶ ነበር:: ለቤተ መንግሥቱ የቀረበውን የጽሕፈት ሚኒስቴር ለረጅም ጊዜ በመያዙና በፖለቲካ ሽኩቻም የተካነ በመሆኑ ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ እጅግ የተፈራና የተከበረ ሰው ነበር:: በዚሁ ዘመኑ ጸሐፌ ትእዛዝ ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ጊዜያት የአገር አገዛዝንና የፍርድ ሚኒስትርነትንም ይዞ ነበር::

በመጨረሻ የወልደ ጊዮርጊስን ውድቀት ለማምጣት ተግተው ከሠሩት መካከል ከሱ ቀጥሎ በድኅረ 1933 የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፍተኛ ሚና





5.5 ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው፣ ደራሲና ጠቅላይ ሚኒስትር



5.6 ጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር

የተጫወተው መኰንን ሀብተ ወልድ ይገኝበታል:: የቂስ ልጅ የነበረው መኰንን የፖለቲካ ሕይወቱ የጀመረው እንደ ወልደ ጊዮርጊስ ከ1928 በፊት ሲሆን፣ በአምስቱ ዓመት የፋሽስት ኢጣልያ አገዛዝ ወቅትም ፈረንሳይ አገር በስደት ቆየ:: ነፃነት ከተመለሰ በኋላ የንግድና ቀጥሎም የእርሻ ሚኒስትር ሆኖ ካገለገለ በኋላ፣ ለረጅም ጊዜ ከስሙ ጋር የተቆራኘውንና ከፍተኛ አስተዋፅኦም ያደረገበትን የገንዘብ ሚኒስትርነት ያዘ:: ሰዎችን በማቅረብና በመርዳት ብዙ ተከታዮች ከማፍራቱም በላይ የግሉ የሆነ የስለላ መረብ በመዘርጋት በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድም ቅርበት ለማግኘትና ብሎም ወልደ ጊዮርጊስን ለመፈንገል ቻለ:: በመጨረሻ በ1953 በነመንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት ከሌሎች መሳፍንትና መኳንንት ጋር ከታገተ በኋላ ተረሸነ::

ታናሽ ወንድሙ አክሊሉ ሀብተወልድ ወደ ፖለቲካ መድረክ ሊወጣ የቻለው በመኰንን ጥላ ሥር ነው:: የኋላ ኋላ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ረጅም ዘመን ሊያገለግል የበቃው አክሊሉ የፖለቲካ ሕይወቱን የጀመረው በውጭ ጉዳይ መስክ ነው:: በተለይም የኤርትራ ጥያቄ ለተባበሩት መንግሥታት ቀርቦ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያን የይገባኛል ክርክር በመምራት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: በ1950 በራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው እግር ተተክቶ እስከ 1953 በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ ከዚያም እስከ አብዮቱ በጠቅላይ

ሚኒስትርነት ሠርቷል። ጠቅላይ ሚኒስትርም ጸሐፊ ትእዛዝም በመሆኑም ባህላዊውንና ዘመናዊውን ሥልጣን ለማጣመር ችሎ ነበር። ይሁንና ጸሐፊ ትእዛዝነቱ ከማዕረግ ስምነቱ በስተቀር በተግባራዊነቱ ረገድ እየከሰመ ሲሄድ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ግን እየጐለበተ የሚመጣ ነበር። ይህም ሆኖ አክሊሉ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ትቶ የሄደው አሻራ ይኸን ያህልም የጎላ አይደለም። የቀዳሚውን የጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስንም ሆነ የወንድሙን የመኰንንን የፖለቲካ ብልጠት አልተካነም ነበር። ስለሆነም ከግንባር ቀደም ባለሟልነት አልፎ እንደ ሁለቱ አድራጊ ፈጣሪ የመሆን አቅሙ የደከመ ነበር።

ከላይ በተጠቀሱት የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ምሰሶዎች አንፃር መሳፍንቱ ከመንግሥት ጋር የነበራቸው ግንኙነት ላላ ያለ ነበር። ይህንንም ወደ ኋላ የመሳፍንቱ ቁንጮ ለመሆን በበቃው በልዑል ራስ ዐሥራተ ካሣ የፖለቲካ ሕይወት መረዳት ይቻላል። የተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች አገረ ገዢ (እንደራሴ) እና በመጨረሻም የዘውድ አማካሪ ከመሆን አልፎ ሚኒስትር የሆነበት ወቅት የለም። እንደዚሁም ልጅ እንዳልካቸው መኰንን (የራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ልጅ) እና ልጅ ሚካኤል እምሩ (የልዑል ራስ እምሩ ልጅ) አብዛኛውን ጊዜ የሚመረጡት ለአምባሳደርነት ነበር። ከዚህ ግምገማ ትንሽ ለየት የሚለው የንጉሠ ነገሥቱ አማች የነበረው ልጅ (ኋላ ጄኔራል) ዓቢይ አበበ ነው። በ1930ዎቹና በ1940ዎቹ ዓመታት የጦር ሚኒስትር ከመሆኑም ሌላ የፍርድና የአገር ግዛት ሚኒስትርም ሆኖ ሠርቷል። እሱም ቢሆን ግን በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የፖለቲካ ሕይወቱን ያሳረገው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት በመሆን ነው። ሌላው ከመሳፍንቱ ወገን ለማዕከላዊ ፖለቲካ ሥልጣን የበቃው ደግሞ የወሊጋው መስፍን ይልማ ዴሬሳ ነው። ለረጅም ጊዜ የገንዘብ ሚኒስትር በመሆን ከመኰንን ሀብተወልድ ቀጥሎ ባገሪቱ የገንዘብ አስተዳደር ላይ አሻራውን ትቶ ለመሄድ ችሏል።

ነገር ግን ከዚህ በላይ ከተደረገው ግምገማ ተነሥቶ መሳፍንቱ ወደ ፖለቲካ ግዑዝነት ተሸጋግረው ነበር ማለት የተሳሳተ ይሆናል። የዘውድ ምክር ቤት ተብሎ በተቋቋመው አካል አማካይነት የንጉሠ ነገሥቱን ጆሮ ለማግኘት ችለው ነበር። እንደ ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ራስ ሥዩም መንገሻ፣ ራስ መስፍን ስለሺ፣ ራስ ኃይሉ በለው፣ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ያሉ መሳፍንትና አቡኑም በተለያየ ወቅት የምክር ቤቱ አባል ሆነዋል። አንዳንድ የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላትም በፖለቲካ ሂደቱ የማይናቅ ሚና ነበራቸው። በዚህ ረገድ በተለይ ልትጠቀስ የሚገባት የንጉሠ ነገሥቱ አንጋፋ ልጅ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ናት። ባጠቃላይ ሁኔታውን ስንገመግም፣ አፄ ኃይለ ሥላሴ በተለመደ የፖለቲካ ጥበቡ መሳፍንቱንና መኳንንቱን በማፋጠጥ የራሱን የፖለቲካ የበላይነት ይበልጥ ለማጠናከር እንደሚረዳው የተገነዘበ ይመስላል።

## የተሻሻለው የ1948 ሕገ መንግሥት

በ1948 አፄ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓሉን የብር ኢዮቤልዩ ሲያከብር የ1923ቱን ሕገ መንግሥት የሚያሻሽል አዲስ ሕገ መንግሥት ዐወጀ። ይህም አዲስ ሕገ መንግሥት ያስፈለገበት በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛው ኢትዮጵያን በዓለም ፊት የዘመናዊነት ካባ ለማስጠት ነው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በ1945 ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ከተቀላቀለች በኋላ ገዛድ የወጣውን



የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት ኋላቀርነት ከኤርትራው ሕገ መንግሥት ጋር የሚቀራረብ ሕገ መንግሥት በማውጣት ለማድበዝበዝ ተብሎ ነው። ይህንን አዲሱን ሕገ መንግሥት እንዲያረቁ የተሰየሙት ሦስት አሜሪካዊ አማካሪዎችና ሁለቱ የሥርዓቱ ዋና ተጠሪዎች፣ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስና አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ ነበሩ። የዘውዱም ምክር ቤት የኮሚቴውን ሥራ በቅርብ በመከታተል በተለይም የዙፋኑ ሥልጣን እንዳይበረዝ ተግቶ ጠብቋል። ይህም ስለሆነ ይመስላል ሕገ መንግሥቱ የሚጀምረው ዙፋኑን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከመሆኑም በላይ ከጠቅላላ ድንጋጌው ሩብ ያህል ያተኮረው በወራሴ መንግሥትና በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ላይ ነው።

የ1948ቱ ሕገ መንግሥት የመጨረሻ ፋይዳም ከ1923ቱ በበለጠ አኳኋን ለፍጹማዊ አገዛዝ ሕጋዊ መሠረት መስጠት ሆነ። ሕገ መንግሥቱን በማርቀቅ ከተሳተፉት አሜሪካዊ አማካሪዎች አንዱ ጆን እስፔንሰር እንዳለው፣ ሕገ መንግሥቱ ሥርዓቱ ተከብሮና ጸንቶ እንዲቆይ ለማድረግ ጥሩ ሽፋን ነበር (Spencer, 260)። የንጉሠ ነገሥቱ ፍጹማዊ ሥልጣን በማያሻማ መንገድ ነበር የተገለጸው፣

> ንጉሠ ነገሥቱ የነጋሢ ዘር በመሆኑና ቅብዐ መንግሥት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ፣ ማዕረጉ የማይገሠሥ፣ ሥልጣኑ የማይደፈር ሆኖ በቀየውም ልማድ በአዲሱም ሕግ በሚገባው ክብር ሁሉ ይከበራል። ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የሚነሣ ማንም ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል። (አንቀጽ 4)

የመናገርና የፕሬስ ነፃነትን የመሳሰሉ ሰብአዊ መብቶችን የሚያስከብሩ አንቀጾች ቢገኙም «በሕግ መሠረት»፣ «በሕግ ተዘርዝሮ በሚወሰነው መሠረት» በሚሉ ሐረጎች እየተሸበቡ ለይስሙላ ሆነው ቀርተዋል።

በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ግን አዲሱ ሕገ መንግሥት አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ ከፈተ ማለት ይቻላል። እነዚህም የመምረጥን መብት ለአቅመ አዳምና ሔዋን ለደረሱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ መስጠቱና በሕዝብ የተመረጠ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት እንዲቋቋም መደንገጉ ነው። በተግባር ግን የሁለቱም ድንጋጌዎች ፖለቲካ ጠቀሜታ ምንም ያህል የጎላ አልነበረም። ሕዝቡ በአማካሪዎች ምርጫ የሚያደርገው ተሳትፎ ዝቅተኛ ሲሆን ተመራጮቹም ለመረጣቸው ሕዝብ ያን ያህል አሳቢና ተቆርቋሪ ሆነው አልተገኙም። ለመመረጥ የሚያበቃው የንብረት መስፈርትም የምክር ቤቱን የመደብ ዝንባሌ ከመጀመሪያው አጥቦት ነበር ማለት ይቻላል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ባለመፈቀዳቸውም የፓርላማ ምርጫ ከግል ሰቦች ፉክክር ከፍ ሊል አልቻለም። የፓርላማ አማካሪነት በደመወዙም ሆነ በክብሬታው የሚያጓጓ በመሆኑ ግን ለመመረጥ የሚደረገው ፉክክር ቀላል አልነበረም። ስለዚህ ፖርላማ ለግል ብልፅግና አመቺ ጎዳና ከመክፈቱ በስተቀር ሕዝባዊ ውክልናን አጎለበተ ብሎ ለመናገር ያዳግታል።

## የጭቆና አውታር

ተሻሽለ የተባለው ሕገ መንግሥት ለይስሙላ ሲሆን፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት እንደዋዛ የማያየው ነገር ቢኖር ሕዝቡ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ የሚያስችለውን የጭቆና መዋቅር መዘርጋቱን ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት እንደተመለሰ መጀመሪያ ካተኮረባቸው ነገሮች አንዱ የኢጣልያ ወረራ ያቋረጠውን ዘመናዊ ጦር የማደራጀቱን ተግባር እንደገና መቀጠል ነው። ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው፣ የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘብ በስዊድኖች እርዳታ እንደገና ተቋቁሞ ከ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ እስከተበተነ ድረስ የመንግሥቱ ምርጥ ሠራዊት ሆኖ ቆየ። የታሪክ እንቆቅልሽ ሆኖ ንጉሠ ነገሥቱንና ሥርዓቱን እንዲጠብቅ ባንደኛ ደረጃ የተዋቀረው ሠራዊት የሥርዓቱ ዋና ጠላት ሆኖ ተገኘ። ይህን ሠራዊት ለዐሥራ አምስት ዓመታት የመራው በጦር ኃይሎች ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያፈራው ሜጀር ጄኔራል መሉጌታ ቡሊ ነው። ከጠላት በፊት በሆለታ የጦር ት/ቤት እጩ መኰንንና ኋላም አስተማሪ የነበረው ይህ መኰንን ምናልባትም የግብፁን የገማል ዐብደል ናስርን ፈለግ በመከተል አንድ ቀን መንግሥት ይገለብጥ ይሆናል የሚል ግምት በብዙ ሰዎች ዘንድ አድሮ ነበር። ይህ ሳይሆን ቀረና በ1953 አብርት ካዴት በነበረውና ኋላም በሱ እግር የክብር ዘበኛ አዛዥ ሆኖ በተተካው በብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተመራው መፈንቅለ መንግሥት ሰላባ ለመሆን በቃ።

በ1934፣ ዘመናዊው የኢትዮጵያ ፖሊስ ሠራዊት በእንግሊዞች አምሳያ ተፈጠረ። የእዙን አወቃቀር የተመለከተን እንደሆነ እንደ እንግሊዞች ሥርዓት ኮንስታብል፣ ሱፐርኢንቴንደንት እና ኮሚሽነር በሚሉ ስያሜዎች የታወቀ ነበር። ከጊዜ በኋላ ሠራዊቱ ዋናውን ድጋፍ ከእንግሊዞች ይልቅ ከጀርመንና ከእሥራኤል ማግኘት ጀመረ። ከፖሊስ ሠራዊት ጋር የሀገር ውስጥ ፀጥታ በመጠበቅ ቁልፍ ሚና ይጫወት የነበረው የሕዝብ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ሆነ። የዲሞክራሲ መብቶች በተነፈጉባቸው አገሮች እንደሚሆነው ሁሉ፣ እዚህም የፖለቲካ ተቃውሞን ለማኮላሸትና ለማስወገድ ይህ መሥሪያ ቤት የመንግሥቱ ዋና አለኝታ ሆነ። ከፖሊስ ሠራዊቱ ባሻገር፣ የውጭ ጠላትን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን የውስጥ ተቃውሞንም ለመደምሰስ ታስቦ የጦር ሠራዊት መጀመሪያ በእንግሊዞች ኋላ ደግሞ ባሜሪካኖች አጋዥነት ተቋቋመ። ሌላው የጦር ኃይሎች አካል ደግሞ በነፃነት ማግሥት ጠላትን ሲዋጉ የነበሩትን አርበኞች ለመቆጣጠር እንዲያመች ተቋቁሞ ኋላ ብሔራዊ ጦር በመባል የታወቀው የገጠር ሚሊሺያ ነው።

ይህ ወታደራዊ መዋቅር ምን ያህል የመንግሥቱን ልዩ ትኩረት እንደሳበ የሚታወቀው በተመደበለት በጀት ነው። ከመንግሥት በጀት ውስጥ በተከታታይ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት የመከላከያና ያገር ግዛት ሚኒስቴሮች ነበሩ። ለምሳሌ በ1957 ከተመደበው 38 ሚሊዮን ብር በጀት ውስጥ 11 ሚሊዮን ያህሉ ለአገር ግዛት ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 5 ሚሊዮን ለፀጥታ ነበር። የጦር ሚኒስቴር (በዚያን ጊዜ አጠራሩ) ድርሻ ደግሞ 8 ሚሊዮን ገደማ ነበር። በ1960 ደግሞ ከጠቅላላው 400 ሚሊዮን ብር የሚሆን በጀት ከ80 ሚሊዮን በላይ ለመከላከያ ሚኒስቴር፣ 60 ሚሊዮን ያህል ደግሞ ለአገር ግዛት የተመደበ ነበር። ያም ሆኖ ግን መንግሥት እንዲህ የተንከባከባቸው የጦር ኃይሎች ናቸው በ1966 በመንግሥት ላይ መሣሪያቸውን ያዞሩት። ሕዝብ እንዲያስገብሩ የተመለመሉት ወታደሮች ከሕዝብ ጋር ሆነው በመንግሥት ላይ አመፁ። ይህ አዝማሚያ





5.7 ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ የክብር ዘበኛ ጠቅላይ አዛዥ

መጀመሪያ የታየው በ1953 ነበር። የፖለቲካ አስተያየቶች በተደራጀ መንገድ እንዲገለጹ ያልፈቀደ መንግሥት ዕጣው ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም ነበር። የሕዝብ ቁጣ እንደ ማዕበል ሲነሣ የጦር ኃይሎቹም ዞሮ ዞሮ የሕዝብ አካል ናቸውና ወደዚያው መሳባቸው አልቀረም። ይህ ማዕበል በ1966 ድንገተኛ ይምሰል እንጂ ለረጅም ጊዜ ሥር የሰደደና ሲብላላ የቆየ ነው። በሚቀጥሉት ገጾች የዚህን የፖለቲካ ተቃውሞ አመጣጥ በተለያየ ፈርጅ እንቃኛለን።

## ተቃውሞ

እንደ 1948ቱ ሕገ መንግሥት ቢሆን ኖሮ፣ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ በኋላ ኢትዮጵያን ማን እንደሚገዛ መቼም ታይቶ ባልታወቀ ዝርዝርና ጥንቃቄ ተደንግጎ ነበር። ነገር ግን በ1966 የተቀጣጠለው አብዮት በረጅምነቱ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙም ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ዘመነ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የሕይወት ዘመኑን በምእት ሳይሆን በሺህ ዓመታት የሚቆጥረውንም ሥርወ መንግሥት

## የጭቆና አውታር

ተሻሻለ የተባለው ሕገ መንግሥት ለይስሙላ ሲሆን፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት እንደዋዛ የማያየው ነገር ቢኖር ሕዝቡ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ የሚያስችለውን የጭቆና መዋቅር መዘርጋቱን ነው:: ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት እንደተመለሰ መጀመሪያ ካተኮረባቸው ነገሮች አንዱ የኢጣልያ ወረራ ያቋረጠውን ዘመናዊ ጦር የማደራጀቱን ተግባር እንደገና መቀጠል ነው:: ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው፣ የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘብ በስዊድኖች እርዳታ እንደገና ተቋቁሞ ከ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ እስከተበተነ ድረስ የመንግሥቱ ምርጥ ሠራዊት ሆኖ ቆየ:: የታሪክ እንቆቅልሽ ሆኖ ንጉሠ ነገሥቱንና ሥርዓቱን እንዲጠብቅ ባንደኛ ደረጃ የተዋቀረው ሠራዊት የሥርዓቱ ዋና ጠላት ሆኖ ተገኘ:: ይህን ሠራዊት ለዐሥራ አምስት ዓመታት የመራው በጦር ኃይሎች ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያፈራው ሜጀር ጄኔራል መሉጌታ ቡሊ ነው:: ከጠላት በፊት በሆለታ የጦር ት/ቤት እጩ መኰንንና ኋላም አስተማሪ የነበረው ይህ መኰንን ምናልባትም የግብፁን የገማል ዐብደል ናስርን ፈለግ በመከተል አንድ ቀን መንግሥት ይገለብጥ ይሆናል የሚል ግምት በብዙ ሰዎች ዘንድ አድሮ ነበር:: ይህ ሳይሆን ቀረና በ1953 አብርት ካዴት በነበረውና ኋላም በሱ እግር የክብር ዘበኛ አዛዥ ሆኖ በተተካው በብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተመራው መፈንቅለ መንግሥት ሰላባ ለመሆን በቃ::

በ1934፣ ዘመናዊው የኢትዮጵያ ፖሊስ ሠራዊት በእንግሊዞች አምሳያ ተፈጠረ:: የእዙን አወቃቀር የተመለከትን እንደሆነ እንደ እንግሊዞች ሥርዓት ኮንስታብል፣ ሱፐርኢንቴንደንት እና ኮሚሽነር በሚሉ ስያሜዎች የታወቀ ነበር:: ከጊዜ በኋላ ሠራዊቱ ዋናውን ድጋፍ ከእንግሊዞች ይልቅ ከጀርመንና ከእሥራኤል ማግኘት ጀመረ:: ከፖሊስ ሠራዊት ጋር የሀገር ውስጥ ፀጥታ በመጠበቅ ቁልፍ ሚና ይጫወት የነበረው የሕዝብ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ሆነ:: የዲሞክራሲ መብቶች በተነፈጉባቸው አገሮች እንደሚሆነው ሁሉ፣ እዚህም የፖለቲካ ተቃውሞን ለማኰላሸትና ለማስወገድ ይህ መሥሪያ ቤት የመንግሥቱ ዋና አለኝታ ሆነ:: ከፖሊስ ሠራዊቱ ባሻገር፣ የውጭ ጠላትን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን የውስጥ ተቃውሞንም ለመደምሰስ ታስቦ የጦር ሠራዊት መጀመሪያ በእንግሊዞች ኋላ ደግሞ በሜሪካኖች እጋዥነት ተቋቋመ:: ሌላው የጦር ኃይሎች አካል ደግሞ በነፃነት ማግሥት ጠላትን ሲዋጉ የነበሩትን አርበኞች ለመቆጣጠር እንዲያመች ተቋቁሞ ኋላ ብሔራዊ ጦር በመባል የታወቀው የገጠር ሚሊሽያ ነው::

ይህ ወታደራዊ መዋቅር ምን ያህል የመንግሥቱን ልዩ ትኩረት እንደሳበ የሚታወቀው በተመደበለት በጀት ነው:: ከመንግሥት በጀት ውስጥ በተከታታይ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት የመከላከያና ያገር ግዛት ሚኒስቴሮች ነበሩ:: ለምሳሌ በ1957 ከተመደበው 38 ሚሊዮን ብር በጀት ውስጥ 11 ሚሊዮን ያህሉ ለአገር ግዛት ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 5 ሚሊዮን ለፀጥታ ነበር:: የጦር ሚኒስቴር (በዚያን ጊዜ አጠራሩ) ድርሻ ደግሞ 8 ሚሊዮን ገደማ ነበር:: በ1960 ደግሞ ከጠቅላላው 400 ሚሊዮን ብር የሚሆን በጀት ከ80 ሚሊዮን በላይ ለመከላከያ ሚኒስቴር፣ 60 ሚሊዮን ያህል ደግሞ ለአገር ግዛት የተመደበ ነበር:: ያም ሆኖ ግን መንግሥት እንዲህ የተንከባከባቸው የጦር ኃይሎች ናቸው በ1966 በመንግሥት ላይ መሣሪያቸውን ያዞሩት:: ሕዝብ እንዲያስገብሩ የተመለመሉት ወታደሮች ከሕዝብ ጋር ሆነው በመንግሥት ላይ አመፁ:: ይህ አዝማሚያ





5.7 ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ የክብር ዘበኛ ጠቅላይ አዛዥ

መጀመሪያ የታየው በ1953 ነበር:: የፖለቲካ አስተያየቶች በተደራጀ መንገድ እንዲገለጹ ያልፈቀደ መንግሥት ዕጣው ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም ነበር:: የሕዝብ ቁጣ እንደ ማዕበል ሲነሣ የጦር ኃይሎቹም ዞሮ ዞሮ የሕዝብ አካል ናቸውና ወደዚያው መሳባቸው አልቀረም:: ይህ ማዕበል በ1966 ድንገተኛ ይምሰል እንጂ ለረጅም ጊዜ ሥር የሰደደና ሲብላላ የቆየ ነው:: በሚቀጥሉት ገጾች የዚህን የፖለቲካ ተቃውሞ አመጣጥ በተለያየ ፈርጅ እንቃኛለን::

## ተቃውሞ

እንደ 1948ቱ ሕገ መንግሥት ቢሆን ኖሮ፣ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ በኋላ ኢትዮጵያን ማን እንደሚገዛ መቼም ታይቶ ባልታወቀ ዝርዝርና ጥንቃቄ ተደንግጎ ነበር:: ነገር ግን በ1966 የተቀጣጠለው አብዮት በረጅምነቱ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙም ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ዘመነ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የሕይወት ዘመኑን በምእት ሳይሆን በሺህ ዓመታት የሚቆጥረውንም ሥርወ መንግሥት

ጭምር ነው ያስወገደው:: የኃይለ ሥላሴ ኃጢአት የዘመነ መንግሥቱ ያለቅጥ መንዛዛት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ዕጣው ሆነና ወግ አጥባቂዎችን በመፋለም የፖለቲካ ሕይወቱን የጀመረው መስፍን የለውጥ እንቅፋት በመሆን ደመደመው:: በመሠረታዊ መልኩ ሲታይ የኃይለ ሥላሴ ፍጻሜ የፊውዳሊዝም ቀውስ ውጤት ነው:: ከማንም ይበልጥ በመሪ ተዋናይነት የፈጠረው የዳበረ የፊውዳል ሥርዓት በውስጡ ያዘላቸውን የለውጥ ኃይሎች አፍኖ ሊያቆይ አልቻለም:: ውጤቱም አብዮት ሆነ::

የዚህ አብዮት መቅድም በግልጽም በኅቡዕም ሲካሄድ የቆየ የብዙ ዓመታት የፖለቲካ ተቃውሞ ነው:: አዲስ ሕይወት *Ethiopia From Autocracy to Revolution* በሚል ርእስ በጻፈው መጽሐፍ በትክክል እንደገለጸው፣ የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በድኅረ ነፃነት ኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃውሞ ታሪክ ያንድ ምዕራፍ መጨረሻና የሌላው መጀመሪያ ሆነ:: ከሙከራው በፊት ተቃውሞ ብዙውን ጊዜ የአድማ መልክ ሲኖረው የተወሰነውም በመኳንንቱ ክልል ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን አደባባይ ከመውጣቱም በላይ ሰፊ መሠረት ያዘ:: ይህም ተቃውሞ የተለያዩ ገጽታዎች ነበሩት:: ገበሬዎች ለኤኮኖሚያዊ ፍትሕ፣ ብሔረሰቦች ለዲሞክራሲያዊ መብት ብረት አነሡ:: ምሁራን ፍትሕና እኩልነት ለሰፈነበት አዲስ ሥርዓት ታገሉ:: አንዳንድ የገዢው መደብ አባላት ሳይቀሩ ሥርዓቱን ከሚጠብቀው መዓት ለማዳን ሲባል የሥርዓቱ መሻሻል ወይም የኃይለ ሥላሴ መወገድ የማይቀር መሆኑን በመገንዘብ መጪውን ፍርድ ለማለዘብ የፊናቸውን እንቅስቃሴ ጀመሩ::

## አድማዎች

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ላይ መጀመሪያ የተነሣው ተቃውሞ የአምስቱ ዓመት የአርበኞች ትግል ተቀጽላነት ባሕርይ አለው:: ይህም በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል:: ባንድ መልኩ ንጉሠ ነገሥቱ በ1928 አገር ጥሎ በመሄዱ ዘግይቶ የመጣ የቅሬታ መግለጫ ነው ሊባል ይችላል:: ቀረብ ስንል ደግሞ አርበኞቹ አምስቱን ዓመት በመከራና በሥቃት አሳልፈው እሱ ባንፃሩ ከተደላደለ የስደት ኑሮ ተመልሶ ሥልጣን ላይ ቁጢጥ በማለቱ ቅሬታን መግለጫ መንገድ ነው ሊባል ይችላል:: በተለይም ቅሬታውን ያባባሰው ባዲሱ ሥርዓት ባንዳዎች ያገኙት ሹመትና ማዕረግ ነው:: በዚህ ረገድ በኃይለ ሥላሴ ላይ ያመፁ ሦስት የቀድሞ አርበኞች ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህና ብላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያት ናቸው::

በላይ ዘለቀ ምናልባትም ከአምስቱ ዓመት የአርነት ትግል መሪዎች በጣም ተወዳጅ የነበረ ነው:: መሠረቱን በምሥራቅ ጎጃም በብቸና አድርጎ ጣልያኖችን ያርበደበደ ተዋጊ ነበር:: ይህ በሕዝብ ዘንድ የነበረው ተወዳጅነት ግን ሥልጣኑ ላይ ተመልሶ ለመደላደል በሚሞክረው ንጉሠ ነገሥት ፊት ሳያስወጋው አልቀረም:: ኃይሉ ከገነነበት አካባቢ ለማራቅ ይመስላል ንጉሠ ነገሥቱ ራስ አስኝቶ በደቡብ ኢትዮጵያ አገረ ገዥ እንዲሆንም ለይሞት ነበር:: ሆኖም በላይ ተንኰሉን ስለደረሰበት ይመስላል እምቢ አለ:: በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች የጎጃም የአርበኞች መሪዎች የተሰጠው ከፍተኛ ክብርና ማዕረግ ሳያስኩርፈው አልቀረም፤ ልጅ ኃይሉ በለው በራስነት ማዕረግ የጎጃም ጠቅላይ አገረ ገዥ፣ ደጃች መንገሻ ጀምበሬ ደግሞ በቢትወደድነት ማዕረግ ምክትል



ጠቅላይ አገረ ገዥ ሆነው ነበር:: እሱ ያዝባቸው የነበሩትን የሞጣንና በከፊል የደብረ ማርቆስን አውራጃ ማጣቱም የበለጠ ሳያበግነው አልቀረም:: ቅሬታውንም ከአዲስ አበባና ከደብረ ማርቆስ የሚመጡትን ትእዛዞች አሻፈረኝ ብሎ ባለመቀበል ገለጸ:: በመጨረሻም በሚያዝያ 1934 ከጎጃምና ከአዲስ አበባ የተውጣጣ ጦር ግዛቱን ወረረው:: ሦስት ወር ከተዋጋ በኋላ ተሸንፎ እጁን ሰጥቶ አዲስ አበባ በእስር ቆየ:: ከጥቂት ወራት በኋላ ከእስር ቤት አምልጦ ወደ ጎጃም ሲያመራ ተያዘና እንደገና ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ተደርጎ በአደባባይ ተሰቀለ::

የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የልጅ ልጅ የነበረው ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህም እንደ በላይ በጎጃም የአርበኞች መሪ ነበር:: ከነፃነት በኋላ መጀመሪያ በምክትል ሚኒስትርነት ቀጥሎም በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት ሠርቷል:: በ1943 በንጉሠ ነገሥቱ ላይ አደመ:: በአድማው አንዳንድ ወታደራዊ መኰንኖችና በተለይም ዋና አቀናባሪው ነበር ተብሎ የሚነገርለት በቀለ አናሲሞስ የተሳተፉበት ሲሆን፣ ዓላማውም ንጉሠ ነገሥቱን ገድሎ ሬፑብሊክ ለማወጅ የነበረ ይመስላል:: አድመኞቹን ያጋለጠው እንዲሳተፍ ጥሪ ተደርጎለት የነበረው ሌላው የአርበኞች መሪ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ነው:: የሚገርመው ነገር አድመኞቹን አድብቶ እንዲይዝ ኃላፊነቱ የተሰጠው ኋላ ራሱ መፈንቅለ መንግሥት የሚመራው የያኔው ኰሎኔል መንግሥቱ ንዋይ መሆኑ ነው:: አድመኞቹም ስብሰባ ላይ እንዳሉ ተይዘው ለፍርድ ከቀረቡ በኋላ የተለያየ የእሥራት ዘመን ተፈረደባቸው::

ንጉሠ ነገሥቱ ላይ በማመፅ የብላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያትን ሬከርድ የሚስተካከል ለማሰብ እጅግ ያዳግታል:: ለሠላሳ ዓመታት ያህል ባለማወላወልና ባለመታከት ከመታገሉም በላይ ተቃውሞው የግል ቂም እንዳለው ሁሉ ከፍተኛ ምሬት ነበረው:: ነገሩ የጀመረው ንጉሠ ነገሥቱ በ1928 አገር ጥሎ በሄደበት ወቅት ነው:: ከዚያ በፊትማ በተፈሪ አልጋ ወራሽነት ዘመንም ሆነ በአፄ ኃይለ ሥላሴ አምስት ዓመት ዘመነ መንግሥቱ ታከለ ከታማኝ አገልጋዮቹ አንዱ ነበር:: የንጉሠ ነገሥቱን ስደት ግን አምሮ ነበር የተቃወመው:: ከዚህ በኋላም ኃይለ ሥላሴ ተመልሶ ሥልጣን ላይ እንዳይወጣ ማድረግ ዋና ተልእኮው ነበር:: በእንግሊዞች እርዳታ እንደገና ዙፋኑን ሲያስመልስም ንጉሠ ነገሥቱን ከዙፋን ማውረድ የሕይወቱ ዓላማ ሆነና ቀረ::

በዚህ ረገድ ታከለ አድማውን የጀመረው ነፃነት በተመለሰ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ነው:: አድማውን የቀሰቀሰውም ከላይ የጠቀስነው በመፈጠር ላይ የነበረው የባንዳዎችና የስደተኞች ኅብረት ያሳደረበት ምሬት ነው:: የታከለ ዓላማም በሕግ የታረቀ ዘውዳዊ አገዛዝን በመቀጠል ነገር ግን ኃይለ ሥላሴን አውርዶ በምትኩ ከኢያሱ ልጆች አንዱ የሆነውን ዮሐንስን ዙፋን ላይ ለማስቀመጥ ነበር:: ለዚህ ዓላማም አንዳንድ የሠራዊቱን አባሎች ለማስተባበር ችሎ ነበር:: ሆኖም አድማው ተደርሶበት መሪው ታከለም ታሰረ:: ከእስር ተለቆ ቢለዝብ ተብሎ በ1938 ምክትል አፈ ንጉሥነት ተሾመ:: እሱ ግን በዓመቱ ሌላ ሴራ ጠነሰሰ:: አሁንም ተነቅቶበት ሰባት ዓመት ታሰረ:: እንደገና ከእስር ሲፈታ ከሥርዓቱ ጋር ቢታረቅ ተብሎ በተከታታይ የአገር ግዛት ምክትል ሚኒስትርና አፈ ንጉሥ ተባለ:: በእርግጥም ለጥቂት ዓመታት አረጋዊው ታጋይ የበረደለት መሰለ:: ነገር ግን እሱ አመቺ ጊዜ መጠበቁ ኖሯል:: በ1962 የመጨረሻውን

ድራማ ተጫወተ:: በሰበታ መንገድ ንጉሡን በቦምብ ለመግደል ያጠመደው ወጥመድ ሲከሽፍበት ቤቱ መሸጎ ከፖሊሶች ጋር ተታኩሶ ሞተ::

## የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ

ከ1966 አብዮት በፊት ዙፋኑን ክፉኛ ያናጋ ተቃውሞ ቢኖር የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ነው:: ሙከራው ባይሳካም ከፍ ብለን እንደጠቀስነው በፖለቲካ ተቃውሞ ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆነ ምዕራፍ መክፈቻ ነበር:: ሙከራውን ያቀነባበሩት ሁለት ወንድማማቾች መንግሥቱና ገርማሜ ንዋይ፣ ከ1953 በፊትም ሆነ በኋላ የታየውን የተቃውሞውን ሁለት ገጽታዎች፣ ማለትም ወታደራዊና ሲቪላዊ፣ የሚያንጸባርቁ ናቸው::

ብርጋዲየር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ከ1928 በፊት በካዴትነት ይሰለጥኑ የነበሩትና ከጦርነቱ በኋላም የጥቁር አንበሳን ድርጅቶች አቋቁመው ጠላትን የተፋለሙት የወጣት አርበኞች ትውልድ አባል ነው:: ይህ ማለት ግን እነዚያ ካዴቶች ሁሉ በኋላ በፀረ ኃይለ ሥላሴ የተቃውሞ ጎራ ተሰለፉ ማለት አይደለም:: እንዲያውም ከጠላት ጥይት የተረፉት ሌሎች ጓደኞቹ በ1953ቱ ፍጥጫ መንግሥቱን ተቃውመው ከመሰለፋቸውም በላይ ለሙከራው መክሸፍ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል:: በዚህም ረገድ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ጄኔራሎች፣ ዓቢይ አበበ፣ እሰፋ አያና፣ ኢሳይያስ ገብረ ሥላሴ እና ከበደ ገብሬ ናቸው:: የነሱም አቋም እምብዛም የሚያስገርም አልነበረም:: ለኃይለ ሥላሴ ታማኝ ሆነው መጽናት በወጣትነት ዘመናቸው የገቡት ቃለ መሐላ ከመሆኑም በላይ፣ በድኅረ 1933ቱ ሥርዓት የተሾሙና የተሸለሙ ነበሩ:: የመንግሥቱ የተቃውሞ አቋምም ወደ መጨረሻው ብቅ ያለ እንጂ ሥር የሰደደ ነበር ለማለት የዳግታል::

የተቃውሞ ሪከርዱ ብዙም የማያጠያይቀው ወንድሙ ገርማሜ ነው:: በብዙ መንገድ ገርማሜ በቅድመ 1928ቱ ተራማጅ ምሁራንና በ1950ዎቹ ዓመታት ብቅ ባሉት ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ ተማሪዎች መካከል የነበረ ድልድይ ነው ማለት ይቻላል:: የአገር ቤት ትምህርቱን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ኮተቤ) ካጠናቀቀ በኋላ ወደ አሜሪካ ተጉዞ ከዊስኮንሲን ዩኒቨርሲቲ በቢኤ ዲግሪ፣ ቀጥሎ ከኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በኤም ኤ ዲግሪ ተመረቀ:: ገርማሜ ቀደም ካሉት ምሁራን የሚለየው በሁለት ነገሮች ነው:: አንደኛ ውጭ አገር ቆይቶ አንዳንድ ነገሮች ቀስሞ መመለስ ብቻ ሳይሆን መደበኛ ትምህርት ተከታትሎ ለዚህም ምስክርነት ዲግሪውን ይዞ በመመለሱ ነው:: በዚህም የወደፊቱን አቅጣጫ የሚተልም ነበር:: ሁለተኛው ደግሞ ከቀድሞዎቹ ምሁራን የላቀ የድርጅት ስሜት ማሳየቱ ነው:: አሜሪካ በነበረበት ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ኘሬዚዳንት ከመሆኑም በላይ ከተመለሰም በኋላ የኮተቤን ምሩቃን በስውር አሰባስቦ ማኅበር በማቋቋም የዚሁ ማኅበር ኘሬዚዳንት ሆኖ ተመርጧል:: ዞሮ ዞሮ ግን የቀድሞዎቹ ምሁራን ለውጥ ለማምጣት የተራማጅ መስፍንን ተገን እንደፈለጉ ሁሉ ገርማሜም የወንድሙን ሠራዊት ለዚሁ ተግባር ማዋል ነበረበት::

የመፈንቅለ መንግሥቱ ፅንሰ ሐሳብ በመሠረቱ ከመንግሥቱ ይልቅ የገርማሜ ለመሆኑ ብዙ ጠቋሚ መረጃዎች አሉ:: ትምህርቱን ጨርሶ





5.8 የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መሪዎች ከግራ ወደቀኝ ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ

በመንግሥት ሥራ ከተሰማራበት ጊዜ ጀምሮ ዓይነተኛ ባሕርዩ ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜትና መቆርቆር ነው:: መንግሥት ይህን አዝማሚያውን አልወደደለትም:: ስለዚህም በተከታታይ በስውር ግዞት የሩቅ ግዛቶች አስተዳዳሪ እየተደረገ ተሾመ፣ መጀመሪያ ወላይታ፣ ኋላ ጅጅጋ:: እሱ ግን እነዚህን የግዞት ቦታዎች የፍትሓዊ አስተዳደር ሙከራ ጣቢያዎች አደረጋቸው:: የወላይታ አስተዳዳሪ በነበረበት ጊዜ የሰፈራ ኘሮግራም በመጀመርና የጭሰኝነት ውልም በጽሑፍ እንዲሆን በመደንገግ የጭሰኛውን መከራ ከፈለለት:: በጅጅጋም የሶማሌዎቹን ሕይወት ለማሻሻል በወሰዳቸው እርምጃዎች ከፍተኛ ተወዳጅነትን አገኘ:: ሆኖም መንግሥት በዚህ በጠረፍ አስተዳደሩም ጣልቃ እየገባበት ያደናቅፈው ገባ:: ያኔ ነው ማስከሉን መለወጥ አማራጭ የሌለው ተግባር መሆኑን ተረድቶ ወንድሙን ለዚህ ዓላማ ማነሣሣት የጀመረው:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳ የገርማሜ ለውጥ ፈላጊነት የማያጠያይቅ ቢሆንም የወንድማማቾቹ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በዓላማ ግልጽነትም ሆነ በአደረጃጀት ብቃት ብዙ የጐደለው ነበር:: ይህም ጉድለት ነው ሙከራውን ለመጨናገፍ ያበቃው::

ወንድማማቾቹ ሙከራውን ለሕዝብ ሲያስተዋውቁ ለማስተላለፍ የፈለጉት ዐቢይ መልእክት ኢትዮጵያ በቅርብ ነፃ ከወጡት የአፍሪቃ አገሮች ጋር እንኳ ስትነፃፀር ምን ያህል ወደ ኋላ እንደቀረችና የመፈንቅለ መንግሥቱም ሙከራ የአገሪቱን የቀድሞ ዝናና ክብር ለማደስ መሆኑን ነው:: እንደ አሜሪካ ያሉትን የቃል ኪዳን ጓደኞች ለማረጋጋትም ይመስላል በውጭ ግንኙነት በኩል አገሪቱ ያደረገችውን ስምምነቶች እንደሚያከብሩና የአፄው መንግሥት

ድራማ ተጫወተ:: በሰበታ መንገድ ንጉሡን በቦምብ ለመግደል ያጠመደው ወጥመድ ሲከሽፍበት ቤቱ መሽጎ ከፖሊሶች ጋር ተታኩሶ ሞተ::

### የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ

ከ1966 አብዮት በፊት ዙፋኑን ክፉኛ ያናጋ ተቃውሞ ቢኖር የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ነው:: ሙከራው ባይሳካም ከፍ ብለን እንደጠቀስነው በፖለቲካ ተቃውሞ ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆነ ምዕራፍ መክፈቻ ነበር:: ሙከራውን ያቀነባበሩት ሁለት ወንድማማቾች መንግሥቱና ገርማሜ ንዋይ፤ ከ1953 በፊትም ሆነ በኋላ የታየውን የተቃውሞውን ሁለት ገጽታዎች፣ ማለትም ወታደራዊና ሲቪላዊ፣ የሚያንጸባርቁ ናቸው::

ብርጋዲዬር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ከ1928 በፊት በካዴትነት ይሰለጥኑ የነበሩትና ከጦርነቱ በኋላም የጥቁር አንበሳን ድርጅቶች አቋቁመው ጠላትን የተፋለሙት የወጣት አርበኞች ትውልድ አባል ነው:: ይህ ማለት ግን እነዚያ ካዴቶች ሁሉ በኋላ በፀረ ኃይለ ሥላሴ የተቃውሞ ጎራ ተሰለፉ ማለት አይደለም:: እንዲያውም ከጠላት ጥይት የተረፉት ሌሎች ጓደኞቹ በ1953ቱ ፍጥጫ መንግሥቱን ተቃውመው ከመሰለፋቸውም በላይ ለሙከራው መክሸፍ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል:: በዚህም ረገድ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ጄኔራሎች፣ ዓቢይ አበበ፣ አሰፋ አያና፣ ኢሳይያስ ገብረ ሥላሴ እና ከበደ ገብሬ ናቸው:: የነሱም አቋም እምብዛም የሚያስገርም አልነበረም:: ለኃይለ ሥላሴ ታማኝ ሆነው መጽናት በወጣትነት ዘመናቸው የገቡት ቃል መሐላ ከመሆኑም በላይ፣ በድኅረ 1933ቱ ሥርዓት የተሾሙና የተሸለሙ ነበሩ:: የመንግሥቱ የተቃውሞ አቋምም ወደ መጨረሻው ብቅ ያለ እንጂ ሥር የሰደደ ነበር ለማለት የዳግታል::

የተቃውሞ ሪከርዱ ብዙም የማያጠያይቀው ወንድሙ ገርማሜ ነው:: በብዙ መንገድ ገርማሜ በቅድመ 1928ቱ ተራማጅ ምሁራንና በ1950ዎቹ ዓመታት ብቅ ባሉት ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ ተማሪዎች መካከል የነበረ ድልድይ ነው ማለት ይቻላል:: የአገር ቤት ትምህርቱን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ኮተቤ) ካጠናቀቀ በኋላ ወደ አሜሪካ ተጉዞ ከዊስኮንሲን ዩኒቨርሲቲ በቢኤ ዲግሪ፣ ቀጥሎ ከኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በኤም ኤ ዲግሪ ተመረቀ:: ገርማሜ ቀደም ካሉት ምሁራን የሚለየው በሁለት ነገሮች ነው:: አንደኛ ውጭ አገር ቆይቶ አንዳንድ ነገሮች ቀስሞ መመለስ ብቻ ሳይሆን መደበኛ ትምህርት ተከታትሎ ለዚህም ምስክርነት ዲግሪውን ይዞ በመመለሱ ነው:: በዚህም የወደፊቱን አቅጣጫ የሚተልም ነበር:: ሁለተኛው ደግሞ ከቀድሞዎቹ ምሁራን የላቀ የድርጅት ስሜት ማሳየቱ ነው:: አሜሪካ በነበረበት ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ከመሆኑም በላይ ከተመለሰም በኋላ የኮተቤን ምሩቃን በስውር አሰባስቦ ማኅበር በማቋቋም የዚሁ ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆኖ ተመርጧል:: ዞሮ ዞሮ ግን የቀድሞዎቹ ምሁራን ለውጥ ለማምጣት የተራማጅ መስፍንን ተገን እንደፈለጉ ሁሉ ገርማሜም የወንድሙን ሠራዊት ለዚሁ ተግባር ማዋል ነበረበት::

የመፈንቅለ መንግሥቱ ፅንሰ ሐሳብ በመሠረቱ ከመንግሥቱ ይልቅ የገርማሜ ስለመሆኑ ብዙ ጠቋሚ መረጃዎች አሉ:: ትምህርቱን ጨርሶ





5.8 የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መሪዎች ከግራ ወደቀኝ ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ

በመንግሥት ሥራ ከተሰማራበት ጊዜ ጀምሮ ዓይነተኛ ባሕርዩ ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜትና መቆርቆር ነው:: መንግሥት ይህን አዝማሚያውን አልወደደለትም:: ስለዚህም በተከታታይ በስውር ግዞት የሩቅ ግዛቶች አስተዳዳሪ እየተደረገ ተሾመ፤ መጀመሪያ ወላይታ፣ ኋላ ጅጅጋ:: እሱ ግን እነዚህን የግዞት ቦታዎች የፍትሐዊ አስተዳደር ሙከራ ጣቢያዎች አደረጋቸው:: የወላይታ አስተዳዳሪ በነበረበት ጊዜ የሰፈራ ፕሮግራም በመጀመርና የጭሰኝነት ውልም በጽሑፍ እንዲሆን በመደንገግ የጭሰኛውን መከራ ከፈለለት:: በጅጅጋም የሶማሌዎቹን ሕይወት ለማሻሻል በወሰዳቸው እርምጃዎች ከፍተኛ ተወዳጅነትን አገኘ:: ሆኖም መንግሥት በዚህ በጠረፍ አስተዳደሩም ጣልቃ እየገባበት ያደናቅፈው ገባ:: ያኔ ነው ማዕከሉን መለወጥ አማራጭ የሌለው ተግባር መሆኑን ተረድቶ ወንድሙን ለዚህ ዓላማ ማነሣሣት የጀመረው:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳ የገርማሜ ለውጥ ፈላጊነት የማያጠያይቅ ቢሆንም የወንድማማቾቹ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በዓላማ ግልጽነትም ሆነ በአደረጃጀት ብቃት ብዙ የጐደለው ነበር:: ይህም ጉድለት ነው ሙከራውን ለመጨናገፍ ያበቃው::

ወንድማማቾቹ ሙከራውን ለሕዝብ ሲያስተዋውቁ ለማስተላለፍ የፈለጉት ዐቢይ መልእክት ኢትዮጵያ በቅርብ ነፃ ከወጡት የአፍሪቃ አገሮች ጋር እንኳ ስትነፃፀር ምን ያህል ወደ ኋላ እንደቀረችና የመፈንቅለ መንግሥቱም ሙከራ የአገሪቱን የቀድሞ ዝናና ክብር ለማደስ መሆኑን ነው:: እንደ አሜሪካ ያሉትን የቃል ኪዳን ጓደኞች ለማረጋጋትም ይመስላል በውጭ ግንኙነት በኩል አገሪቱ ያደረገችውን ስምምነቶች እንደሚያከብሩና የአፄው መንግሥት

የሚከተለውን ፖሊሲም እንደሚቀጥሉ ማረጋገጫ ሰጡ፡፡ የሰፊው ሕዝብ ብሶት የቀረቀራቸው መሆኑን በመግለጽም ፋብሪካዎች ለማቋቋምና ትምህርት ቤቶች ለመክፈት ቃል ገቡ፡፡ ይሁን እንጂ ሰፊውን ሕዝብ ባንደኛ ደረጃ የሚመለከተውን የመሬት ጥያቄ በአግባቡ አላተኮሩበትም፡፡ የመፈንቅለ መንግሥቱ መግለጫ የእርሻ ምርትን ለማሳደግ ተስፋ ከመስጠቱ በስተቀር መሠረታዊውን የሥሪት ጉዳይ ከቶም አላነሣውም፡፡ አልጋ ወራሹን አስፋ ወሰንን አግባብተው (አስገድደውም ይባላል) መንግሥት በቀረጠለት ደመወዝ ለሕገ መንግሥት የሚገዛ ንጉሥ ሆኖ እንደሚያገለግል በሬዲዮ መልእክቱን ለሕዝብ እንዲያስተላልፍ አደረጉ፡፡ በታኅሣሥ 5፣ 1953 በለውጥ ፈላጊው መስፍን በራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚመራ መንግሥት ሲቋቋም፣ ተወዳጁ ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊም የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም ሆኖ ተሰየመ፡፡ የወታደሮች ደመወዝም ከፍ እንደሚል ቃል ተገባ፡፡

የአመፁ መሪዎች ዐቢይ ስሕተት ዋና ዋናዎቹን የጦር ኃይል አካሎች፣ በተለይም የምድር ጦሩንና የአየር ኃይሉን፣ ለማሳተፍ አለመቻላቸው ወይም አለመሞከራቸው፣ አልያም ሳይቀደሙ ቀድመው ከጥቅም ውጭ አለማድረጋቸው ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ ያቀጣናል ብለው የተለሙት ዘዴ እውነተኛ ዓላማቸውን በመሰወር የመንግሥቱን ባለሥልጣኖች ጦር ሠራዊቱ ከድቷል ብለው ለማሳመን መሞከርን ነው፡፡ ሚኒስትሮችንና ሌሎቹን የሥርዓቱን ቁንጮዎች እየለቀሙ ሲያስሩ የሰጧቸው ማረጋገጫ ጦር ሠራዊት ስላመፀ ለራሳቸው ጥበቃ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ግፋ ቢል የማዘናጊያ ዘዴ እንጂ ለዓላማቸው መሳካት ምንም እርባና አላመጣም፡፡ ወዲያውኑም የጦር ሠራዊቱና የአየር ኃይሉ የተባበረ ተቃውሞ ገጠማቸው፡፡ የንጉሡ አማችና በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ የነበረው ጄኔራል ዐቢይ አበበ በደቡብ አሜሪካ ጉብኝት በማድረግ ላይ የነበረውን ንጉሠ ነገሥት ከታማኝ ጄኔራሎቹ ጋር በማገናኘት ቁልፍ ሚና ተጫወተ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱም ጉብኝቱን አቋርጦ አደጋ ላይ የወደቀውን ዙፋኑን ለማዳን ወደ አገሩ ገሰገሰ፡፡ ፓትርያርኩም አማፅያኑን በማውገዝ የቤተ ክህነትን የማይናቅ ድጋፍ ከታማኞቹ ጀርባ አሠለፈ፡፡ አሜሪካኖች በበኩላቸው ሁኔታውን ለማጤን ጥቂት ጊዜ ከወሰዱ በኋላ ድጋፋቸውን እንዲሁ ለታማኞቹ ሰጡ፡፡ ይህን የተባበረ ኃይል ለመቋቋም የክብር ዘበኛና በብርጋዴር ጄኔራል ፅጌ ዲቡ የሚመራው የፖሊስ ሠራዊት ብቻ በግልጽ ብቁ አልነበሩም፡፡

ይህ የኃይል አሰላለፍ አስደንግጧቸውም ይመስላል የተኩስ ልውውጥ እንደተጀመረ ብዙም ሳይቆይ አማፅያኑ ተኩስ ለማቆም ዝግጁነታቸውን ገለጹ፡፡ ታማኞቹ ግን ድል ሩቅ አለመሆኑን ስለተረዱ አሻፈረኝ አሉ፡፡ የፈለጉትንም ድል ከሁለት ቀን ጦርነት በኋላ አገኙ፡፡ የአመፁ መሪ የሆኑት ሁለቱ ወንድማማቾች ነገሩ እንዳልሠመረላቸው ሲያውቁ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (የአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ሕንፃ) አጉረዋቸው የነበሩትን መሳፍንትና መኳንንት ረሽነው ከአዲስ አበባ ለመውጣት ሽሽታቸውን ጀመሩ፡፡ እነሱ ከተማይቱን ለቀው ሲወጡ ንጉሠ ነገሥቱ በድል ወደ መናገሻ ከተማው ገባ፡፡ ካላወቁት መልአክ ያወቁት ሰይጣን ይሻላል በሚለው ዘይቤም ይመስላል ሕዝቡ በዕልልታ ተቀበለው፡፡ የለውጡ መሪዎች እየታደኑ አለቁ፡፡ ከሁለቱ ወንድማማቾች ጋር ሆኖ መፈንቅለ መንግሥቱን በማስተባበር ከፍተኛ ድርሻ የነበረው የፀጥታው ኃላፊ ሌተና ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ራሱን ገደለ፡፡ ገርማሜ ዝቋላ አካባቢ ከሚያድኑት ፖሊሶችና ወዶ ዘማቾች ጋር ተታኩሶ ሞተ፡፡ መንግሥቱ እዚያው ላይ ክፉኛ ቆስሎ ተይዞ ከመጣ በኋላ ለፍርድ ቀርቦ በስቅላት ተቀጣ፡፡



ንጉሠ ነገሥቱም ፍርዱን ከሰጠ በኋላ እሮይ ብሎ እንደቀድሞው ለመግዛት ዙፋኑን አደላደለ፡፡ በሱ አስተሳሰብ መፈንቅለ መንግሥቱ የጥቂት ውስታ ቢሶች ሤራ እንጂ ማኅበራዊ መሠረት ያለው የለውጥ እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡ ስለዚህም ዋና ተግባር አድርጎ ያየው ዙፋኑን የጠበቁለትን ታማኞች መሸምና መሸለም እንጂ አማፅያኑ የጠቆሟቸውን ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮች ለመፍታት አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ የለውጥን ሰዓት ጠምዞ ወደ ቀድሞ ቦታው መመለስ ያዳግታል፡፡ አንደኛ ነገር ሠራዊቱን ማስታገስ ያስፈልግ ነበር፡፡ አማፅያኑ የሠራዊቱን ደመወዝ እንደሚጨምሩ ቃል ሲገቡ ይህንን ለማጨናገፍ ታማኞቹም ተመሳሳይ ተስፋ ሰጥተው ነበር፡፡ የቀድሞው ሥርዓት እንደገና ሲመለስም ሠራዊቱ ያንን የተገባለትን ቃል በማያወላዳ መንገድ ለመንግሥት አስታወሰ፡፡ መንግሥትም ከረጅም ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የወታደሮችንና የመኰንንኖችንም ደመወዝ ከፍ ማድረግ ነበረበት፡፡ ይህ የደመወዝ ጭማሪ ግን የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አልሆነም፡፡ ወታደሩ ጡንቻውን እንዲህ ከለካ በኋላ ወደፊትም ይህን መሣሪያ ሊጠቀምበት እንደሚችል ተረድቶ አደፈጠ፡፡

አማፅያኑ ቢወገዱም ያቀጣጠሉት የለውጥ ችቦ ከነሱ ጋር አልጠፋም፡፡ እንዲያውም በመንግሥት ላይ የሚታየው ተቃውሞ ይበልጥ እየከረረና ይበልጥ ድፍረት እያገኘ መጣ፡፡ ይህንንም በመፈንቅለ መንግሥቱ ማግስት በኅቡእ ይወጡ የነበሩትን በራሪ ወረቀቶች በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ ወረቀቶች የሚከተሉትን ዓይነት የማያወላውል አቋም የሚያንጸባርቁ መፈክሮች ያዘሉ ነበሩ፤ «አንድ ሺህ ቀኖች በግ ሆኖ ከመኖር አንድ ቀን አንበሳ ሆኖ መሞት ይሻላል»፣ «ካለ ደም ስርየት የለም»፣ «ለአመፀኞች መገዛት ኃጢአት ሲሆን በአመፀኞች ላይ ማመፅ የተቀደሰ ሥራ ነው»፣ «የታኅሣሥ ሰማዕታት አልሞቱም፤ እሱ በሕይወት»፡፡ በተለይም ተማሪዎች የአማፅያኑ ሐቀኛ ወራሾች ሆኑ፡፡ በ1953 ፈራ ተባ እያሉም ቢሆን አማፅያኑን በመደገፍ ሰልፍ ወጥተው ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ አማፅያኑ ብዙም ባልተደራጀ መንገድ ለጀመሩት ተቃውሞ ስፋትና የሐሳብ ጥራት በመስጠት ሥርዓቱን መጋፈጥ ጀመሩ፡፡ ሥርዓቱም የማሻሻያ ለውጥ ለመቀበል ዝግጁ ባለመሆኑ ዕጣው በአብዮት ጎርፍ ተጠራርጎ መውደም ሆነ፡፡

## የገበሬዎች አመፅ

በሥርዓቱ ላይ የተነሣው ተቃውሞ በመኳንንቱና በምሁራኑ የተወሰነ አልነበረም፡፡ በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች የተነሣሣው የገበሬዎች አመፅ ይህን ተቃውሞ ሰፋ ያለ መልክ ሰጥቶታል፡፡ እነዚህ አመፆች ቀደም ባሉት ዘመናት ከነበሩት የከረሩና ተደጋጋሚም በመሆናቸው ገበሬው ምን ያህል እየተገፋ መምጣቱን የሚጠቁሙ ነበሩ፡፡ ይሁንና አመፆቹ የተለያየ ባሕርያት ያሳዩ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ በጥቂት ቀን ሲቀጩ ሌሎቹ መንግሥቱን ለዓመታት ወጥረው ይዘውት ነበር፡፡ አንዳንዶቹ የግብታዊነት ባሕርይ ሲያሳዩ ሌሎቹ ደግሞ ይበልጥ የተደራጀ መልክ ነበራቸው፡፡ ከዚህም በላይ አመፆቹ የውጭ ኃይላት የተጫወቱት ሚናና መንግሥትም እነሱን ለመቋቋም ባሳየው የከረረ ወይም ዘብ ያለ አቋም ይለያያሉ፡፡

ከነዚህ አመፆች መጀመሪያ የተከሰተው በነፃነት ማግሥት በትግራ ጠቅላይ ግዛት የተቀሰቀሰው የወያኔ አመፅ ነው። ከመነሾ ምክንያቶቹ አንዱ ከነፃነት በኋላ ባሉት ጥቂት ዓመታት ማዕከላዊው መንግሥት ገና ያልተደላደለ በመሆኑና ጣልያኖች ትተውት የሄዱት የጦር መሣሪያም ለመሸፈት ላሰበ ሰው የሚጋብዝ መሆኑ ነው። በስፋት ይታይ የነበረው የአስተዳደር ጉድለትና ምዝበራም ይህን የሸፍትነት ስሜት ወደ ፖለቲካ አመፅ ለወጠው። በሌላ በኩል ደግሞ ከ1928 በፊት በተለይ በራያና አዘቦ ሕዝብና በማዕከላዊው መንግሥት መካከል የነበረው ደም መቃባትም አንድ ሌላ አስተዋፅኦ ነበረው። ያኔ እንደሆነው ሁሉ፣ አሁንም አመፁን የለኮሰው የራያና አዘቦ ሕዝብ በአፋሮች ላይ ያደረገው ዝርፊያ የማዕከላዊውን መንግሥት የበቀል እርምጃ ማስከተሉ ነው። በመጨረሻም ከ1881 ጀምሮ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ማዕከል የነበረው የትግሬ ግዛት ዳርቻ በመሆኑ፣ ክብሩና ጥቅሙ የተጓደለባቸው የትግራይ መሣፍንት የነበረውን አጠቃላይ የአመፅ ስሜት ለፖለቲካ ዓላማቸው ተጠቅመውበት ነበር ማለት ይቻላል።

አማፅያኑ የመጀመሪያ ድላቸውን የተጎናጸፉት በግንቦት 14፣ 1935 በተምቤን አውራጃ አዲ አቡን በተባለ ስፍራ ነው። ከዚያም በማከታተል መቀሌ አጠገብ የሚገኙትን ቅዊሓንና እንዳ ኢየሱስን፣ በመጨረሻም የጠቅላይ ግዛቱን ዋና ከተማ መቀሌን ራሷን ያዙ። ለአመፁ መሳካት አንዱ ምክንያት የሕዝቡን ቅሬታ ሃይማኖታዊ ርእዮት በመስጠት ማስተባበር የቻለው የብላታ ኃይለማርያም ረዳ አመራር ነው። የአመፁ ስፋትና እድገት መንግሥትን ክፉኛ ስላስደነገጠው መንግሥት በአርበኝነት ዘመን ስመ ጥር ተዋጊነትን ያተረፈውን ራስ አበበ አረጋይን የጦር አዝማች አድርጎ ላከ። ከዚያም በላይ የእንግሊዞችን ዕርዳታ በመጠየቁ፣ በተለይም የእንግሊዝ የጦር አውሮፕላኖች ያደረሱት ጥቃት በ1936 መስከረም ወር መጨረሻ ላይ የወያኔውን ጦር ፈታው።

የሚቀጥለው የገበሬዎች አመፅ የተከሠተው ከሃያ ዓመታት በኋላ ነው። እሱም በባሌ የተነሣውና ሰባት ዓመት ያህል የቆየው ጦርነት ነው። ትግራይ ውስጥ ከነበረውም ሁኔታ በበለጠ የባሌ አመፅ ዋና መነሾ በገበሬዎች ላይ የደረሰው ግፊት ነው ማለት ይቻላል። በ1940ዎቹ አጋማሽ ላይ ቀላድ ሲጣል አያሌ ገበሬዎች ለጭሰኝነት ተዳረጉ። መሬት መስፈር ከተጀመረ በኋላ እያደገ የመጣውን ግብር አብዛኛዎቹ ገበሬዎች መክፈል ስላቃታቸው ዕጣቸው መሬታቸውን ማስረከብ ሆነ። ሁኔታውን ያባባሰው ሌላ ጉዳይ ደግሞ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ብዛትና በዝባዥነት ነው። በተጨማሪም በአብዛኛው የእስልምና ተከታይ በሆነው ሕዝብ መሀል ክርስቲያን ሰፋሪዎች ማስፈሩ የሃይማኖት ቅራኔንም ፈጠረ። የነዚህ መጤ ሰፋሪዎች የፖለቲካና የኤኮኖሚ የበላይነት የፈጠረው የማን አለብኝ ስሜት በተለይ ፊታውራሪ ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ የጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ሆኖ በ1955 ሲሾም ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ። አመፁንም ያቀጣጠለው ይህ ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል።

ሶማሌዎችንና ኦሮሞዎችን ያስለፈው አመፅ የእስልምናን ርእዮት ያነገበ ነበር። ከዚያም ባሻገር አመፁ ጽናትም ስፋትም ሊያገኝ የቻለበት ሌላ አጋጣሚ ወደዚህ አካባቢ ለመስፋፋት ቋሚ ዓላማ ላለው ለሶማሌ መንግሥት አመቺ መሣሪያ ሆኖ መገኘቱ ነው። እንዲያውም ከዚሁ ዓላማቸው እንዲጣጣም ሱማሌዎች እንቅስቃሴውን የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ግንባር የሚል ስያሜ ሰጥተውት ነበር። አመፁ የጀመረው ባብዛኛው የሱማሌ ብሔረ ሰብ ተወላጆች



በሚኖሩበት በኤልከሬ አውራጃ ነው። የሚመራውም ልጁ ግብር ባለመክፈሉ ሲታሰርበት በሸፈተው በካህን ዓብዲ ነበር። ወዲያውኑ አመፁ ወደ ሌሎች አውራጃዎች (ዋቤ፣ ደሎና ገናሌ) ተዛመተ። አዳዲስ መሪዎችም ተፈጠሩ። ከነዚህም ዝነኛ ሊሆን የበቃው በአካባቢው የምዕራብ ሶማሊያ ጄኔራል ተብሎ የታወቀው ዋቆ ጉቱ ነው። እሱም ሶማሊያን ከመጐብኘቱም በላይ መሣሪያና የጦር ሥልጠና ከሚሰጡት ሶማሌዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው።

መንግሥት በመጀመሪያ አመፁ በሰላም የሚበርድበትን መንገድ የፈለገ ይመስል ነበር። ለሌላ ግለሰብ እስካልተላለፉ ድረስ የተወረሱ መሬቶችን ለቀድሞ ባለቤቶች ለመመለስ ቃል ገባ። ያገሬውን መኳንንት ለማባበልም ለባላባቱ ሢሦ መሬት ሰጠ። ነገር ግን አመፁ በዚህ የማይመለስ ሆኖ በተለይም በተከታታይ የሁለት አውራጃ ገዥዎች ሕይወት ሲያጠፋ፣ መንግሥትም ጦርነት ዐወጀ። በታኅሣሥ 1959 በጠቅላይ ግዛቱ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ ዓዋጅ ዐውጆ ለአራተኛ ክፍለ ጦር አዛዡ ለጄኔራል ጃጋማ ኬሎ ሙሉ ሥልጣን ሰጠው። ቀጥሎም የጦር ሠራዊት፣ ፖሊስ፣ የገጠር ሚሊሺያ፣ ነጭ ለባሽና ወዶ ዘማቾችን ያስተባበረ ከፍተኛ ጦር በአማፅያኑ ላይ አዘመተ። በዚህ ከፍተኛ ግፊት ተገደው አማፅያኑ ደጀናቸው ወደ ነበረው ወደ ሶማሊያ ድንበር ሲያፈገፍጉ፣ ሶማሌዎችም በ1962 በራሳቸው አገር በተፈጠረው ለውጥ ተውጠው ስለነበር እርዳታ ሊያረጉላቸው ዝግጁ አልነበሩም። በዚሁም አመፁ ተበትኖ መሪው ዋቆ ጉቱም በመጋቢት 1962 እጁን ሰጠ።

መንግሥት የባሌን አመፅ ለማክሸፍ በመሯሯጥ ላይ እያለ በጎጃም ደግሞ ሌላ አመፅ ተቀሰቀሰ። ማዕከላዊው መንግሥት በዚያ ጠቅላይ ግዛት ላይ የነበረው ቁጥጥር ለረጅም ጊዜ የላላ ነበር። ከነፃነት ወዲህ መንግሥት ከጠቅላይ ግዛቱ ግብር ለመሰብሰብ እንኳ የቻለበት ወቅት ጥቂት ነው። የተሰበሰበውም በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሣ የጠቅላይ ግዛቱን የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ እንኳ መሸፈን አልቻለም። በ1942 እንደራሴ ሆኖ የተሰየመው ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ይህን ሁኔታ ለመለወጥ በመሻት እስከዚያን ጊዜ ድረስ ይሠራበት የነበረውን የቅድመ 1928 የግብር ተመን ከፍ አደረገ። በተጨማሪም ግብር ለመወሰን እንዲያመች መሬት ገምግሞ ደረጃ የማውጣት ፖሊሲ ጀመረ። ጎጃሜዎች ግብር መጨመሩን ከመጥላታቸውም በላይ፣ ለመሬት ደረጃ ማውጣቱ የተጠላውንና የተፈራውን የቀላድ ሥርዓት ለመጫን መንገድ መጥረግ ነው ብለው ተጠራጠሩ። በዚህ ሁኔታ ነው በሞጣ፣ በቆላ ደጋ ዳሞትና በሜጫ አውራጃዎች አመፁ የተቀጣጠለው። ንጉሠ ነገሥቱም አመፁን ለማብረድ አዲሱን የግብር ተመን በሢሶ ከመቀነሱም በላይ ከበደ ተሰማን ሽሮ ያገሬውን ተወላጅ ኃይሉ በለውን እንደራሴ አርጎ ለመሾም ተገደደ።

ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቈ ሥላሴ እንደራሴ ሆኖ ሲሾም ያገሬው አመፅ እንደገና አገረሸበት። ፊትም ቢሆን አገሬው በደጃች ከበደ ተሰማ የነበረው አንዱ ቅሬታ የሸዋ ተወላጅ መሆኑ ነው። አሁን ደግሞ ፀሐዩ ሸዋ ከመሆኑም በላይ ወንድሙ ወርቁ ዕንቈ ሥላሴ በባሌ እንዳደረገው ሁሉ ግፍና ደንታቢስነት የመላበት አስተዳደር መሠረተ። ራሱን በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ከማስወደድ በስተቀር ለሕዝቡ ምንም የማይጠቅመውን የንጉሠ ነገሥቱን ሐውልት አሠራለሁ ብሎ ሕዝቡ መዋጮ እንዲያደርግ አስገደደ። ሽፍትነትን አጠፋለሁ ብሎ በሕዝቡ ላይ ነጭ ለባሾችን መረን ለቀቀ። ንጉሠ ነገሥቱ

የጀመረውን የማረጋጋት ፖሊሲ ሽሮም ውዝፍ ግብር ከነመቀጫው እንዲከፈልና የጦር መሣሪያም እንዲመዘገብ ደንብ አወጣ።

በመጨረሻ የ1960ን አመፅ ያቀጣጠለው አዲሱን የእርሻ ገቢ ታክስ ሥራ ላይ ለማዋል መንግሥት የወሰደው እርምጃ ነው። አገሬው ከዚያ በፊት ከተወሰዱት እርምጃዎች ሁሉ አዲሱን ታክስ ሲወርድ ሲዋረድ ለመጣው የርስት መሬት ስሪት ጠንቀኛ ሆኖ አገኘው። ስለዚህ የአዲሱን ግብር መጠን ለመተመን የተላኩትን ገማቾች በመቃወም ለንጉሠ ነገሥቱ ያቤቱታ ድምፁን አሰማ። መልስ ሲያጣም አምፆ ተነሣ። ያመፁ እምብርት ሞጣና ደጋ ዳሞት ሲሆን፣ ከመሪዎቹም መካከል ለራሳቸው የልዑልና የፊታውራሪ ማዕረግ የሰጡ የቀድሞ አርበኞችም ነበሩበት። የታሪክ አጋጣሚ ሆነና ራሱም ስመ ጥር አርበኛ የነበረው ፀሐዩ ዕንቁ ሥላሴ ከቀድሞ የትግል አጋሮቹ ጋር ተፋጠጠ።

ከባሌው ሁኔታ ይበልጥ መንግሥት አማፅያኑን ለማስታገስ አንዳንድ እርምጃዎችን ወሰደ። ሁኔታውን ለማጥናትና ለማርገብ ኮሚቴዎች ተቋቋሙ። ከነዚህ ኮሚቴዎች አንዱ ባቀረበው ሐሳብም ንጉሠ ነገሥቱ ፀሐዩን ወደ ከፋ አዘዋውሮ ጠቅላላ የምሕረት ዐዋጅ ዐወጀ። አመፁ በዚህ ተግ አልልም ሲል ግን መንግሥት ከጦር ሠራዊት ከፖሊስና ከነጭ ለባሽ የተውጣጣ ጦር አዘመተ። በ1965 መጀመሪያ ላይም አመፁ ተገታ። ይሁን እንጂ ገበሬዎቹ ሙሉ በሙሉ አልከሰሩም። አዲሱ ግብር ከመሻሩም በላይ እስከ 1960 ድረስ የነበረባቸውን የ18 ዓመት ውዝፍ ግብርም ተማሩ። ባገሬው የተጠሉ አያሌ የመንግሥት ባለሥልጣኖችም ወደ ሌላ ሥፍራ ተዘዋወሩ።

የገበሬ አመፆች የታዩባቸው ሁለት ሌላ ቦታዎች የጁ (ወሎ) እና ጌዴኦ (ሲዳሞ) ናቸው። በየጁ ከነፃነት እስከ አብዮት ባለው ዘመን ሁለት አመፆች ተካሂደዋል። በመጀመሪያ በ1940 ገበሬዎች መሬታችንን ተገፋን ብለው አቤቱታ ቢያቀርቡም አድማጭ በማጣታቸው አምፀው ተነሡ። በቀኛዝማች መላኩ ታዬና በኡንዳ ሙሐመድ እየተመሩ የዋና ከተማውን የወልድያን እስር ቤት አጥቅተው እስረኞቹን ነፃ ለቀቁ። ኋላ አመፁ በነጭ ለባሾች ተደምስሶ መሪዎቹም በገበያ ቀን በአደባባይ ተገረፉ። እ.ኤ.አ በ1970 ዓ.ም ደግሞ የመኪና እርሻ ከአፅመ ርስታቸው ሊነቅላቸው ሲሆን ገበሬዎች እንደገና አመፁ። የዚህ የመስፋፋት ሂደት ዋና ተጠቃሚ ከሆኑት አንዱ የነበረውን ቀኛዝማች አባተ ኃይሉንም ገደሉ።

በ1952 በጌዴኦ አውራጃ የተቀሰቀሰው አመፅም እንዲሁ በእርሶ አደሩ መሬት ላይ የሚደረገውን ግፊት በመቃወም ነበር። በተለይም አውራጃው በቡና ሀብቱ የታወቀ ስለነበር ከሰሜን ለሚመጡ መኳንንትና መሳፍንት የተጋለጠ ነበር። በዚህ የመሬት ዝርፊያ ከተሳተፉት መካከል የንጉሠ ነገሥቱ የበኩር ልጅ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴም ትገኝበታለች። የዚህ ሂደት ድምር ውጤትም አያሌ የጌዴኦ ተወላጆችን ለጭሰኝነት መዳረግ ሆነ። ይህም አልበቃ ብሎ በሌሎች የደቡብ ግዛቶች እንደታየው ሁሉ የኤኮኖሚ ብዝበዛንና የፖለቲካ ጭቆናን ተከትሎ ያገሬው ሕዝብ ባህል የተናቀና የተዋረደ ነበር። በሌሎች የገበሬ አመፆች እንደታየው ሁሉ ገበሬዎቹ በመጀመሪያ ለበላይ አቤት በማለት ብሶታቸውን አቀረቡ። ምንም መልስ ሲያጡ ጭሰኛ ለባለመሬት የሚከፍለውን እርቦ አንከፍልም ብለው አደሙ። ወትሮ እንደሚደረገው ገማቾች መጥተው



እርቦውን እስከሚገምቱ ድረስ ሳይጠብቁም ቡናቸውን መልቀም ጀመሩ። ያኔ ነው ግጭቱ የጀመረው።

ግን ትግሉ ያልተመጣጠነ ነበር። አማፅያኑ ያነገቡት ጦርና ጎራዴ ባለመሬቶቹና መንግሥት የላከው ሠራዊት የታጠቀውን ዘመናዊ መሣሪያ የሚቋቋም አልነበረም። በመጀመሪያው ግጭት ከመንግሥት ወገን ሦስት ሰው ብቻ ሲሞት ከገበሬው ያለቀው ሰማንያ ስምንት ነበር። በመጨረሻ ሚቼሌ ላይ በተደረገው ጦርነትም ከመቶ በላይ የሚቆጠሩ ገበሬዎች ካለቁና ንብረታቸውም ከተወረሰ በኋላ አመፁ ተገታ። ገበሬዎቹ ሰላማዊ መስሎ በቀረበው በመንግሥት ልዑክ በአፈ ንጉሥ እሸቴ ገዳ ስለተዘናጉ ለወረደባቸው መዓት ዝግጁ አልነበሩም። በአፈ ንጉሡ የሚመራ «የእርቅ ኮሚሲዮን» ተቋቁሞም የአመፁን መሪዎች በመቅጣትና የቀድሞውን ሥርዓት በመመለስ የገበሬዎቹን ሽንፈት ፍፁምነት አረጋገጠ።

## ኤርትራ፤ ፌዴሬሽን፣ ውሕደትና የመገንጠል ንቅናቄ

የማዕከላዊውን መንግሥት በማዳከምና ኃይሉቹንም ቀሥፎ በመያዝ በኤርትራ ከ1954 ጀምሮ የተካሄደውን የትጥቅ ትግል የሚወዳደር አልነበረም። በአደረጃጀቱም ሆነ በጽናቱና ከውጭ ባገኘው ድጋፍ መንግሥትን እንደሱ ፈትኖ የያዘ አመፅ አልነበረም። ከፍ ብለው ከተዘረዘሩት ሌሎች ሕዝባዊ አመፆች የሚለየው ምንም እንኳ አብዛኛው እንቅስቃሴው እንደ ገበሬዎች አመፅ በገጠር ቢሆንም፣ አመራሩም ሆነ በርከት ያለ ተዋጊ ኃይሉ ከከተማ የንኡስ ከበርቴው መደብ የመነጨ በመሆኑ ነበር። በኤርትራ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ ለዐሥራ ሦስት ዓመት ያህል የጸናው እንቅስቃሴ በራሱ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ በኢትዮጵያ በነበረው የጸረ ሥርዓቱ ተቃውሞ ላይ ባሳደረው ተጽዕኖ ለሥርዓቱ መገርሰስ ዐቢይ አስተዋፅኦ አድርጓል። እሱም በፊናው ከዚያ ተቃውሞ ባገኘው የሞራልና የሰው ኃይል እርዳታ ሊያድግና ሊመነደግ ችሏል።

ቀደም ተብሎ እንደተገለፀው ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሐድ የተቀመመው የፌዴሬሽን ፎርሙላ እምብዛም ወዳጆች አልነበሩትም። ለአንድነት ወይም ለነፃነት ብለው በተፋላሚ ጎራ የተሰለፉት ሁለቱም ተቃራኒ ወገኖች አልተደሰቱበትም። ሁለቱም ወገኖች ቢሆኑ ይህን የፌዴሬሽን ዕቅድ ብዙም ዕድል ለመስጠት ፍላጎት አልነበራቸውም ማለት ይቻላል። ምንም እንኳ ከፌዴሬሽን በኋላ በኤርትራ አንዳንድ መዋቅሮች ተዘርግተው የእድገት ምልክት ቢታይም፣ ለነፃነት የቆሙት ተፃራሪዎቹ የፌዴራል ንብረቱን ፅልመታዊ ገጽታ በመስጠት ኢትዮጵያ በኤርትራ ኪሳራ በማደግና በመበልፀግ ላይ እንዳለች ለማሳመን ሞከሩ። የኢትዮጵያ መንግሥትም ቢሆን ለፌዴሬሽኑ የተለየ ከበሬታ አልነበረውም። በመላ ኢትዮጵያ ሰፍኖ ከነበረው የጭቆና የፖለቲካ ሥርዓት አንፃር፣ ውስጣዊ ነፃነትን የተጎናጸፈችና ባንፃሩም ቢሆን የዴሞክራቲክና የሲቪክ መብቶች የተረጋገጡባት ኤርትራ አደገኛ አርአያ ሆና ነው የታየችው።

ፈንጠቅ ያለውን የነፃነት አየር በማዳፈኑ ሂደት የማእከላዊ መንግሥት እንደራሴዎች ብቻ ሳይሆኑ በአዲሱ የኤርትራ ሕገ መንግሥት መሠረት የተመረጡት ፕሬዚዳንቶችም ተባባሪዎች ነበሩ። ለምሳሌ የአንድነት ፓርቲ ዋና

ጸሐፊና የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት የነበረው ተድላ ባይሩ ኋላ ራሱም አኩርፎ ስደት እስከሚመርጥ ድረስ ተቃዋሚ ሐሳቦችን ለማስተናገድ ዝግጁ ባለመሆኑ ሁኔታዎችን አባብሷል። በዚህ ዓይነት የፖለቲካ አየር ነው ፌዴሬሽኑ ለኤርትራ ያጎናጸፈውን መብቶች የሚሸረሽሩ እርምጃዎች መወሰድ የተጀመሩት። በመጨረሻም በኅዳር 5፣ 1955 የኤርትራ ፓርላማ የፌዴራል ስምምነቱን በማፍረስና ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ሙሉ በሙሉ እንድትቀላቀል በመወሰን ራሱን በራሱ አከሰመ።

ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ሁኔታው ያልጣማቸው ኤርትራውያን ኤርትራን ከኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ነፃ ማውጣት አለብን ብለው መታገል ጀመሩ። በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ድርጅት በ1951 የተቋቋመው የኤርትራ አርነት ንቅናቄ ነው። በጎረቤት አገሮች የተመሠረተው ይህ ድርጅት ዋናው ዓላማው የሆነውን የኤርትራን ነፃነት በፖለቲካና በዲፕሎማሲያዊ ትግል፣ በተለይም የተባበሩት መንግሥታትን በመማጠን፣ ለማስፈጸም የሚጥር ነበር። ብዙም ሳይቆይ ግን የኤርትራን ነፃነት በሰላማዊ መንገድ ሳይሆን በትጥቅ ትግል ለማምጣት የተለመው የኤርትራ ነፃነት ግንባር ተቋቋመ። ግንባሩ በመካከለኛው ምሥራቅ በስደት ላይ በሚገኙ ሙስሊም ኤርትራውያን በ1952 ተቋቁሞ ወዲያውኑ ቀድሞውኑ በሸፍትነት ተሰማርቶ በነበረው በኢድሪስ አዋቴ አዝማችነት የትጥቅ ትግሉን ጀመረ። ግንባሩ ትግሉን የነደፈው የዐረብ ሕዝቦች ትግል አካል አድርጎ በመሆኑ በዐረቡ ዓለም ከፍተኛ ድጋፍ አስገኝለት። በተለይም ሶርያና ዒራቅ ለረጅም ዓመታት የግንባሩ ዋና ደጋፊዎች ሆነው ቆዩ።

ነገር ግን ይህ የግንባሩ ዐረባዊና እስላማዊ አዝማሚያ ቀስ በቀስ በውስጡ ውጥረትና መከፋፈልን ወለደ። በጊዜው የተደራጀ ኃይል እሱ ብቻ በመሆኑ በአርማው ሥር የተሰለፉትን ሃይማኖታቸውም ሆነ አስተሳሰባቸው ለየት ያሉትን ወገኖች በቅጡ ማስተናገድ አቃተው። የግንባሩ መሠረት ከሆነው ከባርካ በመጡና ከቀይ ባሕር ዳርቻ በመጡ ተዋጊዎች፣ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች፣ እንዲሁም በተለያዩ ቀጣና እዞች መካከል ግጭት ይፈጠር ጀመር። በርካታ ክርስቲያን ነዋሪዎች ክትትሉና አፈናው ቢባባባቸው ለመንግሥት እጃቸውን ለመስጠት ተገደዱ። በዚህ ምክንያት ከግንባሩ ያፈነገጡ ሦስት ቡድኖች ተቋቋሙ፤ በባርካ አካባቢ «የኤርትራ ነፃነት ኃይሎች» (ኦቤላይት ተብለው የሚታወቁ)፣ በቀይ ባሕር አካባቢ በኦስማን ሳልህ ሳቤ የሚመራው «ሕዝባዊ አርነት ኃይሎች» እና በአካለ ጉዛይ በኢሳይያስ አፈወርቂ የሚመራው «ሰልፊ ናፅነት ኤርትራ»። ከዚያም በ1964 ሦስቱ ቡድኖች ግንባር ፈጥረው «የኤርትራ ነፃነት ሕዝባዊ ኃይሎች» የሚል ድርጅት አቋቋሙ። ይህም በሚቀጥለው ዓመት «የኤርትራ ሕዝባዊ አርነት ግንባር (ሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ)» ተብሎ እንደገና ተደራጀ።

እንግዲህ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወደ መውደቂያው ሲቃረብ በኤርትራ ምድር ለኤርትራ ነፃነት ቆሚያለሁ የሚሉ ሁለት ተፃራሪ ድርጅቶች ነበሩ ማለት ነው፤ የኤርትራ አርነት ግንባር እና የኤርትራ ሕዝባዊ አርነት ግንባር፣ ወይም በዐረብኛ አጠራራቸው ጀብሀና ሻዕቢያ። የሁለቱ ልዩነት ከአመለካከትም አልፎ ብዙ ደም ያፋሰሰ ነበር። እንዲያውም ከ1964 እስከ 1966 ባሉት ዓመታት ድርጅቶቹ ለበላይነት ሲፎካከሩ ከመንግሥት ወታደሮች ጋር ውጊያ ከማድረግ ይልቅ የርስ በርስ ጦርነት እያካሄዱ ነበር ማለት ይቻላል። ብዙውን ጊዜ የሁለቱ ግንባሮች ልዩነት ርእዮተ ዓለማዊ ወይም ሃይማኖታዊ እንደሆነ ሲወሳ ቆይቷል። ጀብሀ የሙስሊሞች፣ ሻዕቢያ የክርስቲያኖች፣ ሻዕቢያ ማርክሳዊ ሌኒናዊ፣ ጀብሀ ከዚህ የተለየ እንደሆኑ ተደርጎም ተገልጿል። ሐቁ ግን እንዲህ ቁልጭ ያለ አልነበረም። ክርስቲያን የሆኑ የጀብሀ ተዋጊዎች እንደነበሩ ሁሉ ሙስሊም የሆኑ የሻዕቢያ ተዋጊዎችም ነበሩ። በጀብሀ ውስጥ ማርክሲስቶች እንዳልታጡ ሁሉ ሻዕቢያንም ሙሉ በሙሉ እንደ ማርክሲስት ድርጅት አድርጎ ማየቱ የተሳሳተ ነው። ብዙውን ጊዜ በፖለቲካ ትግል እንደሚከሰተው ሁሉ የሁለቱ ድርጅቶች ልዩነት መሠረቱ ከርእዮት ይልቅ የሥልጣን ሽሚያ ነበር ማለት ይቻላል።



### የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ

ለሥርዓቱ ከፍተኛ ፀር የሆነው ግን ከገበሬውም ሆነ ከብሔርተኛው ይበልጥ ተማሪው ነበር። ተማሪዎቹ በመንግሥቱ ላይ ከነበራቸው የከረረና የማይለዝብ ተቃውሞ ሌላ፣ እንቅስቃሴያቸው በከተማ ውስጥ በመሆኑ ሥርዓቱን በብርቱ ፈትነውት ነበር። የገጠር አመፅ፣ የቱን ያህልም የተደራጀና የፀና ቢሆን፣ ትኩረት ስቦ፣ በሚያገኘውም ትኩረት ይበልጥ ዳብሮ የመቀጠል ችሎታው አነስተኛ ነበር። የተማሪዎቹ ግን የተለየ ነው። ከ1957 ጀምሮ በየዓመቱ ማለት ይቻላል ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ሌሎች ዜጎችን ፀጥ ለጥ አርጎ ለመግዛት የቻለውን መንግሥት በብርቱ ፈተኑት። የማይበገሩ የለውጥ ተፋላሚዎች በመሆናቸውም ከማንኛውም የኅብረተሰቡ አካል ይልቅ ያለፈው ሥርዓት ቀባሪና የኢትዮጵያ አብዮት አንቀሳቃሽ ሞተር ለመሆን በቁ።

ከ1933 በኋላ በኢትዮጵያ የትምህርት ተቋሞች መጠነኛ እድገት ማሳየት ችለዋል። ምንም እንኳ ሙሉ በሙሉ የአገሪቱ የትምህርት ፍላጎት ሊረካ ችሎ ነበር ባይባልም፣ ከ1928ቱ ጦርነት በፊት ካለው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር የትምህርት ስርጭት ጉልህ የሆነ መሻሻል አሳይቷል። በ1960ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ጠቅላላ የተማሪው ብዛት 700,000 ደርሶ ነበር። እነዚህን ተማሪዎች የሚያስተናግዱት ትምህርት ቤቶች ግን በሙሉ በመንግሥት የተቋቋሙ አልነበሩም። አያሌ የሚሲዮንና የግል ትምህርት ቤቶች ከመከፈታቸውም በላይ እያደር በሕዝቡ መዋጮ የሚሠሩት ትምህርት ቤቶች ቁጥርም እየተበራከተ መጣ። ከዚህም በተጨማሪ እንደ ስዊድን ዓለም አቀፍ ተራድኦ (ሲዳ) ያሉ የውጭ አገር ድርጅቶች በተለይ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በመሥራት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ነገር ግን የትምህርት እድል ከቀድሞው እየሰፋ ቢመጣም አንዳንድ ጉልህ ድክመቶች ይታዩበት ነበር። ለምሳሌ የወንድና የሴት ተማሪዎች ቁጥር ሲነፃፀር የሴቶቹ እጅግ ያነሰ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት ተቋሞች ስርጭት ግልጽ የሆነ አድልዎ ይታይበት ነበር። አብዛኛዎቹ ተቋሞች የሚገኙት በአዲስ አበባና ከዚያ ቀጥሎ በኤርትራና በሸዋ ነበር። ተማሪዎች ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው ለመውጣት ተገደዋል። በተጨማሪም ለቀለም ትምህርት እንጂ ለሙያ ትምህርት ብዙም ትኩረት አልተሰጠውም። ይህን ሁኔታ ለማስተካከል ተብሎ በ1964 የተነደፈው ሁለገብ የሆነ የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ እቅድም ደህውን አቋርቁዞ ለማስቀረት የተረቀቀ ሴራ ነው የሚል ተቃውሞ ስለተነሣበት መክኖ ቀርቷል።

የድኅረ 1933 የትምህርት ስርጭት አንደኛው በጎ ገጽታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሥረት ነው። ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በሀገሪቱ ሕይወት ውስጥ የጎላ ስፍራ ለመያዝ የበቁት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደጃ ት/ቤት (ኮተቤ) እና የጀኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ናቸው። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ የ2ኛ ደረጃ የአዳሪዎች ት/ቤት ከመሆናቸው ባሻገር ሀገሪቱን ለማስተዳደር የተመለመሉትን አዲሶቹን መኳንንትም ያፈሩ ናቸው። የኮተቤ 2ኛ ደጃ ት/ቤት በጣልያን ጊዜ የእርሻ ምርምር ማዕከል የነበረውን ሕንጻ በመውረስ በ1935 የተቋቋመ ሲሆን፣ ከቤተ መንግሥት ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበረው። እንዲያውም የት/ቤቱ ምግብ ማብሰያ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለተማሪዎች ምግብ የሚቀርብላቸው ከቤተ መንግሥት ነበር። የትምህርት አሰጣጡ የእንግሊዝን ሥርዓት የተከተለ ሲሆን ዲሬክተሮቹ ባብዛኛው ካናዳውያን ነበሩ። ይበልጡኑ የእንግሊዝን ሞዴል የተከተለው የጀኔራል ዊንጌት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ደግሞ የተቋቋመው በ1938 በትምህርት ሚኒስቴርና በብሪቲሽ ካውንስል ተራድኦ ነው።

ከፍተኛ ትምህርት በኢትዮጵያ የተጀመረው በ1943 የአርትስና የሳይንስ ፋኩልቲዎችን ያቀፈው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሲመሠረት ነው። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ በተከታታይ የመሀንዲስ ኮሌጅና የሕንጻ ኮሌጅ በአዲስ አበባ፣ የእርሻ ኮሌጅ በዓለማያ፣ የጤና ጥበቃ ኮሌጅ በጎንደር ተከፈቱ። በ1953 እነዚህን የተለያዩ ኮሌጆችና ፋኩልቲዎች ጠቅሎ እንዲያስተዳድር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (ከአብዮት በኋላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተባለው) ተመሠረተ። ዩኒቨርሲቲው ከተመሠረተ በኋላ ሌሎች ተጨማሪ ኮሌጆችና ፋኩልቲዎች (የማኅበራዊ ሥራ፣ የንግድ አስተዳደር፣ የሕግና የሕክምና) በዚሁ በዩኒቨርሲቲ መዋቅር ሥር ተከፈቱ። የተማሪውን ብዛት በተመለከተም በ1942 ሰባ አንድ የነበረው ቁጥር በ1965 የማታ ተማሪዎችን ጨምሮ ወደ አሥር ሺ አድጎ ነበር። ለድኅረ ምረቃ ትምህርት ግን አሁንም ተማሪዎች ወደ ውጭ አገር በተለይም ወደ አሜሪካ መሄድ ነበረባቸው። ለምሳሌ በ1962 በአሜሪካ ድኅረ ምረቃ ትምህርት የሚከታተሉት ኢትዮጵያውን ቁጥር ሰባት መቶ ነው ተብሎ ይገመት ነበር።

የዚህ ትምህርት መስፋፋት ውጤት የሆነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች አልፏል። መጀመሪያ የምሁራን የባህልና የምርምር መድረክነት ባሕርይ የነበረው ሁኔታ በ1950ዎቹ መጨረሻና በ1960ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊሆን ችሏል። የንቅናቄው ዓይነተኛ ባሕርይ እያደር እየከረረ የሚሄድ የፀረ ሥርዓት ተቃውሞ ነው። ለዚህም አጋዥ የሆኑ ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች ነበሩ። በመጀመሪያ የአገሪቱ ሁኔታ በተለይም የገጠሩ እርሶ አደርና የከተማው ሠርቶ አደር የኑሮ ደረጃ እየከፋ መምጣቱ የዚህ የከረረ ተቃውሞ ነባራዊ መሠረት ነው። መንግሥት ንቅናቄውን ለማፈን የሚወስዳቸውም እርምጃዎች ተማሪዎቹን ይበልጥ እልህ አስገባቸው። የተማሪ ተቃውሞና የመንግሥት አፈና እርስ በርስ እየተፋጩ መጥተው በመጨረሻም የ1966ቱን አብዮት ወለዱ።

በኅሊናዊ ደረጃ፣ ተማሪዎች የኅብረተ ሰባቸውን ኋላ ቀርነት የበለጠ እንዲገነዘቡና ለሥር ነቀል ለውጥ እንዲታገሉ የተለያዩ ምክንያቶች ገፋፏቸው። ከ1951 ጀምሮ የልዩ ልዩ የአፍሪቃ አገር ተማሪዎች የነፃ ትምህርት እድል



በማግኘት ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በኢትዮጵያውያኑ ተማሪዎች አስተሳሰብ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ አስከተለ። በተመሳሳይ መንገድም ተማሪዎቹ ፈራ ተባ እያሉ የደገፉት የ1953ቱ መፈንቅለ መንግሥት ምንም እንኳ ቢጨናገፍ መለኮታዊ ባሕርይ ተጎናጽፎ የቆየውን ንጉሣዊ ሥልጣን በመድፈሩ ዐይን ገላጭ ነበር። የነመንግሥቱ ንዋይን ዱካ ተከትለውም፣ ተማሪዎች በሥርዓቱ ላይ ለተነሣሣው ተቃውሞ ስፋትና ጥልቀት ሰጡት። በመጨረሻም በ1956 የተጀመረው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ አገልግሎት፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከትምህርት ዘመናቸው ውስጥ አንዱን ዓመት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲያሳልፉ በማድረግ ለውጥ እናመጣልሃለን ብለው የተነሡለትን ኅብረተሰብ ይበልጥ እንዲያውቁ አደረጋቸው። ከዚያም አልፎ የዩኒቨርሲቲን ተማሪዎች ከ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ጋር በማቀራረብ ይህ የአገልግሎት ዘመን ሌላም አስተዋፅኦ ነበረው።

ተማሪዎቹ በንቅናቄያቸው የመጀመሪያ ዓመታት የታገሉት በነፃ ማህበር ለመደራጀትና ሐሳባቸውን በነፃ ለመግለጽ የሚችሉበት መጽሔት ለማቋቋም ነበር። ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እንደተከፈተ የነበረው «ዩ.ሲ.ኮልስ» («የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጥሪ») የተሰኘው መጽሔት ኢፖለቲካዊና ሞራላዊ ባሕርይ ነበረው። በ1952 የተቋቋመው «ኒውስ ኤንድ ቪውስ» («ዜናና አስተያየት») ምንም እንኳ የዩኒቨርሲቲ ባለሥልጣኖች ጫና ባይለቀውም ወደ ነፃነት ጎዳና የሚወስድ አንድ እርምጃ ነበር። ድርጅትን በተመለከተም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እንደተመሠረተ የተቋቋመው የተማሪዎች ምክር ቤት በተማሪዎች ዲን ቁጥጥር ሥር የነበረ በመሆኑ ነፃ ነው ለማለት አያስደፍርም ነበር። ይህ ለነፃ ፕሬስና ነፃ ድርጅት ይካሄድ የነበረው ትግል በመሠረቱ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ የተከለለ ነበር። ተማሪዎቹ የሚፋለሙት ከመንግሥት ጋር ሳይሆን በኮሌጁ ውስጥ በማስተማርም ሆነ በአስተዳደር ቁልፍ ስፍራ ከያዙት ከካናዳውያኑ ኢየሱሳውያን መምህራንና አስተዳዳሪዎች ጋር ነበር።

ቀደም ብለን የፀረ ሥርዓቱን ተቃውሞ ታሪክ ስንገመግም እንደጠቆምነው ሁሉ በተማሪዎች ግንዛቤም በኩል የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አዲስ ምዕራፍ ከፋች ነበር። ከዚያ በፊት የተማሪዎች እንቅስቃሴ ባብዛኛው ያተኰረው አእምሯቸውን በማጐልበትና የቅጥር ግቢያቸውን ሕይወት በማዳበሩ ላይ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ተማሪዎች አይታቸውን ወደ ኅብረተሰቡ ሲያዞሩ እንመለከታለን። ከፍተኛ ድምቀት የነበረው የክርክር ክበብ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሲሆን፣ ከ1953 ጀምሮ በየዓመቱ የኮሌጅ ቀን በሚከበርበት ዕለት ይነበቡ የነበሩት ግጥሞች ደግሞ የሁለተኛው ምዕራፍ ማብሠሪያ ነበሩ። እነዚህ ግጥሞች ያዘሉት ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ትችት መንግሥትን እያስደነገጠና እያስቆጣ መጥቶ በ1954 ባለቅኔዎቹና አስተናጋጆቹ የተማሪዎች ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከትምህርታቸው ታግደው ነበር።

የተማሪ ንቅናቄ የፀረ ሥርዓት ተቃውሞ እየከረረ የመጣው ወደ 1950ዎቹ መገባደጃ ላይ ነው። ለዚህም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገው በ1956 ግድም የተቋቋመው «ክሮኮዳይልስ (አዞ)» ተብሎ የታወቀው የተማሪዎች ቡድን ነው። እንደ ስማቸው ሁሉ አዞዎች ብዙውን ጊዜ ፊት ለፊት ሳይጋለጡና ሳይጋፈጡ (ማለትም በተማሪዎች ምክር ቤት ሥልጣን ሳይዙ) ሐሳባቸውንና ዓላማቸውን መድረክ ላይ በሚያወጧቸው ተማሪዎች አማካይነት የማራመድ



5.9 ተማሪዎች የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ


ልምድ ነበራቸው። ተማሪዎች ሥርዓቱን ለመገርሰስ ቆርጠው የተነሡትና የማርክሲዝም ፅንሰ ሐሳብ መስረግ የጀመረውም በነሱ አማካይነት ነው። የተማሪዎች ንቅናቄ አኩሪ ገድሎችም ሆነ መዘዛቸው እስካሁን ያልጠፋው ስሕተቶች ዞሮ ዞሮ ከነሱ አያልፍም።



የከረረ ተቃውሞ የመጀመሪያው ምልክት በ1957 አጋማሽ ላይ ታየ። የፓርላማ አባሎች ጭሰኝነትን ለመደንገግ ሲከራከሩ ተማሪዎች መሬት ላራሹ ብለው የአዲስ አበባን መንገዶች አጥቀለቋቸው። ይህ እስካሁን ድረስ አብዮታዊነቱ የሚነገርለት ድርጊት ነው የማታ ማታ ወደ አብዮቱ የመራውን ፊር የቀደደው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተማሪዎች ያለማቋረጥ በየዓመቱ በሰልፍ እየወጡ «ፊውዶ ቡርዧ» የሚል ስያሜ የተሰጠውን ሥርዓት በማጋለጥና በዓለም ዙሪያ ለሚካሄደው የፀረ ኢምፔሪያሊስትና የፀረ ኮሎኒያሊስት ትግል አጋርነታቸውን በመግለጥ ከመንግሥትና ከፀጥታ አስከባሪ ኃይሉቹ ጋር የከረረ ፍልሚያ ያዙ።

ተማሪዎቹ የሚያነሧቸው ነጥቦችና ጥብቅና የሚቆሙላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከዓመት ዓመት ይለያዩ ነበር። ለምሳሌ በ1958 የተማሪዎች ተቃውሞ ያተኮረው ሸላ ላም በረት አጠገብ በሚገኘው መንግሥት ድሆችን ባጎረበት መጠለያ (ተማሪዎቹ «የሸላ እስር ቤት» ብለው በሰየሙት) ላይ ነበር። በዓመቱ ደግሞ ሲቪክ መብቶችን ለመገደብ የተጠነሰሰውና ፓርላማ የቀረበ የሕግ ረቂቅ የተማሪዎቹን ቁጣ አስነሣ። በሚቀጥለው ዓመት ተማሪዎች መጀመሪያ የቪዬትናምን ሕዝብ ፀረ አሜሪካ ትግል በመደገፍና በርዴሽያ የተቋቋመውን የኢያን ስሚዝን አምባገነን የነጭ መንግሥት በመኰነን ሰልፍ ሲወጡ፣ በዓመቱ መገባደጃ ላይ ደግሞ በስድስት ኪሎ ቅጥር ግቢ ይካሄድ የነበረውንና የባህላዊ ኢምፔሪያሊዝም ነጸብራቅ ነው ያሉትን «ፋሽን ሾው» በመቃወም ከመንግሥት ወታደሮች ጋር ግብ ግብ ገጠሙ። በ1961 ሥርዓተ ትምህርቱ ይሻሻል በሚል የተነሣሣው እንቅስቃሴ ከዩኒቨርሲቲው አልፎ መላ ያገሪቱን 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አዳረሰ። የ1962 የትምህርት ዘመን ሲጀመር ተማሪዎች ብሔረ ሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸው መረጋገጥ አለበት ብለው በመወሰናቸው መንግሥት ከፋኛ ተደናግጦ በተማሪዎቹ ላይ ብርቱ ጥቃት ሰነዘረ። በጋዜጦቹ አማካይነት የፀረ ተማሪ ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ከካሄደ በኋላ በታኅሣሥ 19 የተማሪዎቹ መሪ ጥላሁን ግዛው በአደባባይ ተገደለ። በማግስቱም መሪያችንን በክብር እንቀብራለን ብሎ በስድስት ኪሎ ቅጥር ግቢ በተሰበሰበው ተማሪ ላይ የፀጥታ ኃይሉች በከፈቱት ተኩስ የተወሰኑ ተማሪዎች ሞቱ፤ አያሌ ቆሰሉ።

የተማሪዎቹ ተቃውሞ እየከረረ በመጣ ቁጥር ድርጅታቸውም እየጐለበተ መጣ፤ ሁለቱ ክሥተቶች ተደጋጋፊ ናቸው ማለት ይቻላል። የአርትስና የትምህርት ፋኩልቲዎች በ1958 ከአራት ኪሎ ወደ ስድስት ኪሎ እስከተዛወሩበት ጊዜ ድረስ የተማሪዎቹ ዋና ድርጅት የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ዩኒየን (የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማኅበር) የተባለው ነበር። አዲስ የተዘዋወሩት ተማሪዎች ቀድሞ እዚያው ከነበሩት (የማኅበራዊ አገልግሎትና የንግድ አስተዳደር) ተማሪዎች ጋር ሲደመሩ በርከት ያለ ማኅበረ ሰብ በመፍጠራቸው አዲስ ማኅበር ማቋቋም አስፈልጎ «የዋናው ግቢ ተማሪዎች ማኅበር» የተባለው ተቋቋመ። ዓመቱ ሳያልቅ የተማሪው አክራሪ ክንፍ የከተማው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሙሉ ባንድ ማኅበር ተጠቃለው መደራጀት አለባቸው የሚል ቅስቀሳ ማካሄድ ጀመረ። በ1955 የተቋቋመው አገር አቀፉ ብሔራዊ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ተማሪውን በትግል በማሰለፉ ረገድ ዳተኛ ነው ተብሎ ተነቀፈ። ከተሟሟፈ ክርክር በኋላ የተማሪውን ትግል ጥንካሬና ስለት ለመስጠት ያለው ብቸኛ አማራጭ የዋናው ከተማይቱን ተማሪዎች ባንድ ድርጅት ጥላ ሥር ማሰባሰብ



5.9 ተማሪዎች የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ

ልምድ ነበራቸው:: ተማሪዎች ሥርዓቱን ለመገርሰስ ቆርጠው የተነሡትና የማርክሲዝም ፅንሰ ሐሳብ መስረግ የጀመረውም በነሱ አማካይነት ነው:: የተማሪዎች ንቅናቄ አኩሪ ገድሎችም ሆነ መዘዛቸው እስካሁን ያልጠፋው ስሕተቶች ዞሮ ዞሮ ከነሱ አያልፍም::



የከረረ ተቃውሞ የመጀመሪያው ምልክት በ1957 አጋማሽ ላይ ታየ:: የፓርላማ አባሎች ጭሰኝነትን ለመደንገግ ሲከራከሩ ተማሪዎች መሬት ላራሹ ብለው የአዲስ አበባን መንገዶች አጥቀለቋቸው:: ይህ እስካሁን ድረስ አብዮታዊነቱ የሚነገርለት ድርጊት ነው የማታ ማታ ወደ አብዮቱ የመራውን ፊር የቀደደው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተማሪዎች ያለማቋረጥ በየዓመቱ በሰልፍ እየወጡ «ፊውዶ ቡርዧ» የሚል ስያሜ የተሰጠውን ሥርዓት በማጋለጥና በዓለም ዙሪያ ለሚካሄደው የፀረ ኢምፔሪያሊስትና የፀረ ኮሎኒያሊስት ትግል አጋርነታቸውን በመግለጥ ከመንግሥትና ከፀጥታ አስከባሪ ኃይሎቹ ጋር የከረረ ፍልሚያ ያዙ::

ተማሪዎቹ የሚያነሧቸው ነጥቦችና ጥብቅና የሚቆሙላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከዓመት ዓመት ይለያዩ ነበር:: ለምሳሌ በ1958 የተማሪዎች ተቃውሞ ያተኰረው ሾላ ላም በረት አጠገብ በሚገኘው መንግሥት ድሆችን ባጎረበት መጠለያ (ተማሪዎቹ «የሾላ እስር ቤት» ብለው በሰየሙት) ላይ ነበር:: በዓመቱ ደግሞ ሲቪክ መብቶችን ለመገደብ የተጠነሰሰውና ፓርላማ የቀረበ የሕግ ረቂቅ የተማሪዎቹን ቁጣ አስነሣ:: በሚቀጥለው ዓመት ተማሪዎች መጀመሪያ የቬትናምን ሕዝብ ፀረ አሜሪካ ትግል በመደገፍና በሮዴሽያ የተቋቋመውን የኢያን ስሚዝን አምባገነን የነጭ መንግሥት በመኰነን ሰልፍ ሲወጡ፣ በዓመቱ መገባደጃ ላይ ደግሞ በስድስት ኪሎ ቅጥር ግቢ ይካሄድ የነበረውንና የባህላዊ ኢምፔሪያሊዝም ነጸብራቅ ነው ያሉትን «ፋሽን ሾው» በመቃወም ከመንግሥት ወታደሮች ጋር ግብ ግብ ገጠሙ:: በ1961 ሥርዓተ ትምህርቱ ይሻሻል በሚል የተነሣሣው እንቅስቃሴ ከዩኒቨርሲቲው አልፎ መላ ያገሪቱን 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አዳረሰ:: የ1962 የትምህርት ዘመን ሲጀመር ተማሪዎች ብሔረ ሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸው መረጋገጥ አለበት ብለው በመወሰናቸው መንግሥት ክፉኛ ተደናግጦ በተማሪዎቹ ላይ ብርቱ ጥቃት ሰነዘረ:: በጋዜጦቹ አማካይነት የፀረ ተማሪ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ካካሄደ በኋላ በታኅሣሥ 19 የተማሪዎቹ መሪ ጥላሁን ግዛው በአደባባይ ተገደለ:: በማግስቱም መሪያችንን በክብር እንቀብራለን ብሎ በስድስት ኪሎ ቅጥር ግቢ በተሰበሰበው ተማሪ ላይ የፀጥታ ኃይሎች በከፈቱት ተኩስ የተወሰኑ ተማሪዎች ሞቱ፤ አያሌ ቆሰሉ::

የተማሪዎቹ ተቃውሞ እየከረረ በመጣ ቁጥር ድርጅታቸውም እየጐለበተ መጣ፤ ሁለቱ ክሥተቶች ተደጋጋፊ ናቸው ማለት ይቻላል:: የአርትስና የትምህርት ፋኩልቲዎች በ1958 ከአራት ኪሎ ወደ ስድስት ኪሎ እስከተዛወሩበት ጊዜ ድረስ የተማሪዎቹ ዋና ድርጅት የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ዩኒየን (የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማኅበር) የተባለው ነበር:: አዲስ የተዘዋወሩት ተማሪዎች ቀድሞ እዚያው ከነበሩት (የማኅበራዊ አገልግሎትና የንግድ አስተዳደር) ተማሪዎች ጋር ሲደመሩ በርከት ያለ ማኅበረ ሰብ በመፍጠራቸው አዲስ ማኅበር ማቋቋም አስፈልጎ «የዋናው ግቢ ተማሪዎች ማኅበር» የተባለው ተቋቋመ:: ዓመቱ ሳያልቅ የተማሪው አክራሪ ክንፍ የከተማው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሙሉ ባንድ ማኅበር ተጠቃለው መደራጀት አለባቸው የሚል ቅስቀሳ ማካሄድ ጀመረ:: በ1955 የተቋቋመው አገር አቀፉ ብሔራዊ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ተማሪውን በትግል በማሰለፉ ረገድ ዳተኛ ነው ተብሎ ተነቀፈ:: ከተጧጧፈ ክርክር በኋላ የተማሪውን ትግል ጥንካሬና ስለት ለመስጠት ያለው ብቸኛ አማራጭ የዋናው ከተማይቱን ተማሪዎች ባንድ ድርጅት ጥላ ሥር ማሰባሰብ

ነው የሚለው ቡድን አይሎ በመምጣቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ተመሠረተ። በእንግሊዝኛ ምኅጻረ ቃሉ ይበልጥ የሚታወቀው «ኡዙዋ»ና መጽሔቱ *Struggle* («ታገል») በኢትዮጵያ ተማሪዎች ፖለቲካ ውስጥ የግራ ክንፉን ድርጅታዊና ርእዮተ ዓለማዊ የበላይነት አረጋገጡ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ባገር ውስጥ ብቻ ሳይወሰን በውጭ ሀገርም ጠንካራ ዘርፍ ነበረው። በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር («ኤዙና») እና በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር («ኤዙዌ») የዚህ ዘርፍ አስተባባሪዎች ነበሩ። በውጭ ያሉት ተማሪዎች ካገር ከመራቃቸውም ሌላ አብዮታዊ ሥነ ጽሑፍ ያላንዳች ገደብና ሳንሱር ማግኘት በመቻላቸው ከዕለት ዕለት የፖለቲካ ትግሉ ይልቅ በቲዎሪና ርእዮተ ዓለሙ የመራቀቅ ዝንባሌ ይታይባቸው ነበር። በተለይም የሁለቱ ዐበይት ማኅበራት ልሳኖች፣ ማለትም የ«ኤዙና» «ቻሌንጅ» እና የ«ኤዙዌ» «ታጠቅ» የጠቅላላ የተማሪው ንቅናቄ የቲዎሪ መጽሔት ለመሆን በቁ። ይሁን እንጂ በውጭው የቲዎሪ ርቀትና ባገር ቤቱ የፖለቲካ ትግል መካከል የነበረው ቅንብር አነስተኛ ነበር። አብዮቱ መዳረሻ ላይም ውጭ ያለው ተማሪ ሁለት ቦታ ተከፍሎ የከረረና የመረረ የቃላት ጦርነት ያካሄድ ነበር። ከአብዮቱ በኋላ ይኸው ክፍፍል ወዳገር ቤት ተዛምቶ ከፍተኛ እልቂት አስከተለ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ለለውጥ ባለው ጽናትና በመሥዋዕትነት ስሜቱ ብዙም ወደር የሚገኝለት አይደለም። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ግልጽ የፖለቲካ ተቃውሞ በታገተበት ሥርዓት ውስጥ የተቃውሞን ሰንደቅ በኩራትና በጀግንነት አነሡ። ዳሩ ግን ያገራቸው የፖለቲካ ባህል ለዚህ ከባድ ተግባር በቅጡ ያዘጋጃቸው አልነበረም። ዲሞክራሲያዊና የነፃ አመለካከት ባህል ላገሪቱ እንግዳ በመሆኑ ይኸው ችግር የተማሪዎቹን ንቅናቄ ተጠናወተው። ንቅናቄው ለተቃዋሚ ሐሳብ ስፍራ የለውም ነበር። የርእዮተ ዓለም ክርክሮች እንደ ዘመነ መሳፍንቱ የሃይማኖት ክርክሮች ከፀጉር የሰለሉና ደም የሚያቃቡ ሆኑ። ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርእዮት የአስተሳሰብ ዘይቤ መሆኑ ቀረና እንደ እምነት ተወሰደ። መፈክሮች የቴዎሪን ስፍራ ያዙ። የከረረ የተቃውሞ አቋም መያዝ በአግባብ ነው ወይስ አለአግባብ ብሎ ከመመዘን ይልቅ በራሱ የሚፈለግ ሁኔታ ሆነ። የሁሉም ፉክክር ከግራም በላይ ግራ ለመሆን ነበር።

ለዚህ ዓይነት አክራሪ የፖለቲካ ባህል አንድ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገው መንግሥት ራሱ የወሰደው ያፈና አቋም ነው። መንግሥት በተማሪዎች ላይ የሚወስደው እርምጃ መሪዎችን ላጭር ጊዜ በፖሊስ ጣቢያ በማሰር ይጀምርና ወደ ኋላ በገፍ ተማሪዎችን ወደ በረሃ ማጋዝ ይደርሳል። ተማሪዎችም ባንፃሩ በሰልፍና መፈክር በማነብነብ የጀመሩትን ተቃውሞ ወደ አውሮኘላን ጠለፋ አሸጋገሩት። በተለይም አብዮቱ መዳረሻ ላይ የመንግሥት አፈና እየከፋ ሲሄድ አያሌ ተማሪዎች ስደትን መረጡ። ይህም ሁኔታ በተለይ በሰሜን አሜሪካ የነበረውን የተማሪዎች ንቅናቄ በማጠናከር ጉልህ ለውጥ አመጣ። የሆነው ሆኖ የተማሪና የመንግሥት ፍጥጫ እየከረረ ይምጣ እንጂ፣ የ1966ቱ አብዮት ሁለቱም ባልጠበቁት ሰዓትና ሁኔታ ነበር የፈነዳው። ሥርዓቱም የፍጻሜውን መቃረብ አልተረዳም ነበር። ለዓመታት የታገሉት ተማሪዎችም ያን የጠሉትን ሥርዓት በምን እንደሚተኩት ገና አውጠንጥነው አልጨረሱም ነበር።

# ምዕራፍ ስድስት

# አብዮትና መዘዙ

## መግቢያ

የ1966 አብዮት ለሁሉም ዱብ ዕዳ ነበር። ለአሥር ዓመታት ያህል የታገሉለትን ተማሪዎችም ሳይቀር አብዮቱ እንደ ማዕበል ነው የመታቸው። የገኘው መደብማ ምን እንደመታው ሳያውቅ ማዕበሉ ጠርጎ ወሰደው። «አብዮት» የሚለውን ቃል ራሱ ብዙዎች ምን እንደሆነ ያጤኑት ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ነው። የሂደቱን ድንገተኛነት ለመግለፅም «አብዮት ፈነዳ» ከሚለው የተሻለ አገላለፅ ማሰብ ያዳግታል። እንደማንኛውም ፍንዳታ ሁሉ፣ አብዮቱ በመንግሥትም ሆነ በጠላቶቹ ጎራ መደናበርና መደናገርን አስከተለ። ስለሆነም አብዮቱን መምራት ይቅርና ሰልፍን ከሂደቱ ጋር ማስተካከሉ ብርቱ ፈተና ሆኖ፣ የማታ ማታ አገሪቱን ለፍፁማዊ ወታደራዊ አገዛዝ አሳልፎ ሰጠ።

ይሁንና የኢትዮጵያ አብዮት ድንገተኛነት እንግዳ ነገር አይደለም። የዓለምን ታላላቅ አብዮቶች ያጠናው አሜሪካዊው ታሪክ ተመራማሪ ክሬን ብሪንተን እንዳለው፣ «አብዮት ምንጊዜም ቢሆን ድንገተኛ ነው።» ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት ከሌሎች ታሪካዊ አብዮቶች ጋር የሚጋራው ድንገተኝነትን ብቻ አይደለም። እንደነሱ ሁሉ ፈጣን፣ ግዙፍና አመፅ የተሞላበት፣ ማኅበራዊ ለውጥ የታየበት፣ ላይ የነበረው ወደታችና ታች የነበረው ወደ ላይ የተሸጋገረበት ክስተት ነው። ዝነኛውን የሌኒንን የአብዮታዊ ወቅት አገላለፅ ተከትሎ፣ ገዥዎች እንደ ጥንቱ መግዛት የተሳናቸው ተገዥዎችም እንደ ቀድሞው አልገዛም፣ አሻፈረኝ ያሉበት ወቅት ነው። የኢትዮጵያ አብዮት ከቀደምት አብዮቶች ጋር የሚጋራው ሌላ ነጥብ ደግሞ፣ ብሩህ ሕልምን ያለመ አብዮታዊ ትውልድ መኖሩ፤ የዚያኑ ያህል ደግሞ አብዮቱን ያቀጣጠለው ወገን አብዮቱን ለመቆጣጠር አለመቻሉ ነው።

የገጠሩን ሕይወት በማያሻማ መንገድ የለወጠ ምጡቅ የመሬት ድልድልን በማወጁ ደግሞ የኢትዮጵያ አብዮት ከቻይናው አብዮት ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል። ይሁን እንጂ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ይበልጥ የሚቀራረበው ከፈረንሣይና ከሩሲያ አብዮቶች ጋር ነው ቢባል እምብዛም ውል የሳተ አይሆንም። እንደነሱ ሁሉ የኢትዮጵያ አብዮትም ለዘመናት የቆየ ሥርወ መንግሥትን ገርስሷል (ምንም እንኳ የፈረንሣዩ ሥርወ መንግሥት በ19ኛው መቶ ዓመት ለጥቂት አሠርት ዓመታት እንደገና ለማንሰራራት ቢችልም)። በሦስቱም አገሮች፣ በብሩህ ተስፋ የጀመረው አብዮት ብዙም ሳይቆይ ወደ ሽብርና ፅልመት ተሸጋገረ። ሕዝባዊ ሥልጣንና ዳኝነትም በአምባገነናዊ አገዛዝ ተተካ። የፈረንሣይ አብዮት ናፖሊዮንን፣ የሩሲያ አብዮት ስታሊንን፣ የኢትዮጵያ አብዮት ደግሞ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ወለደ። እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ ኦርዌል «አኒማል ፋርም» በተሰኘው ምጸታዊ ልብ ወለዱ እንዳስቀመጠው፣ አብዮት